# የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት

## የተማሪ መጽሐፍ

## አስራ አንደኛ ክፍል


አዘጋጅ፡-

የሺጥላ መንግሥቴ

አርታኢ፡-

የኋላሸት ደሳለኝ

ገምጋሚዎች፡-

መኮንን አስማማው

ተስፋዬ ወ/ሚካኤል

ወርቁ አድማስ



AL GHURAIR
PRINTING AND PUBLISHING LLC

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

## ምስጋና


የዚህ መጽሐፍ ዲዛይን ህትመትና ስርጭት ማከናወኛ ገንዘብ የተገኘው በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ኘሮጀክት (GEQIP) አማካኝነት ነው:: የኘ ሮጀክቱ ዋና ዓላማ በአገሪቱ በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከ1ኛ-12ኛ ክፍሎች የሚሰጠውን የትምህርት ጥራት ማሻሻል ነው::

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ለGEQIP የዋለውን ገንዘብ ያገኘው በብድር/በእርዳታ ሲሆን ብድሩን/ እርዳታውን የሰጡት ዓለምአቀፍ የልማት ማህበራት (IDA)፣ ፋስት ትራክ ኢንሼትቭ ካታሊቲክ ፈንድ (FTI CF) እና ሌሎችም የልማት አጋሮች ማለት የፊንላንድ፣ የኢጣሊያ የልማት ማህበር፣ የኔዘርላንድና የታላቋ ብሪታኒያ የእርዳታ ድርጅት አለምአቀፍ የልማት ዋና ክፍል (DFID) ናቸው::

ሁሉንም በዝርዝር መጥቀስ የማይቻል በርካታ ግለሰቦችና ድርጅቶች ይህ የተማሪ መጽሀፍና የመምህር መምሪያ እውን እንዲሆኑ ያልተቆጠበ ድጋፍቸውን ሰጥተዋል:: በዚህም ትምህርት ሚኒስቴር ምስጋናውን ያቀርባል::



© በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር



1ኛ እትም፣ 2004 ዓ.ም

ISBN 978-99944-2-257-9

**የአል-ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅት**
**የፖ.ሳ.ቁጥር 5613**
**ዱባይ፣**
**የተባበሩት የአረብ ኤሜሬት**

**ኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር**
**የፖ.ሳ.ቁጥር 100767**
**አዲስ አበባ**
**ኢትዮጵያ**

ጋር በመተባበር ይህን መጽሐፍ ለኢፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴር አዘጋጅተው አትመው፣ አሰራጭተዋል::



ሁሉም የህትመት መብቶች ተከብረዋል::

የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም እንደማይቻል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 410/2004 የኮፒራይትና የተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ 10ኛ አመት ቁጥር 55 አዲስ አበባ ጁላይ 19, 2004 ይከለክላል::

የስዕሎችን የኮፒ ራይት መብቶች ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል:: ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን::

# ማውጫ


**ይዘት** **ገጽ**

መግቢያ ........................................................ i

ምዕራፍ አንድ:- ቋንቋና ህብረተሰብ ........................ ፩

ምዕራፍ ሁለት:- ቅርሶቻችን.................................. ፴

ምዕራፍ ሦስት:- ወግ ........................................ ፶፬

ምዕራፍ አራት:- ልቦለድ .................................... ፷፬

ምዕራፍ አምስት:- የቋንቋ ለዛ .............................. ፹፪

ምዕራፍ ስድስት:- ግጥም .................................... ፻፫

ምዕራፍ ሰባት:- አርበኝነት ................................ ፻፳፫

ምዕራፍ ስምንት:- ትውፊት .................................. ፻፶፩

ምዕራፍ ዘጠኝ:- ስኬት...................................... ፻፸፱

ምዕራፍ አስር:- ኪነጥበብ .................................. ፻፺፮

አባሪዎች ...................................................... ፪፻

ማጣቀሻ መጻሕፍት.......................................... ፪፻፪

ቃላት ከነፍቻቸው .......................................... ፪፻፮

ፈሊጣዊ አነጋገሮች ከነፍቻቸው............................ ፪፻፲

# መግቢያ

በ፳፻፩ ዓ.ም. በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት እንደተጠቆመው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ አላማዎች የተማሪዎችን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ማዳበርና የስነልሳንና የስነጽሑፍ እውቀታቸውን ማጎልበት ናቸው፡፡ ይህ የአሥራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ እነዚህን ዓላማዎች መሠረት በማድረግ የተመረጡ ይዘቶችን አካትቶ ቀርቧል፡፡

መማሪያ መጽሐፉ በአስር ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን፣ በውስጡ  ምንባቦችን እንዲሁም በአራቱ የቋንቋ ክሂሎችና በሁለቱ የቋንቋ እውቀት ዘርፎች ተለይተው የተሰናዱ መልመጃዎችን ይዟል፡፡ በየምእራፉ ማብቂያ አበይት ነጥቦች በማጠቃለያ መልክ ከመቅረባቸውም በላይ ተማሪዎች የየምዕራፉን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ የሚያመሳክሩባቸው ቅጾች ተካተዋል፡፡

የመጽሐፉ ይዘት ለቅድመ ኮሌጅ ደረጃ እንዲመጥን ተገቢው ጥንቃቄ ከመወሰዱም በላይ፣ ተማሪዎች መልመጃዎቹን ሲሰሩ ግር እንዳይሰኙ ግልጽ መመሪያዎች፣ አስረጅዎች ልዩ ልዩ ማብራሪያዎችና ማስታወሻዎች እንዲያካትት ተደርጓል፡፡ አቀራረቡም የአሥራ አንደኛ መሰናዶ ተማሪዎች ትምህርቱን በቀላሉ ለመረዳት እንዲችሉ ያግዛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ መጽሐፉ ለቋንቋ ትምህርት ዝንባሌው ላላቸውና ወደፊት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቋንቋ ዘርፍ ትምህርታቸውን ለመቀጠል ለሚሹም ተማሪዎች የመነሻ ዕውቀት ያስጨብጣል ተብሎ ታምኖበታል፡፡

በሌላ በኩል አንድ የመማሪያ መጽሐፍ ታትሞ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ፣ በተግባር እየተፈተሸና እየተገመገመ በየጊዜው የሚሻሻል በመሆኑ፣ በዚህ መጽሐፍ የምትገለገሉ ተማሪዎች፣ መምህራን፣ የትምህርት ባለሙያዎችና የሚመለከታችሁ ወገኖች የማሻሻያ አስተያየታችሁን ብትልኩልን ለመቀበል ዝግጁ መሆናችንን እንገልጻለን፡፡

በመጨረሻም፣ የመማሪያ መጽሐፉ ሲዘጋጅ በርካታ ጽሑፎች በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል፡፡ ሥራዎቹን ላበረከቱ ግለሰቦች፣ ድርጅቶችና ተቋማት ላቅ ያለ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## ቋንቋና ህብረተሰብ

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡- ተማሪዎች! ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- ✓ የቋንቋንና የጽሕፈትን ምንነት ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ የቋንቋንና የጽሕፈትን ግንኙነትና ልዩነት በማወዳደር ታስረዳላችሁ፡፡
- ✓ የአማርኛ አናባቢና ተናባቢ ድምጾችን በመለየት ታሳያላችሁ፡፡
- ✓ ቃላትን በድምጸ ልሳናዊና በቀለማዊ አጻጻፍ ስልት ተጠቅማችሁ ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ ለሚቀርቡላችሁ ቃላት ቀጥተኛ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- ✓ የሚሰጧችሁን መመሪያዎች ተከትላችሁ ትተገብራላችሁ፡፡
- ✓ የአንቀጽ ማስፋፊያ ዘዴዎችን ተጠቅማችሁ አንቀጾችን ታስፋፋላችሁ፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች

፩. ቋንቋና ጽሕፈት ለሰው ልጆች የሚሰጧቸውን ጥቅሞች ዘርዝሩ::
፪. የምታውቋቸውን የአጻጻፍ ስርዓቶች ጥቀሱ::
፫. የጽሕፈት ባህል ያላቸው የቋንቋ ተናጋሪዎች የሚያገኙትን ጥቅም የጽሕፈት ባህል ከሌላቸው የቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር በማነጻጸር መልሳችሁን በማስታወሻችሁ ላይ ከዘረዘራችሁ በኋላ፣ ከምንባቡ ከምታገኙት ፍሬ ነገር ጋር አስተያዩ::

# ቋንቋና ጽሕፈት

ቋንቋ ወይም ንግግር በዘፈቀደ የተፈጠረ አንደበታዊ መግባቢያ ነው:: በቋንቋ አማካይነት ተግባቦት ሲካሄድ አንዱ ከሌላው ያልተጋራውን መረጃ ይቀበላል፤ መልሶም የራሱን ያቀብላል:: የተግባቦት ስኬቱ መልእክት ከተናጋሪው ወደ ተቀባዩ ደርሶ ተቀባዩ በሚሰጠው ግብረ መልስ ይወሰናል:: እንዲህ ያለው መግባቢያ ከሌሎች ተራ መግባቢያዎች የሚለይበት የራሱ ባህሪያት አሉት:: ከነሱም መካከል ሰብአዊነቱ፣ ስርዓታዊነቱ፣ አንደበታዊነቱና ትእምርታዊነቱ ተጠቃሽ ናቸው::

ይህ የተለየ ባህሪ ያለው ሰብአዊ መግባቢያ በትክክል መቼና እንዴት ተፈጥሮ አገልግሎት ላይ እንደዋለ በተጨባጭ መረጃ ላይ ተመስርቶ ለማወቅ ያዳግታል:: ያም ሆኖ፣ በጥናት ላይ የተመሠረተው የምሁራን ግምት፣ ጊዜው ከብዙ ሚሊዮን አመታት በፊት እንደሆነ ያስረዳል::

የሰው ልጅ ለብዙ ሚሊዮን አመታት ቃላዊ በሆነው ቋንቋው ተግባብቶ ተፈጥሮን እየለወጠ ህልውናውን ጠብቆ መቆየት ቢችልም፣ በንግግር የሚለዋወጠው መልዕክት የጊዜና የቦታ እስረኛ ነበር:: ሰው ይህንን የንግግሩን ውስንነት ለማስወገድና ታሪኩን፣ ባህሉንና፣ ትውፊቱን ቀርጾ ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ እንዲሁም ሩቅ ቦታ ለሚኖር መሰሉ ሐሳቡንና ተግባሩን፣ ምኞቱና ተስፋውን ለማድረስ ሲል፣ የጽሕፈት ጥበብን እንደፈጠረ ይገመታል:: የዚህ ስልት መፈጠርም ራሱንና


በዙሪያው ያለውን ዓለም እንዲገነዘብ ረድቶታል። ጽሕፈት ለሰው ልጅ የቀደሙ አባቶቹን ውርስ፣ የራሱን ቅርስና ረጃት ለተተኪው ለማስተላለፍና ለገዛ ህልውናው ልማት መሠረት ለመጣል ብሎም በተፈጥሮ ላይ ለመሰልጠንም አግዞታል።

የጽሕፈት መፈልሰፍ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ዐብይ እርምጃ ቢሆንም፣ "ጽሕፈት መቼ፣ የትና እንዴት ተፈጠረ?" ለሚሉ ጥያቄዎች የተሟላ ምላሽ ማግኘት ያዳግታል። ተመራማሪዎች እንደሚገልጹት፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት እስከ ሃያ ሺህ ዓመት የሚሞላቸው የዋሻ ውስጥ ስዕሎች፣ በትንንሽ ነገሮች ላይ የተቀረጹ ቅርጻ ቅርጾች በመካከለኛውና ሩቅ ምስራቅ፣ በአሜሪካ (በነባር ህንዶች መኖሪያ) እና በሌሎችም እጅግ ጥንታዊ የሰው ልጅ መኖሪያ ነበሩ በሚባሉ የዓለማችን አካባቢዎች ተገኝተዋል። የጥንቱ ሰው በየዕለት ህይወቱ የሚጋጥመውን ክስተት በስእል መግለጹ፣ ለስርዓተ-ጽሕፈት መነሻ እንደሆነም ይታመናል። ይሁን እንጂ፣ ይህ ሂደት በስልትና በስርዓት የተዋቀረና ሙሉ የጽሕፈት ቅርጽ የያዘ አልነበረም። ስዕሎቹ ባንድ በኩል አንድ ወይም ብዙ ሁነቶችን የሚያሳዩና በንግግር ፍቻቸውን ለመዘርዘር የሚቻል ቢሆንም፣ በነሱ አማካይነት ሰዓሊው (ጸሐፊው) ለማስተላለፍ የፈለገውን መልዕክት በተሟላ መንገድ አንባቢው አያገኘውም። ከዚህ በተጨማሪም ድምጻችንን ከፍ አድርገን ቃል በቃል ልናነባቸው አንችልም።

አብዛኛዎቹ ምሁራን እንደሚስማሙት፣ በወጉ የተሳለና የተዋደደ የጽሕፈት ስልት ለመጀመሪያ ጊዜ ብቅ ያለው፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከአርባኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ወዲህ ነው። የተጀመረበትን ቦታ በተመለከተም አንዳንዶች ከጥንታዊ ቻይና ስልጣኔ ጋር ሲያያይዙት፣ ብዙዎቹ በመካከለኛው ምስራቅ አካባቢ እንደሆነና በተለይ ከጥንቷ ሜሶፖታሚያ ስልጣኔና በጊዜው በንግድና በባህል ጥብቅ ትስስር ከነበራቸው የጥንት ግብፃውያን ስልጣኔ የፈለቀ እንደሆነ ያስረዳሉ። እነዚህ ወገኖች በጣም ጥንታዊ የሆነው ሥርዓተ-ጽሕፈት፣ የሰመራውያን የጽሕፈት ስርዓት እንደሆነ ያምናሉ።

ይህ የጽሕፈት ስርዓት የተጀመረው በታችኛው ሜሶፖታሚያ (የዛሬዋ ኢራቅ) በግምት ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ፵፻ እስከ ፴፻ ዓመተ ዓለም በነበረው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ በወቅቱ ሰመራውያን ከሸክላ አፈር በሚዘጋጁ መጻፊያዎች ላይ በመጻፍ ለቀረጥና ለመሰል አገልግሎት ይጠቀሙ እንደነበር የሚጠቁሙ የታሪክ ማስረጃዎች ተገኝተዋል፡፡ አጻጻፉም በመነሻው ላይ የሚከተለውን ይመስል ነበር፡፡

**የጽሑፍ መልክት፣**



**የሚይዘው ፍች፣** ራስ ውሃ መጠጣት

*(የስነልሳን ኢንሳይክሎፒዲያ፣ 2004፣ ገጽ 560)*

የሰመራውያን ስርዓተ ጽሕፈት የተለያዩ ለውጦችን እያስተናገደና በፍጥነት እያደገ ከመጣ በኋላ፣ “ኩዊኒፎርም” በሚል ስያሜ ይታወቅ ነበር፡፡ ይህን የአጻጻፍ ስርዓት በ፳፰፻ ዓመተ ዓለም አካባቢ ጎረቤቶቻቸው አካኒያውያንና (በኋላ ባቢሎናውያን ተብለዋል) ቆይቶም ግብፃውያን ለየቋንቋቸው እንዲስማማ አድርገው በማሻሻልና በመለወጥ ተገልግለውበታል፡፡

ከዚህ በላይ ጽሕፈት መቼና የት እንደተጀመረ አብዛኞቹ ምሁራን የሚስማሙበትን ገለጻ ለማየት ሞክረናል፡፡ ከዚሁ ነጥብ ሳንወጣ፣ የሀገራችን አንዱ መለያ የሆነውን የግዕዝ ፊደልና የአጻጻፍ ስርዓት አነሳስ በጨረፍታም ቢሆን ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡

የግዕዝ ፊደል አመጣጥ ምንጩ የደቡብ ሴም ፊደል መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ ስርዓተ ጽሕፈት ሥራ ላይ የዋለው ከክርስቶስ ልደት በፊት በአስረኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ እንደነበር በታሪክ ተመዝግቧል፡፡ ከደቡብ ሴማዊ ክፍል መንጭቶ፣ ለግዕዝ ፊደል መነሻ የሆነው ሳባዊ ፊደል ሲሆን፣ የጀመረበት ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ፲፻ እስከ ፭፻ ዓመተ ዓለም እንደነበር ይገመታል፡፡ በኋላም የግዕዝ ፊደል በሰሜን ኢትዮጵያ በጥንታዊ አክሱም ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፫፻ ዓመተ ዓለም አካባቢ እንደጀመረ ታሪክ ይነግረናል፡፡ ዛሬ ይህ በግዕዝ በኩል የተገኘው ሳባዊ ፊደል አማርኛን ጨምሮ ሌሎች ኢትዮ-ሴማዊ ቋንቋዎች ይገለገሉበታል፡፡

ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ጽሕፈት ከጥንቱ የመካከለኛውና የሩቅ ምስራቅ አካባቢ ሳይፈልቅ አልቀረም ቢባልም ዛሬ ካለበት ደረጃ ለመድረስ በየዘመናቱ የተለያዩ ጉልህ የእድገት ደረጃዎችን ተሸጋግሯል፡፡ በነዚህ የእድገት ደረጃዎች የታዩ የጽሕፈት ዓይነቶች በቅደም ተከተል ስዕላዊ የአጻጻፍ ዘዴ፣ ቃላዊ የአጻጻፍ ዘዴ፣ ቀለማዊ የአጻጻፍ ዘዴና ፊደላዊ የአጻጻፍ ዘዴ በሚል ተለይተው ይታወቃሉ፡፡

### ስዕላዊ የአጻጻፍ ዘዴ፡-

አስቀድሞ እንደተብራራው ስዕላዊ የአጻጻፍ ዘዴ በግምት ከዛሬ አምስት ሺህ ዓመት በፊት ሳይፈልቅ እንዳልቀረ ለሚገመተውና እስከዛሬ ለዘለቀው ስርዓተ ጽሕፈት መነሻ መሠረት ነበር፡፡ ነገር ግን በንግግር መልክ የሚወጣውን ቋንቋ በቀጥታ የሚወክል ባለመሆኑ እንደትክክለኛው ስርዓተ ጽሕፈት አይቆጠርም፡፡ እድሜውም ከቋንቋ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ካለው ስርዓተ ጽሕፈት ከአራት እጥፍ በላይ የበዛ ነው፡፡ ይህ የአጻጻፍ መንገድ በተለያዩ የዓለማችን አካባቢዎች ጥቅም ላይ ከመዋሉም በላይ፣ አንባቢው ከሰዓሊው ጋር አንድ ዓይነት ቋንቋ ባይናገርም ስዕሉን ተመልክቶ መልእክቱን ለመረዳት አያዳግተውም፡፡ ይሁን እንጂ፣ የሰው ልጅ ከቋንቋው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለውና ንግግሩን ሙሉ በሙሉ በመወከል፣ ከጊዜና ከቦታ ውስንነት ነፃ የሚያደርገውን የጽሕፈት ስርዓት

ለማበጀት ከነበረው ጽኑ ፍላጎት የተነሳ፣ ቃላዊ የአጻጻፍ ዘዴን አፍልቆ ወደ መጠቀም ሽግግር አድርጓል፡፡

**ቃላዊ የአጻጻፍ ዘዴ:-**

ቃላዊ የአጻጻፍ ዘዴ ለመጀመሪያ ጊዜ የንግግር ቋንቋና ጽሕፈት ቀጥተኛ ግንኙነት ያሳዩበት ከመሆኑም በላይ፣ አንድ ምልክት በቋንቋው ውስጥ የሚገኝ አንድ ቃልን እንዲወክል እየተደረገ በአገልግሎት ላይ የዋለበት ነበር፡፡ ለዚህ የአጻጻፍ ዘዴ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው የአረብኛው የቁጥር ስርዓት ነው፡፡ በዚህ የቁጥር ስርዓት መሠረት አንድ ምልክት የሚቆመው ለአንድ ቃል ነው፡፡ ለምሳሌ፣ “2” የሚለው ምልክት በቃል ሲመነዘር “ሁለት” ይሆናል፡፡ የዚህ ዓይነት ቃላዊ የአጻጻፍ ዘዴ የሚጠቀሙ ቋንቋዎች በውስጣቸው ላሉ በብዙ ሺህ ለሚቆጠሩ ቃላት ወካይ ምልክቶች ይኖሯቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ በተራው የቋንቋውን ስርዓተ ጽሕፈት ለመማር ከባድ፣ ለመጠቀም ውስብስብ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም የተሻለ የአጻጻፍ ስርዓት ለመፍጠር በተደረገው ጥረት ከቃላዊ የአጻጻፍ ዘዴ ቀጥሎ ቀለማዊ የአጻጻፍ ዘዴ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

**ቀለማዊ የአጻጻፍ ዘዴ:-**

ጽሕፈት ወደ ቀለማዊ የአጻጻፍ ዘዴ የተሸጋገረው ሰው አንድን ቃል በውስጡ በሚይዛቸው ቀለሞች ከፋፍሎ መጻፍ እንደሚቻል ከደረሰበት በኋላ ነበር፡፡ ለዚህ የአጻጻፍ ዘዴ ሙሉ በሙሉም ባይሆን ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው የሀገራችን የሴም ቋንቋዎች የሚጠቀሙበት የአጻጻፍ ስርዓት ነው፡፡ በአማርኛና በሌሎች የሀገራችን የሴም ቋንቋዎች የአጻጻፍ ስርዓት መሰረት በአመዛኙ እያንዳንዱ ቀለም በአንድ ምልክት ሲገለጽ፣ ቃሉ ደግሞ በተወሰኑ ቀለማዊ ምልክቶች ይገለጻል፡፡ ሁኔታውን ለማየት እንዲረዳን “ዘለቀ” የሚለውን ቃል ወስደን የያዛቸውን ድምጾች ከፋፍለን ብንመለከት /ዘኧልልኧቅኧ/ ይሆናል፡፡ ይህ ሰባት ድምጾችን የያዘ ቃል በያዛቸው ቀለሞች ብንከፋፍለው ዘኧል-ልኧ-ቅኧ ይሆናል፡፡ በዚሁ

መሠረት ዝኧል- የሚለው በ”ዘ” -ልኧ- የሚለው በ”ለ” እና -ቅኧ የሚለው በ”ቀ” ተወክሏል፡፡ በሦስቱም ቀለሞች ውስጥ አናባቢዎቹ አይቀሬ ሲሆኑ ለቀለሙ ማዕከል በመሆን ያገለግላሉ፡፡

**ፊደላዊ የአጻጻፍ ዘዴ:-**

ከቀለማዊ የአጻጻፍ ስርዓት ቀጥሎ ተግባራዊ የሆነው በአሁኑ ጊዜ በስፋት በማገልገል ላይ ያለው ፊደላዊ የአጻጻፍ ዘዴ ነው፡፡ ይህ የአጻጻፍ ዘዴ ከቀደመው ቀለማዊ አጻጻፍ ዘዴ የፈለቀ ሲሆን፣ በጽሕፈት ታሪክ ውስጥ የቅርብ የሚሰኝ ነው፡፡ በዚህ ስርዓተ ጽሕፈት ስልት ውስጥ ተግባራዊ የሚሆኑ የጽሑፍ ምልክቶች ብዛት ከቀደሙት ዘዴዎች አንጻር ሲታዩ አነስተኛ ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ምልክትም የሚወክለው አንድ ነጠላ ድምጽን ነው፡፡ ለዚህ ስልት ሙሉ ለሙሉም ባይሆን ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው እንግሊዝኛ፣ ላቲንና የላቲን ቋንቋዎች የሚጠቀሙበት የጽሕፈት ስርዓት ነው፡፡

በአጠቃላይ፣ ሰው የሚያወጣውን ንግግር በጽሑፍ መልክ ቀርጾ ለማስተላለፍ በነበረው ፍላጎት ጽሕፈት መጀመሩንና ጽሕፈትም አሁን ያለበት ደረጃ ለመድረስ ብዙ ደረጃዎች ማለፉን ተመልክተናል፡፡ በጽሕፈትና በቋንቋ መካከል ተፈጥሮአዊ ዝምድና የሌለ በመሆኑ የትኛውም የጽሕፈት ስርዓት እንዳስፈላጊነቱ ተገቢው ማሻሻያ ከተደረገለት የትኛውንም ቋንቋ ሊያገለግል ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታም በቋንቋና በጽሕፈት መካከል ተፈጥሮአዊ ዝምድና ላለመኖሩ ማሳያ ነው፡፡

*(ከቀድሞ 11ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ተሻሽሎ የቀረበ)*

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ:- አንብቦ መረዳት

**፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በተሰጣችሁ ምሳሌ መሰረት፣ ትክክለኛ የሆነውን "እውነት"፣ ስህተት የሆነውን "ሐሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ፣ ምክንያታችሁን ባጭሩ ግለጹ::**

**ምሳሌ:-** ማንኛውም ማህበረሰብ ባህሉን የሚገልጽበት የንግግርና የጽሑፍ ቋንቋ አለው:: ሐሰት

**ምክንያት:-** የባህል መመስረቻውም ሆነ መግለጫው ቋንቋ ቢሆንም፣ በዓለም ላይ የንግግር እንጂ የጽሑፍ ቋንቋ የሌላቸው ብዙ ባህሎች ስላሉ ነው::


1. ቋንቋ መግባቢያ ነው፤ መግባቢያ ሁሉ ደግሞ ቋንቋ ነው::
   ምክንያት፣ ______________________________
2. መልእክት ከተናጋሪው ወደ አድማጩ ደርሶ ግብረ መልስ እስካስገኘ ድረስ፣ ተግባቦት ተከናውኗል ለማለት ይቻላል::
   ምክንያት፣ ______________________________
3. በወጉ የተዋደደ የጽሕፈት ሥርአት የተፈለሰፈበት ጊዜ በትክክል ባይታወቅም፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት ሃያ ሺህ ዓመት ገደማ እንደሆነ ይገመታል::
   ምክንያት፣ ______________________________
4. ለመጀመሪያ ጊዜ የንግግር ቋንቋ ከንግግር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያሳየው በቃላዊ አጻጻፍ ዘዴ ነው::
   ምክንያት፣ ______________________________
5. በንግግርና በጽሕፈት መካከል ተፈጥሮአዊ የሆነ ዝምድና የለም::
   ምክንያት፣ ______________________________

## ፪. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ከተሰጡ አማራጮች ተስማሚውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ከሚከተሉት አንዱ በወጉና በስልት ለተደራጀ የጽሕፈት ስርዓት መፈልሰፍ መነሻ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡
   ሀ. የሰመራውያን ሐሳብን በጽሑፍ የማስፈር ስልት፣
   ለ. የጥንቱ ሰው ገጠመኙን በስዕል የመግለጽ ስልት፣
   ሐ. የጥንት ግብፃውያን የጽሕፈት ስርዓት ግኝት፣
   መ. የጥንት ቻይናውያን የጽሕፈት ስርዓት ግኝት፤
2. ቋንቋ በባህሪው ትእምርታዊ ነው ሲባል፣ ምን ማለት ነው?
   ሀ. ለተናጋሪው ማህበረሰብ መታወቂያ ምልክቱ ነው፡፡
   ለ. ቋንቋ የሚለመድ ነው፡፡
   ሐ. የቋንቋ ድምጾችም ሆኑ ቃላት ለቆሙለት ነገር በምልክትነት ያገለግላሉ፡፡
   መ. ቋንቋ በዘፈቀደ የተፈጠረ ነው፡፡
3. ከሚከተሉት ስለግዕዝ ፊደል ትክክለኛ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ሥራ ላይ የዋለው በአስረኛው ምእተ ዓመት መጀመሪያ ላይ ነው፡፡
   ለ. የግዕዝና የሳባ ፊደል አንድ ዓይነት ነው፡፡
   ሐ. የግዕዝ ፊደል የመነጨው ከሳባ ፊደል ነው፡፡
   መ. የግእዝ ፊደል ለሳባ ፊደል መፈጠር ምክንያት ነው፡፡
4. ከሚከተሉት በጣም ጥንታዊ የሆነው የጽሕፈት ስርዓት የትኛው ነው?
   ሀ. የግብጻውያን ሐ. የሳባውያን
   ለ. የሰመራውያን መ. የአካኒያውያን
5. ስለ ቃላዊ አጻጻፍ ዘዴ ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. እያንዳንዱን ቃል የሚወክሉ ብዙ ሺህ ምልክቶች ይኖሩታል፡፡
   ለ. እድሜው እስከ ሃያ ሺህ አመት ይደርሳል፡፡
   ሐ. በጽሕፈት ታሪክ ወደ መጨረሻው አካባቢ የተፈለሰፈ ነው፡፡
   መ. ምልክቶቹ ከቋንቋ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የላቸውም፡፡

6. ከሚከተሉት የአጻጻፍ ስርዓቶች ለመማር ከባድ፣ ለአጠቃቀም ውስብስብ የሚሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. ፊደላዊ
   ለ. ቀለማዊ
   ሐ. ቃላዊ
   መ. ቀላልና ከባድ የሚባል የጽሕፈት ስርዓት የለም።
7. ከሚከተሉት ስለቋንቋና ጽሕፈት ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. ከአንደበት የፈለቀ ሁሉ ቋንቋ ነው።
   ለ. ቋንቋ የሰብአዊ ፍጡር መግባቢያ ነው።
   ሐ. አንድ የጽሕፈት ስርዓት የተለያዩ ቋንቋዎችን ሊያገለግል ይችላል።
   መ. ቋንቋ ስርዓታዊ ነው።
8. የሰመራውያን የጽሕፈት ስርዓት የጀመረው መቼ ነው?
   ሀ. ከ፫፻ እስከ ፶፻ ዓመተ ዓለም፣
   ለ. በ፴፪፻ ዓመተ ዓለም ገደማ፣
   ሐ. ከ፶፻ እስከ ፷፻ ዓመተ ዓለም፣
   መ. ከ፷፻ እስከ ፸፻ ዓመተ ዓለም።

**፫. የጽሕፈት እድገት ሽግግርን ቀጥሎ በቀረቡት ሳጥኖች ውስጥ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቃችሁ በደብተራችሁ አሳዩ።**



## ክፍል ሁለት:- መናገር

**፩. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት፣ ቡድኖችን መስርታችሁ ከሚከተሉት ጥያቄዎች በአንዱ ላይ ከተወያያችሁ በኋላ፣...... የደረሳችሁበትን በቡድን መሪያችሁ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡**

1. ጽሕፈት ለአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ የሚያስገኘው ጠቀሜታ ምንድን ነው? በምሳሌ የተደገፈ ማብራሪያ ስጡ፡፡
2. ለጽሕፈት መጀመር ምክንያት የነበሩ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?
3. “ጽሕፈት የሰውን ልጅ ለህልውናው ልማት መሠረት እንዲጥልና በተፈጥሮ ላይ እንዲሰለጥን አግዞታል” የሚለውን ሐሳብ አብራሩ፡፡
4. “የጽሕፈት ባህል ያለው ቋንቋ በቋንቋነቱ የጽሕፈት ባህል ከሌለው ቋንቋ ጋር እኩል ነው” በሚለው ሐሳብ ላይ የጋራ አቋማችሁን በማስረጃ አስደግፋችሁ አቅርቡ፡፡
5. ስዕላዊ የአጻጻፍ ዘዴ እንደ ትክክለኛ ስርዓተ ጽሕፈት የማይቆጠርባቸው ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?
6. “ማንኛውም የጽሕፈት ስርዓት የቋንቋውን ድምጾች የሚወክሉ ምልክቶች ይኖሩታል” በሚለው ሐሳብ መስማማት አለመስማማታችሁን በማስረጃ በመደገፍ አቅርቡ፡፡

**፪. በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን ከሃያ ሦስት በላይ ቋንቋዎች የራሳቸው የጽሕፈት ስርአት አላቸው፡፡ ከነዚህ ቋንቋዎች መካከል አንዱን መርጣችሁ፤ ከዚህ በታች በሠፈሩት መመሪያዎች መሠረት፣ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ ለአስር ደቂቃ የቃል ንግግር ተራ በተራ አድርጉ፤**

*የንግግራችሁ ትኩረት፣*

- ቋንቋው ስለሚነገርበት አካባቢ፣
- ስለተናጋሪዎቹ ብዛት፣
- ስለቋንቋው አመጣጥ፣
- ቋንቋው ወደ ጽሕፈት ስለተሻገረበት ዘመን፣
- ዛሬ ስለደረሰበት የእድገት ደረጃ፣ (ከትምህርት፣ ከስነጽሑፋዊ ሀብት፣ ወዘተ፣ አንጻር መሆን ይችላል፡፡)

**፪. በዓለም ላይ አንድ ዓይነት የጽሕፈት ስርዓት ቢኖር ይሻላል? ወይስ አሁን እንዳለው የተለያየ የጽሕፈት ስርዓት? በቡድን ሆናችሁ በሁለቱ ሐሳቦች ጥቅምና ጉዳት ላይ ተወያይታችሁ አንድ ድምዳሜ ላይ ድረሱ፡፡**

## የቃል ንግግር ዝግጅትና አቀራረብ

### ሀ. ዝግጅት

*የቃል ንግግር ዝግጅት ስታደርጉ ማስታወስ ከሚገባችሁ መሠረታዊ ነጥቦች መካከል ቀጥሎ የተዘረዘሩት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡*

- አድማጮቻችሁን ማወቅ (እድሜውን፣ ጾታውን፣ የእውቀት ደረጃውን፣ ግላዊ አቋሙን፣ ወዘተ.)፤
- በምን ያህል ጥልቀት ስለርዕሱ ማውሳት እንዳለባችሁ መወሰን፤
- ርዕሱን የተመለከተ መረጃ ከቤተመጻሕፍት፣ ከሚመለከታቸው የግልና የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ከባለሙያዎችና ከልዩ ልዩ ምንጮች ማሰባሰብ፣
- ካሰባሰባችኋቸው መረጃዎች ውስጥ ለምትዘጋጁለት የንግግር ርዕስ ይመጥናሉ የምትሏቸውን መርጣችሁ መያዝ፤
- በንግግራችሁ መካተት ያለባቸውንና የሌለባቸውን መለየት፤
- ንግግራችሁን መልክ ማስያዝ፤
  - በጊዜ ቅደም ተከተል በማደራጀት፣
  - በስፍራ ቅደም ተከተል በማስቀመጥ፣
  - ፍሬ ሐሳቦችን በሚያነጻጽር መልክ በማደራጀት፣
  - ፍሬ ሐሳቦችን በአጎዛ ከፋፍሎ ለማየት በሚያስችል መልክ በማደራጀት፣
  - ፍሬ ሐሳቦችን ለማቅረብ በሚያመች አኳኋን በጭብጥ በመደገፍ፣
  - ፍሬ ሐሳቦችን በስሌትና በስዕላዊ መግለጫ በማስደገፍ እንዲብራሩ በማድረግ መልክ ማስያዝ፤

- መልክ ያስያዛችኋቸውን ዋናና ዝርዝር ነጥቦች ተከትላችሁ አድማጫችሁን በምናባችሁ በመሳል ብቻችሁን ንግግር በማድረግ መለማመድ፤
- ንግግራችሁ ለተሰጣችሁ ጊዜ መጣኝና ያልተንዛዛ መሆኑን ማረጋገጥ ናቸው፡፡

**ሰ. አቀራረብ**

እንደ ንግግር ርዕሰ-ጉዳያችሁ ባህሪና አመችነት ዝግጅታችሁን ከላይ በ"ሀ" ስር በተገለጸው መሰረት አጠናቃችሁ በቃል ንግግር ስታደርጉ፣ ማስታወስ ከሚገባችሁ መሠረታዊ ነጥቦች መካከል ቀጥሎ የተዘረዘሩት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

- የንግግሩን ርዕስና ዓላማ ለአድማጫችሁ በሚገባ ማስተዋወቅ፤
- የድምጻችሁን አወራረድ (ኃይል፣ ፍጥነት፣ ቃና) መመጠን፤
- የአካላችሁ እንቅስቃሴ ንግግራችሁን ለማጉላት፣ ሐሳባችሁን ለማጠናከርና የአድማጫችሁን ትኩረት ለመሳብ ስለሚያግዝ በተገቢው መንገድ መጠቀም፤
- በንግግር ሂደት የአድማጫችሁን ስሜትና ፍላጎት መጠበቅ፤
- በተቻለ መጠን ከአድማጫችሁ ጋር የዓይን ግንኙነት ማድረግ፤

## ክፍል ሦስት:- መጻፍ

፩.ጽህፈትና ንግግር ሁለቱም ሐሳብን ለሌላው የምናካፍልባቸው የቋንቋ ክሂሎች በመሆናቸው አንድነት እንዳላቸው ሁሉ ከባህሪያቸው የሚመነጭ ልዩነትም አላቸው:: በጥንድ በመሆን እየተወያያችሁ፣ በተራ ቁጥር 1 ላይ በተሰጣችሁ ምሳሌ መሠረት፣ ልዩነታቸው ላይ በማተኮር ሰንጠረዡን አሟሉ::

| ተራ ቁጥር | ንግግር | ጽሕፈት |
|---|---|---|
| 1 | የሚቀርበው በተፈጠረ አውድ ነው:: ብዙውን ጊዜ ነገርን በመጠቆም ግልጽ ያደርጋል (ለምሳሌ፣ ያ ነገር፣ እዚያ፣ ወዘተ.) | የራሱን አውድ ራሱ ይፈጥራል:: ስለዚህ ሲጻፍ ግልጽና የማያሻማ መሆን አለበት:: |
| 2 | ተናጋሪውና አድማጩ ብዙውን ጊዜ ይተያያሉ፣ ይራከባሉ:: ተራ በተራ ሐሳብ ይለዋወጣሉ:: | |
| 3 | | ጸሐፊ ጽሑፉን የሚያነቡለትን ሰዎች ሊያውቃቸውም ላያውቃቸውም ይችላል:: አንባቢዎቹም እንዲሁ ጸሐፊውን በአካል ሊያውቁትም ላያውቁትም ይችላሉ:: |
| 4 | | ወዲያውኑ ግብረ መልስ ማግኘት አይቻልም:: ጸሐፊው ሲጽፍ አስቀድሞ የአንባቢያንን ስሜትና ለጽሑፉ ሊኖራቸው ይችላል ብሎ የሚገምተውን ምላሽ ማሰብና ጽሑፉን ከዚያ አንጻር እያሰላሰለ መጻፍ አለበት:: |

| | | |
|---|---|---|
| 5 | ንግግር ከአንደበት ሲወጣ፣ ወዲያው እየተደመጠ ያልፋል፤ ይጠፋል። እየተላለፈ ሳለም አድማጩ ይረዳዋል። አድማጩ ካልገባው ግን መጠየቅ ይችላል፤ ይራከባል። የንግግሩ ፍጥነትም በተናጋሪው ይወሰናል። | |
| 6 | ዓረፍተነገሮች ያልተሟሉ ይሆናሉ፤ አንዳንዴም ሰዋስዋዊ ላይሆኑ ይችላሉ። መጠራጠርና ንግግርን ቆም ማድረግ ሊኖር ይችላል፤ ድግግሞሽ ይታያል። | |
| 7 | | መልእክቱን ባግባቡ ለማስተላለፍ ስርዓተ ነጥቦችን መጠቀም፣ ለአጽንኦት ከስር ማስመር፣ የዓረፍተ ነገሮችን ድንበር በግልጽ ማመልከት ይኖራል። |

**፪. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች አንድነቱን፣ አጽንኦቱንና ውህደቱን የጠበቀ አንቀጽ አካላት ናቸው። ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ስላልተቀመጡ እንደገና በቅደም ተከተል አዋቅራችሁ አንቀጽ ጻፉ።**

1. “ይኸ ጎፋፋ ካፖርት ምን አስመስሎኛል! እስቲ ምን ይባላል ካልጠፋ ነጠላ፣ ዘርዛራውን መልበሴ። አዲሱ ጫማ እያለልኝ ጠማማውን ላድርገው!” ሌላም ሌላም አለ።
2. እዚህ ላይ ምን እመስል ይሆን የሚል ጭንቀት አለ።
3. ሰበቡ ተፈልጎ ከጠፋ ግን “እኔ ድሮም ፎቶ አይዋጣልኝም” የምትለዋ አባባል መሸፈኛ ትሆናለች።
4. በፎቶግራፍ ዓለም ጎልተው ከሚታዩ ነገሮች ዋነኛው የማማር ጉዳይ ነው።

5. እንዲያውም ጭንቀቱ ፎቶው ታጥቦ እስኪወጣ ድረስ አይለቅም፤ ፎቶውን ከተነሱም በኋላ መጸጸት አለ፡፡

**፫. ከላይ በተራ ቁጥር ፪. እንደገና ያዋቀራችሁት አንቀጽ፡-**

1. ዋና መልእክቱ ምንድን ነው?
2. አንቀጹ የተስፋፋበትን ስልት ግለጹ፡፡

## የአንቀጽ ማስፋፊያ ዘዴዎች

**የገለጻ ስልት፣** የሚገልጸውን ነገር መልክ፣ ቁመናና ባህሪ በልዩ ልዩ የማነጻጸሪያ ስልቶች በመጠቀም በአንባቢ አእምሮ ውስጥ ምስል የምንፈጥርበትና ጎልቶ እንዲታይ የምናደርግበት ነው፡፡

**የትረካ ስልት፣** አንድን ጉዳይ ወይም ሁነት በጊዜ ቅደም ተከተል ውስጥ አስገብተን ከመቼ እስከ መቼና በየደረጃው ምን እንደተከናወነ ለመጻፍ ያስችለናል፡፡

**የማዋገን ስልት፣** በአንድ አንቀጽ የሚካተቱ ንዑሳን ሃሳቦች ወስደን ተጠይቃዊ ዝምድናቸውንና ግንኙነታቸውን ጠብቀን በወገን በወገናቸው አቀናብረን የምንጽፍበት ስልት ነው፡፡

**የማወዳደር/ የማነጻጸር ስልት፣** በዚህ ስልት ሁለት ነገሮች ባንድ ላይ ይታቀፋሉ፡፡ አንደኛው በአንቀጽ ውስጥ በሚቀርቡ ነገሮች መሀል ባለው ተመሳሳይ ገጽታ ላይ ተመስርተን የምናስፋፋበት "ማወዳደር" የሚባለው ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ፣ በአንቀጹ በሚቀርቡ ነገሮች ልዩነት ላይ ተመስርተን የምናስፋፋበት "ማነጻጸር" የሚባለው ነው፡፡ በመጀመሪያው የምናወዳድረው የነገሮቹን ተመሳሳይ ገጽታዎች ሲሆን፣ በሁለተኛው የምናነጻጽረው የነገሮቹን የልዩነት ገጽታዎች ይሆናል፡፡

**የምስያ ስልት፣** ተመሳሳይ ይሆናሉ ብለን የገመትናቸውን ነገሮች አንድ ላይ በማምጣት፤ የፊተኛው የኋለኛውን ይበልጥ አጉልቶ እንዲያሳይ ለማድረግ ያስችላል።

**የብያኔ ስልት፣** አንድ ነገር ምን እንደሆነና ምን እንዳልሆነ የምናስረዳበት ስልት ነው።

**የምክንያትና ውጤት ስልት፣** በአንቀጹ የሚገለጸው ሀሣብ በተመሠረተባቸው መነሻና መድረሻ ሀሣቦች መካከል ያለውን የምክንያትና ውጤት ዝምድና የምናስረዳበት ነው። ስለዚህም በአንቀጹ በሚገለጽ አንድ ነገር መሆን ወይም አለመሆን ያለውን ምክንያትና ያስከተለውን ውጤት አስፋፍተን እንገልጽበታለን።

**፩. የሚከተሉትን አራት አንቀጾች ከመረመራችሁ በኋላ የየአንቀጾቹን ዋና ሐሳብና የተስፋፉባቸውን ስልቶች ባጭሩ ጻፉ።**

**አንቀጽ አንድ**

በሀገራችን ጸሐፍት ቀደም ብለው የተጻፉ ቁም ነገሮችን ወጣት በመሆናቸው እዘመኑ ላይ ተገኝተው ያላነበቡ ሰዎች አሉ። እዘመኑ ላይ ተገኝተውም የሀገሪቱ ጋዜጣዎች፣ የራድዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ለነዚህ ቁም ነገሮች ተገቢውን ትኩረት ስላልሰጧቸው ያላነበቧቸው፣ ያልሰሟቸው ይኖራሉ። ዘመናዊ የሚባለው የሀገራችን ትምህርትም ባብዛኛው ወደውጭ ማየት እየተጠናወተውና እየተጫነው ስለመጣ፣ ልጆችና ወጣት ተማሪዎች የሀገራቸውን ጸሐፊዎች የሚያውቁበት፣ እንደልባቸው የሚያነቡበትና የሚያጠኑበት አጋጣሚ እየጠበበ ስለመጣም እኒህን ቁም ነገሮች ሊያውቋቸው አልቻሉም ብዬ አስባለሁ። ባለፉት ብዙ ዓመታት፣ በተለይ ደግሞ ባለፈው ሩብ ምዕት ዓመት (ወይም ሃያአምስት

ዓመታት)፣ በታወቁና በእጅግም ባልታወቁ የውጭ ሀገር ደራሲያን፣ የሳይንስ ጠበብት፣ ፈላስፎች፣ ምሁራን፣ ወዘተ. ተነገሩ እየተባለ የአንድ የሁለት መስመር ብሂሎች በየጋዜጣው፣ በየመጽሔቱ፣ በየቴሌቪዥኑ እና በየራዲዮ ፕሮግራሙ ሲጠቀሱ የሚሰሙት ባብላጫው በዚህ የተነሳ ይመስለኛል፡፡ ለጊዜው፣ ጥያቄዬ፣ “ለምን ተጠቀሱ?” አይደለም፡፡ የዛሬው ሐሳቤ ከሀገራችን ቀደምትና ዘመነኛ ደራሲያን፣ ሰዓልያን፣ “ፈላስፎች”፣ ባለቅኔዎችና ልዩ ልዩ ጸሐፊች ሥራዎች ውስጥ የሚገኙ ቁምነገሮችን በብዛት እየጠቀስን ብናቀርብ፣ በተለይ ወጣቱ ትውልድ እውቀትና ፍልስፍና ሁል ጊዜ ከውጭ ሀገር ቋንቋና ከውጭ ሀገር ዜጋዎች ብቻ የማይገኝ መሆኑን ለመጠቆምና ብዙ ጊዜ በየብሔረሰቡ ቋንቋ በሚነገሩት ውስጥም መልካም መልካም ቁም ነገርና ረቀቅ ረቀቅ ያለ ሐሳብ መኖሩን ተገንዝቦ ከጥገኝነት አስተሳሰብ በመጠኑም ቢሆን ይላቀቃልና እንዲህ እንጀምር-እናስፋፋ-እናዳብር ለማለት ነው፡፡

*(ፈቃደ አዘዘ፣ የኢትዮጵያ የቋንቋዎችና የስነጽሑፍ መጽሔት፣ ልዩ እትም፣ ቁ.10፤ 2000፣ 120)*

ዋና ሐሳብ ________________________________________

አንቀጹ የተስፋፋበት ስልት______________________________

## አንቀጽ ሁለት

ብርዳማ ጧት ነበር፡፡ የፀሐይዋ ጮራ ሩብ ያህል ብቅ ብላለች፡፡ ሌሊቱን ሙሉ ሲጋገር ያደረው ውርጭ መቅለጥ ጀምሯል፤ አብዛኛው ግን እንደረጋ ነው፡፡ በውርጩ የወረዛው ደረቅ አሸዋና ጥግ ጥጉን ይዘው ጉች ጉች ያሉት ጎጆዎች፣ ልዩ የሆነ የፀጥታና የብቸኝነት ግርማ የተጎናጸፉ ይመስላል፡፡ ከዚህ በተረፈ ግን ምንም ተንቀሳቃሽ ፍጥረት አይታይም፡፡ እንስሶች ከሌሊት መጠጊያቸው ገና አልወጡም፡፡ ወፎች ደግሞ የወራቱን ለውጥ ተከትለው አየሩ ወደሚስማማቸው ወደ ሰሜን ተጉዘዋል፡፡ በአኗኗር ምርጫ ረገድ ከወፎች የበለጠ እድል ማን አለው?

*(የብርሀኑ ዘሪሁን ቀደምት ሥራዎች፣ 1982፣ 11)*

ዋና ሐሳብ ______________________________

አንቀጹ የተስፋፋበት ስልት______________________________

## አንቀጽ ሦስት

የዑባ ካዎ አስተዳደር ስርዓት የጀመረው ከዑባ-የላ ከፍ ብሎ ኦምፔ በሚባለው ቦታ ነው፡፡ እዚህ መጀመሪያ መጥቶ የነገሰው ካዎው ሾዴ ሲሆን፣ ሦስት የአምልኮ፣ የአስተዳደር ማእከልና የመኖሪያ ቦታዎችን በማዘጋጀት ማስተዳደር ጀመረ፡፡ ቦታዎቹም ዶጓ (የነጋሲያን የአምልኮ ስፍራ)፣አምፔ (የአስተዳደር ማዕከል)፣ ካምባ (የመኖሪያ ቦታ) ነበሩ፡፡ ከዚያም በኋላ ጥንታዊ የዑባ ግዛት ተብሎ የሚታወቀውን አካባቢ ይገዙ የነበሩ ካዎች ዋና መኖሪያቸውንና የአስተዳደር ማእከላቸውን እዚሁ አድርገዋል፡፡ ሆኖም  አስተዳደሩ እየተጠናከረ ሲሄድ በየላ፣ በቡኔ፣ በገልፃ እና በሌሎችም ቦታዎች መቀመጫቸውን ያደረጉት የበታች ተሸዋሚዎች ተጠሪነታቸው ለሻዎው ሆኖ ሲያስተዳድሩ ቆይተዋል፡፡ ከላይ በተጠቀሱት የአስተዳደር አካባቢዎች ሀላፊነት ይዘው ያስተዳድሩ የነበሩት “ማይጫ ዳና” የሚል የማእረግ ስም የያዙ ነበሩ፡፡

*(ጋሞ ጎፋ ዞን ማስታወቂያና ባህል ዋና መምሪያ፣ የጋሞ ጎፋ ህዝቦች ታሪክ፣ 162)*

ዋና ሐሳብ ______________________________

አንቀጹ የተስፋፋበት ስልት______________________________

## አንቀጽ አራት

ስለአፅምሯዊ ንብረቶች ከማንሳታችን በፊት ንብረት ምን እንደሆነ በጥቂቱ ማብራራት ይገባል፡፡ በህግ ንብረቶች የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ተብለው ለሁለት የሚከፈሉ ሲሆን፣ የሚዳሰሱ ንብረቶች የሚባሉት የሚንቀሳቀሱ ወይም የማይንቀሳቀሱ ዋጋ ያላቸውና ራሳቸውን በቀጥታ ጥቅም ላይ የምናውላቸው ወይም የምንገለገልባቸው ናቸው፡፡ በአንጻሩ የማይዳሰሱ ንብረቶች የምንላቸው ረቂቅና ራሳቸውን በተዘዋዋሪ ወይም በቀጥታ መንገድ አገልግሎት ላይ የምናውላቸውን ሲሆን፣ የገንዘብ ኖቶችን፣ ቼኮችን፣ የተፈለሰፉ ሐሳቦችን ስነጽሑፋዊና ኪነጥበባዊ

ፈጠራዎችን ወዘተ. ይጨምራሉ:: ስለዚህም አዕምሯዊ ንብረቶች የምንላቸው የማይዳሰሱ (ረቂቅ) ከሆኑት የንብረት ዓይነቶች የሚመደቡ ሲሆን፣ እነኝህም አብዛኛውን ጊዜ የፈጠራ ሥራዎች ወይም የተፈለሰፉ ሐሳቦች ናቸው::

*(ታምራት ኪዳነማርያም፣ የዐማዳዊ እውቀቶች የህግ ጥበቃ፣ 1997፣ 57)*

ዋና ሐሳብ ___________________________________

አንቀጹ የተስፋፋነት ስልት______________________

**፮. በጥንድ ሆናችሁ "ትምህርት ቤቴ" በሚል ርዕስ አንድ አንቀጽ ለመጻፍ እንድትችሉ:-**

1. ርዕሱን ተመርኩዛችሁ ለአንቀጹ መንደርደሪያ ዓረፍተነገር (ኃይለ-ቃል) ሊሆኑ የሚችሉትን ዐ.ነገሮች ዘርዝሩ፤
2. ከዘረዘራችኋቸው ውስጥ ይበልጥ የተሻለውን መንደርደሪያ ዓረፍተነገር ምረጡ፤
3 ለመረጣችሁት መንደርደሪያ ዓረፍተነገር ደጋፊ ሐሳቦችን ዘርዝሩ፤
4. አንድ የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልትን ተጠቅማችሁ አንቀጹን ጻፉ::

**፯. ከሚከተሉት ርዕሶች አንዱን በመምረጥ፣ የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልቶችን ተጠቅማችሁ አንድ አንቀጽ ጻፉ::**

1. የወላጆች ቀን
2. ወርኃ ክረምት

## ክፍል አራት:- ስነልሳን

### ድምጸ-ልሳናት

የማንኛውም ቋንቋ መሰረት ድምጸ-ልሳናት ናቸው:: ድምጸ-ልሳናት የሚፈጠሩት በአንደበት ሲሆን፣ ተናባቢና አናባቢ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ::

## 1. ተናባቢ ድምጸ-ልሳናት

ተናባቢ የሚባሉት በአንደበት አካላት ንክኪ አማካይነት የሚፈጠሩ ድምጸ-ልሳናት ናቸው፡፡ የሚፈጠሩትም፣ ከአንደበት አካላት መንቀሳቀስ የሚችሉት (ከንፈር፣ ምላስና እንጥል) መንቀሳቀስ ወደማይችሉት (ጥርስ፣ ድድ፣ ላንቃ፣ ትናጋና ጉሮሮ) ተጠግተው በሚነካኩበት ጊዜ ከሳንባ የሚወጣውና የሚገባው አየር በከፊል ወይም ሙሉ ለሙሉ ሲታገድ ነው፡፡ ድምጸ-ልሳናት እንደ የሚፈጠሩበት የአንደበት ክፍል የከንፈር፣ የድድ፣ የላንቃ፣ ወዘተ. እየተባሉ ይጠራሉ፡፡ የአማርኛ ተናባቢ ድምጸ-ልሳናት ከሚፈጠሩበት ቦታ (መካነ-ፍጥረት) አንጻር ሲታዩ የሚከተለውን ይመስላሉ፡፡

፩. የከናፍር፡- /ብ/ /ፕ/ /ጵ/ /ም/ /ው/
፪. የከንፈርና የጥርስ (ስነፈር)፡- /ፍ/
፫. የድድ፡- /ት/ /ድ/ /ጥ/ /ስ/ /ዝ/ /ፅ/ /ን/ /ል/ /ር/
፬. የላንቃ፡- /ሽ/ /ዥ/ /ች/ /ጅ/ /ጭ/ /ኝ/ /ይ/
፭. የትናጋ፡- /ክ/ /ግ/ /ቅ/
፮. የማንቁርት፡- /ዕ/ /ህ/

ተናበቢ ድምጸ-ልሳናት በመካነ ፍጥረታቸው ብቻ ሳይሆን፣ በአፈጣጠር ባህሪቸውም ይለያያሉ፡፡ በመሆኑም ሲፈጠሩ ከሳንባ የሚወጣው አየር በሚኖረው የአወጣጥ ልዩነት አንጻር በባህርየ-ፍጥረታቸው እንደሚከተለው ይመደባሉ፡፡

፩. እግድ፡- /ብ/ /ፕ/ /ጵ/ /ት/ /ድ/ /ጥ/ /ግ/ /ክ/ /ቅ/ /ዕ/
፪. ሹልክልክ፡- /ፍ/ /ስ/ /ዝ/ /ፅ/ /ሽ/ /ዥ/ /ህ/
፫. ፍትግ፡- /ች/ /ጅ/ /ጭ/
፬. ሰርናዊ፡- /ም/ /ን/ /ኝ/
፭. ጎናዊ፡- /ል/ /ር/
፮. ከፊል አናባቢ፡- /ው/ /ይ/

## 2. አናባቢ ድምጸ-ልሳናት

የአንደበት አካላት በማይነካኩበት ጊዜ የሚፈጠሩ ድምጾች አናባቢ ድምጸ-ልሳናት ይባላሉ፡፡ አናባቢ ድምጸ-ልሳናት ከተናባቢዎቹ የሚለዩበት ከሳንባችን የሚነሳው አየር ልቅ ሆኖ ሲወጣ የሚፈጠሩ በመሆናቸውና ሲጠሩ (ሲባሉ) ባላቸው የማስተጋባት እንዲሁም ከተናባቢዎች የበለጠ የመሰማት ባህሪ ነው፡፡ የአማርኛ አናባቢ ድምጸ-ልሳናት የሚከተሉት ናቸው፡፡

/አ/ /ኡ/ /ኢ/ /ኣ/ /ኤ/ /እ/ /ኦ/

ጌታሁን አማረ (1989፡ 2-5)

## ፩. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ።

1. አማርኛ ቋንቋ ስንት ተናባቢ ድምጸ ልሳናት አሉት?
2. /ቭ/ ድምጽ እንደ መሠረታዊ አማርኛ ተናባቢ አይቆጠርም፤ ለምን ይመስላችኋል?
3. የአማርኛ ቋንቋ አናባቢ ድምጸ-ልሳናት ስንት ናቸው?
4. አናባቢ ድምጸ-ልሳናት ከተናባቢ ድምጸ-ልሳናት የሚለዩበት ባህሪ ምንድን ነው?
5. አማርኛ ቋንቋ በጠቅላላው ምን ያህል ድምጸ-ልሳናት አሉት?

## ፪. የሚከተሉትን ድምጸ-ልሳናት መካነ-ፍጥረትና ባህርየ-ፍጥረት ግለጹ።

*ምሳሌ፡-*

| ድምጸ-ልሳን | መካነ-ፍጥረት | ባህርየ-ፍጥረት |
|---|---|---|
| ም | ከናፍራዊ | ሰርናዊ |
| ግ | ትናጋዊ | እግድ |

| ተራ ቁ. | ድምጸ-ልሳን | መካነ-ፍጥረት | ባህርየ-ፍጥረት |
|---|---|---|---|
| 1 | ዥ | | |
| 2 | ጭ | | |
| 3 | ል | | |
| 4 | ው | | |
| 5 | ጥ | | |
| 6 | ህ | | |

## የድምጸ-ልሳናት አቀነጃጀት

1. የተናባቢና የአናባቢ ድምጸ ልሳናት ቅንጅት ቀለምን የሚያስገኝ ሲሆን፣ ቀለም ትርጉም ሊኖረውም ላይኖረውም ይችላል። ቀለም የሚያሰኘው አንድ አናባቢ ብቻውን ወይም ከተናባቢ (ዎች) ጋር ሆኖ አንድ ቅንጅታዊ አካል መፍጠሩ ነው። በቀለም መዋቅር አናባቢው ድምጸ-ልሳን አይቀሬ ነው።

   ምሳሌ፡- 1. በግ [ብኧግ]

   2. ላም [ልኣም]

   3. ድመት [ድእም-ምኧት]

በምሳሌ 1. እና 2. እንደሚታየው ሁለቱም ቃላት በሦስት በሦስት ድምጸ-ልሳናት የተዋቀሩ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ጊዜ ቀለምም ቃልም ሆነው መገኘታቸው ብቻ ሳይሆን ትርጉምም አላቸው። በምሳሌ 3. ደግሞ ቃሉ አንድ ቢሆንም፣ በሁለት ቀለሞችና በስድስት ድምጸ-ልሳናት ተቀናጅቷል። ቀለሞቹ በተናጠል ሲታዩ እንደ ምሳሌ 1. እና 2. የየራሳቸው ትርጉም የላቸውም።

2. አንድ ድምጸ-ልሳን ረዥም ወይም ጠባቂ የሚባለው ንበቱ ጥብቅ ካልሆነው ድምጸ-ልሳን የበለጠ ጊዜ መውሰዱ ነው። ለምሳሌ፣ “አመል” እና “ድመት” ከሚሉትን ቃላት ወስደን በድምጸ-ልሳናዊ አጻጻፍ ጽፈን እንመልከት፣

   አመል [ኣ**ም**ኧል]

   ድመት [ድእ**ምም**ኧት]

በግልጽ እንደሚታየው “አመል” በሚለው ቃል /**ም**/ አይጠብቅም፤ የሚወስደውም ጊዜ “ድመት” በሚለው ቃል ውስጥ ካለው /**ምም**/ ያነሰ ነው። ይህንን ለማወቅ ሁለቱንም ቃላት ደጋግሞ በማንበብ (በማለት) መለየት ትችላላችሁ። ይህ የጥብቀት ሁኔታ በቃላቱ የቀለም አወቃቀር ላይም ልዩነት ያስከትላል፤ ”አመል” የሚለው በቀለማዊ አጻጻፍ [ኣ-**ም**ኧል] ሲሆን፣ ድመት የሚለው ደግሞ [ድእ**ም-ም**ኧት] ይሆናል። በዚህ መሰረት የጠበቀው /**ምም**/ አንዱ በመጀመሪያው ቀለም መጨረሻ

ሲገኝ፣ አንዱ በሁለተኛው ቀለም መነሻ ላይ የቀለሙ ከፋች ሆኖ ይታያል፡፡

3. ቀለም የምንለው በአማርኛ ስርአተ ጽህፈት ውስጥ ከምናውቀው ቀለም የተለየ ነው፡፡ ምክንያቱም በስርአተ ጽህፈቱ ውስጥ ያለው ቀለም የአንድ ተናባቢና የአንድ አናባቢ ቅንጅትን በአንድ “ቀለም” (ሆሄ) ስለሚወክል ቢመሳሰልም፣ እዚህ ያለው ቀለም ግን በውስጡ ከአንድ ተናባቢ ድምጸ-ልሳን በላይ ስለሚይዝና ትርጉምም ሊኖረው ስለሚችል ነው፡፡

ጌታሁን አማረ (1989፡ 20-21)

**፫. የሚከተሉትን ቃላት፣ ሐረጋትና ዓረፍተነገሮች በምሳሌው መሠረት በድምጸ-ልሳናዊ አጻጻፍ ጽፋችሁ አሳዩ፡፡**

**ምሳሌ፡-** 1. መከራ [ምኧክኧርኣ]

2. ልፋት [ልእፍኣት]

3. ከመረ [ክኧምምኧርኧ]

4. አስቴር አረጋን ጠላችው፡፡ [ኣስትኤር ኣርኧግግኣን ጥኧልልኣችው]

1. ጎጆ __________________________
2. ለጠፈ ________________________
3. ጥገና _________________________
4. ለመነ _________________________
5. ደለደለ _______________________
6. የሱፍ ክር_______________________
7. ስካር ያዋርዳል፡፡ ________________
8. አባት መካሪ ነው፡፡ _______________
9. እናት ምትክ የላትም፡፡ _____________

**፬. የሚከተሉትን ቃላት፣ ሐረጋትና ዓረፍተ ነገሮች በምሳሌው መሰረት በቀለማዊ አጻጻፍ ጽፋችሁ አሳዩ፡፡**

***ምሳሌ፡-*** 1. ሰረቀ [ስኧር-ርኧ-ቅኧ]፣ (ሦስት ቀለሞች)

2. ዳኛ [ድኣኝ-ኝኣ]፣ (ሁለት ቀለሞች)

3. ገመገመ [ግኧ-ምኧግ-ግኧ-ምኧ] (አራት ቀለሞች)

4. ከበደ አረጋን ፈልጎ አጣው፡፡ [ክኧብ-ብኧ-ድኧ ኣ-ርኧግ-ግኣን ፍኧል-ልእ-ግኦ ኣጥ-ጥኣው] (አስራ አንድ ቀለሞች)

1. በቀለ ________________________ (_____ቀለሞች)
2. ለከፈ ________________________ (_____ቀለሞች)
3. ለቀመ ________________________ (_____ቀለሞች)
4. ቀባጠረ ________________________ (_____ቀለሞች)
5. ተሳሰረ ________________________ (_____ቀለሞች)
6. የገና ዳቦ ________________________ (_____ቀለሞች)
7. አበበ ስጋውን መተረ፡፡ _____________ (_____ቀለሞች)

**፭. የሚከተሉት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፤ መዝገበ ቃላት ተጠቅማችሁ ቀጥተኛ ፍቻቸውን ስጡ፡፡**

***ምሳሌ፡-*** ህልውና = ኑሮ፣ የመኖር ባህርይ

ቅርስ = 1. የተካበተ ሀብት፣ ጥሪት

2. እንደሀውልት፣ ህንፃ፣ የዕደጥበብ ውጤቶች፣ … የመሳሰለ የአንድን ሀገር ጥንታዊ ታሪክና ባህል የሚያንጸባርቅ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፈና የሚተላለፍ ቋሚ መረጃ፡፡

| | |
|---|---|
| 1. ሰላ | 6. ረጃት |
| 2. ባህርይ | 7. ክስተት |
| 3. ሁነት | 8. ተዋደደ |
| 4. ታሪክ | 9. ባህል |
| 5. ትውፊት | 10. ተግባቦት |

፮. ከላይ በተራ ቁጥር ፩ በሰፈሩት ቃላት ዓረፍተ ነገር በመሥራት ቀጥተኛ ፍቻቸውን አሳዩ፡፡

# የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የቋንቋና ጽሕፈት ምንነት፣ ግንኙነትና ልዩነት እንዲሁም የጽሕፈት አነሳስና በየዘመናቱ ያስፈባቸው የእድገት ደረጃዎች ተወስተዋል፡፡ በዚህ መሰረት ቋንቋ ወይም ንግግር በዘፈቀደ የተፈጠረ መግባቢያ መሆኑንና ተስይቶ ከሚታወቅባቸው ባህርያቱ መካከል ሰብአዊነቱ፣ ስርአታዊነቱ፣ አንደበታዊነቱ፣ ዘፈቀዳዊነቱና ትእምርታዊነቱ ተጠቃሽ መሆናቸውን ተመልክተናል፡፡ በአፈጣጠሩም ከጽሕፈት ቀደምት እንደነበርና የጽሕፈት አነሳስ ከቋንቋ ጋር ሲተያይ የቅርብ ጊዜ ክስተት መሆኑን ተረድተናል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በዋሻ ውስጥ ስዕሎች፣ በጥንት የመኖሪያ ቤት ፍርስራሾች አካባቢ የተገኙ ማስረጃዎች በጠቆሙት መሰረት ከቋንቋ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌለውና (የጽሕፈት ምልክቶች በቀጥታ ድምጾችን ወይም ቃላትን ወክለው የማይገኙበት) በኋላ ስታየው እውነተኛው ጽሕፈት መነሻ የነበረው ስዕላዊ አጻጻፍ ዘዴ የተጀመረው በግምት ከዛሬ ሃያ ሺህ ዓመት በፊት እንደነበር ተገንዝበናል፡፡ ከስዕላዊ አጻጻፍ ዘዴ በኋላ ከቋንቋ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የነበራቸውና ከዛሬ አምስት ሺህ ዓመት በፊት አንስቶ በተከታታይ የታዩት የጽሕፈት ዘዴዎች በቅደም ተከተል ቃላዊ፣ ቀለማዊና ፊደላዊ የጽሕፈት ዘዴዎች እንደነበሩም ተመልክተናል፡፡

የሀገራችንን የግዕዝ ፊደል በተመለከተም ከክርስቶስ ልደት በፊት በሦስት መቶ ዓመተ ዓለም አካባቢ በጥንት አክሱማውያን አማካይነት ከሳባ ፊደል ለግዕዝ እንደሚስማማ ተደርጎ የተወሰደ እንደነበርና በግዕዝ በኩል ወስደው አማርኛን ጨምሮ ሌሎች ኢትዮ-ሴማዊ ቋንቋዎች እንደሚስማማቸው መለስተኛ ለውጥ እያደረጉ እንደሚጠቀሙበት ተረድተናል፡፡

ስለ አማርኛ ቋንቋ ድምጸ-ልሳናት ባነሳንበት ክፍል፣ ሁሉም ተናባቢ ድምጸ-ልሳናት አየር በተለያዩ የአንደበታችን ክፍሎች እየታገደና እየተለቀቀ በሚወጣ ጊዜ የሚፈጠሩ መሆናቸውን፤ በአንፃሩ አናባቢ ድምጸ-ልሳናት አፈጣጠራቸው ከምላስና ከከንፈር እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ ሆኖ አየርን የማያግድ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ አናባቢ ድምጸ-ልሳናት ከተናባቢዎቹ የሚለዩበትም ከሳንባችን የሚነሳው አየር ልቅ ሆኖ ሲወጣ የሚፈጠሩ በመሆናቸውና ሲጠሩ ባላቸው የማስተጋባት እንዲሁም ከተናባቢዎች የበለጠ የመሰማት ባህሪ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡

የተናባቢና የአናባቢ ድምጸ-ልሳናት ቅንጅት ቀለምን የሚያስገኝ መሆኑን፣ ቀለም ትርጉም ሲኖረውም ሳይኖረውም እንደሚችልና ቀለም የሚያሰኘው አንድ አናባቢ ብቻውን ወይም ከተናባቢ(ዎች) ጋር ሆኖ አንድ ቅንጅታዊ አካል መፍጠሩ እንደሆነ አይተናል፡፡ የድምጸ-ልሳናዊና የቀለማዊ አጻጻፍ ስልትንም በለዩናቸው የአማርኛ አናባቢና ተናባቢ ድምጸ-ልሳናትን በመጠቀም ተስማምደናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

፩. ስለቋንቋና ጽሕፈት ምንነት፣ አጀማመርና አገልግሎት ምን ተረዳችሁ?
፪. የቀለም፣ የሆሄና ፊደል አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?
፫. አማርኛ ቋንቋ የሚጠቀምበት የአጻጻፍ ዘዴ ምን ተብሎ ይታወቃል?
፬. "አንቀጽ ስለአንድ ሐሳብ ብቻ ያወራል" ሲባል፣ ምን ማለት ነው?
፭. የሚከተሉትን ድምጾች መካነ-ፍጥረትና ባህርየ-ፍጥረት ግለጹ።

| ተራ ቁ. | ድምጸ-ልሳን | መካነ-ፍጥረት | ባህርየ-ፍጥረት |
|---|---|---|---|
| 1 | ስ | | |
| 2 | ች | | |
| 3 | ዕ | | |
| 4 | ይ | | |
| 5 | ቅ | | |
| 6 | ክ | | |

፮. የሚከተሉት ቃላት በውስጣቸው የያዙትን የቀለም ብዛት ግለጹ።

1. የደስታ ______________
2. የክብር ______________
3. ድምጾች ______________
4. አናባቢ ______________
5. ተናባቢ ______________

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፉ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተራ ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የቋንቋና ጽሕፈት ምንነትንና አጀማመርን ማስረዳት ችያለሁ፡፡ | | | |
| 2 | በጽሕፈትና በቋንቋ መካከል ያለውን ግንኙነትና ልዩነት በዝርዝር ተገንዝቤአለሁ፡፡ | | | |
| 3 | አናባቢና ተናባቢ ድምጾችን ለይቻለሁ፤ ቃላትን በድምጸ-ልሳናዊና ቀለማዊ የአጻጻፍ ስርአት መጻፍ ችያለሁ፡፡ | | | |
| 4 | ለቃላት ቀጥተኛ ፍች ሰጥቻለሁ፡፡ | | | |
| 5 | የቃል ንግግር ዝግጅትና አቀራረብ መመሪያን ተከትዬ የቃል ንግግር አድርጌያለሁ፡፡ | | | |
| 6 | የመረጃ ምንጮችን በማገላበጥ ያገኘሁትን መረጃ ክፍል ውስጥ ማቅረብ ችያለሁ፡፡ | | | |
| 7 | የተለያዩ የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልቶችን ተጠቅሜ አንቀጽ አስፋፍቻለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ቅርሶቻችን

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡- ተማሪዎች! ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- ✓ በሀገራችን ስለሚገኙ ቅርሶቻችን ዓይነት፣ ጥቅምና አያያዝ ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ በዐረፍተ ነገር ውስጥ የቃል ክፍሎችን ሙያ በመለየት ታሳያላችሁ፡፡
- ✓ የቃላትና የሐረጋትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ዓረፍተነገር በመሥራት ታሳያላችሁ፡፡
- ✓ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅማችሁ ያገኛችሁትን ሐሳብ ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ መመሪያዎችን ተከትላችሁ የሚቀርብላችሁን ጽሑፍ በማሳጠር ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ ዘገባ ታቀርባላችሁ፡፡
- ✓ ውይይት ታካሂዳላችሁ፡፡

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

፩. ከዚህ ቀጥሎ "ቅርሶቻችን" በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ጽሑፍ ታነባላችሁ፡፡ ከዚያ በፊት ግን በየግላችሁ ስለቅርሶች ዓይነት ጥቅምና አያያዝ በእርግጠኝነት የምታውቁትን፣ እርግጠኛ ያልሆናችሁበትንና፣ ስለቅርሶች ማወቅ የምትፈልጉትን እንድትዘረዝሩ ተከታዩ ሰንጠረዥ ቀርቦላችኋል፡፡ ሰንጠረዡን በደብተራችሁ ላይ በማስፈር በየረድፉ ነጥቦችን በአጫጭር ሐረጋት በመጠቀም በአስተዋጽኦ መልክ ጻፉ፡፡ ምንባቡን ካነበባችሁ በኋላ ደግሞ አዲስ የተገነዘባችሁትን ፍሬ ነገር አስፍሩ፡፡

| ስለቅርሶች | | | |
|---|---|---|---|
| የማውቀው | እርግጠኛ ያልሆንኩበት | ማወቅ የምፈልገው | ካነበብኩ በኋላ በአዲስነት የተገነዘብኩት |
| | | | |

፪. በጥንድ በመሆን ከላይ በሰጣችኋቸው መልሶች ላይ ተወያይታችሁ፣ የምትመሳሰሉባቸውንና የምትለያዩባቸውን መልሶች ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡

፫. ቅርሶቻችን በሚል ርዕስ የቀረበውን ጽሑፍ በየግል ለማንበብ የሚሰጣችሁ ጊዜ ስምንት ደቂቃ ብቻ ነው፡፡ ንባብ ከመጀመራችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በሚገባ መረዳታችሁን አረጋግጡ፤ ጥያቄዎቹን በአእምሮአችሁ በመያዝም መልሶቻቸውን ከምንባቡ ማግኘት ይጠበቅባችኋል፡፡

1. ግዝፈት ያለው ቅርስ በስንት ይከፈላል?
2. የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት በየትኛው የቅርስ ቡድን ውስጥ ይመደባሉ?
3. ታሪካዊና ባህላዊ አልባሳት በየትኛው የቅርስ ምድብ ውስጥ ይካተታሉ?
4. የቅርሶችን ጉዳትና ብልሽት የሚያስከትሉ አራት ሰው ሠራሽ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?
5. ሁለቱ ዋና ዋና የቅርስ ጉዳት ምንጮች ምን ምን ናቸው?

# ቅርሶቻችን

ቅርስ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲተረጎም፣ የሕዝቦች ማንነት የሚገለጽበትና የረጅም ዘመን ባህላቸውንና ታሪካቸውን እንዲገነዘቡ የሚረዳ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብት ነው፡፡ ቅርስ ከምንጩ አንፃር ባንድ በኩል በተፈጥሮ የታደልነውን ተፈጥሮአዊ ቅርስ ሲመለከት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ካለፈው ትውልድ የወረስነውን የሰዎች የፈጠራ ሥራን፣ ባህላዊ እና ታሪካዊ ውጤቶችን የሚመለከት ነው፡፡ ሰው ሠራሽ፣ ታሪካዊና ባህላዊ የሆነው ቅርስ ግዝፈት ሊኖረውም ላይኖረውም ይችላል፡፡ የሀገራችን የቅርስ ጥናትና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር ፪፻፱/፲፱፻፺፪ የቅርስን ቁሳዊና መንፈሳዊ ይዘት ሲያብራራ "ቅርስ ማለት በቅድመ ታሪክና በታሪክ ዘመን የሰው ልጅ የፈጠራና የሥራ እንቅስቃሴ ውጤት የሆነ፣ የተፈጥሮ የለውጥ ሂደትን የሚገልጽና የሚመሰክር በሳይንስ፣ በታሪክ፣ በባህል፣ በስነጥበብና በዕደጥበብ ይዘቱ ከፍተኛ ተፈላጊነትና ዋጋ ያለው ማንኛውም ግዙፍነት ያለውና የሌለው ነገር ነው" ይለዋል፡፡


ሰው ሠራሽ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርስ ግዝፈት ያለውና የሌለው ተብሎ ለመከፈል የራሱ መመዘኛዎች አሉት፡፡ ግዝፈት ያለው ቅርስ ቀደምት አባቶችና እናቶች መሠረታዊና እያደገ የሚሄድ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ሠርተውትና ተጠቅመውበት ትተውት ያለፉትን በዓይን ሊታይ በእጅ ሊዳሰስ የሚችለውን ሁሉ አጠቃሎ ይይዛል፡፡ በአንጻሩ ግዝፈት የሌለው ቅርስ፣ በእጅ ለመዳሰስ የሚያዳግት ነገር ግን፣ በዓይን ለመታየትና በጆሮ ለመስማት የሚችል ሲሆን፣ የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ልዩ ልዩ ትርኢቶችና ጨዋታዎች፣ የጋብቻና የሀዘን ስነስርዓቶችና ተመሳሳይ የማህበረሰቡ ወግና ልማዶች ተጠቃለው የሚመደቡበት ነው፡፡

ግዝፈት ያለው ቅርስ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ተብሎ በሁለት ሰፊ ምድብ ይከፈላል፡፡ የማይንቀሳቀስ ቅርስ በመሠረት የተገነባ ወይም ከቋሚ ነገር ጋር የተያያዘ ስለሆነ ማንቀሳቀስ አይቻልም፧ ለቅርሱ ደህንነት ሲባልም የማንቀሳቀስ ድርጊት መፈጸም በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡ እንዲህ

ያለው ቅርስ የሚጠናው፣ በእንክብካቤ የሚጠበቀውና ለኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚውለው ባለበት ቦታ ላይ ብቻ ነው፡፡ በሀገራችን የሚገኙ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፣ የአክሱም ሀውልቶች እና የጎንደር ቤተመንግሥቶች ለአብነት የሚጠቀሱ የማይንቀሳቀሱ ቅርሶች ናቸው፡፡ የሚንቀሳቀስ ቅርስ ለጥናትና ምርምር፣ ለባህል ልውውጥና ለመሰል ዓላማዎች ከቦታ ቦታ በቀላሉ ማዛወር የሚቻለውን ግዙፍነት ያለው ቅርስ ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ የሚንቀሳቀስ ቅርስ በአብዛኛው የሃይማኖት መገለጫዎችን፣ ታሪካዊና ባህላዊ አልባሳትን ያካተተ ሲሆን፣ ለስጦታ እቃዎች ቅጂ ሥራ መሠረት በመሆን ያገለግላል፡፡

አንድ ነገር በቅርስነት እንዲመዘገብና እንዲጠበቅ በቅድሚያ የቅርስ መመዘኛዎችን አሟልቶ መገኘት ይኖርበታል፡፡ መመዘኛዎቹም በእድሜው ጥንታዊ መሆን፣ ለሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር ከፍተኛ ጠቀሜታ መስጠት፣ በሥነ ጥበባዊ ይዘት ድንቅ መሆን፣ የተሠራበት ቁስ የማይገኝ መሆንና ሠሪው ግለሰብ በሕይወት ባለመኖሩ ምክንያት ሥራው የቆመ (በጅምር የቀረ) የሚሉ ናቸው፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች የሚያሟላ ቅርስ ጠቀሜታው ላንድ ግለሰብ ወይም ለተወሰነ የህብረተሰብ ክፍል ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ዜጋ በመሆኑ፣ በህዝቡ ተጠብቆና ተረማምዶ ለተከታዩ ትውልድ እንዲደርስ መደረግ አለበት፡፡

ባግባቡና በሚፈለገው ደረጃ የተጠበቀ ቅርስ ጠቀሜታው ፈርጀ-ብዙ ነው፡፡ በቱሪዝም ዘርፍ ገቢ በማስገኘት ኢኮኖሚን ከመደገፉም በላይ፣ በህዝቦች መካከል የእውቀትና የልምድ ልውውጥ እንዲደረግ እንደስንስለት ሆኖ ያገለግላል፡፡ በፈጠራ ችሎታ መነሻነት የሚሰጠው አገልግሎትም በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ ታዋቂ የሀገራችን የፈጠራ ሥራዎች ካለፈው ትውልድ የቅርስ ሀብት የፈጠራ ቴክኒክ እውቀትን በመቅሰምና ይበልጥ አሻሽሎ በመፍጠር የተገኙ ናቸው፡፡ ቅርስ የብሔራዊ ማንነት መለያ ማሀተም በመሆን በኩል የላቀ አገልግሎት አለው፤ መስዋዕትነትን ለመዘከር የቆሙ ሀውልቶች፣ ጠላት ድል የሆነባቸው ታሪካዊ ስፍራ ዎች፣ በጦርነት ጊዜ የተዜሙ ሽለላዎች፣ ግጥሞች፣ ድራማዎች፣ ወዘተ. የብሔራዊ ማንነት አሻራ በመሆን ያገለግላሉ፡፡




ከላይ እንደተገለጸው ሰፊ ጥቅም የሚያስገኙ ቅርሶች በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ጉዳትና ብልሽት ይደርስባቸዋል፡፡ የሰው ሠራሽ ጥፋቶች ከሚያደርሱ ምክንያቶች ቀዳሚው የዲፕሎማቶች፣ የተመራማሪዎችና የሃይማኖት መልዕክተኞች እንቅስቃሴ ነው፡፡ ሀገራችን ባላት የውጪ ግንኙነት ሳቢያ ዲፕሎማቶችን፣ ተመራማሪዎችን፣ የሃይማኖት መልእክተኞችንና ቱሪስቶችን ተቀብላ ታስተናግዳለች፡፡ በዚህ እንቅስቃሴ የቅርሶች መጎዳትና መጥፋት ሊከሰት ይችላል፡፡ ሁለተኛው ጦርነት ሲሆን፣ በሀገራችን በተለያዩ ዘመናት በተካሔዱ የእርስ በእርስ ግጭቶችና ከውጪ ወራሪዎች ጋር በተደረጉ ጦርነቶች አያሌ ቅርሶችን አጥተናል፡፡ ሦስተኛው ሽያጭ ነው፡፡ በተለያዩ ጊዜያት የተሰሩ ጥንታዊ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች በክብር ከተቀመጡበት አብያተክርስቲያናት፣ ሙዚየሞችና መሰጊዶች እየወጡ በህገወጦች ተሸጠዋል፡፡ አራተኛውና የመጨረሻው የዜጎች ግንዛቤ ማነስ ነው፡፡ ብዙ ዜጎች የቅርሶች ጠቀሜታ

ግንዛቤ ስለሌላቸው የተቀበረ ሀብት ፍለጋ፣ አብያተ ክርስቲያናትንና መስጊዶችን ጥገና በሚያደርጉበት ጊዜ ውድመት ተከትሏል፡፡ አንዳንዶችም የዋሻ ውስጥ ስዕሎችን፣ ሀውልቶችንና የድንጋይ ላይ ጽሑፎችን እየሰበሩ ለአጥር አገልግሎት ሲያውሉ፤ የጥንት ግብረ ህንጻዎች ያረፉበትን ግቢ ለእርሻ ሥራ፣ ለከብት ማስፈሪያና ለመጸዳጃ እንዲውል በማድረግ ሲያወድሙ ይስተዋላል፡፡ የተፈጥሮ ጥፋቶችም ቅርሶቻችንን ከሚያወድሙ ምክንያቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የእድሜ ሂደት፣ ቅዝቃዜ፣ እርጥበት፣ ዝናብ፣ ፀሐይ፣ ነፋስ፣ የእሳት ቃጠሎ፣ ወዘተ. በየዘመናቱ በቅርሶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከተሉ ናቸው፡፡

ከላይ የተመለከትናቸው የቅርስ ጥፋት መንስኤዎች ዘርፈ-ብዙ ጥቅም የሚሰጡትን የሀገራችንን ቅርሶች ያወደሙና የሚያወድሙ በመሆናቸው፣ በጥናት ላይ የተመሠረተ ተገቢ የሚባል የቅርስ ጥበቃ ስልት ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በሀገራችን ካሉ ዋና ዋና የቅርስ ጥበቃ ስልቶች መካከል ጥቂቶቹ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ውጪ ሀገር የተወሰዱ ቅርሶቻችንን ማስመለስ፤ ቅርሶቻችንን ለይቶ አውቆ ለመጠበቅ በሚያስችል መልክ ምዝገባ ማካሔድ፤ ጠንካራ፣ የተቀናጀና የተዋጣለት የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋትና በየደረጃው ተግባራዊ ማድረግ፤ ህብረተሰባችን የራሱን ቅርሶች እንዲጠብቅና እንዲንከባከብ መደበኛና መደበኛ ባልሆነ መንገድ መቀስቀስ ማስተማር ናቸው፡፡ በነዚህና በሌሎችም ስልቶች በመጠቀም እስከ ዛሬ በተካሄዱ ጥረቶች የአክሱም ሀውልት ማስመለስን ጨምሮ በርካታ ውጤቶች ቢመዘገቡም ከቅርስ ሀብታችን መጠን፣ እድሜ ጠገብነት፣ ብርቅዬነትና ተፈላጊነት አንጻር ገና ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል፡፡

*(ጥር 26/ 2000 በቅርስ ምዝገባና ቁጥጥር መምሪያ ስተካሔደ ሲምፖዚየም ከተዘጋጀ ጽሑፍ ተሻሽሎ የቀረበ)*

# መልመጃዎች

## ክፍል አንድ:- አንብቦ መረዳት

**፩. ከዚህ ቀጥሎ ምንባቡን መሠረት አድርገው ለቀረቡ ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ::**

1. ቁሳዊ ሀብት ምንድን ነው? በምሳሌ በማስደገፍ አብራሩ::
2. መንፈሳዊ ሀብት ምንድን ነው? በምሳሌ የተደገፈ ማብራሪያ ስጡ::
3. በቁሳዊ ሀብትና በመንፈሳዊ ሀብት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት አስረዱ::
4. ቅርስን አዋጅ በመደንገግ ብቻ በተሟላ መልኩ ከጥፋት ለመጠበቅ ይቻላል ብላችሁ ታምናላችሁ? ሐሳባችሁን በአስረጅ አስደግፋችሁ ግለጹ::
5. የቅርስ ጥበቃ አዋጅ ለአንድ ሀገር የሚሰጠው ጠቀሜታ ምንድን ነው?
6. ቅርስ የመጠበቅ ሀላፊነት የየትኛው ወገን ይመስላችኋል? ለምን?

**፪. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን "እውነት" ስህተቱን "ሐሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያታችሁን በቃል አስረዱ::**


1. ግዝፈት የሌላቸው ቅርሶች ዋነኛ መለኪያ በመጠን አነስተኛ መሆንና ከቦታ ቦታ ለማዘዋወር ምቹነት ነው::
2. በቅርሶች አመዳደብ መሰረት፤ ቀደምት አባቶቻችንና እናቶቻችን ሠርተውና ተጠቅመውበት ትተውት ያለፉት በዓይን የሚታይና በእጅ የሚዳሰስ "ግዝፈት ያለው ቅርስ" በሚለው ክፍል ይመደባል::
3. ለጥናትና ምርምር፤ ለባህል ልውውጥ ከቦታ ቦታ በቀላሉ ሊዛወሩ የሚችሉ ቅርሶች ሁሉ ግዝፈት ባለው ቅርስ ምድብ ስር የሚጠቃለሉ ናቸው::
4. ማንኛውም ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጣ ንብረት በቅርስነት ተመዝግቦ ልዩ ጥበቃና እንክብካቤ ሊደረግለት ይገባል::

5. የጥንታዊ አብያተክርስቲያናትና መስጊዶች እድሳት ከመከናወኑ በፊት በጥንታዊ ቅርሶች ላይ ጉዳት ማስከተልና አለማስከተሉ በባለሙያ መጠናት ይኖርበታል።
6. በጦርነት ጊዜ የተዘሙ ሽለላዎች በቅርስነት ለመመዝገብ የሚያበ ቃቸውን መስፈርት ያሟላሉ።
7. ለቅርሶች መጥፋትና ብልሽት ቀዳሚው ምክንያት የዲፕሎማቶች፣ የተመራማሪዎችና የሃይማኖት መልእክተኞች እንቅስቃሴ ነው።

ፎ. ቅርሶቻችን በሚል ርዕስ ያነበባችሁት ጽሑፍ ሰባት አንቀጾችን ይዟል። ከዚህ በታች በ "ለ" ስር የቀረቡትን የየአንቀጾችን ዋና ፍሬ ሐሳቦች በ "ሀ" ስር ከተሰጡት የአንቀጾቹ ቁጥሮች ጋር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. _____ አንቀጽ አንድ | ሀ. የቅርስ ስርቆት |
| 2. _____ አንቀጽ ሁለት | ለ. የቅርስ ጉዳትን የሚያስከትሉ ነገሮች |
| 3. _____ አንቀጽ ሦስት | ሐ. የቅርስ ጥበቃ ስልቶች |
| 4. _____ አንቀጽ አራት | መ. የቅርስ አገልግሎትና የሚያስገኘው ጥቅም |
| 5. _____ አንቀጽ አምስት | ሠ. የቅርስ ምንነት |
| 6. _____ አንቀጽ ስድስት | ረ. የቅርስ ምዝገባ መመዘኛዎች |
| 7. _____ አንቀጽ ሰባት | ሰ. ቋሚ ቅርስን ማንቀሳቀስ ክልክል ስለመሆኑ |
| | ሸ. የቅርሱ እድሜ ጥንታዊ መሆን እንዲጠበቅ ያስመርጠዋል። |
| | ቀ. የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ቅርስ ምንነት |
| | በ. ግዝፈት ያለውና የሌለው ቅርስ ምንነት |

፬. ተከታዩ ቻርት የቅርሶችን አከፋፈል እንድታሳዩበት የቀረበ ነው:: በጥንድ በመሆን እየተወያያችሁ በምንባቡ መሰረት የተጓደሉትን የቅርስ ዓይነቶች ሳጥኖቹ ውስጥ ሙሉ::




፭. የሚከተሉት ከምንባቡ የወጡ ቃላታና ሀረጋት የያዙትን ፍች አብራሩ::

1. ቁስ
2. መንደፍ
3. መተግበር
4. በዘመነ መሳፍንት
5. አኮኖሚያዊ ፍላጎት
6. መስዋእትነትን መዘከር
7. የሀይማኖት መገለጫዎች
8. ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች
9. የብሔራዊ ማንነት መለያ ማህተም
10. ካለፈው ትውልድ የተወረሰ የሰዎች የፈጠራ ሥራ

፮. በተራ ቁጥር ፭. ላይ ለሰፈሩ ቃላትና ሐረጋት የሰጣችሁትን ፍች ግልጽ የሚያደርጉ ዓረፍተነገሮች ሥሩባቸው::

## ክፍል ሁለት:- መናገር

፩. ስለቅርሶቻችን በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በጋዜጣና በመጽሔት የተላለፉ መልእክቶችን በመከታተልና በምዕራፍ አንድ ስለ ቃል ንግግር የተሰጣችሁን መመሪያ በመጠቀም፣ መረጃ ሰብስባችሁ በተከታዩ ክፍለ ጊዜ ለክፍል ጓደኞቻችሁ የአስር ደቂቃ ንግግር አድርጉ:: (ስለቅርሶቻችን ከመገናኛ ብዙሃን

የተሳለፉ መልእክቶችን ማግኘት ያልቻላችሁ ተማሪዎች በአካባቢያችሁ ከሚገኙ የእድሜ ባለጸጎች፣ ከታሪክ መምህራን፣ ወዘተ. ስለቅርሶቻችን አይነት፣ ጥቅምና አያያዝ መረጃ ሰብስባችሁ በመመሪያው መሰረት የአስር ደቂቃ ንግግር ማድረግ ትችላላችሁ::)

፪. መምህራችሁ በሚነግሯችሁ መሠረት ከዚህ በታች በቀርቡላችሁ ነጥቦች ላይ በቡድን ተወያዩ:: በየርዕሱ የምታነሷቸው ሐሣቦች በምሳሌና በጭብጥ የተደገፉ መሆን እንዳለባቸው አትዘንጉ፤ በውይይታችሁ የደረሳችሁበትን በመረጣችሁት ጸሐፊ አማካይነት በቃል ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ::

1. የቅርስ ዓይነቶችና በሀገራችን ያላቸው ይዞታ፣
2. በሀገራችን ከጥንታዊ ቅርሶቻችን የሚገኘው ጥቅም ያለበት ደረጃ፣
3. የሀገራችን ቅርሶች አያያዝና ጥበቃ፣

፫. በቡድን ሆናችሁ ሕገወጥ የቅርስ ዝውውርን ለመቀነስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ አካላት ስለሚያበረክቱት ድርሻ ተወያዩበት፤ የደረሳችሁበትንም ፍሬ ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ::

1. የፌደራልና የክልል ባህል ቢሮዎች፣
2. የጉምሩክ ባለስልጣን መሥሪያ ቤት፣
3. መላው የሀገራችን ዜጎች፣
4. ፖሊስ፣
5. የሃይማኖት ተቋማት (የክርስትና፣ የእስልምና …)

፬. በአካባቢያችሁ የሚገኝ ወይም ከዚህ ቀደም የምታውቁት መስዋዕትነትን ለመዘከር የቆመ አንድ ታሪካዊ ቅርስ ጠቅሳችሁ ስለቅርሱ ዓይነት፣ አያያዝና ስለሚያስገኘው ጠቀሜታ አጭር ማብራሪያ ስጡ::

## ክፍል ሦስት:- መጻፍ

### አኀጽሮተ-ጽሑፍ

፩. በቡድን ሆናችሁ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት መልሳችሁን በአንድ አንቀጽ በመጻፍ አቅርቡ::

1. አንድን ጽሑፍ እንደገና ማሳጠር የሚያስፈልግበት ምክንያት ምንድን ነው?

2. ጽሑፍን በማሳጠር ሂደት የጽሑፉ ዋና መልእክት ሳይዛባ እንዲተላለፍ፣ ጸሐፊው እንዴት ያለ ስልት ቢከተል የተሻለ ይሆናል?

**፪. የሚከተሉትን ሦስት አንቀጾች ሐሳባቸውን ከተረዳችሁ በኋላ በትዕዛዛቸው መሠረት አሳጥራችሁ እንደገና ጻፏቸው፡፡**

1. ተከታዩን አንቀጽ ከሃያ አምስት ባልበለጡ ቃላት አሳጥራችሁ ጻፉ፡፡

አለቃ ዘነብ የቴዎድሮስን ታሪክ የሚጀምሩት በዘመነ መሳፍንት የነበረውን ሁኔታ በመዘርዘር ነው፡፡ ይኸውም አገሪቷን ይቆጣጠሩ የነበሩት ባለስልጣናት ምግባረ ብልሹዎችና ምንም ዓይነት ራእይ የሌላቸው መሆኑን በጽሑፋቸው አስረድተዋል፡፡ በዘመኑ የነበሩ መሳፍንት አገሪቷን በመቀራመት በህዝቡ ላይ በቃላት ተዘርዝሮ የማያልቅ እጅግ ከፍ ያለ በደል ከመፈፀማቸውም በላይ፣ እርስ በእርሳቸው ስምምነት ስለሌላቸው አገሪቷን በጦርነት ሲያምሷት ህዝቡን ቁም ስቅሉን ሲያሳዩት ነበር፡፡ እንዲያውም ፈሪሀ እግዚአብሔር፣ ትክክለኛ ፍርድ፣ ሀቀኝነት ከኢትዮጵያ ምድር ተወግደው በምትካቸው ስካር፣ ቧልት፣ ወዘተ. ሰፍነው እንደነበር ጸሐፊው ገልጸዋል፡፡

*(ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን የዓለማቀፍ ስገልግሎት፣ ቅርስ መጽሔት፣ ሰኔ 1999)*

2. ተከታዩን አንቀጽ ከሃያ ባልበለጡ ቃላት አሳጥርችሁ ጻፉ፡፡

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ሀገራችን የሚገኙ የማይንቀሳቀሱ ቅርሶችን የያዘ ካታሎግ አሳትሟል፡፡ የዚህ ካታሎግ መታተም ሳይታወቁ የቀሩትን ቅርሶቻችንን በማስተዋወቅ ለቱሪዝም አገልግሎት በሰፊው እንዲውሉ ከማስቻሉም በተጨማሪ፣ የኢትዮጵያ ቅርሶችን ማጥናት ለሚፈልጉ ሁሉ የማይናቅ ጠቀሜታ ያበረክታል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይኸው በባለ አራት ቀለም ሆኖ የተዘጋጀው የቅርስ ካታሎግ ለክልሎች፣ ለኤምባሲዎች በውጪ ሀገራት ለተሾሙ የኢትዮጵያ አምባሳደራትና ለተለያዩ መንግሥታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶችና ግለሰቦች ተሰራጭቷል፡፡

*(ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን የዓለማቀፍ ስገልግሎት፣ ቅርስ መጽሔት፣ ሰኔ1999)*

**3. ተከታዩን አንቀጽ ከአስራ አምስት ባልበለጡ ቃላት አሳጥራችሁ ጻፉ፡፡**

ሐረር ማህበራዊ ተቋሞቿ፣ ባህሏ እንዲሁም የአየር ንብረቷ ከሌሎች ከተሞች ለየት እንድትል አድርገዋታል፡፡ ሐረር ቅድመ እንዱስትሪ የከተማ ሕይወትን ለማጥናት አመቺ ስትሆን፤ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በአፍሪካ ቀንድ የእስልምና ትምህርት ማዕከል ነበረች፡፡ የእስልምናን እድገትና ይዘት ከአፍሪካ ቀንድ ከተሞች ጋር ለማወዳደር አመቺ የጥናት ማዕከል ናት፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የራሷ የሆነ የከተማ ባህል ያላት፣ ለነዋሪቿ ምቹ የሆነች፣ በኢትዮጵያ ካሉት ቀደምት ከተሞች አንዷ ናት፡፡

*(ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን የዓለማቀፍ ስገልግሎት፣ ቅርስ መጽሔት፣ ሰኔ 1999)*

**የአንጽርተ-ጽሑፍ ዝግጅት መመሪያ**

አንጽሮተ-ጽሑፍ፣ አንድ ጽሑፍ ያነሳውን ርዕስ ጉዳይ በሰፊው ተመልክቶና በዝርዝር ቃኝቶ፣ የጽሑፉን ፍሬ ነገር ጨምቆ በማውጣት በሚፈለገው መጠን አሳጥሮ እንደገና በጥሩ ቋንቋ መጻፍ ማለት ነው፡፡ ይህ ተግባር የጽሑፉን ዋና ዋና ይዘቶች በጠበቀ አኳኋን በልዩ ጥንቃቄ የሚከናወን ከመሆኑም በላይ፣ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ነጥቦች መከተል፣ የማሳጠር ተግባሩን ስኬታማ ያደርገዋል፡፡

**የዋናውን ጽሑፍ አጠቃላይ ሐሳብ ለመጨበጥ ደጋግሞ ማንበብ**

- ፍሬ ሐሳቦችን የያዙ እንግዳ ቃላት ሲያጋጥሙ ከአውዳቸው ፍቻቸውን ለመረዳት መሞከር፣
- መዝገበ ቃላትን በመጠቀም በጽሑፉ ቃላቱ ከገቡበት አውድ ጋር የሚጣጣም ፍቻቸውን መውስድና ስለፍሬ ነገሩ ግንዛቤን ማዳበር፣

- እያነበቡ አጫጭር ማስታወሻዎችን ሐሳቡ ከሚገኝበት ገጽ ጋር እያጣቀሱ መያዝ፣
- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በፍሬ ሀሣቦቹ ስር በእርሳስ ማስመር ወይም ልዩ ምልክት መጠቀም፣
- ጽሑፉንና የተመዘገበውን ማስታወሻ እያገናዘቡ ዋናውን ሐሳብ መለየት።

**በዚህ መንገድ የዋናውን ጽሑፍ ማእከላዊ ሐሳብ ከተረዳን በኋላ፣**

- የጽሑፉን ዋና ሐሳብ በራሳችን አገላለጽ መጻፍ፣
- ፍሬ ነገሮች ሳይድበሰበሱና ሳይዛቡ ሳቢነትንና ተነባቢነትን ተላብሰው መስፈራቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

**ፎ. ከዚህ በላይ የቀረበውን የአንጽርተ ጽሑፍ መመሪያን ተከትላችሁ ቀጥሎ የቀረበውንና ስለ አሸንዳዬ ባህላዊ ጨዋታ የሚያወሳውን ጽሑፍ በሲሶ (ከሰባ አምስት ቃላት ባልበለጠ) አሳጥራችሁ ጻፉ።**

## የአሸንዳዬ ማህበራዊ ፋይዳ

አሸንዳዬ የባህላዊ ጨዋታ መጠሪያ፣ አሸንዳ ከሚለው የዕጽዋት ስም የመጣ ነው። ለአሸንዳዬ ጨዋታ ለምን ይህ ተክል ብቻ ተመረጠ የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ በተሟላ መልኩ የሚያብራራ ባይገኝም፣ አሸንዳ በሰሜን ኢትዮጵያ (በትግራይና አማራ ክልል) የባህላዊ ጨዋታ መጠሪያ በመሆን ያገለግላል። ይህ ባህላዊ ጨዋታ ከክዋኔው በፊት የራሱ ቅድመ ዝግጅት ያለው ሲሆን፣ ካሉት ዘርፈ ብዙ ማህበራዊ ፋይዳዎች ውስጥ ለማህበራዊ ግንኙነቶች ማስተሳሰሪያ ገመድ በመሆን የሚያበረክተው አገልግሎት ተጠቃሽ ነው።

የአሸንዳዬ ባህላዊ ጨዋታ፣ ማኅበራዊ ግንኙነትን በተለያየ ደረጃ የሚያጠናክር ሲሆን፣ ወላጆች ለልጃገረድ ልጆቻቸው ለአሸንዳዬ ባህላዊ ጨዋታ የሚስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ በተቻለ መጠን ለማሟላት ጥረት ያደርጋሉ፡፡ በተጨማሪም በአሸንዳዬ ባህላዊ ጨዋታ ወቅት ልጃገረዶችን አንፃራዊ በሆነ መንገድ ከቤት ሥራ ነፃ በማድረግ እንዲጫወቱ ይፈቅዳሉ፡፡ በመሆኑም፣ በልጃገረዶችና በወላጆች መካከል ያለው መተሳሰብ ከመቼውም ጊዜ እንዲልቅና ልጃገረዶች በወላጆቻቸው ደስተኛ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

ከቤተሰብ ግንኙነት ባሻገር፣ የአሸንዳዬ ባህላዊ ጨዋታ የዝምድና ግንኙነት እንዲጠናከር አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ልጃገረዶች ጌጣጌጥ የሚዋሱት ከዘመዶቻቸው በመሆኑና አሸንዳዬ ባህላዊ ጨዋታን የሚጫወቱትም በዘመዶቻቸውና በመንደራቸው ባሉ ቤቶች እየተዘዋወሩ በመሆኑ፣ ዘመዶቻቸውና የመንደራቸው ሰዎች ለነሱ ስጦታ ያበረክታሉ፡፡ በዚህ የተነሳም፣ የዝምድናና የመንደር ግንኙነት በአሸንዳዬ ባህላዊ ጨዋታ ወቅት የተጠናከረ ይሆናል፡፡

የአሸንዳዬ ባህላዊ ጨዋታ በልጃገረዶች ጓደኝነት ላይ ያለው አዎንታዊ ተጽእኖ በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ ልጃገረዶች በዚህ ወቅት ብዙ የመቀራረብና ብዙ ሰዓት አብረው የማሳለፍ ዕድል ስላላቸው፣ የጓደኝነት ግንኙነታቸው የተጠናከረ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ የአሸንዳዬ ጓደኞቻቸው ስታገባ ለሰርግ ጤፍ ያበጥራሉ፤ ይፈጫሉ፣ ይጋግራሉ፤ ውሃ ይቀዳሉ፤ ሚዜ ሆነው ዘፍነው ይድራሉ፡፡ ወጣቶች ትዳር ከመሰረቱም በኋላ፣ አንድ ላይ "የማርያም ጽዋ" የሚጠጡ በመሆናቸው የጓደኝነት ትስስሩ ከአሸንዳዬ ጨዋታም ባሻገር የማህበራዊ ቁርኝታቸው መሠረት የሚጣልበት ነው ማለት ይቻላል፡፡

*(ጌታቸው ስንሻው፣ የአሸንዳዬ ባህላዊ ጨዋታ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ፣ ኢንታንጀብል ቅርሳችን ሌላው ገጽታ፣ ሰኔ 23/ 1997፣ ገጽ 96)*

**፩. ቀደም ሲል ስለዘገባ ምንነትና አቀራረብ የተማራችሁትን መሠረት በማድረግ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከአንድ አንቀጽ ባልበለጠ ጽሑፍ መልሱ፡፡**

1. ዘገባ ምንድን ነው?
2. የዘገባ ዓበይት ባህርያት የሚባሉት የትኞቹ ናቸው?
3. የዘገባ ዓይነቶች የሚባሉት ምን ምን ናቸው?
4. ከሚቀርብበት ቅርጽ አንጻር የጽሑፍ ዘገባ ከቃል ዘገባ የሚለየው በምንድን ነው?

**፪. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ቅርሶችን ከጎበኛችሁ በኋላ ስለጉብኝታችሁ ከአራት መቶ ባልበለጡ ቃላት በየግላችሁ ዘገባ በመጻፍ በተከታዩ ክፍለ ጊዜ አቅርቡ፡፡**

1. መምህራችሁ በሚገልጹላችሁ መሠረት በጥንድ ሆናችሁ የጻፋችሁትን ዘገባ በመቀያየር ከዚህ በታች ከቀረበላችሁ የጉዞ ወይም የመስክ ዘገባ አጻጻፍ መመሪያ አንጻር ገምግሙ፤
2. በግምገማው ስለደረሳችሁባቸው ነጥቦች አስተያየት ተለዋወጡና ዘገባችሁን አሻሽላችሁ ጻፉ፡፡

## የጉዞ ወይም የመስክ ዘገባ

ዘገባ፣ ጠቅለል ባለ አነጋገር መደበኛና ኢ-መደበኛ ተብሎ ሊከፈል ይችላል፡፡ የጉዞ ወይም የመስክ ዘገባ በኢ-መደበኛ ዘገባ የሚጠቃለል ሆኖ፣ አንድ የተወሰነ ስፍራ ወይም ክንውን ታይቶ፣ ተጎብኝቶ፣ ተጠንቶና ተመርምሮ ካበቃ በኋላ የሚዘገበውን የሚመለከት ነው፡፡ የጉዞ ወይም የመስክ ዘገባ ስናዘጋጅ የሚከተሉትን ደረጃዎች ተከትለን መጻፍ ይጠበቅብናል፡፡

**1. የዝግጅት ደረጃዎች**

ሀ. ዘገባው የሚጻፍበትን ዓላማ መለየት፣
ለ. በቦታው ተገኝቶ መረጃ መሰብሰብ፣
ሐ. ጠቃሚና ጠቃሚ ያልሆነውን መረጃ መለየት፣
መ. የመረጃውን ትክክለኛነት መፈተሽ፣

ሠ. መረጃውን መገምገም፣

ረ. መረጃውን በመልክ በመልኩ ማደራጀት፣

ሰ. ለዘገባው ርዕስ መስጠት (ርዕሱ የዘገባውን አጠቃላይ መንፈስ የሚያንፀባርቅ መሆኑን፣ አጭር መሆኑን፣ አንባቢውን የሚስብ መሆኑን ማረጋገጥ)፣

ሸ. የዘገባውን የመጀመሪያ ረቂቅ መጻፍ፣

ቀ. ዘገባውን መከለስ፣

በ. የመጨረሻውን ረቂቅ መጻፍ፡፡

## 2. የዘገባው ቅርጽ

የጉዞ ወይም የመስክ ገላጭ ዘገባ በቅርጽ ደረጃ የሚከተሉትን ነጥቦች መዘርዘር ይጠበቅበታል፡፡

ሀ. የዘገባው ርዕስ

ለ. መግቢያ

ሐ. ዝርዝር መግለጫ

መ. መደምደሚያ

ሠ. ቀን

ረ. ፊርማ

ሰ. ዘገባውን የጻፈው ሰው ማንነት

## 3. የዘገባው ይዘት

ሀ. ዘገባው ጉዞውን ወይም የመስክ እንቅስቃሴውን አጠቃላይ መልክ መዳሰስ አለበት፣

ለ. ዘጋቢው ከጉዞው ወይም ከመስክ እንቅስቃሴው ውጪ የሆነ ነገር ላለማስፈር መጠንቀቅ አለበት፣

ሐ. በይዘቱ የጉዞውን ወይም የመስክ እንቅስቃሴውን ዓላማ፣ የተሳታፊዎቹን ዝርዝር ወይም ማንነት የጉብኝቱን ባህሪና የተሳታፊዎቹን አመለካከት መግለጽ ይጠበቅበታል፡፡

መ. በጉዞው ወይም በመስክ እንቅስቃሴው የተገኘ አዲስ ነገር ካለ፣ በዘገባው ውስጥ ተጠቃሎ መቅረብ አለበት፡፡

*(አስም አሸቱ፣ መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ፣1992፣ከገፅ 99-102)*

፮. ከዚህ በላይ የቀረበውን የመስክ ዘገባ አቀራረብ መመሪያ በመከተል በአካባቢያችሁ ስላለው የስፖርት እንቅስቃሴ ተዘዋውራችሁ መረጃ ሰብስባችሁ መምህራችሁ በሚነግሯችሁ መሠረት በቡድን አንድ ዘገባ አቅርቡ።

፯. ቡድን መስርታችሁ ወደምትኖሩበት ቀበሌ በመሄድ፣ በቀበሌው ስር ስለሚተዳደሩ ማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (ትምህርት ቤት፣ ጤና ኬላ፣ የግብርና ማእከል፣ ወዘተ.) የአገልግሎት አሰጣጥ መረጃ በመሰብሰብ ያያችሁትንና የሰማችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ዘግቡ።

## ክፍል አራት:- ስነልሳን

፩. ከዚህ በታች ለቀረቡ ቃላትና ሐረጋት በምሳሌው መሠረት ተቃራኒ ፍች ከሰጣችሁ በኋላ፣ ዓረፍተነገር በመሥራት አሳዩ።

**ምሳሌ:-** ህገ-ወጥ = ህጋዊ

ህጋዊ የስጦታ እቃዎች ነጋዴ፣ ጥንታዊ ቅርሶችን ሳይሆን በማስመሰል የተሰሩ የእደጥበብ ውጤቶችን ይሸጣል።

| | |
|---|---|
| 1. ምግባረ-ብልሹ | 6. ቧልት |
| 2. ግሳፄ | 7. ማሞካሸት |
| 3. መሳፍንት | 8. አዘቦት |
| 4. ቁምስቅል | 9. ሀቀኝነት |
| 5. መቀራመት | 10. ጠፍ ጨረቃ |

፪. ቀጥሎ የቀረቡት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው። በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከሰጣችሁ በኋላ ዓረፍተ ነገር ሥሩባቸው።

**ምሳሌ:-** ልማድ = አመል፣ ባህሪ

ወይኒቱ እየበሉ መዝፈንን ልማድ አድርጋዋለች።

| | |
|---|---|
| 1. አልባሳት | 6. ቅርስ |
| 2. ስነጥበብ | 7. ተረማመደ |
| 3. ፈርጅ | 8. አሻራ |
| 4. አያሌ | 9. የተዋጣለት |
| 5. ትርኢት | 10. መለያ |

ፎ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡ አማራጭ መልሶች ትክክለኛውን ምረጡ፡፡

1. “መንግስታችን ጥንታዊ ቅርሶቻችንን ይጠብቃል፡፡” በሚለው ዓረፍተነገር የተሳቢነት ሙያ ያለው ቃል፣
   ሀ. ቅርሶቻችን ሐ. ይጠብቃል
   ለ. ጥንታዊ መ. መንግሥት
2. “ይህ አገር የገጣሚያን ምድር ነው፡፡” በዚህ ዓረፍተነገር የዘርፍነት ሙያን የተወጣው ቃል የትኛው ነው?
   ሀ. ይህ ሐ. የገጣሚያን
   ለ. ይህ አገር መ. ምድር
3. “የሰው ልጅ ለነፍሱና ለሥጋው ይኖራል፡፡” በሚለው ዓረፍተነገር “ይኖራል” ስለሚለው ቃል ትክክል የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. ሳቢ ግስ በመሆኑ ድርጊት ፈፃሚ ባለቤት ይፈልጋል፡፡
   ለ. ሳቢ ግስ በመሆኑ ተሳቢ ስም ይፈልጋል፡፡
   ሐ. ሳቢ ግስ በመሆኑ ነፍስ ስጋን በተሳቢነት ወስዷል፡፡
   መ. በዐረፍተ ነገሩ የማሰሪያ አንቀጽነት ሙያን ተወጥቷል፡፡
4. “በሀገራችን የንባብና የሂስ ባህል አልዳበረም፡፡” በዚህ ዓረፍተነገር የባለቤትነት ሙያን የተወጣው ቃል፣
   ሀ. በሀገራችን ሐ. ባህል
   ለ. የሂስ መ. አልዳበረም
5. “ደራሲ የሆነ ሰው ራሱን በሂስ ጥበብ ለማነጽ ቀጭን ትእዛዝ አያስፈልገውም፡፡” በሚለው ዓረፍተነገር የገላጭነት ተግባርን የተወጣ ቃል የትኛው ነው?
   ሀ. ጥበብ ሐ. ትእዛዝ
   ለ. ደራሲ መ. ቀጭን
6. “ከበደ ህመሙ ስለጠናበት ሐኪሞቹ ቀዶ ጥገና አደረጉለት፡፡” በሚለው ዓረፍተነገር ባለቤቱ ማን ነው?
   ሀ. ከበደ ሐ. ሐኪሞቹ
   ለ. ቀዶ ጥገና መ. ስለጠናበት

7. “ወይኒቱ የአስረኛ ክፍል ትምህርቷን በአጥጋቢ ሁኔታ ስላጠናቀቀች፣ አባቷ የአንገት ሀብል ሸለሟት፡፡” የዚህ ዐረፍተ ነገር ባለቤት፣
   ሀ. አባቷ
   ሐ. የአንገት ሀብል
   ለ. ወይኒቱ
   መ. ትምህርቷን

## የቃል ክፍሎች ሙያ

በቃል ክፍሎች (በስም፣ በቅጽል፣ በግስ፣ በተውሳከ ግስና በመስተዋድድ) የሚካተቱ ቃላት በዓረፍተነገር ውስጥ በተወሰነ ቦታ በመገኘት ወይም ቅጥያዎችን በመቀበል የሚያከናውኑት የራሳቸው ሙያ ወይም ሰዋስዋዊ ተግባር ይኖራቸዋል፡፡ በዚህ መሰረት፣ ስሞች በዓረፍተ ነገር ውስጥ ሦስት ዓይነት ተግባር ይኖራቸዋል፡፡ እነሱም፣ የባለቤትነት፣ የተሳቢነት፣ የዘርፍነት ተግባር ናቸው፡፡

**ምሳሌ** 1. ቅርስ የህዝብ ሀብት ነው፡፡
2. ሕዝብ ጥንታዊ ቅርሶችን ይንከባከባል፡፡

በምሳሌ1. “ቅርስ”፣ በምሳሌ 2. ደግሞ “ህዝብ” የሚሉ ስሞች የባለቤትነት ሙያን ይዘው ገብተዋል፡፡ ይሁንና ባለቤት ስለመሆናቸው የሚያመለክት ቅጥያ የላቸውም፡፡ በ1ኛው ዐረፍተ ነገር “የሕዝብ” የሚለው ስማዊ ሀረግ፣ የሀብቱ ባለገንዘብ ማን እንደሆነ ለመግለጽ “ሕዝብ” በሚለው ስም ላይ [የ-] ቅጥያን በመነሻው ተቀብሎ የዘርፍነት ሙያን ፈጽሟል፡፡

**በምሳሌ** 2. ቅርሶችን [ቅርስ-ኦች-ን] የሚለውን ቃል ብንወስድ፣ “ቅርስ” የሚለው ስም በመድረሻው [-ኦች] እና [-ን] የሚሉ ቅጥያዎችን ተቀብሏል፡፡ [-ኦች] ቅርሱ ብዙ መሆኑን ለማመልከት የገባች የብዙ ቁጥር አመልካች ስትሆን፣ [-ን] ደግሞ ስሙ የተሳቢነት ሙያ ያለው መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

ከላይ በሁለቱ ምሳሌዎች እንደሚታየው ስሞች በዓረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤት ሆነው ሲገቡ፣ ባለቤት መሆናቸውን ለማመልከት የሚቆም ቅጥያ አይቀበሉም፡፡ በዓረፍተነገር ውስጥ ቦታቸውም በመጀመሪያ ላይ ነው፡፡ የተሳቢነትን ሙያ ሲወጡ ደግሞ [-ን] ን መቀበል ብቻ ሳይሆን ቦታቸውም በዐረፍተ ነገሩ መካከል ላይ ይሆናል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በምሳሌ 2. “ጥንታዊ” የሚለው ቃል ክፍሉ ቅጽል  ነው፡፡ ሙያውም እሱን ተከትሎ የገባውን ስም መግለጽ ሲሆን፣ ቦታው ደግሞ በዓረፍተነገር ውስጥ ከሚገልፀው ስም በፊት መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

በመጨረሻም በምሳሌ 1 እና 2 በዐረፍተነገሮቹ መጨረሻ የገቡት “ነው” እና “ይንከባከባል” የሚሉትን ቃላት ብንመለከት የቃል ክፍላቸው ግስ ነው፡፡ ቦታቸው በዐረፍተ ነገሩ መጨረሻ ሆኖ ሙያቸው የማሰሪያ አንቀጽነት ነው፡፡

በአጠቃላይ ስሞች በዓረፍተነገር ውስጥ የባለቤትነት፣ የተሳቢነትና የዘርፍነት ሙያን ሲወጡ፣ ቅጽሎች ደግሞ ስሞችን የመግለጽ ሙያን ይወጣሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ግሶች በዓረፍተነገር መጨረሻ በመገኘት የማሰሪያ አንቀጽነት ሙያ ሲኖራቸው፣ ተውሳከ ግሶች ደግሞ በግሱ የተገለጸውን ሁኔታ ወይም ድርጊት የመግለጽ ሙያ ይኖራቸዋል፡፡

**፬. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የቃል ክፍሎቹን ሙያ በመመርመር የዓረፍተነገሮቹን ሰዋስዋዊ ስህተት ከለያችሁ በኋላ፣ ዓረፍተነገሮቹን አቃንታችሁ ጻፉ::**

***ምሳሌ፡-*** *የህብረት ሥራ ማህበሩ የቡና መጋዘን አፈረሱት::*

*ስህተቱ፡- የተሳቢ ሙያ አመልካች [-ን] መገደፍ*

*ሲቃና፡- የህብረት ሥራ ማህበሩን የቡና መጋዘን አፈረሱት::*

1. እህቴ የገዛችው ቀሚስ መልኩ አልወደድኩትም::
2. ያ አረንጓዴ እስክሪፕቶህን ለነገ ማስታወሻ እንድይዝበት ታውሰኛለህ::
3. የስነጽሑፍ ክበባችን አባላት ቁጥር ከአንድ መቶ በላይ ናቸው::
4. የወጣት ማህበሩ ለጠንካራው መሪ ታደሰ ሽልማት አበረከተ::
5. ሴቶች ማህበሩ ባልትና ሱቅ ከፈተ::

# የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ከምንባብ ለወጡ ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍችን ሰጥተናል፡፡ የቃል ንግግር መመሪያን ተከትለንም በተሰጠን ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የአስር ደቂቃ የቃል ንግግር ማድረግ ችለናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ በሀገራችን ባሉ ጥንታዊ ቅርሶች ዓይነት፣ አያያዝና ጥበቃ ላይ በመወያየት የደረስንበትን መደምደሚያ አቅርበናል፡፡

የቃል ክፍሎች ሙያን በተመለከትንበት ክፍልም፣ የቃል ክፍሎች እየተቀናጁ በሚያዋቅሩት ዓረፍተነገር ውስጥ የየራሳቸው ሙያ እንዳላቸው ተመልክተናል፡፡ ከዚህ አንፃር ስሞች በዐረፍተነገር ውስጥ ባለቤት ሲሆኑ የዓረፍተነገሩ ባለቤት መሆናቸውን የሚያመለክት ቅጥያን እንደማይቀበሉ፣ የተሳቢነትና የዘርፍነት ሙያን ሲወጡ ግን፣ ተሳቢ ሲሆኑ /-ን/ን ዘርፍ ሲሆኑ ደግሞ /የ-/ን እንደሚቀበሉ ተረድተናል፡፡ ከዚህም ሌላ፣ የአንድን ዓረፍተነገር ባለቤት ለመለየት ስሙ በዓረፍተነገሩ መጀመሪያ ላይ መገኘቱ ብቻ በቂ እንደማይሆንና በዓረፍተነገሩ ማሰሪያ አንቀጽ (ግስ) ላይ ያለውን የባለቤት አፀፋ በመመርመር ልንደርስበት እንደምንችል አይተናል፡፡

በሌላ በኩል ሐሳብን በመግለጽ ሂደት፣ ተገቢ የመረጃ ምንጮችን መሰብሰብና መጠቀም የምንችልበትን ስልት አውቀናል፡፡ በዚህም በአካባቢያችን የሚገኙ ቅርሶችን ተዘዋውረን በመጎብኘት የመስክ ዘገባ አዘጋጅተን አቅርበናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የአኅጽሮተ-ጽሑፍ ምንነትን በተመለከትንበት ክፍል፣ አኅጽሮተ-ጽሑፍ ማለት አንድ ጽሑፍ ያነሳውን ርዕስ ጉዳይ በሰፊው ተመልክቶና ዘርዝር አድርጎ ሲያቀርብ፣ የጽሑፉን ፍሬ ነገር ጨምቆ በማውጣት በሚፈለገው መጠን አሳጥሮ እንደገና በጥሩ ቋንቋ መጻፍ ማለት እንደሆነ አውቀናል፡፡ ጽሑፍ የማሳጠር ተግባር የጽሑፉን ዋና ዋና ይዘቶች በጠበቀ አኳኋን፣ በልዩ ጥንቃቄ የሚከናወን መሆኑን በመገንዘብ የአኅጽሮተ-ጽሑፍ መመሪያን ተከትለን የቀረበልንን ጽሑፍ በተሰጠን መመሪያ መሰረት በሲሦ (1/3) አሳጥረናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

፩. በዓረፍተነገር ውስጥ የቃል ክፍሎችን ሙያ እንዴት እንለያለን?

፪. አንድን ጽሑፍ አሳጥረን ለመጻፍ ትኩረት የምናደርግባቸው ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?

፫. በቅርስና በስጦታ እቃዎች መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?

፬. የተዘረፉና ያልተመለሱ ቅርሶቻችንን በምን በምን ስልት ተጠቅመን ልናስመልስ እንችላለን?

፭. የቅርሶችን መጥፋትና መበላሸት እንዴት መቀነስ ይቻላል?

፮. ተፈጥሮአዊ ቅርሶች የሚባሉት ምን ዓይነት ቅርሶች ናቸው? ከሀገራችን ተፈጥሮአዊ የቅርስ ሀብቶች ምሳሌ በመጥቀስ ግለጹ፡፡

፯. በአካባቢያችሁ የሚገኝ አንድ የጤና ተቋም በመጎብኘት፣ የተቋሙ የአገልግሎት ዘርፎች ምን ምን እንደሆኑ፣ በየዘርፎቹ የሚሰጠው አገልግሎት እድገት ምን እንደሚመስልና የተገልጋዮች እርካታን የተመለከቱ መረጃዎች ሰብስባችሁ የመስክ ዘገባ አቅርቡ፡፡

፰. "ቅርሶቻችን" በሚል ርዕስ የቀረበላችሁን ምንባብ በሲሦ አሳጥራችሁ አቅርቡ፡፡

# የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

ሀ. ከዚህ በታች በምዕራፉ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል። በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ (√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ተራ ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስለቅርሶቻችን የቀረበን ጽሑፍ አንብቤ ተረድቻለሁ። | | | |
| 2 | በዓረፍተነገር ውስጥ የቃል ክፍሎችን ሙያ ለይቻለሁ። | | | |
| 3 | ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ሰጥቻለሁ። | | | |
| 4 | ከመገናኛ ብዙሀን የሚተላለፉ መልክቶችን ሃሳብ ክፍል ውስጥ ማቅረብ ችያለሁ። | | | |
| 5 | የውይይት ስርዓትን ተከትዬ በቅርሶቻችን ዓይነት ጥቅምና አያያዝ ላይ ተወያይቻለሁ። | | | |
| 6 | ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የተሰባሰቡትን የመርጃ ሃሣቦች ክፍል ውስጥ ማቅረብ ችያለሁ። | | | |
| 7 | የተሰጠኝን ጽሑፍ አሳጥሬአለሁ። | | | |
| 8 | የዘገባ አቀራረብ መመሪያን ተከትዬ ያቀረብኩትን ዘገባ በጓደኛዬ አስገምግሜአለሁ። | | | |

ለ. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስከተረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።

# ምዕራፍ ሦስት

# ወግ

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡- ተማሪዎች! ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- ✓ የወግ ጽሑፍን ምንነት ከሌሎች የስነጽሑፍ ዘሮች ጋር በማነጻጸር ታስረዳላችሁ፡፡
- ✓ መጻሕፍት አንብባችሁ ያገኛችሁትን ፍሬ ነገር በራሳችሁ አባባል ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ ቅጥያዎችን ተጠቅማችሁ ቃላትን ታረባላችሁ፡፡
- ✓ ቅጥያዎችን ተጠቅማችሁ ቃላትን ትመሰርታላችሁ፡፡
- ✓ ለቃላት አገባባዊ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- ✓ ከጽሑፋችሁ ውስጥ የቃላት ድግግሞሽን፣ ድረታን፣ አላስፈላጊ የቃላት ውሰትን፣ የተሰለቹ ቃላትን በማስወገድ አቃንታችሁ ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ የዕለት ተዕለት ገጠመኞቻችሁን በማስታወሻ ትይዛላችሁ፡፡
- ✓ ተምሳሌታዊና አያዎ ዘይቤዎችን ከወግ ጽሑፎች ውስጥ ለይታችሁ ታወጣላችሁ፡፡

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

፩. ስነጽሑፍ ምንድን ነው?
፪. የምታውቋቸውን የስነጽሑፍ ዘርፎች ተናገሩ፡፡
፫. በዕለት ተዕለት ህይወታችሁ ወግ አውግታችሁ ታውቃላችሁ? ያወጋችሁት ስለምን ርዕሰ ጉዳይ ነበር? የምታስታውሱትን ተናገሩ፡፡
፬. ቀጥሎ “ወግ” በሚል ርዕስ ምንባብ ቀርቦላችኋል፡፡ ከርዕሱ ምን ቁምነገር የምታገኙ ይመስላችኋል? ምንባቡን ካነበባችሁ በኋላ ግምታችሁ ምን ያህል ትክክል እንደነበር አመሳክሩ፡፡

## ወግ

ወግ አጭር፣ ዝርዋዊና (ስድ ንባባዊ) ኢ-ልቦለዳዊ የስነጽሑፍ ዘር ነው፡፡ ወግ እንደ ረጅም ልቦለድ ወንዝ ተሻግሮ፣ ባህር አቋርጦ በመሄድ ከልደት እስከሞት አይተርክም፡፡ የሚቀርብበት ጽሑፋዊ ቅርጽ ዝርው ሲሆን፣ ጸሐፊው ከየእለት ገጠመኙ ሚዛን ደፍቶ ውስጡን የነካውን መዝዞ በቀጥታ የሚያወጋበት ነው፡፡ ደራሲው በጉዳዮቹ ወደ ወጎቹ የተሳቡትን ሰዎች በሚገባ ከማወቁም በላይ፣ በብሩህ አእምሮው ጉዳዮቹን እንደተረዳቸው ለአንባቢ የሚያስገነዝብበት ነው፡፡ ይህን ሲያደርግም ወጉ በሳባቸው ሰዎች ድክመት ሳያመር፣ እኛን ተደራሲያንን ሳያስመርር ለግርምት፣ ትንሽ ጠንከር ሲልም ለትዝብት ያህል ብቻ ስቀን እንድንሸኛቸው ያደርጋል፡፡

ከአትኩሮት አንጻር ሲታይ፣ ወግ አትኩሮቱን የሚያኖረው እንደ አጭር ልብ ወለድ ሁሉ፣ አንድ የተወሰነ ጉዳይ ወይም ነጠላ ጭብጥ ላይ ነው፡፡ ሆኖም አትኩሮቱን በሚያውልበት መንገድ ካጭር ልቦለድ ይለያል፡፡ የአጭር ልቦለድ ትኩረት ግራ ቀኝ የማያስብል፣ በቀጥታ መስመር የሚሄድ ድድር ነው፡፡ ለጭብጡ መጉላት ፋይዳ የሌለውን ምንም ነገር አያስገባም፡፡ በአንጻሩ ወግ ግን ዙሪያ ጥምጥምነትና ልልነት አለው፡፡ ስለሆነም ወግ መነሻውን ጉዳይ ደጋግሞ፣ አሰልሶ ይቃኘው፤ ይህንንም እንደ ዓላማ ይውሰደው እንጂ፣ ወደሌሎች ጉዳዮች እንደልቡ መዝመት መመላለስ ይችላል ማለት ነው፡፡

ስለዚህም ልክ በገሀዱ ዓለም ገጠመኞችንን እንደምናወጋ ሁሉ፣ አንድ ነገር ሌላውን ሲያስከትል “ጨዋታን ጨዋታ ሲያመጣው” እንዲሉ ከዋናው ጉዳይ ጋር እጅጉንና በቅርበት ያልተዛመዱ ጉዳዮች ቢሆኑም እንኳን፣ አይገድባቸውም። ለምን ቢሉ፣ ራሱን እንዲያርም ጥብቅ ተፅዕኖ የለበትም። ወዴትም አቅጣጫ በምንም መንገድ ይነጉዳል። ዋናው ቁምነገር መነሻውን ዓላማ አውቆ “በምን ነበር ይህን ነገር ያነሳው?” በሚል አይነት ወደ ዋናው ጉዳዩ ለመመለስ የሚያደርገው ሙከራ መኖሩ ብቻ ነው።

አብዛኛውን ጊዜ በወግ ውስጥ የምናየው ሌላው ዐቢይ ባሕርይ፣ ዋናውን ጉዳይና ከሱም እየተቀነጨቡ የሚወጡትን ዝርዝር ጉዳዮች በልዩ ልዩ ዘዴዎች ለማብራራት ሲል በማወዳደርና በማነጻጸር፣ በአስረጅዎች፣ በትርክቶች፣ በተዋስኦቶች ወዘተ. ሊጠቀም መቻሉ ነው። ይህ ባህሪ በሌሎችም ኢ-ልቦለድ ጽሑፎች ሊኖር ቢችልም፣ በወግ ውስጥ የሚኖረው ግን ከነውበታዊ እሴቱና አየል ብሎ ነው። እዚህ መልእክቱ መሸጋገር ብቻ ሳይሆን፣ ለዛ ባለው መንገድ እንዲተላለፍ ያስፈልጋል። ለዚህ ነው እንግዲህ የወግ ደርዳሪዎች ነባር የወግ አዝማች “ነገር በምሳሌ፣ ጠጅ በብርሌ” የሆነው።

ሌላው ሳይጠቀስ ሊታፍ የማይገባው፣ ተጨማሪ ነጥብ፣ ወግ በደራሲውና በተደራሲው መካከል አንዳች ውስጣዊ ትውውቅን፣ ጥብቅ ግብብነትን የመፍጠር ባሕርይው ነው። የነዚህ፣ ማለት የደራሲውና የተደራሲው ግብብነት፣ ከአስተማሪነትና ከተማሪነት እሚመነጭ ዓይነት አይደለም፤ የአለቃና ምንዝር ብጤም አይደለም። ይልቅስ የወዳጅነት ዓይነት ነው፤ የእኩዮሽ ተደማማጭነት ዓይነት። ደራሲው ይህን ወጉን ሲደረድር፣ ተደራሲው “እውነትህንኮ ነው!” እያለ፣ በአዎንታ ራሱን እየነቀነቀ እንደሚመልስ ብጤ ውይይታዊና አዝናኝ ባህሪ አለው። ቋንቋውም ብዙውን ጊዜ መደበኛ (ጽሑፋዊ) ሳይሆን፣ ኢመደበኛ (ንግግራዊ) ነው።

በልቦለድ፣ በድራማና በስነግጥም ሥራዎችም ሆነ በሌሎች የኢ-ልቦለድ ሥራዎች ውስጥ (የህይወት ታሪክን ሳይጨምር)፣ የደራሲውን “የኔነት አሻራ” ሊያድበሰብሱ የሚችሉ አያሌ ዘዴዎችና ምክንያቶች አሉ። በወግ ውስጥ ግን የደራሲው ማንነት ሊደበቅ አይችልም። ደራሲው በአንዳች ጉዳይ ላይ ያለው ሐሳብ ይበልጡንም ስሜቱና አስተያየቱ ጎልቶ ይወጣል። ጥላቻዎቹና ውዴታዎቹ፣ ምፀቱና “የእስቲ ይሁን” ትዝብቱ፣ ሽርደዳውና አድናቆቱ ሊሰወር ከሚችል በላይ ነው። “እኔን እንዳይመስል” የማያስብል ዓይነት ወግ ደራሲውም ቢሆን አያወጋም።

ከዚህ ሁኔታ መረዳት የሚቻለው የወግ ደራሲ አንዳችን ጉዳይ በሱነቱ ቀለም ሳያፍካካ (ወይም ሳያጠይም)፣ በሱነቱ ሚዛንም ሳይመጥን እንዲሁ በቁሙ ወይም በደምሳሳው አንዳችን ጉዳይ ሊያነሳ አይችልም። ሥራው ያንዳች ጉዳይ መበለቻ የመሆኑን ያህል፣ የስብእናው መከሰቻም ነው። ስለዚህ በወግ ውስጥ የወጉ ምንነት ብቻ ሳይሆን፣ የወግ ደርዳሪም ማንነት ባንድ ላይ አብሮ ይገኛል፤ ይለያልም። በዚህ ዓይነት ሞት የሚያበስር፣ ሹመት እሚያረዳ ዓይነት ወግ ደርዳሪ እውነተኛ እሱነቱን፣ ውስጣዊ ገመናውን አውጥቶ ፍንትው አድርጎ አላሳየም ለማለት ትደፍራላችሁ?

የወግን ምንነት በሚመለከት የምናነሣው ጉልህና የመጨረሻ ነጥብ፣ ድምፀትን በሚመለከት ይሆናል። መቼውንም የአንዳች ሥራ ድምፀት መደበኛ መልክ የሚታወቀው፣ ደራሲው በአንዳች ጉዳይ ላይ ካለው አተያየትና ከዚሁ አተያይ ጋር የሚሰናኝ የቋንቋ አጠቃቀም ዘዴና ችሎታ ሲኖረው ነው። ቀደም ብሎ በደምሳሳው እንደተነሳው፣ ወግ ውይይታዊና ንግግራዊ እንደመሆኑ፣ የተግሳጽ፣ የቁጣ፣ ወዘተ. ድምጸት ብዙ ጊዜ አናገኝበትም። በወግ ውስጥ የሚገኙ ገናን ድምጸቶች፣ የትዕዝብት፣ የትርብት፣ ግፋም ቢል የምጸትና የሽርደዳ ዓይነት ናቸው። ጉዳዩ ተደራሲያንን እጅግ ቀርቦ የሚነካ ቢሆን እንኳ፣ ጎንጦ የማያቆስል፣ ወግቶ የማያደማ ነው። ከዚህ የተነሳም ተደራስያን ከወግ ደራሲው ጋር “ጉዳቸውን” እንኳን ሲወያዩ አይሰቀጥጣቸውም። ይልቅስ በራስ እንደማሾፍ ያህል ያዝናናቸዋል። ይህ ከዝርዝር ነገሮች በላይ፣ በድምር

ድምፀቱ ውስጥ እሚገኝ የማዝናናት፣ የማዋዛት ባሕርይ ወግን ወግ ያሰኘ ነው ማለት ይቻላል፡፡

*(መስፍን ሀብተማርያም፣ የቡናቤት ስእሎችና ሌሎች ወጎች፣ከገጽ 1-6፣ በመጠኑ ተሻሽሎ የቀረበ)*

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ፡- አንብቦ መረዳት

**፩. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ከተሰጡ አማራጮች መካከል ተስማሚውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. ከሚከተሉት ስለ ወግ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. በዝርው የሚቀርብ አጭር ልቦለዳዊ ጽሑፍ ነው፡፡
   ለ. ደራሲው በፈጠራ መንገድ ገጸባህሪያትን ስሎ ጭብጡን አውጠንጥኖ የሚተርክበት ረጅም ልቦለድ ነው፡፡
   ሐ. ደራሲው ወጉ ያተኮረባቸውን ሰዎች በሚገባ ያውቃቸዋል፡፡
   መ. ወግ ጸሐፊዎች ብዙ ያላተኮሩበት የልብ ወለድ አንዱ ዘርፍ ነው፡፡

2. ወግ ከአጭር ልቦለድ ጋር የሚመሳሰለው ከሚከተሉት በየትኛው ነው?
   ሀ. ሁለቱም አንድ ነጠላ ጭብጥ ላይ በማተኮራቸው ነው፡፡
   ለ. ሁለቱም የልቦለድ ዘርፎች በመሆናቸው ነው፡፡
   ሐ. ሁለቱም ግራ ቀኝ ሳይሉ በቀጥታ ነገረ ጉዳያቸውን በመግለጻቸው ነው፡፡
   መ. ሁለቱም ካነሱት ፍሬ ነገር ባለማፈንገጣቸው ነው፡፡

3. “ወግ እራሱን እንዲያርም ጥብቅ ተጽእኖ የለበትም” ሲባል ምን ለማለት ተፈልጎ ነው?
   ሀ. ከዋናው ጉዳይ ጋር የተዛመዱ ነገሮችን ሁሉ በዘፈቀደ መተረክ ይችላል፡፡

ለ. ከዋናው ጉዳይ ለአፍታ እንኳን መውጣት አይችልም፡፡

ሐ. ለጭብጡ መጉላት ፋይዳ የሌለውን ምንም ነገር አያስገባም፡፡

መ. የሚደረድረው ወግ ሌላውን ወግ ከጠራ በቅርበት የማይዛመድ ቢሆንም እንኳ፣ ይደረድረዋል፡፡

4. "በወግ ውስጥ የደራሲው ማንነት ሊደበቅ አይችልም፡፡" ሲባል ምን ማለት ነው?

ሀ. በሌሎች የስነጽሑፍ ዘርፎች የደራሲው ማንነት ድብቅ ነው፡፡

ለ. የወግ ደራሲ ጉዳዩን ከሚደረድርልን በስተቀር የግሉን ሐሳብ አይጨምርም፡፡

ሐ. ደራሲው ስለሚደረድረው ወግ ያለው ስሜት፣ ጥላቻና ውዴታ በጽሑፉ ይንጸባረቃል፡፡

መ. ደራሲው የሚደረድረው ወግ ርዕሰ ጉዳይ ስለራሱ የሚያወሳ ብቻ ነው፡፡

5. የወግ ቋንቋ _____________ ነው፡፡

ሀ. መደበኛና ጽሑፋዊ

ለ. መደበኛና ዝርዋዊ

ሐ. ኢ-መደበኛና ንግግራዊ

መ. ኢ-መደበኛና ግጥማዊ

6. ከሚከተሉት የወግ ድምጸት ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የቁጣና የተግሳጽ ሐ. የምፀትና የሽርደዳ

ለ. የትዝብትና የትርብት መ. የማዋዛትና የማዝናናት

**፪. ቀጥሎ በቀረቡላችሁ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሠረት አገባባዊ ፍቻቸውን ስጡ፡፡**

**ምሳሌ፣** <u>በደምሳሳው</u> ሲታይ ወግ ውይይታዊና ንግግራዊ ነው፡፡ (በጥቅሉ፣ በጅምላው)

1. የአጭር ልቦለድ ትኩረት ግራ ቀኝ የማያስብል በቀጥታ መስመር የሚሔድ ድድር ነው፡፡
2. ወግ ልልነትና ዙሪያ ጥምጥምነት አለው፡፡
3. መልዕክቱ መሸጋገር ብቻ ሳይሆን ለዛ ባለው መንገድ እንዲተላለፍ ያስፈልጋል፡፡
4. ወጌትም አቅጣጫ በምንም መንገድ ይነጉዳል፡፡
5. ለዚህ ነው እንግዲህ የወግ ደርዳሪዎች ነባር የወግ አዝማች "ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ" የሆነው፡፡
6. ሥራው ያንዳች ጉዳይ መበለቻ የመሆኑን ያህል የደራሲው ስብዕና መከሰቻም ነው፡፡
7. ወግ ተደራሲው እውነትህን እኮ ነው እያለ በአወንታ ራሱን እየነቀነቀ እንደሚመልስ ብጤ ውይይታዊና አዝናኝ ባህሪ አለው፡፡

**፫. ምንባቡን በመመርኮዝ ከዚህ በታች የቀረቡ ዓረፍተ ነገሮች የያዙትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አብራሩ፡፡**

1. የወግ ደራሲውና የተደራሲው ግብብነት ከአስተማሪነትና ከተማሪነት የሚመነጭ አይደለም፡፡
2. አንድ ወግ የሚያነሳው ጉዳይ ተደራሲያንን እጅግ ቀርቦ የሚነካ ቢሆን እንኳ ጎንጦ የማያቆስል፣ ወግቶ የማያደማ ነው፡፡
3. በወግ ውስጥ የወግ ምንነት ብቻ ሳይሆን፣ የወግ ደርዳሪውም ማንነት ባንድ ላይ አብሮ ይገኛል፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

፩. መምህራችሁ የሚጠቁሟችሁን ምንጮች እንዲሁም የምታውቋቸውን መጻህፍት፣ መጽሔቶችና ጋዜጦች በማገላበጥ ስሜታችሁን ሰቅዞ በመያዙ ያደነቃችሁትን አንድ ወግ ምረጡ፡፡

፪. በቡድን ሆናችሁ ከላይ በተራ ቁጥር ፩ ላይ ያደነቃችሁትን አንድ ወግ በማሳያነት በመጠቀም የወግ ጽሑፍ ከሌሎች የስነጽሑፍ ዘሮች (አጭርና ረጅም ልብ ወለድ፣ ግጥምና ድራማ) ጋር ባለው አንድነትና ልዩነት ላይ ተወያዩ፤ በቡድን ውይይት የደረሳችሁባቸውን የአንድነትና የልዩነት ነጥቦች ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡

(ውይይታችሁ ወጉ ከሚያነሳው ጭብጥና አትኩሮት፣ ከደራሲው የኄነት አሻራና ከድምፀቱ አንፃር ከሌሎቹ የስነጽሑፍ ዘሮች በሚለይበትና በሚገናኝበት ነጥብ ላይ ሊያተኩር ይገባል::)

፫. በሬድዮና በቴሌቪዥን የሚተላለፉ ወጎችን አዳምጣችሁ ወይም በጋዜጦች የወጡ ወጎችን አንብባችሁ አንዱን በመምረጥ በተከታዩ ክፍለ ጊዜ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በራሳችሁ አባባል አውጉላቸው:: (የሚደመጡት ወጎች ከደብዳቤዎች ማህደር ፕሮግራም የሚተላለፍ ሰሞነኛ ትዝብቶች፣ በትራፊክ ደህንነት ላይ ያተኮሩ ወጎች፣ በመንገዶች አጠቃቀምና በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያተኮሩ ጽሁፎች፣ ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ::)

፬. በጥንድ ሆናችሁ በመወያየት ከምንባቡ ስለወግ የተረዳችኋቸውን ዋና ዋና ሐሳቦች ዘርዝሩ::

## ክፍል ሶስት:- መጻፍ

**፩. ከዚህ በታች የመስፍን ሀብተማሪያም "ጽልመታዊ አመለካከት" የተሰኘው ወግ ተቀንጭቦ ቀርቦላችኋል:: በቡድን ሆናችሁ በማንበብ ከአጭር ልቦለድ ጽሑፍ ጋር ባለው አንድነትና ልዩነት ላይ ተወያዩ፣ የደረሳችሁበትን ከአንድ ገጽ ባልበለጠ ጽሑፋችሁ በክፍል ውስጥ አቅርቡ::**

### ጽልመታዊ አመለካከት

በመሰረቱ ‹‹ጽልመታዊ አመለካከት›› ከ‹‹አምልኮአዊ እምነት›› ይለያል- የቀጭን መስመር ግንኙነት ቢኖራቸውም:: ትልቁ ልዩነታቸው አምልኮአዊ አመለካከት፣ አያት ቅደመአያት ያሉት መሆኑና ይሄኛው እራሱ በራሱ አያት ቅድመአያት መሆኑ ነው:: ጽልመታዊ አመለካከት ያለው ሰው ጽልመትን እየወለደ የሚኖር እንጂ፣ "ከዘር ወረስኩ" የሚለው አንዳችም ነገር የለውም:: ጽልመታዊ አመለካከት (Pessimism) በቀላል አነጋገር፣ መጪውን ጊዜ ጨለማ አድርጎ ማየት ማለት ነው:: የተዳፈነ የስቃይና የመከራ ፍምን በራስ አነሳሽነት አራግቦ ለነበልባሉ መስገብገብ ማለትም ነው:: ጽልመተኛው ሰው ‹‹አውቶብስ ምነው ዘገየ›› ስትሉት፣

‹‹ጎማው መንገድ ፈንድቶ ይሆናል ጌታዬ…›› የሚልና ‹‹ነገ ለመሄድ አስቤ ነበር›› ብትሉት፣ ‹‹አይሄሄ፣ እኔ አያምረኝም …›› የሚላችሁ አይነት ሰው ነው፡፡ ‹‹ምኑ ነው ያላማረህ›› ብላችሁ ከጠየቃችሁት፣ መመለስ የሚችል አይነት አይደለም፡፡ ሆኖም፣ አንገቱን ወደጉልበቱ ዘቅዘቅ እያደረገ፣ ሰለል ደከም ባለች ድምፅ፣ በእርጋታ በሚያወጣቸው አፍዛዥ ቃላቱ ዞሮ ዞሮ እንደሚበልጣችሁ አትጠራጠሩ፡፡ ባያሳምናችሁ ለጊዜው ይስባችኋል፡፡

ጽልመታዊ አመለካከት ያለው ሰው በንግድም ይሁን በሥራ አለም፣ በሌላም፣ በሌላም፣ ሙያ (ትልቅ ደረጃ ላይ የሚያደርስም ቢሆን)፤ በአስተዳደግና በፍቅር፣ በአኗኗርና በመሳሰሉት ማህበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ በቂ ቦታ ያገኘ የማይመስለው ነው፡፡ በኔ ግምት፣ የትም ብትሄዱ ‹‹ማን ያውቃል እስቲ ዝም በሉ …›› የሚል፣ የጥርጣሬ መነፅር የማይለየው፣ ክፉውን ነገር ካለበት ፈልጎ የሚያሸት፣ ጭንቀት አድማጭ ሰው በተአምር አታጡም፡፡ እንዲህ አይነት ሰው ምግብ የሚያላምጠው፣ መንገዱን የሚጓዘውና የቢሮ ፋይሉን ሁሉ የሚያስተካክለው ሟርት በማይለየው ድብቅ ሐሳቡ እየተዋጠ ነው፡፡

በምሳሌዊ አነጋገራችን ድመት ‹‹ሺ ቢታለብ ያው በገሌ ነው›› አለች ይባላል እንጂ፣ ‹‹ምንጊዜም ቢሆን ተጠቅመን አናውቅም›› በማለት ያለገደብ ማማረርን ሙያ አድርገው የያዙ፣ ከሰዎችም መካከል አሉ፡፡ ጉዳዩ ከራስ ጋር መሰላቸት፣ ሌላው ከደረሰበት ደረጃ አለመድረስ፣ “የህይወት መክፈቻ ቁልፍ እድል ነው” በሚል እምነት መጠመድ፣ አካባቢንና ማህበራዊ ኑሮን መጥላትና በውስጣዊ ፍራት መብሰልሰል ሁሉ ያለበት ይመስለኛል፡፡

በመስሪያ ቤቶች አካባቢ ብትሔዱ፣ ነገሮችን ጨለማ አድርገው የሚያዩና ለሌላው የሚያሳዩ ሰዎች አሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች፣ የተጎነጎኑ ነገሮች እንዳይላሉ፣ የተወሳሰቡ ችግሮች እንዳይፈቱ አይነተኛ መሳሪያ የሚሆኑ ናቸው፡፡ እራሳቸው በሚኖሩበት ፍርሀት እና ጭንቀት በተሞላበት አለም፣ ሌላው እንዲገባ ይፈልጋሉ፡፡ ውል የለውም ብለው በጭፍን

የሚያምኑበትን የራሳቸውን ማህበራዊ አመለካከት፣ ወደ ሌላው ለማጋባት ይጥራሉ፡፡

ጽልመታዊ አመለካከት ወደአምልኮ ደረጃ ባይደርስም ከመጥፎ እምነት ጋር አብሮ የተወለደ ያህል ይቆራኛል፡፡ መስመሩ ምን ጊዜም ሰፊ ነው__ ደግ ነገር የለበትም፡፡ ‹‹እንዲህ እንዲህ ሊሆን ነው›› ለሚል ቀና አስተሳሰብ፣ ጋሬጣ ነው፡፡ ለእንዲህ አይነቱ ብሩህ ምኞትና ተስፋ፣ አማራጭ የሌለው አቋራጭ መልስ ‹‹አይሆንም፣ አያምረኝም›› ብቻ ነው፡፡

በቢሮዎች አካባቢ የሚኖር ጸለምተኛ፣ ሁሉ ነገር የማይጥመው፣ አዲስ ሐሳብ የሚያስበረግገውና ከነበረው ልማድ ለየት ያለ አዝማሚያ እንኳ፣ የሚያስኮርፈው ነው፡፡ ለሱ፣ በመስሪያ ቤቱ የሚንቀሳቀሱ ሰዎች በጥቅሉ ፋይዳ ቢስ ናቸው፡፡ ‹‹የረባ ሰው የት አለበት ቤቱ ቤት መሰልዎት?›› ከአፉ እማይለያት አባባል ናት፡፡ በሱ ግምት፣ ዘበኛው ነዝናዛ፣ ተላላኪው ከርፋፋ፣ ደሞዝ ከፋዩ ሸረኛ ነው፡፡ በሱ ግምት፣ አለቃው እሱን አጋፍጦ ሲዞር የሚውል፣ ጸሐፊዎች በመታዘዝ ፋንታ መስታወታቸውን ደጋግመው ማየት ደስ የሚላቸው፣ ክበቡ የማንም ማጠራቀሚያ፣ የማስታወቂያ ሠሌዳው አሰሱን ገሰሱን መለጠፊያ፣ ስልኩ ሁሉ የማንም መጫወቻ ነው፡፡ መመረርና ማማረር የጽልመታዊነት ተጓዳኝ እንደመሆኑ፣ ያየውና የሰማው ቢያበሳጨው አያስገርምም፡፡ ወንበሩ ሰባራ፣ ቁልፉ ጠማማ፣ የሚፃፍበት ወረቀት ሻካራ እየሆነ ይታየዋል፡፡ ‹‹በቢሮው ደስ ተሰኝቻለሁ›› ከሚል ይልቅ፣ የሌለ ቢንቢና ትንኝ በሃሳቡ እየፈለገ ቢገድል እርካታ ያገኛል፡፡

የመስሪያ ቤቱን ጸለምተኛ በዚህ እንለፈውና ሌሎችን ጠቀስ አድርገን ነገራችንን እንቋጨው፡፡ ሁሉ ነገር የማይጥማቸው፣ ከደጉ ይልቅ፣ ክፉ ክፉው ብቻ የሚታሰባቸው ግለሰቦች በተለያዩ የማህበራዊ ህይወት መስኮች ይገኛሉ፡፡ ‹‹ጎበዝ የሚባል ተማሪ የታለ ዛሬ›› የሚል መምህር፣ የቤት ሰራተኞችን ሁል ጊዜ ሌባና ቀጣፊ አድርጋ የምታይ እመቤት፣ ጋራዥን ማመን የማይችል ባለመኪና፣ የሚገዛውን እቃ ሁሉ

የሚጠራጠር ገበያተኛ፣ በየቦታው አለ፡፡  አንዳንድ ጊዜ የሆቴል ምግብ በጭራሽ ምግብ ነው ብሎ የማያምን ሰው፣ እጁን ታጥቦ ገና ቁጭ ከማለቱ፣ አካባቢውን ከመሬት ተነስቶ ሲገላምጥ ሊያጋጥማችሁ ይችላል፡፡ ይሄ፣ ይሄ ሁኔታ እንደቢሮው ሰው መመረርና መበሳጨት ይታከልበታል፡፡

*(መስፍን ሀብተማሪያም፣ የቤቢት ድምፃች እና ሌሎች ወጎች፣ 1992፣ 21-30)*

**፬. ከዚህ በላይ ገጠመኙን እንዳወጋን ሰው፣ እስቲ እናንተም በዚህ ሳምንት የሚያጋጥማችሁን ሁሉ በማስታወሻ ከመዘገባችሁ በኋላ፣ የአድማጭን ቀልብ ይስባል የምትሉትን አንድ ገጠመኝ በመምረጥ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው ፡፡**

**፭. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተደጋገሙ፣ የተሰለቹ፣ የተደረቱ እንዲሁም ሳያስፈልጉ የገቡ የተውሶ ቃላትና ሀረጋት ይገኛሉ፡፡ በጥንድ በመሆን በምሳሌው መሰረት ቃላቱንና ሀረጋቱን በሌሎች ቃላት በመተካት ዓረፍተ ነገሮቹን እንደገና አስተካክላችሁ ጻፉ፡፡**

**ምሳሌ፣** ዓረፍተነገር፣ ስጋዊ ሰውነት ፈራሽ ነው፡፡
መልስ፣ ስጋ ፈራሽ ነው፡፡ ወይም ሰውነት ፈራሽ ነው፡፡

1. ወተት የመሰለው ጥርሱ ከፊቴ አልጠፋም፡፡
2. ወዳጄን ወንበር ውሰድ ብለው፣ ‹‹የቆመ ተጠቀመ ይባላል›› አለኝ፡፡
3. የሰው ልጅ በልቦናው አስቦ የሰራው ነገረ አያዳግመውም፡፡
4. እኔ በሎጂክ አምናለሁ፣ እኔ ምክንያት በሌለው ተግባር አልሰማራም፡፡
5. በሬድዮ የሰማሁት የትራፊክ አደጋ ሆዴ ገብቶ፣ ውስጤንና ልቤን ሰብሮታል፡፡
6. አህያ ባናፋና በጮኸ ቁጥር የጅብ ጉሮሮ ይጮሀል፡፡
7. ዛሬ ሊፍት ባላገኝ ኖሮ ትምህርት ቤት በሰዓቱ አልገኝም ነበር፡፡
8. በተማሪዎች ቀን በዓል አከባበር ስነስርዓት ላይ በካሜራችን የወሰድነው ምስል፣ ሁሉንም የክብር እንግዶች ያሳያል፡፡

9. አውቶቡስ ይገፔ እስከ ዋናው መንገድ ከመጣሁ በኋላ የቀረውን በእግሬ ነካሁት::

## የቃላት አጠቃቀም

በጽሑፍ የምንገልጸውን ሀሳብ መልክ፣ ስሜት፡ ድምጽ፣ ሽታ፣ ቅርጽ፣ አቀማመጥ፣ ጣዕም፣ ወዘተ. ለአንባቢ በሚገባው መንገድ ለማስተላለፍ የቃላት ምርጫችንና አጠቃቀማችን ትልቅ ድርሻ አለው:: ለምሳሌ፣ አንድ ወጣት ለፍቅረኛው በሚጽፈው ደብዳቤ "አኔ መናጢ ድሀ ብሆንም፣ አንቺን በልቤ አፈቀርኩ:: "የሚል ዓረፍተነገር ቢያሰፍር፣ ‹‹መናጢ ድሃ››፣ ‹‹በልቤ አፈቀርኩ›› የሚሉት ሀረጎች ድረታ ይታይባቸዋል:: ምክንያቱም ድሃ ከተባለ ምንም የሌለው እንደሆነ፣ ማፍቀርም "በልብ" እንደሚያድር የሚታወቅ ነው:: ከዚህ ይልቅ "እኔ ድሃ ብሆንም አንቺን አፈቀርኩ::"በሚል ቢጽፈው ኖሮ፣ ሃሳቡ ሳይድበሰበስ ባጭሩ ለመተላለፍ በበቃ ነበር:: እናንተም በዚህ አይነት ከጽሑፋችሁ የቃላት ድረታን፣ የተሰለቹ ቃላትን፣ የማያስፈልግ ውሰትንና ድግግሞሽን ማስወገድ ይኖርባችኋል::

## ክፍል አራት:- ስነልሳን

፩. በሚከተለው ሰንጠረዥ የእርባታና የምሰረታ ቅጥያዎች ያረፉባቸው ቃላት ተሰጥተዋል:: በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት ሰንጠረዡን አሟሉ::

| ተ.ቁ | ቃል | ቅጥያ ምዕሳድ | የቅጥያ ምዕሳድ አይነት | የቅጥያ ምዕሳድ ተግባር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መንፈሳዊ | - ኣዊ | የምስረታ ቅጥያ | ቅጽል መስራችነት |
| 2 | ትምህርት ቤታችን | - ኣችን | የርባታ ቅጥያ | አገናዛቢ አፀፋነት |
| 3 | ዝናባማ | | | |
| 4 | ጠታደርነት | | | |
| 5 | ንጥቂያ | | | |
| 6 | ፈዳቱ | | | |
| 7 | መርዘኛ | | | |
| 8 | ዘመርን | | | |
| 9 | ሰበራችሁ | | | |
| 10 | ፈጣሪ | | | |

## የእርባታና የምስረታ ቅጥያ ምዕሳዶች

ስለ እርባታና ምስራታ ቅጥያዎች ስናነሳ፣ በቅድሚያ “ምዕላድ ምንድን ነው?” የሚለውን መመልከት ጠቃሚ ነው።

**ምዕላድ፡-** ትርጉም አዘል የሆነ፣ ወደ ሌሎች ትርጉም ያላቸው አሀዶች ሊከፋፈል የማይችል የመጨረሻው ክፍል ነው። ምዕላድ በሁለት ይከፈላል።

1. **ነፃ ምዕላድ**፣ እራሱን ችሎ የሚቆም ትርጉም አዘል አሀድ ነው። ምሳሌ፣ ወንዝ፣ ዛፍ፣ አንበሳ፣ ፍየል …
2. **እስር(ጥገኛ) ምዕላድ፡-** ወደ ነፃ ምዕላዶች ካልተጠጋ በስተቀር፣ እራሱን ችሎ የማይቆም ጥገኛ ምዕላድ ነው።

**ምሳሌ**፣ ፍየሎች ፍየል [-ኦች]

[ፍየል] እራሱን ችሎ ስለሚቆም ነፃ ምዕላድ ሲሆን፣ [-ኦች] ደግሞ እራሱን ችሎ የማይቆም ጥገኛ ምእላድ ነው፡፡

ጥገኛ ምእላዶች የእርባታና የምስረታ ቅጥያዎች በመባል በሁለት ይከፈላሉ፡፡

፩. **የእርባታ ቅጥያ ምዕላዶች፡-** የተጠጉበትን ቃል፣ የቃል ክፍሉን ሳይለውጡ ቁጥሩን፣ መደቡን፣ ጾታውን፣ ሙያውን፣ እምርነቱን ለማመልከት የሚገቡ ጥገኛ ምዕላዶች ናቸው፡፡ ከላይ ባነሳነው **ምሣሌ**፣ [ፍየል] የሚለው ቃል [-ኦች]ን አስጠግቶ በቁጥር በዝቷል፡፡ ነገር ግን፣ የቃል ክፍሉ አሁንም "ስም" ነው፡፡ ስለዚህም እንደ [-ኦች] ያሉ የተጠጉበትን ቃል የቃል ክፍል የማይለውጡ ሲሆኑ የእርባታ ቅጥያ ምዕላድ በመባል ይታወቃሉ፡፡

፪. **የምስረታ ቅጥያ ምእላዶች፡-** የተጠጉበትን ቃል፣ የቃል ክፍሉን የሚለውጡ ናቸው፡፡

**ምሳሌ፡-** ባህላዊ ባህል[-ኣዊ]

[-ኣዊ] የተሰኘው ቅጽል መስራች ምዕላድ ባህል በሚለው ስም ላይ ተጠግቶ፣ በቃል ክፍሉ ስም የነበረውን ቃል ወደ ቅጽልነት ለውጦታል፡፡ ስለዚህም እንደ [-ኣዊ] ያሉ ጥገኛ ምዕላዶች የምስረታ ጥገኛ ምዕላዶች በመባል ይታወቃሉ፡፡

**፪. ከዚህ በታች በተሰጡ ቅጥያዎች በምሳሌው መሰረት አንድ አንድ ቃል እያረባችሁ ወይም እየመሰረታችሁ የቅጥያ ምዕላዶቹን ተግባር ግለጹ፡፡**

| ተ.ቁ | ቅጥያ ምዕላድ | ቃል | የቅጥያው ዓይነት | የቅጥያው ተግባር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | - ኤ | መጽሐፌ | የእርባታ | ዘርፍነትን ማመልከት |
| 2 | - ኢታ | | | |
| 3 | - ኣም | | | |
| 4 | - ኣዊ | | | |
| 5 | - ኡ | | | |
| 6 | - ህ | | | |
| 7 | - ን | | | |

## ክፍል አምስት፡- ስነጽሑፍ

፩. ወግ በሚለው ምንባብ ውስጥ ያሉ ዘይቤዎችን ነቅሳችሁ በማውጣት ዓይነታቸውን ግለጹ፤ በምንባቡ የያዙትን ሀሣብ ባጭሩ አብራሩ፡፡

፪. በክፍል ሶስት በቀረበው "ጽልመታዊ አመለካከት" በሚለው ወግ ውስጥ ያሉትን ዘይቤያዊ አገላለጾች ዘርዝራችሁ መልእክታቸውን አብራሩ፡፡

፫. ከዘረዘራችኋቸው ዘይቤያዊ አገላለጾች ውስጥ ተምሳሌትና አያዎ ዘይቤዎችን በመለየት፣ እንዴት የደራሲውን ሀሳብ አጉልተውና አድምቀው ማሳየት እንደቻሉ ባጭሩ አብራሩ፡፡

፬. ከመጻህፍት፣ ከጋዜጦችና ከመጽሔቶች አንድ ወግ ፈልጋችሁ ካነበባችሁ በኋላ፣ ተምሳሌትና አያዎ ዘይቤዎችን በመለየት የደራሲውን ሀሣብ እንዴት ማድመቅ እንደቻሉ በአንድ አንቀጽ አብራሩ፡፡

## ተምሳሌትና አያዎ ዘይቤ

**1. ተምሳሌት ዘይቤ**

ተምሳሌት ዘይቤ የሚባለው አንድ ነገር ለሌላ ነገር በምልክትነት የሚወከልበትና ወካዩን በተወካዩ አማካኝነት አጉልቶ ለማሳየት የሚያገለግል የዘይቤ አይነት ነው::

**ምሳሌ** ሀ. የሰፈሩ አድባር ዛሬ ተረታች::
ለ. አምላኬ ፍሬ ባያድለኝም ሀብት አላሳጣኝም::

በሁለቱ ምሳሌዎች ውስጥ በቅደም ተከተል አድባር፣ ፍሬ የሚሉት ቃላት ተምሳሌታዊ ናቸው:: አገባባቸውም ከተለመደው ፍቻቸው የተለየ ነው::

***በምሳሌ*** ሀ. <u>አድባር</u> ለትልቅ፣ ለባለ ግርማ ሞገስ፣ ላንጋፋ፣ ለመመኪያ ተምሳሌት ነዉ::

***በምሳሌ*** ለ. <u>ፍሬ</u> የአብራክ ክፍያ የልጅ ተምሳሌት ነው::

ተምሳሌት በሦስት የውክልና ደረጃዎች ይከፈላል:: እነሱም፣ አለም አቀፋዊ ተምሳሌት፣ አገራዊ ወይም ተለምዶአዊ ተምሳሌትና ግላዊ ተምሳሌት ናቸው:: ከላይ በምሳሌነት የቀረቡትም አገራዊ ወይም ተለምዶአዊ ተምሳሌቶች ናቸው::

**2. አያዎ ዘይቤ**

ሁለት ተቃራኒ ሀሳቦችን በመያዝ በመጀመሪያ እንደሰሙት ወይም እንዳነበቡት እውነት የማይመስል (አይ! የሚያሰኝ) ሲሆን፣ እየቆዩ ሲያስቡት እውነትነቱ እየተገለጠ የሚሄድ (አዎ! የሚያሰኝ) ነው:: መጠሪያውም "አይ" እና "አዎ" ከሚሉት ቃላት የተገኘ መሆኑን ልብ በሉ::

**ምሳሌ፣** ሀ. ትከሻዬ እያነቡ እስክስታን ለምዷል::
ለ. እራሱን ገድሎ የቀበረ ራሱ ነው::

**በምሳሌ** ሀ. እስክስታ ባለም በደስታ ጊዜ በፈገግታ የሚከናወን ውዝዋዜ በመሆኑ ዘይቤውን በመጀመሪያ ስናነበው እንዴት እያለቀሱ እስክስታ ይወረዳል? እንል ይሆናል:: ቆይተን ስናስበው ግን በጥልቅ ትዝታ አለበለዚያም ከመጠን ባለፈ ደስታ ተውጠን እያነባን ስሜታችንን በጭፈራ የምንገልጽበት አጋጣሚ ይኖራል::

**በምሳሌ** ለ. አባባሉን በመጀመሪያ ስናየው "አንድ ሰው ራሱን ከገደለ እንዴት የራሱን ሬሳ መቅበር ይችላል?" እንል ይሆናል:: ቆይተን ስናስበው ግን ሰውየው በገዛ እጁ ምክር አልሰማ ብሎ ወደቀ የሚል መልዕክት ያስተላልፋል::

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የወግን ምንነት ከሌሎች የስነጽሑፍ ዘሮች ጋር እያነጻጸርን ለማየት ሞክረናል፡፡ ወግ አጭር ዝርዋዊና ኢ- ልቦለዳዊ የስነጽሑፍ ዘር መሆኑን፣ ከአትኩሮት አንጻር በነጠላ ጭብጥ ላይ ማጠንጠኑ ከአጭር ልቦለድ ቢያመሳስለውም፣ አትኩሮቱን በሚያውልበት መንገድ እንደሚለያይ ተመልክተናል፡፡ በዚህ ክፍል አጭር ልቦለድ ለጭብጡ መጉላት ፋይዳ የሌለው ምንም ነገር እንደማያስገባና ታሪኩም ጥድፊያ እንደሚታይበት፣ በአንጻሩ ወግ ዙሪያ ጥምጥምና ልል እንደሆነ ተረድተናል፡፡

ወግ ባነሳው ጭብጥ የሚካተቱ ዝርዝር ጉዳዮችን ለማብራራት ሲል በማወዳደርና በማነጻጸር፤ በአስረጂዎች፣ በትርክቶች፣ በምልልሶች፣ ወዘተ መጠቀሙን፣ ሌሎች የስነጽሑፍ ዘሮች እነዚህን ስልቶች ቢጠቀሙም በወግ ውስጥ ግን እስከነዉበታዊ እሴታቸው አይለው እንደሚገኙ ተመልክተናል፡፡ ወግ ከድምፀቱ አንጻር ሲታይ አብዛኛውን ጊዜ የትዝብት፣ የትርብት፣ የምፀትና የሽርደዳ እንጂ፣ የቁጣ የተግሳጽ፣ ወዘተ እንደማይሆን ተመልክተናል፡፡

በሌላ በኩል ወጎችን አንብበን ፍሬ ሐሳባቸውን በራሳችን አባባል ገልፀናል፡፡ የተለያዩ ቃላትን አገባባዊ ፍቺ ከመለየታችንም በላይ፣ ከጽሑፍ ውስጥ የቃል ድግግሞሽን፣ ድረታን፣ አሳሰፈሳጊ ውሰትን፣ የተሰለቹ ቃላትን አስወግደናል፡፡ የየዕለት ገጠመኛችንን በማስታዉሻ በመያዝ ወግ ጽፈናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ ስለአርባታና ምስረታ ቅጥያ ምዕላዶች ባነሳንበት ክፍል፣ ምዕላድ ትርጉም አዘል የሆነ፣ ወደ ሌሎች ትርጉም ያላቸው አሀዶች ሲከፋፈል የማይችል የመጨረሻው ክፍል መሆኑን ተመልክተናል፡፡ ምዕላድን በነፃና በእስር (ጥገኛ) ምዕላድ በመክፈል በምሳሌ አስደግፈን ከማየታችንም በላይ፣ እስር (ጥገኛ) ምዕላድን በሁለት (በአርባታና በምስረታ ቅጥያ ምዕላድ) ክፍለን አብራርተናል፡፡ በመጨረሻም ተምሳሌትና አያዎ ዘይቤዎችን በመለየትና ከጽሑፍ ውስጥ በመንቀስ ለሀሳብ ማድመቂያነት የዋሉበትን ሁኔታ መርምረናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

፩. በወግና በአጭር ልቦለድ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነትን ግለጹ፡፡

፪. ለሦስቱ የተምሳሌት ዘይቤ ክፍሎች (አለማቀፍዊ፣ተለምዶአዊና ግላዊ ተምሳሌት) ምሳሌ የሚሆኑ ሁለት ሁለት ዘይቤያዊ አገላለጾችን ከሰጣችሁ በኋላ፣ ለሀሳብ ማጉያነት የዋሉበትን ሁኔታ አብራሩ፡፡

፫. ወግን ኢ- ልቦለዳዊ የስነጽሑፍ ዘር የሚያሰኘው ነጥብ ምንድን ነው?

፬. ከመጻሕፍት፣ ከመጽሔቶችና ከጋዜጦች አንድ ወግ ፈልጋችሁ ካነበባችሁ በኋላ፣ ጸሐፊው የተጠቀማቸውን ዘይቤያዊ አገላለጾች ለቅማችሁ በማውጣት፣ ሀሳብን አጉልቶ በማሳየት በኩል የተወጡትን ሚና በጽሑፍ አብራሩ፡፡

፭. የሚከተሉትን ቃላት በምዕላድ ተንትኗቸው፡፡

1. ወላጆቹ
2. መተከዙን
3. ጓደኞቹን
4. መልማዩን
5. ፍርደኛውን

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩ ከዚህ በታች በዚህ ምዕራፍ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል:: በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ (√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ::

| ተ ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ወግ ከሌሎች የሥነጽሑፍ ዘርፎች ጋር ያለውን ዝምድናና ልዩነት ተረድቻለሁ:: | | | |
| 2 | ስቃሳት ዕርባታና ምሥረታ የሚያገለግሉ ቅጥያ ምዕላዶችን ተግባር መግለጽ ችያለሁ:: | | | |
| 3 | ከሚቀርብልኝ ጽሑፍ ውስጥ አሳስፈላጊ ቃላትን ለይቼ አውጥቻለሁ:: | | | |
| 4 | ያነበብኩትንና ያዳመጥኩትን ወግ ያደነቅኩበትን ምክንያት በራሴ አባባል መግለጽ ችያለሁ:: | | | |
| 5 | የየዕለት ገጠመኜን በማስታወሻ በመያዝ ተከታትያለሁ:: | | | |
| 6 | ከወጎች ውስጥ ዘይቤዎችን ለይቼ አውጥቻለሁ:: | | | |
| 7 | ተምሳሌትና አያዎ ዘይቤዎችን ከወግ ጽሑፍ ውስጥ ለይቼ አውጥቻለሁ:: | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ::

# ምዕራፍ አራት

# ልቦለድ

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡- ተማሪዎች! ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- ✓ ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- ✓ ቃላትን በየቃል ክፍሎቻቸው ትመድባላችሁ፡፡
- ✓ የተነወሩ፣ ዘዬ-መጥና የአራዳ ቃላትን በመለየት በተገቢ ቃላት ትተካላችሁ፡፡
- ✓ ለቃላት አውዳዊና መዝገበ ቃላዊ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- ✓ ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- ✓ ከጽሑፍ ውስጥ አስፈላጊና አላስፈላጊ የሆኑ ሐሳቦችን ለይታችሁ ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የምታገኟቸውን መረጃዎች በጽሑፋችሁ ወይም በንግግራችሁ ውስጥ ትጠቀማላችሁ፡፡
- ✓ የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልቶችን በመጠቀም አንቀጽ ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ የስነጽሑፍ ፍሬ ነገር የሆኑትን የግጭትንና የትልምን ምንነት ታብራራላችሁ፡፡
- ✓ ከልቦለድ ውስጥ ግጭትና ትልምን በማውጣት ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ የልቦለድ ማቅረቢያ ዘዴን (ስልትን) ምንነት ታብራራላችሁ፡፡

## ቅድመ ንባብ የመወያያ ነጥቦች

በቡድን ሆናችሁ ተከታዩን ማስታወሻ በማንበብና በአስረኛ ክፍል ስለልቦለድ የተማራችሁትን በማስታወስ በቀረቡት የመወያያ ጥያቄዎች ላይ ሐሳብ ተለዋወጡ፡፡ የደረሳችሁበትንም በቡድን መሪያችሁ አማካይነት በቃል ተናገሩ፡፡

### ልቦለድ

ልቦለድ ከደራሲው ምናባዊ ፈጠራ የሚመነጭ፣ የሰውን ሕይወት ልዩ ልዩ መልኮች በተመሳስሎ ለመቅረጽ የሚያስችል፣ በቁሙ ግን እውነት ያልሆነ የኪነጥበብ ሥራ ነው፡፡ ልቦለድ በእውኑ ዓለም በሰዎች የህይወት ገጠመኝ ከተፈጸመውና ሊፈጸም ከሚችለው በከያኒው ግንዛቤና አመለካከት ተቀምሮ የሚቀርብ የማህበረሰቡ ቁሳዊና ህሊናዊ ገጽታ የሚታይበት ኪነታዊ ሥራ ነው፡፡ የልቦለድ ምንነትን በወጉ ለመረዳት የልቦለድ ባህርያትንና ለህልውናው መሠረት የሆኑትን ፍሬ ነገሮች በዝርዝር ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ የልቦለድ ፍሬ ነገሮች ወይም አላባውያን ተብለው የሚታወቁት ታሪክ፣ ትልም፣ ግጭት፣ ገጸባህሪ፣ መቼት፣ ጭብጥና አንጻር የተሰኙት ናቸው፡፡ እነዚህ የልቦለድ ፍሬ ነገሮች ለአጠናን እንዲያመች ተለይተው ተጠኑ እንጂ፣ በአንድ ልቦለድ ውስጥ በተናጠል ወገን ተለይተው ለየብቻቸው የሚገኙ አይደሉም፡፡

*(ዘሪሁን አስፋው፣ የስነጽሑፍ መሠረታውያን፣ 1992፣ 152-154)*

1. “ልቦለድ በቁሙ እውነት ያልሆነ የኪነጥበብ ሥራ ነው” ሲባል፣ በልቦለድ ውስጥ እውነት የለም ለማለት ነውን?
2. የልቦለድ አላባውያንን ከዘረዘራችሁ በኋላ የተማራችኋቸውንና ያልተማራችኋቸውን ለዩ፤ የምታውቋቸውን በየትኛው የክፍል ደረጃ እንደተማራችኋቸው ግለጹ፡፡

3. ልቦለድ የማህበረሰቡን ቁሳዊና ህሊናዊ ገጽታ የሚያሳየው እንዴት ነው?
4. የልቦለድ አላባውያን በአንድ ልቦለድ ውስጥ በተናጠል ለየብቻው የሚገኙ አይደሉም የሚባለው ለምንድነው?

## የልቦለድ ትልምና ግጭት

ልቦለድ የሰው ልጅ የገሀዱ ዓለም የእለት ተእለት ገጠመኝ ነጸብራቅ እንደ መሆኑ ለድርሰቱ መደርጀት መሠረቱን ከሚጥልባቸው የልቦለድ አላባውያን መካከል ታሪኩ የተዋቀረበት ትልምና በትልሙ ውስጥ የሚውጠነጠነው ግጭት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ትልም በአንድ ልቦለድ ታሪክ ውስጥ ምን? ለምን ተደረገ? ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው መልስ ነው፡፡ ስለዚህም በገፀባህርያት አማካይነት በጊዜ ቅደም ተከተል የተከናወኑ ሁነቶችን ፣ እነዚህ ሁነቶች እንዲፈጸሙ አነሳሽ የነበሩ ምክንያቶችንና ያስከተሏቸውን ውጤቶች ባንድ ላይ አቀራኝቶ የያዘ የልቦለድ አካል ነው፡፡ ይህንን ተግባሩን የተመለከቱ "ትልም ለአንድ ልቦለድ አጽም ነው" ይላሉ፡፡ አጽም የሰው ልጅንና ሌሎች እንስሳትን ስጋቸውን አቅፎ አካላቸውን ደግፎ እንደሚያቆማቸው ሁሉ፣ ትልምም የአንድ ልቦለድ ምሶሶ በመሆን ያገለግላል፡፡

ስለትልም ሲነሳ ብዙ ጊዜ የሚያጋጥመው ችግር፣ ብዙ ሰዎች ትልምንና የልቦለድ ታሪክን አንድ አድርገው መመልከታቸው ነው፡፡ በመሠረቱ ሁለቱም የልቦለድ ፍሬ ነገሮች ቢሆኑም፣ የሚለያዩባቸውና የሚገናኙባቸው ነጥቦች አሉ፡፡ ይህንን አስመልክቶ በብዙ የስነጽሑፍ መምህራን ዘንድ ተደጋግሞ የሚጠቀሰውን የእንግሊዛዊውን የኤ. ኤም. ፎርስተር ምሳሌ ማንሳቱ ጠቃሚ ነው፡፡ ፎርስተር እንደሚገልጸው ታሪክ በጊዜ ቅደም ተከተል የተከናወኑ ሁነቶች ትረካ ነው፡፡ ስለዚህም "ንጉሱ ሞተ፡፡ ንግስቲቱ ሞተች" ሲባል፣ ታሪክ ነው፡፡ ነገር ግን፣ "ንጉሱ ሞተ፤ ከዚያም በሱ ሀዘን የተነሣ ንግሥቲቱ ሞተች " ሲባል ትልም ነው፡፡ ትልም እንደ ታሪክ ሁሉ በድርጊት ቅደም ተከተል ላይ

የተመሠረተ ቢሆንም፣ በምሣሌው እንደሚታየው ድርጊቱ ምክንያታዊ ነው፡፡ “ንግስቲቱ ለምን ሞተች?” ተብሎ ሲጠየቅ፣ በንጉሱ ሞት የተነሣ በሀዘን ተጎድታ መሆኑን ከነምክንያቱ ይዟል፡፡

በሌላ በኩል “ግጭት ምንድን ነው?” ወደሚለው ነጥብ ስንሸጋገር፣ ሰዎች በገሀዱ ዓለም ለኑሮአቸው አስፈላጊ ነገሮችን ለማግኘትና ህልውናቸውን ለማስቀጠል ሲሉ፣ በተለያዩ የህይወት ውጣ ውረዶች ውስጥ ይገባሉ፡፡ ልክ እንደ ገሀዱ ዓለም ሰዎች ሁሉ፣ በልቦለድ ውስጥ ገፀባህርያት እንዲኖሩ በተሰጣቸው ግላዊ ህይወት ያላቸውን ዓላማ፣ አስተሳሰብ፣ እምነት፣ ፍላጎት፣ ወዘተ. ይዘው የእርስ በእርስ ማህበራዊ ግንኙነት ይፈጥራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ቀስ በቀስ በዓላማና ፍላጎት አለመጣጣም ሳቢያ ቅራኔዎች ይፈጠሩና ወደለየለት ግጭት ይሸጋገራሉ፡፡ አንዱ ለመጣልና በሌላው ላይ አይሎ ለመገኘት፣ ሌላው ላለመውደቅና ላለመረታት እልህ አስጨራሽ ትግል ያካሂዳሉ፡፡ ይህ በተቀናቃኝ ሀይላት መካከል በልቦለድ ውስጥ የሚኖር ፍልሚያ ግጭት ይባላል፡፡

ግጭት ከውጥኑ እስከ ፍፃሜው የሚያልፋባቸው የራሱ የሆኑ ባህርያት አሉት፡፡ የመጀመሪያው የግጭት ባህሪ የሚሆነው በበቂ መንስኤ ላይ መመስረቱ ነው፡፡ ሁለት ኃይላት ተጻራሪ እንዲሆኑና በባላንጣነት እንዲተያዩ የሚያደርግ በቂና አስገዳጅ ምክንያት መኖር አለበት፡፡ መንስኤ አልባ ወይም በእውኑ ዓለም ሊደርስ ከሚችለው በጣም የራቀ መንስኤ ግጭት ተአማኒነቱ አጠራጣሪ ከመሆኑም በላይ፣ የልቦለዱን ታሪክ ወደፊት ለማራመድ ብቃት አይኖረውም፡፡ አንባቢ ለልቦለዱ ትኩረቱን እንዳይቸር ምክንያት ይሆናል፡፡

ሌላው የግጭት ባህሪ በአንድ ልቦለድ ውስጥ ያሉ ተጻራሪ ኃይላት በሰበበ ግጭት አስገዳጅነት ግጭት ውስጥ ከገቡ በኋላ፣ የሚያካሂዱትን ፍልሚያ የሚመለከት ነው፡፡ ተፋላሚዎቹ በሀይል መመጣጠን ይኖርባቸዋል፡፡ በሀይል ተመጣጣኝ በሆኑ ተቀናቃኞች የሚካሄደው ትግልና ፍትጊያ

"አሸናፊው ማን ይሆን?" በሚል ልብ ሰቅሎ እየተባባሰ ይሄድና ከፍ ወዳለ ደረጃ ይንራል፡፡ ይህ የግጭት ጡዘት የሚባለው ደረጃ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ የከረረው እየላላና እየረገበ ተበጥሶ ግጭቱ አንድ አይነት መፍትሔ ላይ ይደርሳል፡፡ ይህ የግጭቱ መቋጫ ደግሞ ልቀት ይባላል፡፡

በገፀባህርያቱ መካከል የተከሰተው ግጭት ሲያበቃ በግጭቱ ተሳታፊ በነበሩ ገፀባህርያት ላይ አንድ ዓይነት ለውጥ ይከሰታል፡፡ ይሁንና የለውጡ ደረጃም ሆነ አቅም እንደታሪኩ፣ በታሪኩ ውስጥ ግጭቱ እንዳለው ሚና እና ደረጃ የሚወሰን ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃር በልቦለድ ታሪኩ ዋና የሚባለው ግጭት ከንዑስ ግጭቶች የበለጠ የገፀባህርያቱን እድል በመወሰንና የብዙ ክንዋኔዎችን አቅጣጫ በማስቀየር ሚናው የጎላ ነው፡፡ በግጭቱ ልቀት ላይ የሚመጣው ለውጥ ምንም ይሁን ምን፣ ዋናው ቁም ነገር፣ የግጭቱን ሰንሰለታዊ ሂደት ተከትሎ በምክንያታዊነት መጓዙ ነው፡፡ ከዚህ ሰንሰለታዊ ጉዞ ውጪ የሚፈጠር ከሆነ ልቦለዱ ተአማኒ አይሆንም፡፡

በልቦለድ ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶችን ከአይነታቸው አንጻር ጠቅለል አድርጎ በአራት መክፈል ይቻላል፡፡ አንደኛው የግጭት ዓይነት በሰውና በሰው መካከል የሚፈጠርና ሰው ከሰው የሚባለው ሲሆን፣ ሁለተኛው ሰው ከራሱ ጋር የሚያደርገው ህሊናዊ ወይም ስነ ልቦናዊ ግጭት ነው፡፡ ሦስተኛው ዓይነት ግጭት ሰው ከተፈጥሮ ክስተቶችና ገጽታዎች ጋር የሚጋፈጥበት፣ ሰው ከተፈጥሮ የተሰኘው ነው፡፡ አራተኛውና የመጨረሻው የግጭት ዓይነት ደግሞ ሰው ከማህበረሰብ የሚባለው ነው፡፡

በአጠቃላይ፣ ከዚህ በላይ ለአንድ ልቦለድ ድርሰት መደርጀት መሠረት ከሚጣልባቸው የልቦለድ አላባውያን መካከል፣ ታሪኩ የሚዋቀርበትን ትልምና በትልሙ ውስጥ የሚውጠነጠነውን ግጭት በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ግጭትና ትልም በልቦለድ ፍሬ ነገርነታቸው በአንድ ልቦለድ ውስጥ ከሌሎች አላባውያን ጋር ተሳስረውና ተዋህደው የሚገኙ ናቸው፡፡

*(መነሻ ሐሳብ፣ ዘሪሁን አስፋው፣ የስነጽሑፍ መሰረታዊያን፣ 1992 ገጽ 172-176)*

# መልመጃዎች

## ክፍል አንድ:- አንብቦ መረዳት

**፩. ከዚህ በታች ምንባቡን መሠረት አድርገው የቀረቡ ጥያቄዎችን በቃል መልሱ፡፡**

1. በልቦለድ ትልምና በልቦለድ ታሪክ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት አብራሩ፡፡
2. በልቦለድ ውስጥ ገፀባህርያት ቅራኔ ውስጥ የሚገቡት ለምንድን ነው?
3. በአንድ ልቦለድ ውስጥ በተጻራሪ ኃይላት መካከል ያለው የኃይል ሚዛን ተመጣጣኝ መሆን አለበት የሚባለው ለምንድን ነው?
4. በልቦለድ ግጭት ማብቂያ በገፀባህርያት ላይ ለውጥ እንዴት እንደሚከሰት በምሳሌ አስረዱ፡፡
5. ግጭት ልቀት ደረጃ ላይ ደርሶ በገፀባህርያት ላይ የሚያመጣውን ለውጥ ስፋትና ጥልቀት የሚወስነው ማን ነው?

**፪. ከዚህ በታች በምንባቡ ውስጥ እየተሰመረባቸው የቀረቡ ቃላት ተዘርዝረዋል፡፡ አውዳዊና መዝገበ ቃላዊ ፍቻቸውን ስጡ፡፡**

***ምሳሌ:-***

| ቃል | መዝገበ ቃላዊ ፍች | አውዳዊ ፍች |
|---|---|---|
| ሀ. ነፀብራቅ | 1. ብልጭታ፡፡<br>2. አንድ ሁኔታ፣ አስተሳሰብ የሚያመለክት ድርጊት ወይም ሐሳብ፡፡ | ቅጅ |
| ለ. አጽም | አጥንት | ምሰሶ |

| | ቃል(ሐረግ) | መዝገበ ቃላዊ ፍች | አውዳዊ ፍች |
|---|---|---|---|
| 1. | አነሳሽ | ___ | ___ |
| 2. | አቆራኝቶ | ___ | ___ |
| 3. | በገሃዱ | ___ | ___ |
| 4. | እልህ አስጨራሽ | ___ | ___ |
| 5. | አይሎ | ___ | ___ |
| 6. | መንስኤ | ___ | ___ |
| 7. | በባላንጣነት | ___ | ___ |
| 8. | ሚና | ___ | ___ |
| 9. | ሰንሰለታዊ | ___ | ___ |
| 10. | ተአማኒ | ___ | ___ |

፫. ከላይ በተራ ቁጥር ፪ ከቀረቡ ቃላት ውስጥ አምስቱን መርጣችሁ በመዝገበ ቃላዊ ፍቻቸው ዓረፍተነገር ሥሩባቸው፡፡

## ክፍል ሁለት፡- ማዳመጥ

፩. በቴሌቭዥን ወይም በሬድዮ ከሚተላለፉ ልቦለድ ትረካዎች አንዱን አዳምጣችሁ፣ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት ታሪኩን በራሳችሁ አገላለጽ አቅርቡ፡፡

፪. ባዳመጣችሁት ልቦለድ ውስጥ ትልሙ፣ ዋናና ንዑስ ግጭቶቹ ምን ምን እንደነበሩ አብራሩ፡፡

፫. ቀጥሎ መምህራችሁ "ነጋሪትና ነጋሪት ጋዜጣ" በሚል ርዕስ የተዘጋጀ አንድ ጽሑፍ ያነቡላችኋል፡፡ በጽሑፉ ይዘት ላይ ተመርኩዛችሁ ተከታዮቹን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1. ማዳመጥ ከመጀመራችሁ በፊት ከርዕሱ በመነሳት ምን ምን ፍሬ ሃሳቦች እናዳምጣለን ብላችሁ ትገምታላችሁ? በጥንድ ሆናችሁ እየተወያያችሁ ግምታችሁን ባጭር ባጭሩ በአስተዋጽኦ መልክ ዘርዝሩ፡፡

2. ጽሑፉ ሲነበብ እያዳመጣችሁ የተነሱ ፍሬ ሐሳቦችን ባጭር ባጭሩ በአስተዋጽኦ መልክ መዝግቡ፡፡
3. የያዛችሁትን ማስታወሻ መርምራችሁ ለርዕሱ አስፈላጊና አላስፈላጊ ሃሳቦችን ለዩ፡፡

| አስፈላጊ ሐሳቦች | አላስፈላጊ ሐሳቦች |
|---|---|
| • | • |
| • | • |
| • | • |
| • | • |

4. በጥንድ ሆናችሁ በለያችኋቸው ሐሳቦች ተገቢነት ላይ ተወያዩ፡፡ የደረሳችሁበትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በምክንያት የተደገፈ ገለጻ ስጡ፡፡ የጋራ ስምምነት ላይ ድረሱ፡፡

## ክፍል ሦስት፡- መናገር

፩. ስለልቦለድ የሚያወሱ መጻሕፍትን፣ መጽሔቶችንና ጋዜጦችን ካነበባችሁ በኋላ ያገኛችኋቸውን ፍሬ ሀሣቦች በመጭመቅ፣ በተከታዩ ክፍለ ጊዜ የቃል ገለጻ አቅርቡ፡፡

፪. በቡድን ሆናችሁ አንድ የአማርኛ ልቦለድ መርጣችሁ ካነበባችሁ በኋላ በልቦለዱ ትልም፣ ዋናና ንዑሳን ግጭቶች እንዲሁም ግጭቶቹ በገጸባህርያቱ ላይ ስላስከተሉት ለውጥ ተወያዩ፤ የደረሳችሁበትን መምህራችሁ በሚመሯችሁ መሰረት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

፫. ቀጥሎ በቀረበላችሁ አንቀጽ ውስጥ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች የያዙ ቃላት ይገኛሉ፡፡ በጥንድ ሆናችሁ ቃላቱን በመለየት ከዘረዘራችሁ በኋላ፣ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቻቸውን ተናገሩ፡፡

ይህቺ መጽሔት ከሕሊና ሕሊናት ወርዳ፣ ከተማሪዎች ልፋት ተወልዳ፣ ወደዚህ ዓለም የመጣችው ገና ዛሬ ነው፡፡ ግን ታሪከኛ ነች፡፡ ገና ልትፈጠር ብዙ አመታት ሲቀሯት በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ተማሪዎች አእምሮ ተፀንሳ ነበር፡፡ ፈጣሪዎቿም እርሷን ለመፍጠር

ያነሳሷቸውን ምክንያቶች አውጥተው አውርደው ብዙ አመዛዝነዋል፡፡ በመጽሔቷ አማካይነት ሊፈጽሙ የሚሿቸውን ብዙ ብዙ ዓላማዎች መክረውባቸዋል፤ ዘክረውባቸዋል፡፡ ባጭሩ የመጽሔቷ ታሪክ ረጅም ነው፡፡

*(ከእንዲህ ነው፣ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩንቨርሲቲ ኮሌጅ የሥነ ጽሑፍ መጽሔት፣1957 ገጽ 3 የተወሰደ)*

## ክፍል አራት፣ መጻፍ

**፩. ከዚህ በታች በቀረቡ ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተነወሩ፣ ዘዬ-መጥና የአራዳ ቃላት ገብተዋል፡፡ ቃላቱን ከለያችሁ በኋላ፣ ተገቢነት ባላቸው ሌሎች ቃላት በመተካት ዓረፍተነገሮቹን እነደገና አስተካክላችሁ ጻፉ፤ በምትክ ያስገባችኋቸውን ቃላት ደግሞ ከስራቸው አስምሩባቸው፡፡**

1. አስካለ አሽከሩን ጠርታ ለመስቀል ዳቦት ሊሰራበት ከሰበሰበው ጭራሮ አንድ እቅፍ እንዲሰጣት ለመነችው፤ ያሰማችው ምጎጎ እንዳይበርድባት በማሰብ፡፡
2. ወባ ስለተነሳብኝ ሰውነቴ አተኩሷል፤ ሊያስታውከኝ ይከጅላል፡፡
3. አየለ ጀለሱን ጥበቃ ብዙ ሰዓት አሳልፏል፡፡ ከመጣለት በኋላም ቢሆን ብዙ አብረው አልቀዩም፤ እንዲያውም "እኔ ደርሼ እስክመለስ እዚሁ ዱቅ ብለህ ጠብቀኝ፤ ዋ! እንዳትነካው ነግሬሀለሁ" ብሎት ላሽ አለ፡፡
4. አዲሱ የጽዳት ሠራተኛ ሽንት ቤቱን አያጸዳም፡፡
5. "ከሴትዮህ ስንት ልጅ ወለድህ? መቼም ከተጋባችሁ አስር ዓመት ይሞላችኋል፡፡" አለ ተመስገን፡፡

**፪. ቀጥሎ ከዳኛቸው ወርቁ "አደፍርስ" መጽሐፍ ወ/ሮ አሰጋሽ ከጭሰኛቸው ጋር ያደረጉት ዘዬ-መጥ ቃላትን የያዘ ምልልስ ቀርቦላችኋል፡፡ ከምልልሱ ግርጌ በተሰጣችሁ ሰንጠረዥ ውስጥ ዘዬ-መጥ ቃላቱን ፣ የሚነገሩበትን አካባቢና የሚተካቸውን አቻ መደበኛ ቃል አስፍሩ፡፡**

"የመሄጃ እጦት ነው እመየቴ…

"ግርምቢጠኛነትህን ትንሽ አብርዶልሃል፤ መቼስ ጨርሶ ባይጠፋ፡፡ አዎ ለወደፊቱ መንገድ ስንገናኝም ቢሆን ከፊቴ ሽረር ብለህ መንገዱን

ብትለቅልኝ ነውር የለውም - - - አንዳንዴ እንደሚማልግ ነብር፣ አንዳንዴ እየተፍረገረገ እንደሚለማመጥ ድመት መሆንህ ያስተዛዝባል - - - አዎ ፊት ማጭገግ በኔ አይደለም - - ከግንባርህ ትህትናን አታጥፋ - - -
“እመቤቴ መቼም ከዚህ በፊት አላስቸገርኩዎትም - - -
“እንዴት አዝን ይመስልሃል፣ እንዲህ ተቆራምደህ ሳይ - - -
“ታዲያ ታዘኑ - - -
“እንዴታ ታሳዝነኛለህ ነገር ወዲያ ወዲህ ሆኖብኝ ነው እንጂ …

| ተ.ቁ | ዘዬ-መጥ ቃል | የሚነገርበት አካባቢ | አቻ ቃል |
|---|---|---|---|
| | | | |

**፫. አማርኛ ቋንቋ መደበኛውን ጨምሮ የሸዋ፣ የወሎ፣ የጎንደርና የጎጃም ዘዬዎች እንዳሉት ይታወቃል። ሰዎችን ጠይቃችሁ ወይም መጻሕፍት አንብባችሁ ለእያንዳንዱ የዘዬ አካባቢ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ አምስት አምስት ዘዬ-መጥ ቃላትን በመሰብሰብ የሚነገሩበትን አካባቢና የሚተካቸውን መደበኛ አቻ ቃል ጽፋችሁ አቅርቡ።**

**፬. ከዚህ በታች ከተዘረዘሩ ርዕሶች አንዱን መርጣችሁና በተገቢው የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልት ተጠቅማችሁ አንድ አንቀጽ ጽፋችሁ አቅርቡ።**

1. ጊዜ
2. ፍቅርና ጥላቻ
3. ይቅርታ
4. የአካባቢ ንጽህና

**፭. በጥንድ ሆናችሁ የጻፋችሁትን አንቀጽ በመለዋወጥ፣**

1. ጓደኛችሁ የትኛውን የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልት እንደተጠቀመ ለዩ።
2. አንቀጹ የጥሩ አንቀጽ ባህሪያትን (አንድነት፣ ውህደት፣ አጽንኦት) ስለማሟላቱ ገምግማችሁ አስተያየታችሁን በጽሑፍ ለጓደኛችሁ ስጡ።

3. ከጓደኞቻችሁ በተሰጣችሁ አስተያየት መሰረት አንቀጻችሁን አሻሽላችሁ ጻፉ።

## ክፍል አምስት- ስነልሳን

**፩. ቀጥሎ በቀረቡላችሁ ዓረፍተነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት በተሰጣችሁ ምሳሌ መሠረት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ስጡ።**

*ምሳሌ፡-*

<u>ወለብላባ</u> ሰው የሌላውን ሐሳብ ለማዳመጥ አይሞክርም።

<u>ተመሳሳይ</u>፡- ለፍላፊ፣ ምላሰኛ

<u>ተቃራኒ</u>፡- ዝምተኛ

1. የወንድማችን <u>ሽርክት</u> መሆን፣ የቤተሰቡን ክብር እየነካ ነው።
2. ያለቦታው ገብቶ <u>ማደሽደሽ</u> ምን ቤት ነው ያሰኛል።
3. <u>ውለኛ</u> ሰው ክብርን ያተርፋል።
4. ደመወዜ የተጨመረ ስለመሆኑ ድርጅቱ <u>በቅጅ</u> አሳውቆኛል።
5. ሰውየው አጥፊ ቢሆንም ባለቤቱ ግን <u>ምልስ</u> ናት።
6. ማጣት <u>የኀለሰሰው</u> ሰው፤ ይሉኝታውን ይጥላል።
7. <u>ጋግርታም</u> ሰው እራሱን ይጎዳል።
8. ዘይነባ <u>ኀናዴ</u> ልጅ አላት።
9. የሁሉንም ወቀሳ <u>በአርምሞ</u> ተቀበለ።
10. በችግር <u>ከመቆራመድ</u> ሰርቶ እራስን መለወጥ ብልህነት ነው።

**፪. ቀጥሎ የቃላት ጥያቄዎች ቀርበዋል። እያንዳንዱ ጥያቄ አራት አራት ቃላትን ይዟል። ከአራቱ ሦስቱ በፍች ይዛመዳሉ። በፍች የማይዛመደውን ምረጡ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. ሀ. አረቀ | ለ. አቀና | ሐ. አስተካከለ | መ. አሻከረ |
| 2. ሀ. ተቆጣ | ለ. ደሰቀ | ሐ. ደቃ | መ. ተጫነ |
| 3. ሀ. በረሰ | ለ. ቀዘቀዘ | ሐ. ሞቀ፣ | መ. ተሻረ |
| 4. ሀ. ኮበሌ | ለ. ህፃን | ሐ. ጎረምሳ | መ. ወጣት |
| 5. ሀ. ጥሎሽ | ለ. ዳረጎት | ሐ. ስጦታ | መ. ገጸበረከት |

**፫. ከዚህ በታች በቀረቡ ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ቃላት በተሰጣችሁ *ምሳሌ* መሠረት በየቃል ክፍሎቻቸው መድቡ።**

***ምሳሌ፣*** *በጥያቄና መልስ ውድድር ላይ ቶሎ ትክክለኛ መልስ መስጠት ጎበዝ ያሰኛል።*

| ስም | ቅጽል | ግስ | ተውሳከ ግስ | መስተዋድድ |
|---|---|---|---|---|
| ጥያቄና፣ መልስ፣ ውድድር፣ መስጠት፣ ነጥብ | ትክክለኛ፣ ጎበዝ | ያሰኛል | ቶሎ | በ-ላይ |

1. በልቦለድ ትረካ ወደፊት የሚፈጸም ድርጊትን አስቀድሞ ለመገመት የሚቻለው፣ የተሰጠ ንግር ሲኖር ነው።
2. ብሩህ አእምሮ ያላቸው ሰዎች ያነበቡትን ቶሎ ይረዳሉ።
3. ወኔቢስ ወታደር ለድል አይበቃም።
4. ክፉ አመል እያደረ ይገለጣል።
5. "ዐይኖቿ እንደቀለጠ ብረት ሲንከባለሉ ይታያሉ"።
6. ዘይነባ ክፉኛ በመታመሟ ወደ ሆስፒታል ተወሰደች።

**፬. ከዚህ በታች ሰዋስዋዊ ስህተት ያለባቸው ዓረፍተነገሮች ቀርበዋል። በየዓረፍተነገሮቹ የእያንዳንዱን የቃል ክፍል ሙያ በመመርመር ስህተቱን ከለያችሁ በኋላ፣ ዓረፍተነገሮቹን አቃንታችሁ ጻፉ።**

***ምሳሌ፣*** *ጎበዝ ገበሬ ለፍቶ ማግኘት ያውቃል።*

*ስህተቱ፣ (የተሳቢነት ሙያ በአጸፋ አልተመለከተም)*

*ሲቃና፣ ጎበዝ ገበሬ ለፍቶ ማግኘትን ያውቃል።*

1. አሰራሩና ቅልጥፍናው የተማረ ይመስላል።
2. ሩዝ ሰዎች ይመገባሉ።
3. እህቴ እቃ መግዛትን ትወዳለች።
4. ቤታችን አጠገብ የዘይት መጭመቂያ ፋብሪካ አለ።
5. የአቶ ከበደ ልጅን አስጠናለሁ።

6. የነበረኝ ፍርሀትና ከመኪናው ፍጥነት ጋር ተዳምሮ መንገዱን ለቅቄ እንድወጣ አስገደደኝ፡፡
7. ትክክለኛውን የሀገራችንን ገጽታ በጋዜጣው አልተጠቀሰም፡፡

## ክፍል ስድስት፡- ስነጽሑፍ

**ፌ. ከዚህ በታች የሰፈሩትን የልቦለድ ዘዴዎች መሰረት በማድረግ፣ በቡድን ሆናችሁ የልቦለድ አላባውያንና የልቦለድ ዘዴዎች ባላቸው ትስስር ላይ ተወያዩ፤ የደረሳችሁበትን ድምዳሜ በቡድን መሪያችሁ አማካይነት በቃል አቅርቡ፡፡**

### የልቦለድ ዘዴዎች

በልቦለድ ድርሰት ዋና ዋና የአተራረክ ዘዴዎች የሚባሉት ምልልስ፣ ገለጻ፣ ምልሰትና ንግር ናቸው፡፡

**1. ምልልስ**

ምልልስ፣ በዘዴነቱ የገፀባህርያቱን ስሜት፣ ዓላማ፣ ችግርና ስነልቦናዊ መልክ ወዘተ. ማሳያ ነው፡፡ በአጻጻፉ ግልጽ፣ የተመጠነና ማራኪ እንዲሆን ከማስፈለጉም በላይ ከታሪኩና ከትልሙ ጋር በሚገባ የተቀናጀና ተደራሲያን ከገፀባህርያቱ ጋር የጠለቀ ቅርበት እንዲኖራቸው ማድረግ አለበት፡፡

**ምሳሌ፣**

ሔላ የደረቀ እንባዋ ከረጢቱን ጥሶ መጣሁ መጣሁ እንዳላት ሁሉ፣ የአይኖቿን ሽፋሎች እያርገበገበች በጨመቃ አስጨነቀቻቸው…

"ቦሎክ" አለች አንገቷን ወደ መሬት ቀብራ፡፡
"አቤት" አላት በተሰላቸ አነጋገር፡፡
"ያንተን ውሳኔ ንገረኝ?"
"የኔን ውሳኔ ለመቀበል ወይስ ለማዳመጥ?"
"ለመቀበል፡፡"
"እርግጠኛ ነሽ?"
"ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነኝ፡፡"
ቦሎክ ደስታው መጠን አልፎ ሲሔድ ተሰማው፡፡ ህይወቱ እንደገና

የተፈጠረች መሰለው፡፡ በተስፋ ተሞላ የደስታ ሲቃ ...እንባ...ሳቅ ...እንባ...ሳቅ...
“ሔላ እወድሻለሁ”
“እኔምኮ እወድሃለሁ” እሱ ያለው እንዳይቀርባት እሷም ተጠጋችውና...

*(ይስሀቅ ሁሴን አባቦራ፣ ሔላ፣ 1983፣15)*

ከዚህ በላይ በቦሎክና በሔላ መካከል የተደረገ ምልልስ፣ አንዳቸው ላንዳቸው ያላቸውን ፍቅርና አሁን ለገቡበት ችግር የሚሆን የመፍትሄ እርምጃን ለመቀበል ሔላ ያላትን ዝግጁነት ያሳያል፡፡

## 2. ገለጻ

ይህ የመተረኪያ ዘዴ ስለገፀባህርያት አካላዊና ህሊናዊ መልክ፣ ስለሚኖሩበት አካባቢ፣ የአየር ሁኔታና አጠቃላይ ድባብ፣ ስለሚፈጽሟቸው ድርጊቶችና ስለሚሳተፉባቸው ሁነቶች ወዘተ. ስዕላዊ በሆነ መንገድ የሚቀርብበት ነው፡፡ ገለፃ በተባ ቋንቋ የተደራሲያንን የስሜት ህዋሳት ቀርቦ በቃላት መሣሪያነት እንዲያዩ፣ እንዲያሸቱ፣ እንዲዳስሱ፣ እንዲቀምሱ፣ እንዲያዳምጡ የሚያደርግ ነው፡፡

**ምሳሌ፣**

ቁንዲ አንገቷን አስግጋ ቃፊርነት የቆመች መስላለች፡፡ የአዋዲና የጃውሃ ጅረቶች ደረታቸውን ለፀሐይ ሰጥተው ይንቦገቦጋሉ፡፡ ሰማይና ምድር የተገናኙበት ህይወት ያሸለበችበት የሚመስለውን በስተግርጌ የሚታይ ሜዳ አቧራ ረግቶበታል፡፡ በየስርጓጉጡ፣ በየሸለቆው፣በየተረተሩ፣ በየሸንተሩ ጉርዲ፣ ወፍ ዋሻ፣ ዋንዛበረት፣ ጃናቦራ፣የልቆኪ፣መጢ፣ ዲውዲያምባ፣ አዋዲ፣ ጨኖ፣ አጋምበር፣ ዋይሎ፣ ደብረሲና፣... በየከፍታዎቹ ጉብታዎች ግፋት ሚካኤል፣ ጉርድ ሚካኤል ዋንዛበር ሚካኤል... የይፋትና ጥሙጋ አውራጃን ጣርማበር ተራራ ላይ ሆኖ ሲመለከቱ እግዚአብሔር ዓለምን ሰርቶ ሲያበቃ የተረፈውን ትርክምክም ያጎረበት ዕቃ ቤቱ ይመስላል፡፡

*(ዳኛቸው ወርቁ፣ አደፍርስ፣ 1962፣ 5)*

ከዚህ በላይ በቀረበው ምሳሌ፣ ደራሲው በገለጻ ዘዴ በመጠቀም ጣርማ በር ተራራ ላይ ሆኖ የይፋትና ጥሙጋ አውራጃን ሲመለከቱ ምን እንደሚመስል፣ አጠቃላይ ድባቡን ጭምር ምስል ከሳች በሆነ አገላለጽ "እግዚአብሔር ዓለምን ሰርቶ ሲያበቃ የተረፈውን ትርክምክም ያጎረበት ዕቃ ቤቱ ይመስላል" በማለት አካባቢውን በአይነህሊና እንድንቃኝ ያደርገናል።

## 3. ምልሰት

ምልሰት፣ የገፀባህርያትን የቀደመ ማንነት፣ ገጠመኝ፣ ስሜትና አስተሳሰብ ወደኋላ በመመለስና ቀንጭቦ በማምጣት ያሁኑን የስብእና መሠረታቸውን ለማሳየት የሚጠቅም የአተራረክ ዘዴ ነው።

**ምሳሌ፣**

…ቅንጣት ያህል ጀግንነት አልፈጠረብኝም። ወይ ወኔ ማጣት! አነታደሰ፣ እነገብረመስቀል፣ አይ የከተማ ልጆች! ስምንተኛ ክፍል አብረውኝ ይማሩ ነበር። በትምህርት ቤታችን የታወቁ ልጆች ነበሩ። በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ጨዋታው ሁሉ ስለነሱ ነበር። እኔ ደግሞ የአማርኛን ክፍለ ጊዜ በጣም እጠላ ነበር። በተለይ ንባብ ከሆነ እምባ ይመጣብኛል። የኔ ተራ ደርሶ ተነስቼ ሳነብ በሱሪዬ ቀዳዳ ቂጤን እያዩ ይስቁብኛ ነበር። በዚህ የተነሣ አማርኛን ከነአስተማሪው ነው የምጠላው…

*(ስለሞን ስማ፣ ደብዳቤው፣ ጉዞውና ሌሎች ልብወለዶች፣ 1979፣ 26)*

ከምሳሌው እንደሚታየው፣ ለገፀባህሪው የዛሬ ወኔቢስነቱ መሠረት የሆነው የቀደመው ገጠመኙ ምን እንደነበር በምልሰት አሳይቷል።

## 4. ንግር

በትረካ ዘዴነቱ ወደፊት ስለሚከሰት አንዳች ነገር ድርጊትና ሁኔታ ሁሉንም ነገር ዘርግፎ የሚታተትበት ሳይሆን፣ ጥቆማ ወይም ፍንጭ የሚሰጥበት ነው። ስለዚህም ተደራሲ አንባቢን ወደፊት የሚሆነውን አስቀድሞ በተሰጠው ንግር መሠረት መገመት እንዲችል ያደርጋል።

***ምሳሌ፣***

…ዳንሱን ቀጠሉ፡፡

አበራ ለጥቂት ጊዜ ስልቷን በታላቅ ትዕግስት ሲጠብቅ ቆየና በድንገት ሳታስበው “ከነስምሽ ገደል ልትገቢ ትችያለሽ” ብሏት ወለሉ ላይ እንደቆመች ትቷት ሊሔድ ሲል እጁን ይዛ አስቀረችው፤ አልተነቃነቀም፡፡

… አይኖቿ በዚያ ጨለማ እንደቀለጠ ብር ሲንከባለሉ ይታያሉ፤ የደረቁ ከንፈሮቿን በመላስ አለሰለሰቻቸውና፤ ”ማንም ወንድ ሉሊትን ተራምዷት ሊሔድ አይችልም!” አለችው፤ የቀድሞውን ስልት ባጣ ድምጽ፡፡

*(በዓሉ ግርማ፣ ከአድማስ ባሻገር፣ 1962፣ 35)*

ከምሳሌው እንደምንረዳው፣ በሆቴል በመደነስ ላይ ሳሉ በድንገት አበራ ሉሊትን ሊለያት ሲል እሷ ግን ጠበቅ አድርጋ እንደያዘችው ያሳያል፡፡ ይህ ንግር ነው፡፡ የሚጠቀመውም ወደፊት ሉሊት አበራን በዋዛ እንደማትለቀው ነበር፡፡

**፪. አንድ ረጅም ወይም አጭር ልቦለድ መርጣችሁ በማንበብ ቀጥሎ የሰፈሩትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. ለልቦለድ የአተራረክ ዘዴዎች ማሳያ የሚሆኑ ክፍሎችን እየቀነጨባችሁ በማውጣት፣ ለእያንዳንዳቸው የልቦለድ ዘዴዎች አንድ አንድ አንቀጽ ማብራሪያ ጻፉ፡፡
2. በቡድን ሆናችሁ ባቀረባችሁት ማብራሪያ ላይ ተወያይታችሁ፣ የተሻለውን በመምረጥና በማዳበር በቡድን መሪያችሁ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ በቅድሚያ በልቦለድ ውስጥ ትልምና ግጭት ምን እንደሆኑ አንስተናል፡፡ ትልም፣ በአንድ ልቦለድ ታሪክ ውስጥ “ምን? ለምን ተደረገ?” ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው መልስ እንደሆነ ተረድተናል፡፡ ትልም “ታሪክ” ከተሰኘው የልቦለድ አላባ ጋር የሚለያየው፣ ታሪክ በጊዜ ቅደም ተከተል የተፈጸሙ ሁነቶች ትረካ ሲሆን፣ ትልም ግን የተከናወኑ ሁነቶች ትረካ ብቻ ሳይሆን ሁነቶቹ እንዲፈጸሙ ያስገደዱ ምክንያቶችንም ጭምር የሚይዝ በመሆኑ እንደሆነ አይተናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ፣ ስለ ቃላት ፍች ባነሳንባቸው ክፍሎች የቃላት ፍች እንደገቡበት አውድ እንደሚለያይ፣ አውዳዊና መዝገበቃላዊ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች በመስጠትና በዓረፍተነገር ውስጥ በማስገባት ከማየታችንም በላይ፣ የተነወሩ፣ ዘዬ-መጥና የአራዳ ቃላትን ለይተን በተገቢው ቃላት ተክተናል፡፡ በሌላ በኩል፣ ልቦለዶች አንብበንና አድምጠን መልሰን መተረክ ችለናል፡፡ ካነበብናቸው ልቦለዶችም፣ ትልምና ግጭትን መዝዘን በማውጣት አሳይተናል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ንግግርን አድምጠን አስፈላጊና የማያስፈልጉ ሀሣቦችን መለየት ችለናል፡፡ የአንቀጽ ማስፋፊያ ዘዴዎችን በከለስንበት ክፍል ደግሞ፣ ዋና ዋና የማስፋፊያ ስልቶችን አንስተን በተለያዩ ርዕሰጉዳዮች ላይ ያተኮሩ አንቀጾችን አስፋፍተናል፡፡ በዓረፍተነገር ውስጥ የሚገኙ ቃላትንም በቃል ክፍሎቻቸው መመደብ ችለናል፡፡ በመጨረሻም፣ ስለልቦለድ ዘዴዎች ባነሳንበት ክፍል፣ ዋና ዋና የሚባሉት የልቦለድ ትረካ ዘዴዎች ገለጻ፣ ምልልስ፣ ንግርና ትረካ መሆናቸውን በመረዳት፣ ለዘዴዎቹ ማሳያነት ካነበብናቸው ልቦለዶች ውስጥ ትረካዎችን ቀንጭበን በማውጣት አብራርተናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. አንድ አጭር ልቦለድ በማንበብ የልቦለዱን ታሪክና ትልም በማውጣት፣ ትልም ከታሪክ የሚለይባቸውን ነጥቦች ከልቦለዱ እያጣቀሳችሁ አብራሩ፡፡
2. በልቦለድ ትልምና ግጭት መካከል ያለውን ትስስሮሽ በምሳሌ አስደግፋችሁ ግለጹ፡፡
3. በድርሰት ውስጥ የልቦለድ ዘዴዎችን ሚና ካነበባችሁት ልቦለድ ምሳሌዎችን በመምዘዝ አስረዱ፡፡

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ አራት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል:: በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ (√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ::

| ተራ ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስለልቦለድ ያነበብኩትን ተረድቻለሁ:: | | | |
| 2 | ለቃላት አውዳዊና መዝገበ ቃላዊ ፍች እንዲሁም ተመሳሳይና ተቃራኒ መስጠት ችያለሁ:: | | | |
| 3 | ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ሰጥቻለሁ:: | | | |
| 4 | በዓረፍተነገር ውስጥ ያሉ ቃላት በየትኛው የቃል ክፍል እንደሚመደቡ መግለጽ ችያለሁ:: | | | |
| 5 | ያዳመጥኩትን ልቦለድ መልሼ ተርኬያለሁ:: | | | |
| 6 | በማዳመጥና በማንበብ ያገኘኋቸውን ሃሳቦች አስፈላጊና አላስፈላጊ በማለት መድቤያለሁ:: | | | |
| 7 | የተነወሩ ዘዬ-መጥና የአራዳ ቃላትን ከጽሑፍ ውስጥ ለይቼ በማውጣት በተገቢ ቃላት ተክቻለሁ:: | | | |
| 8 | ከመረጃ ምንጮች ሃሳቦች መሰብሰብና ማጠናቀር ችያለሁ:: | | | |
| 9 | በአንቀጽ ማስፋፊያ ስልቶች ተጠቅሜ አንቀጽ አስፋፍቻለሁ:: | | | |
| 10 | ከልቦለድ ውስጥ የልቦለድ አላባዊያንን በተለይም ግጭቱንና ትልሙን ለይቼ ጠቁሜያለሁ:: | | | |
| 11 | ከልቦለድ ጽሑፍ ውስጥ የልቦለድ ማቅረቢያ ዘዴዎችን /ቴክኒኮችን/ ለይቼ አውጥቻለሁ:: | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ (?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ::

# ምዕራፍ አምስት

# የቋንቋ ለዛ

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡- ተማሪዎች! ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- ✓ አንድን ጽሑፍ የቋንቋ ለዛ እንዲኖረው የሚያደርጉ ነጥቦችን ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ ለቋንቋ ለዛ ይሰጣሉ የሚባሉ ቃላትን፣ ሐረጋትን፣ አባባሎችንና ዓረፍተነገሮችን እየለያችሁ እንዴት ለዛን እንዳስገኙ ታብራራላችሁ፡፡
- ✓ ከጽሑፍ ውስጥ አስፈላጊና የማያስፈልጉ ሐሳቦችን እየለያችሁ የማያስፈልጉትን ታወጣላችሁ፡፡
- ✓ የቅኔ አፈታት ዘዴን ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ የተለያዩ ቅኔዎችን ሰምና ወርቅ በመለየት ትፈታላችሁ፡፡
- ✓ የተለያዩ ዘይቤዎችን በመለየት ትተረጉማላችሁ፡፡
- ✓ የተለያዩ ዘይቤዎችን በጽሑፋችሁና በንግግራችሁ ትጠቀማላችሁ፡፡

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

**፩. ቀጥሎ “የቋንቋ ለዛ” በሚል ርዕስ አንድ ጽሑፍ ታነባላችሁ፡፡ ከዚያ በፊት ግን በቡድን ሆናችሁ “ለዛ ያለውና ለዛ የሌለው ቋንቋ” ሲባል፣ ምን ማለት እንደሆነ ተወያዩ፡፡ ከአራት ደቂቃ ውይይት በኋላም የደረሳችሁበትን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡**

**፪. ጽሑፉን ማንበብ ከመጀመራችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በሚገባ መረዳታችሁን አረጋግጡ፤ ለማንበብ የሚሰጣችሁ ጊዜ ስምንት ደቂቃ ሲሆን፣ ጥያቄዎቹን በአእምሮአችሁ በመያዝ መልሶቻቸውን ከምንባቡ ማግኘት ይጠበቅባችኋል፡፡**

1. በጽሑፉ የተገለጹት ዋና ዋና የቋንቋ ለዛ ማስገኛ ስልቶች ምን ምን ናቸው?
2. ምሳሌያዊ ንግግሮች እንዴት ይፈጠራሉ?
3. የምሳሌያዊ ንግግሮች አገልግሎት ምንድን ነው?
4. በቅኔ ውስጥ የሰምና ወርቅ ሚና ምንድን ነው?

## የቋንቋ ለዛ

የአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች፣ ንግግራቸው ወይም ጽሑፋቸው የሰመረ ሐሳብን ማስገኘት እንዲችል፣ የተለያዩ የቃላትና ሀረጋት ግጥሚያዎችን ያፈልቃሉ፡፡ እነዚህ ግጥሚያዎች ከተለመደውና የዘወትር ከሆነው የቃላት፣ የሐረጋት አደራደርና የሐሳብ አወራረድ ስርዓት ወጣ በማለት የሚገለጸውን ነገር ባህሪ፣ ስሜትና መልክ ጎልቶና ደምቆ እንዲታይ ማድረግ ሲችሉ፣ ለዛውን የጠበቀ አገላለጽን እውን ያደርጋሉ፡፡ ለዛ ያለው ቋንቋ ደግሞ፣ የአድማጭና የአንባቢን ቀልብ ለመግዛት፣ ምናባዊ ሀሴትን ለማጎናጸፍ እጅግ ከፍ ያለ ብርታት አለው፡፡

አንድ ሰው፣ ለስሜት ሕዋሳት ያልቀረቡና ረቂቅ የሆኑ ሐሳቦቹን በተዝናና በተፍታታ መንገድ ለአድማጭ ወይም ለአንባቢ ማሸጋገር እንዲሁም ሌሎች የሚያስተላልፏቸውን መረዳት የሚችልባቸው የቋንቋ

ለዛ ማስገኛ ስልቶች በርካታ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ አንዱ ዘይቤ ነው። ዘይቤ፣ የቋንቋ ሰው ገጠመኙን፣ ለህይወት ያለውን አተያይ፣ ያደገበትንና የሚኖርበትን አካባቢ ማህበራዊ እሴቶችንና ጥልቅ ምናቡን ተጠቅሞ ከተለመደው የእለት ተእለት የቃላት አጠቃቀም ባፈነገጠ መልክ ተገላጩ ነገር ደምቆ እንዲታይ የሚያደርግበት የቋንቋ አጠቃቀም ላቅ ያለ ደረጃ ነው። በቋንቋ ለዛና ውበት ምንጭነቱም በንግግርም ሆነ በጽሑፍ፣ በዝርውም ሆነ በግጥም ሊተላለፍ የተፈለገውን አንዳች ነገር ፣ባህርይ፣ ድርጊት፣ ወዘተ. የመልዕክት ኃይልና ፍካት በማጎናጸፍ ትኩስና ግብ መቺ በሆነ መንገድ ማስተላለፍ ያስችላል። ይህ ባህሪው፣ ዘይቤን ቀጥተኛ ከሆነው ልሙጥ የዘወትር መግባቢያ ቋንቋ የተለየ ያደርገዋል። ይህንኑ በተከታዮቹ ስንኞች እንመልከት፡-

ሰዋስው ጨዋታ ዘይቤ ንግግር፣
ሰሚ ከተገኘ ያምርብን ነበር።
ዘይቤ ካስወደደህ ተቀምጠህ ስማ፣
አዝማሪው አለልህ ለስለምኑማ።

*(ስለማየሁ ሞገስ፣ የአማርኛ ግጥምና ቅኔ ማስተማሪያ፣ 1954፣ 39)*

በነዚህ ስንኞች እንደተመለከተው፣ ዘይቤ ሀሣብን እያዋዙ የሚያስ ተላልፉበት ለዛ ያለው አገላለጽ ነው። ትርጉሙን ለመረዳትም የዘይቤ ስልቱን ማፍታታትና ማጣጣም የሚያስችል እውቀት ያስፈልጋል። ለዚህ ነው ገጣሚው፣ "ሰሚ ከተገኘ ያምርብን ነበር" በማለት የገለጸው።

ዘይቤን ከዘወትሩ ቋንቋ የተለየ የሚያደርገው አፈጣጠሩ ነው። የቋንቋ ተናጋሪው ማስተላለፍ የፈለገውን አንድ ሐሳብ፣ ነገር ወይም ረቂቅ ባህርይ ለመግለጽ ሲል፣ ተገላጩን ከሌላ ነገር ጋር በማነጻጸር፣ በማመሳሰል፣ አንዱን በሌላው በመወከል፣ ያንዱን ባህሪ ለሌላው በመስጠት ዘይቤን ያፈልቃል። ለምሳሌ፣ "በወባ ወረርሽኝ ብዙ ሰዎች ሞቱ" የሚለውን ሐሳብ ወስደን፣ "የወባ ወረርሽኝ ህዝቡን እንደቅጠል አረገፈው።" ከሚለው ጋር ብናነጻጽረው የቀደመው መግለጽ የተፈለገውን

ሀሣብ ልል በሆነ መንገድ በቀጥታ የገለጸው ሲሆን፣ የኋለኛው ግን የሟቹ ቁጥር ብዙ መሆኑን ለማመልከት “ህዝቡን እንደቅጠል” በማለት በማመልከት፣ ሞቱን ደግሞ ከመርገፍ ጋር አያይዞታል፡፡ በመሆኑም፣ ሀሳቡ በዘይቤ በመገለጹ አድማጩ ወይም አንባቢው አእምሮአዊ ምስል እንዲፈጥርና የበሽታውን አስከፊነት  እንዲረዳው ማድረግ የቻለ ነው፡፡

የቋንቋ ለዛን የሚያስገኙ የቃላት አደራደርና የአጠቃቀም ስልቶች በዘይቤ ብቻ የሚቆሙ አይደሉም፡፡ ፈሊጣዊና ምሳሌያዊ ንግግሮችም፣ የቋንቋ ውበትንና የሀሣብ ተደማጭነትን በማስገኘት በኩል ላቅ ያለ ሚና አላቸው፡፡ ፈሊጣዊ አነጋገር፣ ቃላትን በልዩ ልዩ መንገድ በማቀናጀት ለተለየ ጽንሰ ሀሣብ  መግለጫነት  እንዲውሉ የምናደርግበት የቃላት አጠቃቀም ስልት ነው፡፡ በዚህ ስልት፣ አንድ ቃል ከሌላ  ቃል ጋር ሲቀናጅ በመሠረቱ ከነበረው የተለየ ፍች የሚያስገኝበት ሁኔታ እንዳለ ሁሉ፣ ቃሉ መጀመሪያ ከቆመበት እሳቤ ጋር ተመሳሳይ ለሆኑ ሌሎች እሳቤዎች ወኪል በመሆን ትርጉሙን እያሰፋም ሊሄድ ይችላል፡፡ ሁኔታውን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ በምሳሌ መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ፈሊጣዊ አነጋር፣ የተለየ ፍች ከማስገኘቱ አንጻር ሲታይ፣ ለምሳሌ፣ “ነፍሱን መረመረ” የሚለውን ብንወስድ፣ በሁለቱ ቃላት የየቅል ትርጉም መሠረት “ሰውየው የገዛ ነፍሱን አጠና” ለማለት ሳይሆን፣ “ምጽዋት ሰጠ” ለማለት ነው፡፡ በፈሊጣዊ አነጋገር፣ አንድ ቃል ትርጉሙን እያሰፋ የሚሔድበትን ለመመልከት ደግሞ “ቁልፍ” የሚለውን ቃል እንውሰድ፡፡ ቁልፍ መጀመሪያ አንድ ነገር ለመቆለፍና ለመክፈት የሚያገለግል ሲሆን፣ ይኸው ቃል በፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉሙን እያሰፋ ሲሄድ “ሆዱ ተቆለፈ፣ ቁልፍ ሚና፣ ቁልፍ ሰው፣ ቁልፍ ቦታ” እየተባለ ይሰራበታል፡፡

እንደፈሊጦች ሁሉ፣ የደበዘዘን ሐሳብ አፍክቶና ለዛ አላብሶ ሀሣብን እንደ በጋ ሰማይ ፍንትው አድርጎ ባጭሩ ለማሳየት ሲፈለግ ምሳሌያዊ ንግግሮች በጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ ያንድ ቋንቋ ተናጋሪ አንድ ማህበረሰብ ባሳለፈው ረጅም ዘመን ከተፈጥሮ ጋር ባለው መስተጋብር በበርካታ

ገጠመኞች ውስጥ ያልፋል፡፡ ምሳሌያዊ ንግግሮችም ማህበረሰቡ ከገጠመኙ በመነሳት የሚቀምራቸው፣ የገጠመኙ ማንፀባረቂያ የሀሣቡ ማድመቂያ አባባሎች ናቸው፡፡ ዋና ተግባራቸውም ያልታወቀውን የመግለጥ፣ የመምከርና የማስተማር፣ የመግታትና የመቆጣጠር ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሣሌ፣ "አቀበት ያደክማል፤ እርሻ ያዳግማል" የሚለው ምሳሌያዊ ንግግር፣ ሥራ ያንድ ጊዜ ብቻ እንዳልሆነ ወይም ድካምን ሳይቆጥሩ መሥራት እንደሚያስፈልግ ባጭር አገላለጽ ያስተምራል፡፡

ላቅ ያለ የቋንቋ ለዛን በማስገኘት በኩል ከዘይቤ፣ ከፈሊጦችና ምሳሌያዊ ንግግሮች ባሻገር፣ ሰም ለበስ ብሒሎች ቋንቋውን እያዋዙ ለዛውን በማስገኘት በኩል አገልግሎታቸው ጉልህ ነው፡፡ ጠለቅ ረቀቅ ያለን የምናጎላበት ዘዴ ዘይቤ እንደሆነ ሁሉ፣ አንድ የተነገረ ወይም የተጻፈ ሀሣብ፣ ሁለትና ከሁለት በላይ ፍች ኖሮት ተጣምሮ አንድ ሀሣብ (ወርቁን) ለመግለጽ የዋለ እንደሆነ ቅኔ ይባላል፡፡ አንድ ዓረፍተነገር ወይም ስንኝ ቅኔ ለመባል ተሰንጥቆ ቢያንስ ሁለት የተለያዩ ዓረፍተነገሮች ሊወጣው ይገባል፡፡ በዓረፍተነገሩ ወይም ስንኙ ውስጥ ሚስጢሩን የሚሸከመው ቃል (ሐረግ) ህብረ ቃል በመባል ሲታወቅ፣ ፊት ለፊት የሚገኘውና አንቀጹ የሚናገርለት ፍች ሰም ይባላል፡፡ ሚስጢሩና ዋናው የዘራፊው መልእክት ደግሞ ወርቅ ይሰኛል፡፡

**ምሳሌ፣** ምነው ብታስጠሪኝ እኔን አስታውሰሽ፣
እደጅ ተቀምጬ እቤቴ ሳመሽ፡፡

የዚህ ቅኔ ህብረ ቃል፣ "ሳመሽ" የሚለው ሲሆን፣ ሰሙ "ያለ ሥራ ተቀምጬ ሳመሽ ምናለ አስታውሰሽ ብታስጠሪኝ ኖሮ" የሚል ፍች አለው፡፡ ወርቁ ደግሞ "እኔ እደጅ በተቀመጥኩ ጊዜ እቤት ውስጥ አንቺን ሳመሽ" የሚል መልዕክት አለው፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ያነሳናቸው የቋንቋ ለዛ ማስገኛ ስልቶች፣ ለአንድ የቋንቋ ተናጋሪ ሐሳቡን አድምቆና አስውቦ ለማስተላለፍ የሚያስችሉት ናቸው፡፡ ይሁንና፣ በቋንቋ አጠቃቀም ሂደት ተናጋሪው ሐሳቡ

የሚነገርበትን አውድ ጠብቆ በተገቢው ቦታ ተገቢ ቋንቋን መጠቀም ይጠበቅበታል፡፡

## ክፍል አንድ- አንብቦ መረዳት

**፩. ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. ለዛውን የጠበቀ አገላለጽ እውን የሚሆነው እንዴት ነው?
2. ዘይቤን ከዘወትሩ ቋንቋ የተለየ የሚያደርገው ምንድን ነው?
3. የአንድ ፀሐፊ ወይም ተናጋሪ ዘይቤን የመፍጠርና ቋንቋውን ለዛ የማጎናፀፍ ብቃት ምንጩ ምንድን ነው?
4. የፈሊጦችን አፈጣጠር ሁኔታ አብራሩ፡፡
5. ምሳሌያዊ ንግግሮች ሀሣብን ባጭሩ ፍንትው አድርገው እንዴት ማሳየት እንደሚችሉ በምሣሌ የተደገፈ ገለፃ ስጡ፡፡
6. ቅኔ ምንድን ነው? በምሣሌ አስረዱ፡፡
7. አንድን ጽሑፍ ወይም ንግግር የቋንቋ ለዛ እንዲኖረው የሚያደርጉ ነጥቦችን አብራሩ፡፡

**፪. በምንባቡ ውስጥ በመጥበቅና በመላላት፣ የፍች ልዩነት የሚያስከትሉ ሆሄያትን የያዙ ቃላት ይገኛሉ፡፡ ቃላቱን ከምንባቡ ለቅማችሁ ከዘረዘራችሁ በኋላ፣**

1. ሲጠብቁና ሲላሉ ያላቸውን ፍች ስጡ፡፡
2. ቃላቱን ተጠቅማችሁ የሰጣችሁትን ፍች የሚያሳይ ዓረፍተነገር ስሩ፡፡
3. ዓረፍተነገሮቹን በምርጥ ቃላት፣ ሐረጋትና አባባሎች አዋቅሩ፡፡

***ምሳሌ፣*** ቀልብ

*ሲላላ፡-* ልብ፣ ማስተዋል፣ ማስታወስ የሚችል አእምሮ

*ወንድማችን ውሃ አጣጭውን ካገኘ ወዲህ ቀልብ ገዛ፡፡*

*ሲጠብቅ፡-* አብላ፣ አጠጣ

*አንተማ ምን አለብህ፣ እነዚያን "ወፍ አርግፍ" ጓደኞችህን ቀልብ፡፡*

**፫. ከዚህ በታች በቀረቡ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት በፍካሬያዊ ፍቻቸው አገልግሎት ላይ ውለዋል:: ለቃላቱ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ከሰጣችሁ በኋላ፣ እማሬያዊ ፍቻቸውን የሚያሳይ ዓረፍተነገር ስሩባቸው::**

**ምሳሌ፣** ወንድማችን የትምህርት ቤት ወጪያችንን ሸፈነ::

ሀ. ፍካሬያዊ ፍች፣ ቻለ፣ከፈለ፣

ለ. እማሬያዊ ፍች፣ከለለ፣ጋረደ፣አለበሰ፣ደበቀ

ሐ. ዓረፍተነገር፣ ብልሁ ተማሪ ደብተር ገዝቶ በላስቲክ ሸፈነ::

1. ፋናዬ የአባቷን ማረፍ አልሰማችም::
2. የሞተ ተጎዳ፣ ቀሪ ምን አለበት?
3. የተቀባ መሪ ህዝብን ጆሮ ዳባ ልበስ አይልም::
4. ሽማግሌው ቀለሉ::
5. ሰራዊቱ ከያዘው ቦታ እንዲነቅል ታዘዘ::
6. የሴቱ ሁሉ ቁንጮ እሷ ናት::
7. ሌባው እንደተያዘ ባላፊ አግዳሚው ተወቃ::
8. ይህንን ያገጠጠ እውነት አሌ ልንለው አንችልም::
9. ገንዘብ ከሚቀመጥ ቢገላበጥ ትርፍ ያመጣል::
10. ልበብር ለሆነ ሰው ቅኔ መዝረፍ ብዙ ጊዜ ላይወስድበት ይችላል::

**፬. ቀጥሎ በዕለት ተዕለት ተግባቦት ውስጥ የማይዘወተሩና ልታውቋቸው የሚገቡ ቃላት ቀርበውዋል::**

1. መዝገበ ቃላትን ተጠቅማችሁ ቀጥተኛ ፍቻቸውን ስጡ/ጻፉ::

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. በተዛ | መ. አረጥራጭ | ሰ. ቡፍና |
| ለ. ጋሪያታም | ሠ. አምበልጋ | ሸ. ወቀሬ |
| ሐ. ፍጥምጥም | ረ. ሞረሽ | ቀ. ወላንሳ |

ቃላቱን ተጠቅማችሁ የሰጣችኋቸውን ፍችዎች ግልጽ የሚያደርጉ ዓረፍተነገሮች መስርቱ::

## ክፍል ሁለት:- መናገር

**፩. በቡድን ሆናችሁ፣ በያዝነው ሳምንት በቀበሌያችሁ፣ በምትኖሩበት ከተማ፣ ወይም በወረዳ ደረጃ የሚደረጉ ህዝባዊ ስብሰባዎች (የወጣቶች፣ የሴቶች፣ የነዋሪዎች፣ የገበሬዎች፣ የእድሮች፣ ወዘተ.) ላይ ተወያይታችሁ፣ የትኛው ክፍል ስብሰባዎቹን እንደጠራና የስብሰባውን አጀንዳ (አስቀድሞ ከተገለጸ) ለዩ::**

**፪. በቡድን መሪያችሁ አማካይነት የስብሰባዎቹን ዓይነት፣ የተሰብሳቢዎቹን ማንነትና ከተቻለ የውይይት አጀንዳውን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ::**

**፫. ከላይ በተራ ቁጥር -1 ከለያችኋቸው የሳምንቱ ህዝባዊ ስብሰባዎች ውስጥ፣ የሚቀርባችሁንና ለመግባት የምትችሉበትን በመምረጥ፣**

1. ስብሰባውን ተካፈሉ::
2. የስብሰባው ተካፋዮች የሚያደርጉትን ንግግር ተከታትላችሁ ከንግግራቸው ለዛ የሰጡትን ቃላት፣ ሐረጋት፣ ፈሊጣዊና ምሳሌያዊ አባባሎችና የዓረፍተነገር አሰካኮች፣ ተከታትላችሁ መዝግቡ፤ በየተናጋሪው በመለየትና ስለቋንቋ አጠቃቀሙ ማብራሪያ በማከል ገለጻ አድርጉ::
3. ከላይ በተራ ቁጥር ፩ በሳምንቱ የሚካሔዱ ሕዝባዊ ስብሰባዎች አለመኖራቸውን ያረጋገጠ ቡድን አባል የሆናችሁ ሁሉ፤ መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚሰጧችሁን ተመሳሳይ ተግባር ተቀብላችሁ ገለጻ አድርጉ::

## ክፍል ሶስት- ማዳመጥ

**፩. ከዚህ ቀጥሎ በአንድ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት የስነጽሑፍ ክበብ ለማቋቋም በተጠራ ስብሰባ የተካፈለች ተማሪ የተናገረችውን መምህራችሁ አንድ ጊዜ ሲያነቡላችሁ ታዳምጣላችሁ::**

1. ተማሪዋ በንግግሯ ያነሣቻቸውን ሐሳቦች እያዳመጣችሁ በአስተዋጽኦ መልክ ባጭር ባጭሩ መዝግቡ::

2. ከያዛችሁት ማስታወሻ ውስጥ ከስብሰባው ዓላማና መንፈስ ጋር በማገናዘብ “አላስፈላጊ” የሆኑትንና “አስፈላጊ” የሆኑትን ሐሳቦች ለዩ።
3. ጥንድ ሆናችሁ “የማያስፈልጉ” ብላችሁ የለያችኋቸውን ሐሳቦች ዝርዝር አስተያዩ፤ “አያስፈልጉም” ያላችሁበትን ምክንያት ተወያዩበት።
4. በውይይታችሁ በተስማማችሁባቸው “የማያስፈልጉ ሐሳቦች” ላይ በምክንያት የተደገፈ ማብራሪያ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

## ክፍል አራት- መጻፍ

**፩. ከሚከተሉት ርዕሶች አንዱን ከመረጣችሁ በኋላ በተመረጡ ቃላት፣ ሀረጋት እንዲሁም ምሳሌያዊና ዘይቤያዊ አባባሎች ተጠቅማችሁ ከሁለት ገጽ ያልበለጠ ድርሰት ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ።**

1. መስከረም
2. ፈተናና ተፈታኝ
3. ወጣትነት
4. ትዝታ

**፪. ከመጻሕፍት፣ ከመጽሔቶችና ከጋዜጦች ስለቋንቋ ለዛ የሚያወሱ ጽሑፎችን አንብባችሁ ማስታወሻ በመውሰድ ያገኛችሁትን ሀሣብ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ አሰሙ።**
**(ተከታዩ የማስታወሻ አወሳሰድ ስልት ማብራሪያ ለሥራችሁ ያግዛችኋል።)**

## የማስታወሻ አወሳሰድ

ስለምንፈልገው ርዕሰ ጉዳይ መረጃዎችን ከተለያዩ ምንጮች (ከመጽሐፍት፣ መጽሔቶች፣ ጋዜጦች ወዘተ.) ስናሰባስብ ዋና ዋና ሀሣቦችን ማስታወሻ የምንወስድባቸው ሦስት መንገዶች አሉ፡፡

### 1. ቀጥተኛ ጥቅስ

ካነበብነውና ካዳመጥነው የመረጃ ምንጭ የተገኘውን ሀሣብ እንዳለ ቃል በቃል ወስደን ስንጠቀም የምንከተለው መንገድ ነው፡፡ ቀጥተኛ ጥቅስ አጭር ወይም ረጅም ሊሆን ይችላል፡፡ ከአራት መስመር ያነሰ ሲሆን አጭር፣ ከአራት መስመር በላይ ሲሆን ደግሞ ረጅም ቀጥተኛ ጥቅስ ይባላል፡፡ አጭር የሀሣብ ውሰት በጽሑፋችን ስናካትት፣ ከጽሑፋችን አካል ነጥብን ሳናወጣ በጥቅስ ምልክት ውስጥ እናስቀምጠዋለን፡፡ ነገር ግን፣ የወሰድነው ቀጥተኛ ጥቅስ ረጅም ሲሆን፣ ከጽሑፋችን አካል ለይተን ከግራና ቀኝ ህዳጉ ገባ ገባ አድርገን እናሰፍረዋለን፡፡ የጥቅስ ምልክትም አንጠቀምም፡፡ በሁለቱም የቀጥተኛ ጥቅስ አሰፋፈር ከጥቅሱ መነሻ ወይም መድረሻ ላይ ጥቅሱን የወሰድንበትን ምንጭ በትክክል መጥቀስ ይኖርብናል፡፡

### 2. ግለ ገለጻ

ከመረጃ ምንጮች ያገኘነውን ሐሳብ በራሳችን ቋንቋና የአገላለጽ ለዛ ተጠቅመን የፀሐፊውን ሐሳብ ሳንለቅ ስንወስድ ግለ ገለፃ ይባላል፡፡ በግለ ገለፃ የጥቅስ ምልክት ባንጠቀምም፣ ምንጫችንን በሀሳቡ መነሻ ወይም መድረሻ ላይ በቅንፋዊ ማስታወሻ መጥቀስ ይጠበቅብናል፡፡

### 3. ጭምቃሳብ

ያነበብነውን ወይም ያደመጥነውን የሌላ ሰው ፍሬ ሐሳብ በራሳችን አገላለጽ አሳጥረን የምናቀርብበት መንገድ ነው፡፡ ሐሳቡን በማሳጠር ሂደት በጥንቃቄ ማንበብ፣ ማዕከላዊ ሐሳቡን አጥርቶ መረዳትና በራስ ቋንቋ ጨምቆ መጻፍ ይጠበቅብናል፡፡ በዚህ መንገድ የሚሰፍር ጭምቅ ሐሳብ በጥቅስ ምልክት ውስጥ አይቀመጥም:: ነገር ግን፣ በመነሻው ወይም በመድረሻው ስም፣ የህትመት ዘመንና ገጽ በቅንፋዊ ማስታወሻ መጥቀስ አስፈላጊ ነው፡፡

*(መነሻ ሐሳብ፣ አለም እሸቱ፣ መሠረታዊ የምርምርና የዘገባ አጻጻፍ፣1992፣ 25-27)*

## ክፍል አምስት፡- ስነጽሑፍ

**፩. በምዕራፍ ሦስት፣ ክፍል አምስት፣ ስለ ተምሳሌትና አያዎ ዘይቤዎች የቀረበውን ማስታወሻ ካነበባችሁ በኋላ በተከታዮቹ ግጥሞች ውስጥ ያሉትን ዘይቤዎች ነቅሳችሁ በማውጣት አጭር ማብራሪያ ስጡ፡፡**

***ምሳሌ፣*** ኪነት ለዛው ነጣ
ቅኔ ውበት አጣ
የሰቆቃ ሳቁን
የጠኔ ቁንጣኔን
ሊነግረኝ ሲቃጣ

*(ብርሃኑ ገበየሁ፣ የአማርኛ ስነግጥም፣ 1999፣158)*

***ማብራሪያ፣*** በዚህ ግጥም አያዎ ዘይቤ "የሰቆቃ ሳቁን ፣ የጠኔ ቁንጣኔን" በሚሉ መስመሮች ሰፍሯል፡፡ ሰቆቃና ሳቅ፣ ጠኔና ቁንጣን በቁማቸው ተቃራኒ ፍችን ይሰጣሉ፡፡ ሰቆቃ የደረሰበት ሰው ከፊቱ ሀዘን እንጂ ሳቅ አይጠበቅም፤ ጠኔ የያዘውም በረሃብ እንጂ በቁንጣን አይሰቃይም፡፡ ታዲያ ገጣሚው ማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ምንድን ነው? ስንል፣ የግጥሙ ገፀ ባህሪ፣ ተሰቃይቼ ተሳቅቄ እየኖርኩ እንደተደሰትኩ፤ ተርቤ በጠኔ የተሰቃየሁ ያለልክ እንደጠገብኩ መስዬ የምኖረውን ችግርተኛ ቅኔ (ግጥም) ይህንን "መጥገቤን" ለኔው ሊነግረኝ ይፈልጋል፤ በማለት "ለዛ አትጣ" ይለዋል፡፡

1. ዓለምን መውቀሱ፣
   ይቅርብን ተነቅፏል፣
   ሰው ሲስቅ ማልቀሱ፣
   መሆኑ ተጽፏል፡፡

2. ዓለም ሌላ ሆና
   ፍጥረቱ አታላይ
   በክፋት ጎዳና
   ተስማሙበት ወይ?

*(ከበደ ሚካኤል፣ የቅኔውበት፣ 1999፣82-83)*

3. **ጥሬ ጨው**

*መስለውኝ ነበረ፣*
*የበቁ የነቁ*
*ያወቁ የረቀቁ*
*የሰው ፍጡሮች፣*
*ለካ እነሱ ናቸው፣*
*ጥሬ ጨው…ጥሬ ጨው*
*ጥሬ ጨዋዎች፣*
*መፈጨት-መሰለቅ-መደለዝ-መወቀጥ-*
*መታሸት - መቀየጥ*
*ገና እሚቀራቸው፤*
*'እኔ የለሁበትም!'*
*ዘወትር ቋንቋቸው፡፡*

*በገለልተኛ ጨ'ዎች ምሁራን ላይ የተገጠመ*

*(ደበበ ሰይፉ፣ የብርሃን ፍቅር፣ 1980፣ 72)*

**፪. በቡድን ሆናችሁ በሚከተሉት የመወያያ ጥያቄዎች ላይ ሐሳብ ተስዋወጡ፤ የደረሳችሁበትንም በመሪያችሁ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡**

1. ቅኔ ምንድን ነው?
2. ቅኔን እንዴት እንፈታለን?
3. በቅኔ ውስጥ ህብረ-ቃል፣ ሰምና ወርቅ የሚሉት ቃላት የያዟቸው ጽንሰ ሐሳቦች ምንድን ናቸው?

**፫. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቅኔዎች ኅብረቃላቱን ካወጣችሁ በኋላ የሰሙንና የወርቁን ፍች ጻፉ፡፡**

**ምሳሌ፣** በሞቃት አገር የሚኖር
ብርዱን ዝናቡን አይደፍር
ጥሩ ምክንያት ሆነልህ
ክረምቱስ እያልክ ቀረህ፡፡

*(ስምኃ ስለበ፣ ህብረስምዳብ፣1982፡ 11)*

**ህብረ ቃል** = ክረም<u>ቱስ</u> እያልክ

**ሰም** = በሞቃት አየር በመኖርህና እዚህ ክረምት በመሆኑ
ብርዱንና ዝናቡን አመካኝተህ እዚያው አለህበት ቀረህ፡፡

**ወርቅ** = አንተ እዚያው ወሬ እያቀበልህ ቀረህ፡፡

ሀ. ወየው ዳኛ አግኝቶ ዡማን የከሰሰው
ደሞሳ መድረቁ እንዳልወሰደ ሰው፡፡

ለ. አደባባይ ቆሞ አበጀሁ ቢላችሁ፤
ይህን ባለ ጊዜ ምን ትሉታላችሁ፡፡

ሐ. ሁሉም መሳቂያ ነው ጊዜውን ሲስት፣
ብትር ቀን አያምርም ለሚመለከት፡፡

መ. አወይ ባለጌነት እግዜርን ማማረር፣
ሌላ ሰው ይመስል እናት አለማፈር

ሠ. ሙያችሁን ሁሉ መርምረን አውቀናል፣
ቢሆን ጠላችሁን በጣም አድንቀናል፡፡

# የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ፣ አንድ ጽሑፍ የቋንቋ ለዛ እንዲኖረው የሚያደርጉ ጉዳዮችን ተመልክተናል፡፡ በዚሁ መሠረት፣ የቋንቋ ለዛ በማስገኘት በኩል ልዩ ልዩ የቃላት ግጥሚያዎች እንዴት የሰመረና የደመቀ አገላለጽን እውን እንደሚያደርጉ ዘይቤዎችን ፈሊጣዊና ምሳሌያዊ ንግግሮችን ሰም ለበስ አገላለጾችን በማንሳት ተወያይተናል፡፡ ለቋንቋ ለዛን የሚሰጡ ሀረጋትን አባባሎችንና ዓረፍተነገሮችን ከጽሑፍና ከንግግር ውስጥ እየመዘዝን ለዛን እንዴት እንዳስገኙ አብራርተናል፡፡ በተጨማሪም ዘይቤዎችን መተርጎምና በጽሑፋችን ውስጥ መጠቀም ችለናል፡፡

በሌላ በኩል፣ አንድ የተነገረ ወይም የተጻፈ ሀሣብ፣ ሁለትና ከሁለት በላይ ትርጉም ኖሮት ተጣምሮ አንድ ሀሣብ ለመግለጽ የዋለ እንደሆነ፣ ቅኔ እንደሚሰኝ ተረድተናል፡፡ ስለ ቅኔ አፈታት ዘዴ ባየንበት ክፍልም፣ የቀረቡልንን ቅኔዎች በሰምና ወርቅ በመለየት ፍቻቸውን እንዴት ማብራራት እንደሚቻል አይተን ሰምና ወርቅ ፍች ሰጥተናል፡፡ በተጨማሪም፣ ከጽሑፍና ከንግግር ውስጥ አስፈላጊና የማያስፈልጉ ሐሳቦችን ለይቶ የማያስፈልጉትን ማስወገድ የሚቻልበትን ስልት አውቀናል፡፡ የማስታወሻ አወሳሰድ ስልቶችን በሚመለከትም (ቀጥተኛ-ጥቅስ ግለ-ገለጻና ጭምቃሳብ) ተጠቅመን ከጽሑፍና ከንግግር መረጃዎችን በመውሰድ ለክፍል ጓደኞቻችን በጽሑፍ አቅርበናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

፩. ከሚከተሉት ርዕሶች አንዱን መርጣችሁ በሁለት መቶ ሃምሳ ቃላት ድርሰት ጻፉ:: ለሐሳባችሁ ማጉያ በተለይ ተምሳሌታዊና አያዎ ዘይቤዎችን ተጠቀሙ::

1. ዕውቀት
2. የበዓል ዋዜማ
3. ሰኔና ገበሬ

፪. መጻሕፍትን በማንበብና ሰዎችን በመጠየቅ አምስት አምስት ቅኔዎችን ከሰበሰባችሁ በኋላ:-

ሀ. ህብረ ቃላቸውን ለዩ::

ለ. ሰምና ወርቅ ፍቻቸውን ተንትኑ::

፫. ከመጻሕፍት፣ ከጋዜጦች፣ ከመጽሔቶች... በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተጻፈ ስዛ ያለው አንድ ጽሑፍ አንብቡና ፍሬ ነገሮችን ማስታወሻ ያዙ፤ ከጽሑፉ ውስጥ አስፈላጊና አላስፈላጊ የሆኑ ሐሳቦችን በመለየት በሚከተለው ሰንበረዥ አቅርቡ::

| ያነበባችሁት ጽሑፍ ርዕስ | የጽሑፉ አስፈላጊ ሐሳቦች | የጽሑፉ አላስፈላጊ ሐሳቦች |
|---|---|---|
| | | |

፬. ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 3 ያነበባችሁት ጽሑፍ ስዛ ባላቸው አገላለጾች መጠቀሙን በምሳሌ አስደግፋችሁ አብራሩ::

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ቀጥሎ በዚህ ምዕራፍ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል:: በዚሁ መሠረት፣ በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትደዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ (√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ::

| ተ. ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የቀረበውን ጽሑፍ አንብቤ ተረድቻለሁ:: | | | |
| 2 | አንድ ጽሑፍ "የቋንቋ ለዛ አለው" የሚያሰኙትን ነጥቦች ገልጫለሁ:: | | | |
| 3 | እምሬያዊና ፍካሬያዊ ቃላትን በተስማሚ ፍቻቸው ማዛመድ ችያለሁ:: | | | |
| 4 | የድምፅ መጥበቅና መላላት፣ መርዘምና ማጠር ባህሪይ ያላቸውን ቃላት፣ በትክክል ለይቼ ፍቺ ሰጥቻለሁ፤ ፍቻቸውን የሚያመለክት አረፍተ ነገር መስርቻለሁ:: | | | |
| 5 | ለቃላት መዝገበቃላዊ ፍቾ ሰጥቼ በዋናው ቃል አረፍተነገር መስርቻለሁ:: | | | |
| 6 | ካዳመጠጥኩት የሕዝባዊ ስብሰብ ንግግር ውስጥ፣ ለንግግሩ ለዛ የሰጡትን ቃላት፣ ሐረጋት፣ አባባሎችንና አረፍተነገሮችን ለይቼ ገልጫለሁ:: | | | |
| 7 | ካዳመጥኩት ወይም ካነበብኩት ውስጥ "አስፈላጊና የማያስፈልጉ ሃሣቦችን ይዘዋል" የምላቸውን አረፍተ ነገሮች ለይቼ ጽፌያለሁ:: | | | |
| 8 | በቋንቋ ለዛ ዙሪያ ከተለያዩ ምንጮች የሰበሰብኩትን ሃሣብ በክፍል ውስጥ አንብቤያለሁ:: | | | |
| 9 | ከተሰጠኝ ጽሑፍ ውስጥ፣ ዘይቤዎችን በተለይም ተምሳሌትና አያዎን ለይቼ፣ በማውጣት ተገልግየበታለሁ:: | | | |
| 10 | የተለያዩ መልጃዎችን፣ መመሪያ ተከትዬ ሰርቻለሁ:: | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ::

# ምዕራፍ ስድስት

## ግጥም

**የምዕራፉ ዓላማዎች:- ተማሪዎች! ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ:-**

- ✓ የግጥምን ቅርጽና ባህርያት በመለየት ከሌሎች የስነጽሑፍ ዘሮች ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት ትገልጻላችሁ።
- ✓ ቃላትን በድምጸ ልሳናት ትተነትናላችሁ።
- ✓ ለቃላት አውዳዊ፣ እማሬያዊ፣ ፍካሬያዊ፣ ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍችን ትሰጣላችሁ።
- ✓ በቃላት ውስጥ ድምጾች በመርዘምና በማጠር (በመጥበቅና በመላላት) የትርጉም ልዩነት ማስከተላቸውን ታስረዳላችሁ።
- ✓ ከተለያዩ መድረኮችና ጽሑፎች የሚተላለፉ መልዕክቶችን አዳምጣችሁ ትናገራላችሁ።
- ✓ ከመጻሕፍት፣ ከመጽሔቶችና ከጋዜጦች ሐሳብ ወስዳችሁ ትጽፋላችሁ።
- ✓ ከሚሰጣችሁ ግጥም ውስጥ ዘይቤዎችን በዓይነታቸው ትለያላችሁ፣
- ✓ ዘይቤዎች ለግጥም መልእክት መጉላት ያላቸውን ፋይዳ ትተነትናላችሁ።
- ✓ ግጥም ታነባላችሁ።
- ✓ ግጥም ትጽፋላችሁ።
- ✓ መመሪያን ተከትላችሁ ግጥምን ወደ ዝርው (ስድ ንባብ) ትለውጣላችሁ።

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

፩. ስነጽሑፍ የሚለው ስያሜ የሚያጠቃልላቸው የጥበብ ሥራዎች ምን ምን ተብለው ይጠራሉ?
፪. የቃል ግጥምና የተጻፈ ግጥም ሲባል ምን ማለት ነው?
፫. ቀጥሎ "የግጥም ምንነትና ዓበይት ባህርያት" በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ጽሑፍ ታነባላችሁ፡፡ ከርዕሱ በመነሳት ምንባቡ ምን ምን ጉዳዮችን ያነሳል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

# የግጥም ምንነትና ዓበይት ባህርያት

ግጥም ዘመናትን ያስቆጠረ ኪነጥበብ እንደመሆኑ፣ የሰው ልጅ ጽሑፍን ከመፍጠሩ በፊት በቃሉ ስንኝ እየደረደረ፣ ከዜማ እያዋሀደ ሐሳቡን ሲገልፅ ኖሯል፡፡ ይህን ቃላዊ ግጥም በመባል የሚታወቀውን ክፍል በሌላ ምዕራፍ የምናነሳው ሲሆን፣ በዚህ ምዕራፍ ግን፣ ትኩረታችን በተጻፈውና ደራሲው በውል በሚታወቀው ግጥም ምንነትና ባህሪ ላይ ይሆናል፡፡ በዚህ ሐሳብ ከተስማማን የግጥም ምንነትን አንስተን ከመወያየታችን በፊት ከገጣሚ ሰይፉ መታፈሪያ ሥራዎች "ገጣሚ ሲነሸጥ" የተሰኘውን ግጥም እንመልከት፡-

ግጥም ከንፈር ነው ግጥም
ሕይወትን የሚስም፡፡
• •
ገጣሚ ከንፈሩ
ካበባ እስከ ድንጋይ - አፈሩ
ሁሉም የሴት ገላ ነው
ለሱ
ቢሻክርም መለሳለሱ፡፡
• •
ገጣሚ ተነሸጠ
ድንገቱን

እና ለተገኘለት
ከተገኘበት
በተገኘለት
ጠቆም ጠቆም በሹለት
ዝርገት፡፡
• •
ዐይነ ልቦናን መጻፍ
እብደትን መክነፍ
መለፍለፍ
እና መዋደድ
ካፈር ቅጠሉ
ከእውነታ ጋር መናገድ
ዐይነልቦናውን
በግጥም ሕያው መሆን፡፡

*(ስይፉ መታፈሪያ፣ የተጉዋጉዘ ልብ፣1987፣ 225)*

ገጣሚው ግጥምን እንደሕይወት መሳሚያ ከንፈር ወስዶታል፡፡ በሕይወት ጉዞ ደስታና ሀዘኑ ፣ ምኞትና ተስፋው ፣ ስኬትና ውድቀቱ ፣ የኑሮ ውጣ ውረዱ አለ፡፡ እነዚህ ሁሉ የሕይወት ገጽታዎች በገጣሚ ከንፈር ይዳሰሳሉ፤ እጅግ ውብ ከሆነው ባለህብረቀለም አበባ እስከሚሻክረው ድንጋይና አፈር ድረስ፡፡ ለምን ቢሉ ሕይወት ጉራማይሌዋ የገጣሚን ስሜት ፈንቅላ፣ ፍቅሩን ቀስቅሳ እሷን ዳስሶ እንዲወጣለት የማስገደድ ኃይል ስላላት ነው፡፡ እናም ገጣሚው በብዕሩ ሲያቀልም የሕይወትን ዓይነተኛ ምስል ሲስል ይኖራል፡፡ ይህንኑ እውነት ከላይ የጠቀስነው ገጣሚ በስንኝ ቋጠሮ እንዲህ ይገልጸዋል፡፡

መጻፍ መጻፍ አለኝ ማቅለም ወረቀት፣
ብዕሬን ማስቆጣት ቀይ ደም ማስተፋት፡፡

ግጥም የጠንካራ ስሜት ነፀብራቅ እንደመሆኑ ገጣሚው በጥልቅ መርፌ ዐይኑ የሕይወትን ውስጣ ውስጥ በርብሮ አንድ እውነታ ላይ ይደርሳል፡፡ ያኔም ጠንካራ ስሜት ገጣሚውን ሊፈነቅለው ይታገለዋል፡፡ ከዚህ በኋላ፣ በገጣሚው አንደበት እንደተመሠከረው፣ ከእውነታ ጋር ይናገዳል፤ መጻፍ መጻፍ ይለዋል፤ ይጽፋል፤ ብዕሩን ደም ያስተፋል፤ ወረቀቱን ያቀልማል፤ ለመተንፈስ፡፡

> ተማሪዎች! እስቲ እዚህ ላይ ንባባችሁን ገታ አድርጉና እስካሁን ካነበባችሁት መንደርደሪያ ሐሳብ በመነሳት ግጥም ምንድን ነው ትላላችሁ? መልሱን ለአንድ ደቂቃ አሰላስሉና ብያኔያችሁን ባጭሩ በማስታወሻችሁ ላይ አስፍሩ፤ ንባባችሁን ቀጥሉ!

የግጥምን ምንነት በቀጥታ ባጭር ብያኔ መግለጽ ቢያዳግትም ከላይ ካየነው የፈንቃይነት ባህሪው በመነሳት ሲታይ፣ ግጥም ከሌላው የጽሑፍ ቅርጽ ብልጫ ያለው የገጣሚ ጥልቅ ስሜት ገንፍሎ ሲወጣ የሚከሰት የታላላቅ ስሜቶች ነውጥ መግለጫ መንገድ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የስነጽሑፍ መምህርና ሀያሲ ዘሪሁን አስፋው ግጥምን ሲገልጽ፣ “ስነግጥም አንድ ነገር ወይም ድርጊት አድምቆና አጉልቶ የማሳየት፣ ሐሳብን አክርሮና አግዝፎ የማቅረብ ችሎታ ያለው፣ በጥቂት ምርጥ ቃላት ብዙ ነገሮችን አምቆ የሚይዝና በሙዚቃዊ ቃናው የስሜት ሕዋሳትን በቶሎ የሚነካ ለስሜት ቅርብነት ያለው ኪነጥበብ ነው” በማለት ምንነቱን ከተግባሩና ከባህሪው አኳያ በማየት ያስረዳል፡፡

ግጥም አንድ ራሱን የቻለ ስነጽሑፋዊ ቅርጽ ነው፡፡ ስለዚህም ከሌላው ተነጥሎ የሚታወቅባቸው የራሱ መለያ ባህርያት አሉት፡፡ የስነጽሑፍ መምህርና ሀያሲ ብርሃኑ ገበየሁ እነዚህ ባህርያቱ ተጨባጭነት፣ እምቅነትና ቁጥብነት፣ ምናባዊነትና ሙዚቃዊነት እንደሆኑ ይገልፃል፡፡ የመጀመሪያውን የተጨባጭነት ባህሪ እንመልከት፡፡ ተጨባጭነት ሲባል፣ ከውስብስብነታቸው አንፃር በዘወትሩ ጽሑፋዊ ቅርጽ (ዝርው) ለመግለፅ የሚያዳግቱ ስሜቶችንና ገጠመኞችን በግጥም መተንፈስና አድማጭና

አንባቢ ልብ እንዲላቸው ማድረግ መቻሉን የሚመለከት ነው፡፡ ይህንኑ በተከታዩ ምሣሌ ማየት ይቻላል፡፡

## የሂደት ዓይነት

ጉዞ ነው መቀመጥ፤ መቀመጥ ጉዞ ነው
ጊዜ ባቡር እኛ ተሳፋሪዎቹ እየሆነው፡፡
• •
ቅድም ለአሁን
አሁን ለሁዋላ ተቀምጠን
ያለፈም አልመሰለን
ጊዜ
አሳምሮ ሲያታልለን፡፡
• •
ጊዜ ግን አልፉዋል
እድሜም ጨምሩዋል
በደቂቃ
የጊዜ ቋቶች ጶቃ
ሥጋ - ኣልም ተለውጡዋል
• •
ጉዞ ነው ጉዞ፤ መቀመጥ ጉዞ ነውና
ጊዜ ባቡር እኛም ተሳፋሪዎቹ ሆንና፡፡

*ሰይፉ መታፈሪያ፣ ውስጠት፣ 1981፣ 56)*

የዚህ ግጥም ነገረ ጉዳይ ጊዜ ነው፤ ቆሞ የማይጠብቅ ተጓዥ መሆኑ፡፡ ገጣሚው ይህንን እውነት "እነሆ!" ሊለን ሲፈልግ ደግሞ "ጉዞ ነው መቀመጥ፤ መቀመጥ ጉዞ ነው" ይለናል፡፡ ብዙዎቻችን ስንቀመጥ ከጊዜ ጋር መጓዛችንን አናስተውልም፡፡ ነገር ግን፣ የጊዜ ባቡር ይዞን ይነጉዳል፡፡ እድሜያችንም እንደዛው ይጨምራል፡፡ አንዲት ደቂቃ ባሳለፍን ቁጥር በአንድ ደቂቃም ቢሆን እያረጀን ነው፡፡ ይህንኑ ገጣሚው "በደቂቃ/ የጊዜ

ቋቶች ዶቃ/ ስጋ - “ካልም ተለውጧል።” በማለት ይገልጸዋል። በዚህ ዓይነት ጊዜ ተጓዥ ሳይመስል እየተጓዘ እንዳያታልለን ረቂቁን ሐሳብ ተጨባጭ አድርጎ አሳይቶናል። ይኸው ሐሳብ በዝርው ቢገለጽ ኖሮ “ጊዜ ሳናውቀው የሚያልፍ አታላይ ነውና ላለመታለል ንቁ” በሚል ሊገለጽ ይችላል። ታዲያ “ከሁለቱ አገላለጾች የትኛው ለስሜታችን ቅርብና ተጨባጭ ነው? የትኛው ደግሞ ጆሮአችንን ጠልዞ ይመለሳል?” የሚለውን መለየቱ ለናንተ የሚተው ይሆናል።

ሁለተኛው የግጥም ባህሪ ምናባዊነቱ ነው። ገጣሚ ጉዳዬ ያለውን ነገር ተመልክቶ በጥልቅ ስሜትና በኃያል ሐሳብ ቀልቡ ይያዛል። ይህንን በልቡ የሚጉላላውን ሐሳብ ሊናገረው (ሊያወጣው) ይፈልጋል። በዚህ ጊዜ ለምናባዊ ፈጠራ ሁሉንም የስሜት ሕዋሳቱን በማንቀሳቀስ፣ የጉዳዩን የተለያዩ ገጽታዎች ያያይዛል፤ ያደራጃል። በስሜት ሕዋሳቱ ማለትም በዐይነ ሕሊናው ያየውን፣ በዕዝነ ልቦናው የሰማውን፣ ያሸተተውንና የቀመሰውን በዕደ ሕሊናው የዳሰሰውን ሁሉ በቃላት አማካይነት በሚፈጥረው ኃይል በአንደበቱ ያወጣዋል፤ በወረቀት ያቀልመዋል። ገጣሚ ይህንን የሚያደርገው በራሱ ውስጥ የገዘፈውን ማዕበል ለማስታገስ እንጂ፣ በውስጠ ሕሊናው የረቀቀውን ለአድማጭ አንባቢ “እነሆ!” ለማለት አይመስልም። ይህ እንግዲህ በግጥም የሚታየው ምናባዊነት በሌሎች የስነጽሑፍ ዘርፎች ከሚታየው የበለጠ ጥልቀት ያለው እንደሆነ ያሳያል።

ሦስተኛው የግጥም ባሕሪ ቁጥብነቱና እምቅነቱ ነው። እነዚህ ሁለቱ ጽንሰ ሐሳቦች ተደጋጋፊ ናቸው፤ ቁጥብነቱ ወይም ብዙ አለማተቱ የሚመነጨው ከእምቅነቱ ነው። ልክ እንደ ፈንጂ ተበትነው በርካታ ሐሳቦችን መፈንጠቅ በሚችሉ እምቅ ቃላትና ሐረጋት ይጠቀማል። የአንድን ነገር ሁለንተናዊ መልክ ለመግለጽ ሲፈልግ፣ ከውስጡ አንድ ነገር መዝዞ እሱን በታመቁ ቃላት ይገልፃል። እምቅ ቃላቱ ደረጃ በደረጃ እየፈነዱ የነገሩን አጠቃላይ ገጽታ ቁልጭ አድርገው ያሳያሉ። ከዚህ ባሕሪው የተነሳ አንድ ባለ ጥቂት መስመር ግጥም በዝርው ቢገለፅ፣ ብዙ ገጾች ተጽፈውለት እንኳ ሙሉ ለሙሉ ላይገለጽ ይችላል። ይህንኑ በተከታዩ ግጥም እንመልከት።

## ኀሠሣ ሥጋ

እልፍ ከሲታዎች ቀጥነው የሞገጉ

“ስጋችን የት ሄደ? ብለው ሲፈልጉ

በየሸንተረሩ፣ በየጥጋጥጉ

አሥሠው አሥሠው በምድር ሰማይ

አገኙት ቦርጭ ኾኖ ባ'ንድ ሰው ገላ ላይ፡፡

*(በእውቀት ስዩም፣ ስብስብ ግጥሞች፣ 2001፣ 17)*

ይህ ባለ አምስት መስመር ግጥም መልእክቱ የትየለሌ ነው፡፡ በዚች ርህራሄና ጭካኔ ፣ ፍቅርና ጥላቻ ፣ ክፋትና ደግነት ፣ ስጦታና ዘረፋ በነገሱባት ዓለማችን በአካለ መጠናቸው በርካታ ወፍራምና ቀጭን ሰዎች ይመላለሳሉ፡፡ ገጣሚው ይህንን ዘወትር የምናየውን አጠገባችን ያለ እውነት በመምዘዝ ያስተላለፈው መልዕክት በዝርው ቢገለጽ ምናልባትም በመቶዎች የሚቆጠሩ ገጾች ይፈጅ ይሆናል፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፤ ጥቂት ሐብታሞች በሚኖሩባት ዓለማችን እልፍ ድሆች ይኖራሉ፡፡ ሐብታሞቹ ለድሆቹ የሚሰጡት፣ በምትኩ ከድሆቹ የሚወስዱት ይኖራቸዋል፤ አላቸውም፡፡ ጉዳዩ ያለው እንግዲህ ጥቂት ሰጥቶ ብዙ በመውሰድ እመወፈሩ ላይና ብዙ ሰጥቶ ጥቂት ተቀብሎ እመክሳቱ ላይ ነው፡፡ አንዱ በሌላው መድለብ ይኗል ይኸ ነው፡፡ ጉዳዩ ሐብት ባለውና በሌለው፣ በባለስልጣንና በምንዝር፣ በኃያላን ሀገራትና በማደግ ላይ ባሉ ሐገራት መካከል ወዳለው የተዛባ የመስጠት፣ መቀበል ስርዓት ተወስዶ እየተመረመረ ቢተረጎምና በዝርው ቢተነተን እጅግ ብዙ ገጾች ሊፈጅ ይችላል፡፡ ስነግጥም ቁጥብና እምቅ ነው የሚባለውም ከዚህ እውነታ የተነሳ ነው፡፡

አራተኛውና በመጨረሻ የምናነሳው የግጥም ባሕሪ፣ ሙዚቃዊነት ነው፡፡ ግጥም ሙዚቃዊነቱን የሚቀዳጅበት የራሱ ስልት አለው፡፡ ምክንያቱም

በተወሰነ የጊዜ ቆይታ የሚደጋገም ድምጽን ያወጣል፡፡ በግጥም ውስጥ ያለው ስልት ጎልቶ የሚሰማን ግጥሙን ስናነብ ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ በላይ ለአስረጅነት ያቀረብናቸውን ግጥሞች ስልታቸውን ጠብቀን በዜማ ስናነብ ከግጥሙ ቃላት፣ ሐረጋትና ስንኞች ምጣኔ የሚፈልቀውን ሙዚቃዊ ቃና ልብ ልንለው እንችላለን፡፡

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ፡- አንብቦ መረዳት

**፩. ቀጥሎ ምንባቡን መሠረት አድርገው ለቀረቡ ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. “ገጣሚ ጠንካራ ስሜት ሲፈነቅለው ከእውነታ ጋር ይናገዳል” የሚለውን ሐሳብ አብራሩ፡፡
2. “ግጥም የታላላቅ ስሜቶች ነውጥ መግለጫ ነው” ሲል ምን ማለቱ ይመስላችኋል?
3. “ግጥም በተመረጡ ቃላት ይጠቀማል” ሲባል፣ በዝርው ጊዜ የቃላት ምርጫ የግጥምን ያህል ትኩረት አይቸረውም ለማለት ነው? ለምን?
4. የግጥምን የተጨባጭነት ባህሪን አብራሩ፡፡
5. “ገጣሚ የሚጽፈው በውስጡ የገዘፈውን ነውጥ ለማስታገስ እንጂ፣ በውስጠ ሕሊናው የረቀቀውን ለአድማጭ አንባቢ ጆባ ለማለት አይደለም” የሚለውን ሐሳብ በመደገፍ ወይም በመቃወም አስተያየታችሁን ስጡ፡፡
6. በግጥምና በዝርው ጽሑፍ መሀል ያለውን አንድነት ዘርዝራችሁ ተናገሩ፡፡

፪. በጥንድ ሆናችሁ በግጥምና በዝርው የጽሑፍ ቅርጾች መካከል ባሉ ልዩነቶች ላይ ተወያዩ፤ በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት ቢያንስ አምስት የልዩነት ነጥቦችን ዘርዝሩ።

| ዝርው | ግጥም |
|---|---|
| – ቃላት አድገው ሀረግን ብሎም የተሟላ ፍች ያለው ዓረፍተነገርን ያዋቅራሉ። | – ቃላትና ሀረጋት አድገው ስንኝ ያዋቅራሉ። |
| – ከሞላ ጎደል ስቋንቋ ሰዋስው ይገዛል። | – ስቋንቋ ሰዋስው አይገዛም። |
| – | – |
| – | – |
| – | – |
| – | – |
| – | – |

፫. ቀጥሎ የቀረቡላችሁ ቃላት በምንባቡ ከሰፈረው "ገጣሚ ሲነሽጥ" ከተሰኘው ግጥም የተወሰዱ ናቸው፤ ግጥሙን በማንበብና አገባባቸውን በመለየት ያላቸውን አውዳዊ ፍች ስጡ።

ምሣሌ ፤ ጠቆም ጠቆም = ጻፍ ጻፍ ፤ ሞንጨር ሞንጨር

| | |
|---|---|
| 1. ተነሽጠ | 6. በሹለት |
| 2. የሚስም | 7. መክነፍ |
| 3. የሴት ገላ | 8. ካፊር- ቅጠል |
| 4. ከተገኘበት | 9. ሕያው |
| 5. ዐይነ ልቦና | |

## የቃላት ፍች

ቃላት በቁማቸው የተለያየ ፍች ሊኖራቸው ይችላል፡፡ የቃላት ትክክለኛ ፍች የሚታወቀው በዓረፍተነገር ወይም በስንኝ ውስጥ ገብተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡

ቃላት በአውድ ገብተው ሲገኙ በገቡበት ቦታ ላይ የሚኖራቸው ፍችም የተወሰነና አንድ ይሆናል፡፡

ለቃላት አውዳዊ (አገባባዊ) ፍች ስትሰጡ ወይም ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ስትፈልጉ የይዘት መመሳሰልን ወይም መቃረንን ብቻ ሳይሆን የቃላቱ ቅርጾች አቻ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባችኋል፡፡ ለምሣሌ፣ "አርበኝነት፣ ምግባረ ሰናይ" ለሚሉ ቃላት ተቃራኒ እንድትሰጡ ብትጠየቁ በቅደም ተከተል፣ "ባንዳነት፣ ምግባረ ብልሹ" በማለት የተሰጧችሁ ቃላትና የሰጣችሁት መልስ በቅርጽ አቻ መሆናቸውን ማየት ይኖርባችኋል፡፡

**፬. በምንባቡ ውስጥ ለማሳየት የቀረበውን "ኅሠሣ ሥጋ" የተሰኘውን የገጣሚ በእውቀቱ ስዩም ግጥም በድጋሚ በማንበብ፣**

1. እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች የያዙ ቃላትን ለይታችሁ ዘርዝሩ፡፡
2. ቃላቱን ተጠቅማችሁ ዓረፍተነገር በመሥራት እማሬያዊ ፍቻቸውን አሳዩ፡፡

## ክፍል ሁለት፡- ማዳመጥ

**፩. ኪነጥበብን አስመልክቶ በአካባቢያችሁ ሲካሔዱ በታቀዱት የተለያዩ መድረኮች (ዐውደ ርዕይ፣ የስነጽሑፍ ምሽት የስነጽሑፍ ሥራዎች ምረቃ፣ በኪነጥበብ ላይ ያተኮሩ ስብሰባዎች) ላይ ተገኝታችሁ፣**

ሀ. በመድረኩ የሚነሱ ዝርዝር ነጥቦችን እያዳመጣችሁ አጫጭር ማስታወሻ ያዙ፡፡

ለ. ስለተከታተላችሁት ፕሮግራም ጭብጥ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ተናገሩ፡፡

**፪. በአካባቢያችሁ ኪነጥበብን የተመለከቱ መድረኮችን ማግኘት ያልቻላችሁ ተማሪዎች ካላችሁ፣ በሬዲዮ የሚተላለፈውን የሳምንቱን የኪነጥበባት ማህደር ወይም መሰል ፕሮግራም ተከታተሉ፡-**

ሀ. በዕለቱ ፕሮግራም የተነሱ ኪነጥበባዊ ጉዳዮችን እያደመጣችሁ በዝርዝር በማስታወሻ ያዙ፡፡

ለ. የፕሮግራሙን ጭብጥ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ተናገሩ፡፡

## ክፍል ሦስት:- መናገር

በቡድን ሆናችሁ በመወያየት ግጥም ከሌሎች የስነጽሑፍ ዘርፎች (አጭርና ረጅም ልቦለድ፣ ወግ፣ ድራማ) የሚመሳሰልባቸውንና የሚለያይባቸውን ባህሪያት ዘርዝሩ፤ በቡድን መሪያችሁ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

## ክፍል አራት:- መጻፍ

**፩. መጻሕፍትን፣ መጽሔቶችንና ጋዜጦችን በማገላበጥ ግጥምን የተመለከቱ ጽሑፎችን አንብባችሁ፣**

ሀ. የጽሑፉ አቅራቢ ማን እንደሆነ፣

ለ. የጽሑፉ ርዕሰ ጉዳይ ምን እንደሆነ፣

ሐ. ጽሑፉ ስለግጥም ያነሳው ዋና ጭብጥ ምን እንደሆነ፣

መ. ጽሑፉን ስታነቡ የቀሰማችሁትን ቁም ነገር፣

ሠ. "ጽሑፉ በተገቢው መንገድ አልቀረበም" የምትሉም ከሆነ ትችታችሁን ከሁለት ገጽ ባልበለጠ ጽሑፍ አቅርቡ፡፡

**፪. ከዚህ በታች የግጥም ርዕስና ለመክፈቻ የሚሆኑ አንድ አንድ የቤት መምቻ ስንኞች ቀርበዋል፡፡ ከርዕሱ ሐሳብ ተነስታችሁ የቤት መድፊያ ስንኞቹን በመጻፍ አሟሉት፡፡**

1. **ርዕስ፣ <u>ትምህርት ቤት</u>**

   የስልጣኔ በር፤ ገበያ የዕውቀት፣

   ____________________________፡፡

2. **ርዕስ፣** ***<u>አውዳመት</u>***

ባመት አንድ ቀን የሚመጣው፣

________________________________::

3. **ርዕስ፣** ***<u>ዕውቀት</u>***

የማይሰረቅ ነው፣ ብል የማይበላው፣

____________________________________::

**፫. ከዚህ በታች ከተሰጣችሁ ርዕሶች አንዱን በመምረጥ ወይም በዕለት ተዕለት ሕይወታችሁ ስሜታችሁን በነካ አንድ ርዕሰ ጉዳይ ሳይ ግጥም ጽፋችሁ ለተከታዩ ክፍለ ጊዜ አቅርቡ::**

1. አፍቃሪ ልብ
2. ዕውቀትን ፍለጋ
3. ቤተሰብ

**፬. በጥንድ ሆናችሁ አንዳችሁ የጻፋችሁትን ግጥም ሳንዳችሁ በንባብ ካሰማችሁ በኋላ ግጥሙን ተለዋወጡ ፤ ከግጥሙ አወቃቀር ከቃላት አጠቃቀምና ከዘይቤ ምርጫ አንጻር በጓደኛችሁ ግጥም ሳይ አስተያየት ስጡ::**

**፭. ቀጥሎ ግጥምን ወደ ዝርው ለመለወጥ የሚያግዛችሁ መመሪያ ቀርቦላችኋል:: መመሪያውን ተከትሎ የቀረበውን "የአጭር መንገድ ዜጎች" የተሰኘ የዶ/ር ፈቃደ አዘዘን ግጥም ወደ ዝርው ለውጣችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ::**

## ግጥምን ወደ ዝርው የመለወጥ መመሪያ

በግጥም የተጻፈን መልዕክት ወደ ዝርው በመለወጥ ዋናውን ሐሳብ ሳታዛቡ ለአንባቢ ማቅረብ ትችላላችሁ፡፡ ከዚህ በታች ግጥምን ወደ ዝርው ስትለውጡ ደረጃ በደረጃ የምትከተሉት መመሪያ ቀርቧል፡፡

1. የያዘውን መልዕክት ሙሉ ለሙሉ እስክትረዱት ድረስ ግጥሙን ደጋግማችሁ አንብቡ፤
2. የግጥሙን ፍሬ ሐሳቦች እየለያችሁ በማስታወሻችሁ መዝግቡ፤
3. በመዘገባችሁት እየተመራችሁ ግጥሙን ወደ ዝርው ለመለወጥ የሚያስችላችሁን አስተዋጽኦ ንደፉ፤
4. አስተዋጽኦዎቹን መርምራችሁ ዋናና ንዑስ ሐሳቦችን ከለያችሁ በኋላ በሐሳብ የሚቀራረቡትን ባንድ ላይ መድቡ፤
5. ለየምድቡ አንድ መንደርደሪያ ዓረፍተነገርና ዝርዝር ዓረፍተነገሮችን አዋቅሩ፤
6. ጽሑፋችሁ የሐሳብ አንድነት እንዲኖረው የአንቀጾቹንና በየአንቀጾቹ የዐረፍተ ነገሮቹን ተያያዥነት ጠብቁ፤ ተያያዥነታቸውን ለመጠበቅ በሁለት መንገዶች መጠቀም ትችላላችሁ፤
   6.1. በሐሳብ እንዲያያዙ በማድረግ፣
   6.2. በአያያዥ ቃላት እንዲያያዙ በማድረግ፣
7. አስፈላጊ ሲሆን የግጥሙን መልዕክት የያዙ ስንኞችን በማስረጃነት ጥቀሱ፤
8. ጽፋችሁ ስትጨርሱ የጻፋችሁትን ረቂቅ ደጋግማችሁ በማንበብ አስተካክሉ፤
9. ግልጽና ቀላል ቋንቋ መጠቀምን አትዘንጉ፡፡

## የአጭር መንገድ ዜጎች

የምን ጥናት?

ታለ የዐይን ጥራት!
አሻግሮ ተኩሶ፣ ማፈስ ካዝመራው
ሌት ሙሉ ካጠናው፣ ቀን ሙሉ ከፈጋው፤

የምን ታክቶ ማፍረት?
ታለ የዕድሜ ትጋት፣
ቱጃር ሽማግሌ፣
ዘንካታ እመቤት፣
አግብቶ መፋፋት፤

የምን ሰርቶ ማደግ ፣ መሸለም መሾም፣
ታለ ስልጣን ጉያ፣ ተሸጉጦ መትመም፣
ተንበርክኮ - ማበጥ፣
መወጠር መከፈስ፤
በገንዘብ መደለብ፣ በመንፈስ መኮሰስ፤

የምን ትግል፣ ለዓላማ ፅናት

ታለ ተታገለው ፣ ተልመጥምጦ ገብቶ፣ ተጉያው መቦጨቅ፣
እያዋዙ መንጠቅ፤
በእየው ድማሙ፣ ዓላማውን መስለብ፣ ጽናቱንም ማድቀቅ፤

የምን ማጥናት?
የምን ማፍረት?

(ፈቃዱ ለዘዘ፣የዘመን ቀለማት፣ 1999፣29)

## ክፍል አምስት:- ስነልሳን

፩. ለሚከተሉት ቃላት በምሳሌው መሠረት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ከሰጣችሁ በኋላ የሰጣችሁትን ፍች ግልጽ የሚያደርጉ ዓረፍተነገሮች ሥሩባቸው::

ምሳሌ፣

| ተ.ቁ | ቃል | ተመሳሳይ | ተቃራኒ |
|---|---|---|---|
| 1 | አልሄደም | ፈቀቅ አላለም | ተራምዷል |

ሀ. ትላንት የጀመርነው ሥራ ፈቀቅ አላለም::
ለ. ትላንት የጀመርነው ሥራ ተራምዷል::

| | |
|---|---|
| 1. ረባ | 6. ተናቆረ |
| 2. ጉብታ | 7. ተቀደሰ |
| 3. አልቦ | 8. ተከራመተ |
| 4. ሞገደኛ | 9. ተንዘረጠጠ |
| 5. ተጣባ | 10. ጉች አለ |

**፪. በአማርኛ ቋንቋ አንድ ቃል የተለያዩ ድምጾችን በማጥበቅና በማላላት የተለያየ ፍች ሲኖረው ይችላል፡፡ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት በቀረቡት ቃላት ውስጥ ያሉት ድምፃች ሲጠብቁና ሲላሉ ቃሉ የሚኖረውን የተለያየ ፍች ዓረፍተነገር በመሥራት አመልክቱ፡፡**

***ምሳሌ፣***

| ቃል | ሲላላ | ሲጠብቅ |
|---|---|---|
| ቢነሳ | ቢክለክል [ብኢንኽስኣ] | ቢቀሰቀስ [ብኢንንኽስስኣ] |

**ሲላላ፡-** አምላክ ገንዘብ ቢነሳ ጤና ካልነሳ ሰርቶ ማግኘት ይቻላል፡፡
**ሲጠብቅ፡-** በአንድ አካባቢ ጦርነት ቢነሳ የችግሩ ገፈት ቀማሽ የዚያ አካባቢ ሕዝብ ነው፡፡

| | |
|---|---|
| 1. መሳል | 7. የሚጠብቅ |
| 2. አይከፋም | 8. የማይሰማቸው |
| 3. አለቻቸው | 9. እስኪረሳ |
| 4. እንዳለ | 10. ይገባሀል |
| 5. አይገፋም | 11. አዛባ |
| 6. አልገባም | 12. አማት |

**፫. የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሠረት በድምጸ ልሳናዊ አጻጻፍ ተንትናችሁ ጻፉ:: ቃላቱ በመጥበቅና በመላላት ተነበው የፍች ልዩነት የሚያመጡ ከሆነ ይህንኑ በሁለት መንገድ በመተንተን አሳዩ::**

***ምሣሌ፣***

1. አያት = [አይኣት] = ሲላላ - የአባት ወይም የእናት ወላጆች
   [አይይኣት] = ሲጠብቅ - ተመለከታታት

| | |
|---|---|
| 1. መጣል ______________ | 6. ቆም ብላ __________ |
| 2. መልስ _____________ | 7. አይበላም __________ |
| 3. ጥያቄ ______________ | 8. በመጨረሻ _________ |
| 4. ተሰማው ____________ | 9. በጉልበቷ___________ |
| 5. ማንሳት ____________ | 10. ተንቆራጠጠ ________ |

## ክፍል ስድስት፣ ስነጽሑፍ

**፩. ከዚህ በታች በተለያዩ ደራሲያን የተሰናኙ ሦስት አጫጭር ግጥሞች ቀርበዋል እያንዳንዳቸውን መርምራችሁ:-**

ሀ. ግጥሞቹ የያዟቸውን የዘይቤ ዓይነቶች ጻፉ::
ለ. ዘይቤዎቹ ለግጥሙ መልዕክት መተላለፍ ያበረከቱትን ሚና በየግጥሞቹ በመለየት በጽሑፍ ማብራሪያ ስጡ::

### ግጥም አንድ

**መማር**

መማር ተማር፣ ቁልፍ ነውና እሱ
ይህ መች ሆነና፣ የጠፋለት መልሱ
ምንና ምን እና፣ እንዴት እንዴትስ
እስከመቼና የት፣ ደረጃ ድረስ
በሚለው ነው እኮ፤ የጠፋለት መልስ
• • •
ባጭሩ ከቀረ ፣ ትምህርት በጅምሩ፣
ሳያውቁ ማወቅ ነው ፣ ዋነኛ ችግሩ፣

እጅግ ልቆ መጥቆ ፣ ተተሄደ ደግሞ፣
እያወቁ ማለቅ ፣ አይቀርም ፈጽሞ፡፡

*(አስፋው ዳምጤ፣ የዘመን ቀለማት፣ 1999፣ 11)*

## ግጥም ሁለት

### ተጠምጠም!

ከትልቁ ዛፍ ላይ ከተንዠረገገው፣
ቦታም ጊዜም ደልቶት አለወግ ካደገው፤
አረግ ሆይ! ተንጠልጠል፣ እሾሁን አትፍራ፣
ቅርንጫፉን ያዘው በቅጠሉም ኩራ፡፡
ነገር ግን ተጠንቀቅ፣ እንዳትዘናጋ፣
እራስህን ችለህ ለመቆም አትትጋ፡፡
በግራሮች ወኔ እቆማለሁ ብለህ እንዳትቀናጣ፣
ይልቅ ተጠማጠም በዛፎች ላይ ውጣ፡፡
መጠምጠም፣ መንጠልጠል፣ መኖር ነው ያንተ ዕጣ፡፡

*(አበረ አዳሙ ፣ የዘመን ቀለማት፣ 1999፣ 89)*

## ግጥም ሦስት

### ፍረጅኝ ምድሪቱ

እንደሰው ተወልዶ - እንደ ሰው የማይኖር
እንደሰው የማይሞት - እንደሰው ሲቀበር፤
አይተሽ ሰምተሽ - ታውቂያለሽ ወይ ምድር?
ፍረጅኝ መስክሪኝ! - ይህን ክፉ በደል፡፡

ለኔልሰን ማንዴላ

*(አበራ ለማ፣ የማለዳ ስንቅ፣1988፣ 28)*

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ምዕራፍ ስድስት የግጥም ምንነትንና መለያ ባህርያትን የተመለከትንበት ነበር፡፡ ለግጥም አንድ ወጥ ብያኔ ለመስጠት የሚያዳግት ቢሆንም ከቅርጹ፣ ከአፈጣጠሩ፣ ከባህሪው፣ ከአገልግሎቱ... በመነሳት የተለያዩ ብያኔዎች ሊሰጠው እንደሚችል ተረድተናል፡፡ ግጥምን በጥቂት ብያኔዎች ከመቀንበብ ይልቅ በማጥናት ምንነቱን መረዳት የተሻለው መንገድ እንደሆነም ተመልክተናል፡፡


ስለ ግጥም ባህሪያት ባነሳንበት ክፍል ግጥም አንድ ራሱን የቻለ የጽሑፍ ቅርጽ መሆኑንና አራት ዋና ዋና መለያ ባህርያት እንዳሉት ተረድተናል፡፡ የግጥም አንዱ ባህሪ ተጨባጭነት እንደሆነና ተጨባጭነቱ የሚገለፀው በዘወትሩ የጽሑፍ ቅርጽ (ዝርው) ለመግለጽ የሚያዳግቱ ውስብስብ ስሜቶችንና ገጠመኞችን በግጥም መተንፈስ በመቻሉ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ ግጥም የተጨባጭነት ብቻ ሳይሆን የምናባዊነት ባህሪው የጎላ ነው፡፡ ገጣሚው ከህይወት ነቅሶ በውስጡ ያገዘፈውን ማዕበል ለማስታገስ ሲል በውስጠ ህሊናው እውነታን ያረቃል፤ ያሸታል፤ ይቀምሳል፤ በአይነ ህሊናው ያያል፤ በእዝነ ልቦናው ያዳምጣል፤ በእደ ህሊናው ይዳስሳል፡፡ ስለዚህም፣ ምናባዊነት በሌሎችም የስነጽሑፍ ዘሮች ያለ ቢሆንም፣ በግጥም ግን አይሎ የሚገኝ ባህሪ መሆኑን አይተናል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱ ባህሪያት በተጨማሪ የግጥም ቁጥብነትና እምቅነት እንዲሁም ሙዚቃዊነት ባህሪ በዝርው ከሚቀርቡ የስነጽሑፍ ሥራዎች የተለየ እንደሚያደርገው ተወያይተናል፡፡ በግጥምና በዝርው መሀል ያለውን አንድነትና ልዩነት በተመለከተም፣ ከአወቃቀር ከቃላት አመራረጥና አሰዳደር፣ ከቋንቋ ሰዋስዋዊ ህግ አጠባበቅ፣ ከቃላት ፈጠራ፣ ወዘተ. አንፃር ተመልክተን የአንድነትና የልዩነት ነጥቦችን ለይተናል፡፡

በሌላም በኩል ስለ ቃላት ፍች ባነሳንባቸው ክፍሎች የቃላት ትክክለኛው ተመሳሳይና ተቃራኒ የሚለየው በገቡበት አውድ እንደሆነ አጢነናል፡፡ ከግጥም ውስጥ አማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ያላቸውን ቃላት እያወጣን አጠቃቀማቸውን በዓረፍተነገር ውስጥ ተመልክተናል፡፡ በልዩ ልዩ መድረኮች እየተገኘን ስለኪነጥበብ በርካታ ቁም ነገሮችን አድምጠናል፡፡ የሬዲዮና ቴሌቪዥን የኪነጥበብ ዝግጅቶችን ተከታትለን ስለ ዝግጅቶቹ ለክፍል ጓደኞቻችን አብራርተናል፡፡ ግጥም ወደ ዝርው የመለወጥ መመሪያን ተረድተን ግጥምን ወደ ዝርው በመለወጥ ተለማምደናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ግጥም ጽፈናል፤ ዘይቤዎችን (አያዎ፣ ተምሣሌት) ከግጥም ውስጥ በማውጣት ለግጥሙ ጭብጥ መጉላት የተጫወቱትን ሚና አብራርተናል፡፡

# የክለሳ ጥያቄዎች

፩. ተከታዩን ስዕላዊ መግለጫ ተመልክታችሁ የሚያስተላልፈውን ሐሳብ ከአንድ ገጽ ባልበለጠ ጽሑፍ ግለጹ::




**መግለጫ**

1. ስነጽሑፍ
2. ግጥም
3. ድራማ
4. ልቦለድ
5. ዝርው
6. ስነ ግጥም

፪. "አደይ አበባ" በሚል ርዕስ "አንድ ግጥም ጻፉ፤ የተመረጡ ቃላትንና ዘይቤዎችን መጠቀም አትዘንጉ::

፫. በክፍል አራት ተራ ቁጥር ስድስት የቀረበውን "የአጭር መንገድ ዜጎች" የተሰኘ ግጥም በድጋሚ አንብባችሁ ግጥሙ የተጻፈበትን የዘይቤ ስልት ለዩ:: በገጣሚው የዘይቤ ምርጫና ዘይቤው ለግጥሙ ዋና መልእክት ባበረከተው አስተዋጽኦ ላይ በጽሑፍ አስተያየት ስጡ::

# የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ቀጥሎ በዚህ ምዕራፍ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት፣ በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ (√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ (X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተራ ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የቀረበልኝን ጽሑፍ አንብቤ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 2 | ግጥም ከሌሎች የሥነ-ጽሑፍ ዘርፎች ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት አወዳድሬ ገልጫለሁ፡፡ | | | |
| 3 | ለቃላት አውዳዊ፣ መዝገበ ቃላዊና ተቃራኒ ፍች ሰጥቻለሁ፡፡ | | | |
| 4 | ከግጥም ውስጥ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ያላቸውን ቃላት አውጥቼ፣ በእማሬያዊ ፍቻቸው ዓረፍተነገር ሰርቻለሁ፡፡ | | | |
| 5 | የድምጾች መጥበቅና መላላት፣ መርዘምና ማጠር የፍች ልዩነት እንደሚያመጣ፣ በዓረፍተነገር አሳይቻለሁ፡፡ | | | |
| 6 | ቃላትን በድምፀ ልሳናዊ አጻጻፍ ጽፌያለሁ፡፡ | | | |
| 7 | የግጥም ባህርያትን ገልጫለሁ፤ ከግጥም ውስጥ ዘይቤዎችን ለይቼ በማውጣት አስረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 8 | ግጥም ጽፌያለሁ፣ መመሪያውን ጠብቄ ግጥምን ወደ ዝርው (ስድ ጽሑፍ) ለውጫለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ (?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

# አርበኝነት

***የምዕራፉ ዓላማዎች፡- ተማሪዎች! ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-***

- ✓ በዓረፍተ ነገር ውስጥ የቃል ክፍሎችን ሙያ ታስረዳላችሁ፡፡
- ✓ በቃል እርባታና በቃል ምስረታ መካከል ያለውን ልዩነት ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ ለቃላት ቀጥተኛ /መዝገበ ቃላዊ/ ፍችን ትሰጣላችሁ፡፡
- ✓ የዱብዳ ንግግር ታደርጋላችሁ፡፡
- ✓ ጽሑፍን አንብባችሁ ወይም አዳምጣችሁ ሐሳቡን በራሳችሁ አባባል ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ የጥልቅ ንባብ የአነባበብ ዘዴን ተከትላችሁ በማንበብ የተረዳችሁትን ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ የመረጃ ምንጭ አጻጻፍ ስርዓትን ዘርዝራችሁ በመጻፍ ታሳያላችሁ፡፡
- ✓ ግለ ታሪክ ወይም የሕይወት ታሪክ ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ የሚሰጧችሁን ዓረፍተ ነገሮች ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ ትተረጉማላችሁ፡፡
- ✓ የተለያዩ ቅኔዎችን ህብረ-ቃል በመለየት በሰምና በወርቅ ትፈታላችሁ፡፡

## መነሻ የመወያያ ነጥቦች

1. “አርበኝነት” ምን ማለት ነው?
2. በተለያዩ የሙያ መስኮች አንቱ የተባሉ የምታውቋቸውን አርበኞች ጠቅሳችሁ ለአገር የፈጸሙትን ጀብዱ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
3. ‹‹የቋራው ካሣ›› የሚለውን ርዕስ ተመልከታችሁ ከምንባቡ ምን ምን ቁም ነገሮች እናገኛለን ብላችሁ ትገምታላችሁ?

# የቋራው ካሣ



ካሣ ኃይሉ በ፲፰፻፲፩ ዓ.ም በጎንደር አካባቢ፣ በደንቢያ ወረዳ፣ በጊዜው አጠራር ቋራ ቀበሌ፣ በተለይ ሻርጌ ከተባለ ስፍራ ተወለዱ። አባታቸው ገና ህፃን ሳሉ በመሞታቸው እናታቸው እየተቸገሩ አሳደጓቸው። እድሜያቸው ለትምህርት በደረሰ ጊዜ አጎታቸው ማህበረ-ሥላሴ ገዳም ወስደው በትምህርት ተኮትኩተው እንዲያድጉ በማለት፣ በዚያ ለነበሩ መነኮሳት ሰጧቸው። ከፍ ሲሉም፣ ከቋራ ሽፍቶች ጋር ተደባልቀው የዘመቻ እቅድና የጦር መላ ተማሩ። ከዚያም በመጀመሪያ ከደጃች ጎሹ፣ ቀጥሎም ከራስ ዓሊ ቤት ገብተው የቤተመንግሥትን ልማድና ወግ አጠኑ። በኋላም፣ ስናር በተባለ ስፍራ (ዛሬ በሱዳን ግዛት ውስጥ ይገኛል) ከግብጾች ጋር በተደረገው ጦርነት ጠላትን ረፍርፈው ከፍ ያለ ጀብዱ ስለፈጸሙ፣ ስማቸው ገነነ። በዚያን ጊዜ ለይስሙላ ዘውድ ጭኖ በጎንደር የነበረው የዮሐንስ ሦስተኛ ባለቤትና የራስ ዓሊ እናት፣ እቴጌ መነን የልጅ ካሣን ጀግንነት አይተው በጋብቻ ለመተሳሰር ጽኑ ፍላጎት ስላደረባቸው የልጃቸውን ልጅ ወ/ሮ ተዋበችን በ፲፰፻፴፯ ዓ.ም ዳሩላቸው።

ነገር ግን፣ ብዙም ሳይቆዩ ልጅ ካሣ በአማቶቻቸው ላይ ሸፈቱ፡፡ በየቦታው ሲቀናቀኗቸው የነበሩ መሳፍንትንና መኳንንትን በጎንደር፣ በወሎ፣ በትግሬና በሸዋ ድል እየመቱ የማይበገሩ ሆኑ፡፡ በተለይ ደግሞ ከደጃች ውቤና ከባለቤታቸው አባት ከራስ ዓሊ ጋር የተደረገው ጦርነት በካሣ የበላይነት ስለተፈጸመ ሕዝቡ በታላቅ ክብር አጅቦ ተቀበላቸው፡፡ በኋላም፣ የካቲት ፭ ቀን ፲፰፻፵፯ ዓ.ም በጊዜው ጳጳስ፣ በአቡነ ሰላማ እጅ ተቀብተው ‹‹ዳግማዊ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ›› ተብለው ነገሡ፡፡

ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ከሸዋ ዘመቻ መልስ የቤተመንግሥትና የቤተ ክህነት ግንኙነት ተለይቶ እንዲኖር አደረጉ፡፡ ገበሬም ወደርሻው፣ ነጋዴም ወደንግዱ፣ የቀረውም ሰው በየሥራው እንዲመለስ ባዋጅ አስታወቁ፡፡ በኋላም ፲፰፻፶፪ ዓ.ም አቤቶ ሰይፉን ለመውጋት በድጋሚ ወደ ሸዋ ዘምተው በተመለሱ ጊዜ፣ ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች በጠና ታመው አገኟቸው፡፡ በተበሳጩ ጊዜ መክረው የሚያበርዷቸውና የሚያጽናኗቸው፣ መከራና ደስታን ሲካፈሏቸው የኖሩት የትዳር አጋራቸው ብዙም ሳይቆዩ ሞቱ፡፡ ንጉሱም ሀዘን ገርፏቸው ቀጥሎ ያለውን የልቅሶ ግጥም ገጠሙ፡፡

> እጅግ ሥራ አዋቂ ትላንትና ተቀበረች፣
> መድሃኒቱን ምሳ ታበላኝ ነበረች፡፡

እቴጌ ተዋበች በህይወት ሳሉ ምንም እንኳ ካባታቸው ባላቸውን መርጠው ቢቀመጡም፣ አስፈቅደውም ሆነ በስውር ለአባታቸው፣ ለራስ ዓሊ የሚያስፈልጋቸውን አሉበት ድረስ ይልኩ ስለነበር፣ ራስ ዓሊም የልጃቸውን ሞት በሰሙ ጊዜ መሪር ሀዘን ወደቀባቸው፤ እንዲህም ገጠሙ፡፡

> ጠጅ አማረኝ ስላት ማሩን ታስጭናለች፤
> ራበኝም ስላት እህሉን ታስጭናለች፤
> በረደኝም ስላት ሸማ ትሰዳለች፤
> ሌባዬ ተይዛ ባልጋ ትሄዳለች፤
> የት አባቷን አውቃ ታሳዝነኛለች፡፡

የአፄ ቴዎድሮስ ታላቁ አስተሳሰባቸውና ፍላጎታቸው የፈረንጅ አገር ቴክኖሎጂ ወደ አገር እንዲገባና ከትንሹ የእርሻ መሣሪያ እስከከባዱ የጦር መሣሪያ ባገር ልጅ እንዲሰራ ነበር፡፡ ከፈረንጅ አገር ሰው መጣ ሲሏቸው "መሣሪያ የሚሠራ ካልሆነ እንዳይቀመጥ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያነብ ሞልቶኛል" ይሉ ነበር፡፡ የሃይማኖት በዓላት ቀናት እንዲወሰኑና ህዝቡ ሠርቶ ምርታማ እንዲሆን ይመኙ ነበር፡፡ ከዚህ የተነሳ በጊዜው የእንግሊዝ ንግሥት ለነበሩት ለንግሥት ቪክቶሪያ የእንግሊዝን የእደጥበብ አዋቂዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዲልኩላቸው በቆንስሎቻቸው አማካይነት ደብዳቤ ልከው ነበር፡፡

ቴዎድሮስ፣ ባሕር ተሻግረው ኢየሩሳሌምን ለማስገበር የነበራቸው ዓላማም ከኢትዮጵያ አንድነት ጋር የተሳሰረ ነበር፡፡

‹‹መይሳው ካሣ ባጭር ታጣቂ፣
ዘመድ ከዘመድ አደባላቂ
የኢትዮጵያ ባል የኢየሩሳሌም እጮኛ››

እያሉ ሲፎክሩ፣ ሕዝቡም እንዲህ እያለ ይገጥምላቸው ነበር፡፡

‹‹ታጠቅ ብሎ ፈረስ ካሣ ብሎ ስም፣
አርብ አርብ ይሸበራል ኢየሩሳሌም፡፡
አንተ ጌታ አይደለህ እኔም አልሆን ሎሌ፣
የየሩሳሌም ሰው ካልጫነ በርሞሌ፡፡
ታጠቅን ማን አምኖ ባል ብሎ ያገባል፣
ሴሰኛውን ጎበዝ ያራቱን ማዘን ባል፡፡

አፄ ቴዎድሮስ በመጨረሻ ዘመናቸው በመቅደላ ከእንግሊዞች ጋር ተዋጉ፡፡ ታዋቂ የነበሩት የጦር መሪዎቻቸው በውጊያው ተሰዉ፡፡ አፄ ቴዎድሮስን በቅርብ ከሚያውቋቸው እንግሊዛውያን አንዱ የሆነው፣ ጆንሲ በዚያ ቀውጢ ሰዓት የተናገሩትን ሲገልጽ፡-

‹‹ ... ክንዴ ገብርዬ ነበር ሞተ፡፡ ቀኝ እጄ አለሜም ሞተ፤ ስለኔ ማንነት ማን ይመሰክራል? በቅርብ የማያውቀኝ ሕዝብ ጨካኝነቴን ብቻ ነው

የሰማው፡፡ ብጨክን አገሬን አንድ ለማድረግ፣ የመሳፍንትና የመኳንንት መጫወቻ እንዳትሆን መክሬ አልሆን ሲል በኃይል ተጠቀምኩ እንጂ፤ አባቴ ኃይሉ፣ እናቴ አትጠገብ ሰው እየገደሉ አልወለዱኝም፡፡ የቋራው አጎቴ ደጃች ክንፉ በውሃ እንድጠመቅ አድርጎ ማህበረ ሥላሴ ገዳም ወሰዶ አስተማረኝ እንጂ፣ በደም አላጠመቀኝ! ሐገሬን አልወድ እንደሆነ፣ ከባሕር ማዶ ዘልዬ ግዛት እንዲጨመርላት አልተመኘሁ እንደሆን፣ ጠላቷን አንበርክኬ አንዲት ኢትዮጵያን ለመፍጠር አልተነሳሁ እንደሆን ታሪክ ይፍረደኝ! መጪው ትውልድ አጥንቴን ከመቃብር አውጥቶ ያቃጥለው ለሐገሬ የምተውላት ኑዛዜ ይህ ብቻ ነው›› ብለው ሽጉጣቸውን ወደራሳቸው አነጣጠሩ ብሏል፡፡

ቴዎድሮስ የሚያወጡትን አዋጅና የሚሰጡትን መመሪያ የሚቀበለው እየጠፋ በማየታቸው አልፎ አልፎ ጥብቅ እርምጃ የመውሰድ ባሕሪ ይታይባቸው ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉም ነበር ከእንግሊዝ ጦር ጋር የተፋጠጡት፡፡ ከመቅደላ ጦርነት የተረፈው ጦራቸው አፈግፍጎ ወደኋላ ሲመለስ ተመለከቱ፡፡ በጦርነቱ መሐል ከእቴጌ ተዋበች ሞት በኋላ ያገቧቸውንና የሚወዷቸውን እቴጌ ጥሩወርቅን ጠርተው፡-

‹‹ጥሩዬ! የኢትዮጵያ መኳንንትና ራስ ወዳድ ገዢዎች በፈጸሙት ክህደት አንድ አደርጋታለሁ ያልኳትን ኢትዮጵያን ከዚህ ተራራ ላይ ሆኜ ስመለከት አዘንኩ፡፡ ለበጎ ብየ የሠራሁት ሁሉ ወደክፉ እየተለወጠብኝ ቆየ፤ እንተባበር፤ አንድ እንሁን ብላቸው ባንድ ሀገር ሁሉም መሪ ሆኖ በትረ መንግስት የሚጨብጥ ይመስል፣ እኔንም የጎዱ እየመሠላቸው አገራችንን በደሉ፤ ዛሬ ደግሞ የባዕድ ጦር መጥቶ መይሳው ካሣን እጅህን ስጥ አለኝ፡፡ አጋሬና አጋዤ ገብርዬም ለሀገሩ ሲል ተሰዋ፡፡ ዓለሜም ወደቀ፡፡ ስለዚህ ለአገሬና ለራሴ ክብር ስል እራሴን እሰዋለሁና እንዳይጨንቅሽ፡፡ ልጄን ደጉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሳድገው›› አሏቸው፡፡ እቴጌዋም በጣም ተደናግጠው አነቡ፡፡ ‹‹በሰማይ እንጂ በመሬት ከጠላት ጋር እንደማንገናኝ ለእንግሊዝ ነግሬዋለሁ፤ ያንቺና የልጄ የአለማየሁ ጉዳይ ኢምንት ነው፤ ከሐሳቤም የለ፡፡ ሐሣቤና ጭንቀቴ ላንዲት

ኢትዮጵያ ነበር፤ አልተሰካልኝም… አንቺም እድሜ አግኝተሽ አለማየሁም አድጎ ስለኔ ሲጠይቅሽ፣ ‹‹እንዲት ኢትዮጵያ፣ የተባበረች ኢትዮጵያ ባይኑ እንደዞረች ቀረ፤ ብለሽ ንገሪው›› ብለው እቅጩን ነገሯቸው።

ጦርነቱ እየተፋፋመ ቀጠለ። የእንግሊዝ ጦር ቢያይልም ከሁለቱም ወገን እልቂት ሆነ። ቴዎድሮስ በስማቸው በጋፋት ያሠሩት መድፍ ገና አንድ ተኩሶ ሲበታተን፣ የጠላት መድፎች ግን ላንቃቸውን ከፍተው ጦሩን አረገፉት። ይህንን የተረዱት ቆፍጣናው ንጉሥ ካጠገባቸው የነበሩትን ጀግኖች ስመው በማሰናበት ከመቅደላ አምባ ሸሽተው እንዲያመልጡ መክረው ራሳቸውን ሰዉ። ታላቅ ሐዘንም ሆነ። እንዲህም ተገጠመ፤

‹‹ማረክን እንዳይሉ ሰው የለ በጃቸው፣
ገደልን እንዳይሉ ሞተው አገኟቸው፤
ምን አሉ እንግሊዞች ሲገቡ አገራቸው?››

በጀግንነት ሽጉጡን ጠጥቶ ወድቆ የተገኘው፣ ‹‹ሰውየው›› መሆኑን እነ ካፒቴን ካሜሩን ለጄኔራል ናፒየር አረጋገጡለት። ጀነራል ናፒየርም ወደ አስከሬኑ ተጠግቶ ለአንድ መሪ የሚገባ ሰላምታ ሰጥቶ አስከሬኑ ፎቶግራፍ እንዲነሳ አደረገ። ወዲያው በወርቅ ግምጃ እንዲገነዙ ተደረገ። በተወለዱ በ፶ ዓመታቸው ሚያዝያ ፯ ቀን ፲፰፻፷ ዓ.ም አርፈው በመቅደላ መድኃኒዓለም ተቀበሩ።

‹‹መቼ ሞተና መቼ ተረሳ፣
መቅደላ ያለው የቋራው ካሣ፤
የቋራው ካሣ ልበልህ አንዴ፣
የለህም ዘመድ ያለ ጎራዴ፤
አንሱ ካላችሁ እናንሳ ወንድ፣
የቋራው ካሣ አባ ሞገድ።
ጠላቶቹን ሁሉ አጭዶ እንደገባስ፣
መቅደላ ተጣላው እራሱን በራስ›› እየተባለ ተገጠመላቸው።

(11ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ፣ 1985 ተሻሽሉ የቀረበ)

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ:- አንብቦ መረዳት

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በቃል መልሱ።**

1. ‹‹ልጅ ካሣ በአማቶቻቸው ላይ ሸፈቱ›› ሲል፣ የልጅ ካሣ አማቶች እነማን ናቸው?
2. አፄ ቴዎድሮስ ባህር ተሻግረው ኢየሩሳሌምን ለማስገበር የነበራቸው ዓላማ ተገቢ ነበር ትላላችሁ? ለምን?
3. ንጉሡ ነገሥቱ ‹‹ስለኔ ማን ይመሰክራል? በቅርብ የማያውቀኝ ሕዝብ ጨካኝነቴን ብቻ ነው የሰማው›› ለማለት ያበቃቸው ክስተት ምን ነበር? ለመግለጽ የፈለጉትስ ምንድን ነው?
4. ‹‹አባቴ ኃይሉ፣ እናቴ አትጠገብ ሰው እየገደሉ አልወለዱኝም›› ሲሉ፣ ለመግለጽ የፈለጉት ምን ነበር?
5. ‹‹ሁሉም መሪ ሆኖ በትረ መንግሥት ይጨብጥ ይመስል›› ሲሉ ለመግለጽ የፈለጉት ምን ነበር?
6. አፄ ቴዎድሮስ ብርቱ አርበኛና ቆራጥ መሪ እንደነበሩ ከምንባቡ ማስረጃ በመጥቀስ አስረዱ።

**ለ. ከዚህ በታች ለቀረቡ ቃላት ከተሰጡ አማራጮች መካከል ቀጥተኛ ፍች የማይሆነውን ቃል ወይም ሐረግ ምረጡ።**

1. መላ፣
   ሀ. ዘዴ　　ለ. ስልት　　ሐ. መፍትሄ　　መ. ብልሃት
2. ተቀናቀነ፣
   ሀ. ተፎካከረ　　ለ. ተሻኮተ　　ሐ. ተቀያየመ　　መ. ተጋፋ
3. ባዕድ፣
   ሀ. ስጋ ያልሆነ　　ሐ. የራስ አካል ያልሆነ
   ለ. የማይታወቅ　　መ. ዝምድና የሌለው
4. በየነ፣
   ሀ. ደነገገ　　ለ. ስርዓት አበጀ　　ሐ. ወሰነ　　መ. ተናገረ

5. በትረ መንግሥት፣
   - ሀ. ንጉስ የሚጨብጠው ዘንግ
   - ለ. የንጉስ መቀመጫ
   - ሐ. የስልጣን ምልክት
   - መ. የንጉስ የወርቅ ዘንግ
6. ኢምንት፣
   - ሀ. በጣም ትንሽ
   - ለ. ቅንጣት
   - ሐ. ባዶ
   - መ. ከቁጥር የማይገባ
7. ቆፍጣና፣
   - ሀ. አመለቢስ
   - ለ. ንቁ
   - ሐ. ቀልጣፋ
   - መ. ኩሩ
8. እቅጩን፣
   - ሀ. እርግጡን
   - ለ. መሸጫውን
   - ሐ. ትክክለኛውን
   - መ. እውነተኛውን

**፫. አፄ ቴዎድሮስን የተመለከቱ ዋና ዋና ድርጊቶችን በምሳሌው መሰረት በቅደም ተከተል በጽሑፍ ዘርዝሩ፡፡**

***ምሣሌ፣***

- በ1811 ዓ.ም. በቋራ ሻርጌ በተባለ ስፍራ ተወለዱ፡፡
- አባታቸው በህፃንነታቸው ስለሞቱ ከእናታቸው ዘንድ አደጉ፡፡

## ክፍል ሁለት፡- ማዳመጥ

**፩. ቀጥሎ መምህራችሁ በየረድፉ መጀመሪያ ላይ ለተቀመጡ ተማሪዎች አንድ፣ አንድ ዓረፍተነገር በጆሮአቸው ይነግራሉ፡፡ መልዕክቱን ተቀብላችሁ አጠገባችሁ ላለ ተማሪ በሹክሹክታ ንገሩ፡፡ በዚህ ዓይነት እየተቀባበላችሁ በማሳለፍ የረድፋችሁ የመጨረሻው ተማሪ የደረሰውን መልዕክት ለመምህራችሁ ድምጹን ከፍ አድርጎ ይናገር፤ መጀመሪያ ከተነገረው መልእክት ጋር አነፃጽሩ፡፡**

**፪. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ አንድ አጭር ታሪክ አንድ ጊዜ ብቻ ያነቡላችኋል፤ በጥሞና አዳምጣችሁ ታሪኩን እንደገና በራሳችሁ አባባል ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡**


## ክፍል ሦስት:- መናገር

**ፊ. አምስት አምስት አባላት ያሏቸው ቡድኖች ከመሠረታችሁ በኋላ፣ ከዚህ በታች በቀረበው የክብ ስዕል ውስጥ የሰፈሩትን የናንተን የግል አስተያየት የሚጠይቁ ርዕሶች በመከፋፈል:-**

ሀ. በደረሳችሁ ርዕስ ላይ በየተራ አስተያየታችሁን ስጡ፡፡

ለ. ጓደኛችሁ በደረሰው ርዕስ ላይ አስተያየት ሲሰጥ አዳምጣችሁ ከጓደኛችሁ የተለየ አስተያየት ያላችሁ የቡድኑ አባላት ሐሳባችሁን ግለጹ፡፡

ሐ. በቡድናችሁ ጸሐፊ አማካይነት በአምስቱ ነጥቦች ዙሪያ በሰነዘራችኋቸው አስተያየቶች ላይ ጠቅለል ያለ ማብራሪያ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡



**፪. የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በማገላበጥ የምታገኙትን የአንድ ሰው የህይወት ታሪክ በጥልቅ ንባብ ስልት በቤታችሁ አንብቡ:: በተከታዩ ክፍለ ጊዜ ስታነቡ ያስደሰታችሁንና ያሳዘናችሁን የታሪኩን ክፍል ከጠቅላላው የገለሰቡ ታሪክ ጋር በማጣቀስ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ::**

## ጥልቅ ንባብ

ጥልቅ ንባብ፣ ከአንድ ጽሑፍ የተወሰነ መረጃን ለማግኘት ሲባል ጥሞናን ሰብስቦ በትኩረትና በጥንቃቄ የሚከናወን የንባብ ዓይነት ነው:: *ጥልቅ ንባብ* ከጽሑፍ አጠቃላይ መረጃን ለማግኘት ከሚነበው *የፍጥነት ንባብና* ፍላጎትን ለማሟላት፣ ደስታን ለማግኘት ከሚካሔደው *ሰፊ ንባብ* የሚለየው የጸሐፊውን ዓላማ ለማወቅ፣ የቀጥተኛና የአንድምታ (ተመላካች) ፍችዎችን ለመረዳትና ከጽሑፉ መረጃን ለቅሞ ለማውጣት የሚካሔድ የጠለቀ ንባብ በመሆኑ ነው::

**፫. በጥንድ በጥንድ እየሆናችሁ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ርዕሶች ላይ የ፭ ደቂቃ የዱብዳ ንግግር አድርጉ፤ ንግግራችሁ በተሰጣችሁ ርዕስ ዙሪያ አንዳችሁ የተናገራችሁትን አንዳችሁ በማጠናከር ላይ ሲያተኩር ይችላል::**

## የዱብዳ ንግግር

የዱብዳ ንግግር በቃል የሚቀርብ ሆኖ በቅድሚያ ሳንዘጋጅ በገጠመን ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሐሳብን ወዲያው አፍልቀን ለሌሎች የምናስተላልፍበት ነው:: የዱብዳ ንግግር ለማድረግ የሚከተሉትን ነጥቦች ማጤን ጠቃሚ ነው::

1. ርዕሱን እንዳወቅን መነሳት ስላለባቸው ዋና ዋና ነጥቦች በሴኮንዶች ውስጥ ማሰብ፣ መወሰንና ንግግርን መጀመር፣
2. በንግግራችን እንዳስፈላጊነቱ የተመረጡ ቃላት፣ ፈሊጦች፣ ዘይቤዎችና ምሳሌያዊ ንግግሮችን መጠቀም፣

3. የድምጻችንን አወራረድ ኃይሉን፣ ፍጥነቱን፣ ቃናውን መመጠን፣
4. የአድማጫችንን ትኩረት ለመሳብ በተገቢ የአካል እንቅስቃሴ ንግግራችንን ማጀብ፣
5. የአድማጫችንን ስሜትና ፍላጎት መጠበቅ፣
6. ከአድማጫችን ጋር የዐይን ግንኙት ማድረግ፣
7. ንግግራችን ሳቢ አመራማሪና አወያይ እንዲሆን ጥረት ማድረግ ናቸው፡፡

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

**ፅ. ከአምስት ያላነሱ የሕይወት ታሪክ መጻሕፍትን በፍጥነት ንባብ ስልት ካነበባችሁ በኋላ፣**

1. የእያንደንዱን መጽሐፍ አጠቃላይ ሐሳብ በአንድ አንቀጽ አስፍሩ፡፡
2. በጽሑፋችሁ መጨረሻ በመረጃ ምንጭነት ያነበባችኋቸውን መጻሕፍት “ዋቢ መጻሕፍት” የሚል ርዕስ ሰጥታችሁና የመረጃ ምንጭ አጻጻፍ ስርዓትን ተከትላችሁ በመጻፍ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

### የዋቢ ጽሑፎች የአደራደር ስርዓት

የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን አገላብጠን ያገኘነውን መረጃ ለጽሑፋችን ከተጠቀምን በኋላ በጽሑፋችን መጨረሻ “ዋቢ ጽሑፎች” በሚል ርዕስ ስር በፊደል ተራ ቅደም ተከተል የመረጃ ምንጮቻችንን በስርዓት መደርደር ይጠበቅብናል፡፡

ስለ አደራደር ስርዓት ሲነሣ፣ የተለያዩ ስርዓቶች ቢኖሩም በቋንቋ ዘርፍ የተዘወተረውን ስርዓት ወስደን በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ መጻሕፍት እንዴት እንደሚሰፍሩ እንመለከታለን፡፡ በዚህ መሠረት አንድ መጽሐፍ በዋቢነት ሲሰፍር በቅደም ተከተል መደርደር ያለባቸው መጽሐፉን የተመለከቱ መረጃዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

የደራሲው ስም፣ የታተመበት ዓመተ ምህረት (በቅንፍ ውስጥ ገብቶ)፣ የመጽሐፉ ርዕስ (ከስሩ ከተሰመረበት ወይም ኢታሊክ ከሆነ በኋላ አራት ነጥብ አርፎበት)፣ የታተመበት ቦታ (ነጠላ ሰረዝ አርፎበት)፣ የማተሚያ ቤት ስም (አራት ነጠብ አርፎበት) በቅደም ተከተል ወደ ጎን ይደረደራል፡፡

***ምሳሌ 1፡-***

ፈቃደ አዘዘ (1991) <u>*የስነቃል መመሪያ*</u>፡፡ አዲስ አበባ፣ ኢትዮ ጥቁር ዓባይ አሳታሚዎች፡፡

የተጠቀምናቸው መጻሕፍት ሲዘረዘሩ ቅደም ተከተላቸው የሚወስነው በደራሲው ስም የፊደል ተራ ይሆናል፡፡ የደራሲው ስም ባልተጠቀሰ ጊዜ ደግሞ የመጽሐፉ ርዕስ ፊደል ተራ ለአደራደሩ መሪ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል አንዳንድ ጊዜ አንድ መጽሐፍ ከአንድ በላይ ደራሲ ሊኖረው ይችላል፡፡ እንዲህ ያለው ሲያጋጥም እስከ ሦስት የሚደርሱ ከሆነ (እገሌ፣ እገሌና እገሌ) በማለት፣ ከሦስት በላይ ሲሆኑ ደግሞ መጀመሪያ ላይ ያለው ደራሲ ስም ተወስዶ (እገሌና ሌሎች) ተብሎ ይሰፍራል፡፡

***ምሳሌ 2፡-***

መስፍን ሀብተማሪያምና ሌሎች (1977) <u>አባ ደፋር እና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች</u>፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

አምሳሉ አክሊሉና ዳኛቸው ወርቁ (1983) <u>የአማርኛ ፈሊጦች</u>፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

በመጨረሻም በጽሑፋችን ውስጥ ባንድ ደራሲ የተጻፉ ሁለትና በላይ መጻህፍትን አግኝተን ስንጠቀም በመጀመሪያ በምሳሌ 2 መሠረት በፊደል ተራ ከዘረዘርን በኋላ፣ ሁለተኛው መጽሐፍ በደራሲው ስም ትክክል ዳሽ ምልክት (__) ይደረግና የቀረው በስርዓት ይደረደራል፡፡

***ምሳሌ 3፡-***

ዳኛቸው ወርቁ (1962) <u>አደፍርስ</u>፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

________ (1977) <u>*የጽሑፍ ጥበብ መማሪያ*</u>፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

፪. ከዚህ በታች በቀረበው ሠንጠረዥ በሕይወት ታሪክ ዙሪያ የተጻፉ መጻሕፍት ዝርዝር በተዘበራረቀ ቅደም ተከተል ቀርቧል፡፡ እናንተ “ዋቢ መጻሕፍት” የሚል ርዕስ ሰጥታችሁ የመረጃ ምንጭ የአጻጻፍ ስርዓትን በመጠበቅ በቅደም ተከተል መጻሕፍቱን ዘርዝሩ፡፡

| ተ.ቁ | ርዕስ | ደራሲ | ማተሚያ ቤት | የሕትመት ቦታ | የታተመበት ዓ.ም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ብዙ አየሁ፤ የህይወቴ ታሪክና ትዝታ | ታደሰ ገብረኪዳን | ሻማ ቡክስ | አዲስ አበባ | 1999 |
| 2 | ፍኖተ ሕይወት | ሳህለሥላሴ ብርሃን ማርያም | ደረኮ አሳታሚ | አዲስ አበባ | 2000 |
| 3 | የደረስኩበት፤ እኔና ትዝታዎቼ (ክፍል ሁለት) | ማሞ ውድነህ | ንግድ ማተሚያ ድርጅት | አዲስ አበባ | 2000 |
| 4 | ካየሁት ከማስታውሰው ልዑል ራስ እምሩ ሀይለ ሥላሴ | አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኘሬስ | ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት | አዲስ አበባ | 2001 |
| 5 | ህይወቴ፤ ግለታሪክ (1901-1941) | ተመስገን ገብሬ | አልፋ አሳታሚዎች | አዲስ አበባ | 2001 |
| 6 | ትዝታዬ ስለራሴ የማስታውሱው፤ መርሰኤ ሀዘን ወልደቂርቆስ | አመሀ መርስኤ ሀዘን | አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት | አዲስ አበባ | 2001 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 7 | አውቶ ባዮግራፊ (የህይወቴ ታሪክ) ፊታውራሪ ተክለ ኃዋርያት ተክለ ማርያም | አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኘሬስ | አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ማተሚያ ቤት | አዲስ አበባ | 1998 |
| 8 | ብቸኛው ሰው፤ ፀሐፊ ትእዛዝ ተፈራወርቅ ኪዳነወልድ | አበራ ጀምበሬ | ሻማ ቡክስ | አዲስ አበባ | 1997 |
| 9 | ድርሳነ ህይወቴ | አበራ ጀምበሬ | ሻማ ቡክስ | አዲስ አበባ | 2001 |

**፫. ከዚህ በታች በማስታወሻ መልክ የቀረበላችሁን የግለ-ታሪክ አጻጻፍ መመሪያ መሠረት በማድረግ የራሳችሁን የህይወት ታሪክ ከሶስት ገጽ ባልበለጠ ጽፋችሁ በመምጣት በተከታዩ ክፍለ ጊዜ በንባብ አሰሙ፡፡**

## ግለ-ታሪክ አጻጻፍ

የሕይወት ታሪክ (Biography) አጻጻፍ ሁለት አይነት ስልትን የተከተለ ነው፡፡ አንዱ ግለ-ታሪክ (የራስ የሕይወት ታሪክ) የሚጻፍበት ሲሆን፣ ሁለተኛው የሌላን ግለሰብ የህይወት ታሪክ የሚጻፍበት ስልት ነው፡፡ ቀጥሎ ግለ-ታሪክ ስንጽፍ ልንዘነጋቸው የማይገቡ ነጥቦች ቀርበዋል፡፡

1. የትውልድ ቦታችንንና የተወለድንበትን ዘመን መጥቀስ፣
2. ስለአስተዳደጋችን ሁኔታና በየደረጃው ስላለፍንባቸው የትምህርት እርከኖች መጻፍ፣
3. የፈጸምናቸውን ጉልህ ተግባሮችና ያበረከትናቸውን ሚዛን የሚደፉ አስተዋጽኦዎች በቅደም ተከተል መዘርዘር፣
4. ስለፈጸምናቸው አስደናቂ ሥራዎች (ካሉ) ያለንን አስተያየት ማካተት፣
5. ታሪካችንን በቅደም ተከተል ማደራጀት፣
6. ቀላልና ግለጽ ቋንቋን ተጠቅሞ መጻፍ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

**፲. በዚህ ምዕራፍ የቀረበውን የአፄ ቴዎድሮስ የሕይወት ታሪክ መሠረት አድርጋችሁ የፈለጋችሁትን የአንድ ሰው የሕይወት ታሪክ መረጃ በመሰብሰብ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡**

**፲፩. የሌላን ሰው የህይወት ታሪክ ለመጻፍ መረጃ በማሰባሰብ ሂደት ሰለግለሰቡ ሥራ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች የተጻፈን መረጃ ማገላበጥ ሊያስፈልግ ይችላል፡፡ እንዲህ ባለው አጋጣሚ የተጻፈበትን ቋንቋ ማወቅ ብቻ ሳይሆን የመተርጎም ችሎታም ያስፈልጋል፡፡ እናንተም ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ዓረፍተነገሮች መልዕክት ተረድታችሁ፣**

1. በቋንቋው መጻፍ ማንበብ ወደምትችሉት አንድ አገርኛ ቋንቋ ተርጉሟቸው፡፡
2. አማርኛ ቋንቋ ብቻ የምታውቁ ከሆናችሁ ደግሞ፣ ዓረፍተነገሮቹን ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተርጉሙ፡፡
3. በጥንድ ሆናችሁ ሥራችሁን በመለዋወጥ በጓደኞችሁ የአተርጓጎም ትክክለኛነት ላይ አስተያየት ስጡ፡፡

**ምሳሌ፣** የሕይወት ታሪክ፣ በሌላ ሰው የሚጻፍ የአንድ ግለሰብ ሕይወት፣ የጽሑፍ ታሪክ ነው፡፡

Biography is an account of somebody's life written by another person.

ሀ. ግለ-ታሪክ፣ በራሱ በግለሰቡ የሚጻፍ የሕይወቱ ታሪክ ነው፡፡
ለ. አለቃ ዘነብ ከሀገራችን ታላላቅ የሕይወት ታሪክ ጸሐፊዎች አንዱ ነበሩ፡፡
ሐ. በጣም አሳዛኝ ዜና ደረሰኝ፡፡
መ. ጓደኛዬ ድሬዳዋ ይኖራል፡፡
ሠ. የመኪና አደጋ ነበር፡፡
ረ. እኔ ሚስጢሩን እየጠበቅሁ ነበር፤ ነገር ግን፣ እህቴ ወደቤት ሄዳ አወጣችው፡፡

## ክፍል አምስት፡- ስነልሳን፣

**፩. ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት ክፍል አራት ስለ ቃል ክፍሎች ሙያ የሰፈረውን ማስታወሻ በማንበብና የተማራችሁትን በማስታወስ ከዚህ በታች በተዘረዘሩ ዓረፍተነገሮች ውስጥ የሚገኙ የቃል ክፍሎችን ከነሙያቸው ዘርዝሩ፡፡**

**ምሳሌ፡-** የቋራው ካሣ ጠላቶቻቸውን በብልሃት አንበረከኩ፡፡

| ቃል | የቃል ክፍል | ሙያ |
|---|---|---|
| የቋራው | ስም | ዘርፍነት |
| ካሣ | ስም | ባለቤትነት |
| ጠላቶቻቸውን | ስም | ተሳቢነት |
| በብልሀት | መስተዋድድ ያረፈበት ስም | የአንቀጽ ገላጭነት (መስተዋድዳዊ ሐረግ እንደ ተውሳከግስ) |
| አንበረከኩ | ግስ | ማሰሪያ አንቀጽነት |

1. ንቦች አበባውን ቀሰሙ፡፡
2. አየለ ሥራውን ያከብራል፡፡
3. አስተዋዩ ገበሬ ቁጠባን ያውቃል፡፡
4. ተካ የንብ ቀፎ አወረደ፡፡
5. አጭርና ቀልጣፋ አገልግሎት እንሰጣለን፡፡
6. ተፈራ ለእህቱ መጽሐፍ ገዛላት፡፡

**፪. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉ ማሰሪያ አንቀጾችን ከመረመራችሁ በኋላ፡-**

1. ሙያቸውን አድራጊ፣ ተደራጊ፣ አስደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ እያላችሁ ለዩ፡፡
2. በአንቀጾቹ ላይ ያረፉትን ቅጥያዎች በመመርመር፣ የእርባታ ወይም የምስረታ ቅጥያዎች መሆናቸውን ለዩ፡፡

**ምሳሌ፣** አበበ ወንድሙን ሥራ አስቀጠረው፡፡

አስቀጠረው = አስደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ

[አስ-ቀጠር-ኧ-ው]

የምስረታ ምዕላድ     የእርባታ ምዕላድ

ሀ. ዳኛው ፍጹም ቅጣት ምት አስመቱ፡፡
ለ. የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዢን ድርጅት አዳዲስ ፕሮግራሞችን አስተዋወቀ፡፡
ሐ. አስተዳዳሪው ከስልጣን ተሰናበቱ፡፡
መ. የሴቶች እግር ኳስ ቡድናችን የኳስ አፍቃሪውን አስደሰተ፡፡
ሠ. በመንገድ ዳር የተከመረው ቆሻሻ ተቃጠለ፡፡

**፫. ቀጥሎ የእርባታ ምዕላድን ለማስረዳት የሚያስችላችሁ አንድ ግስ ከመረጣችሁ በኋላ፣ በተሰጠው ምሣሌ መሠረት በተለያዩ ምድብ ተውላጠ ስሞች በማርባት አሳዩ፡፡**

**ምሳሌ፣** ተማር

| | |
|---|---|
| እኔ = ተማር-ኩ/-ሁ | (ተማርኩ፣ ተማርሁ) |
| እኛ = ተማር-ን | (ተማርን) |
| አንተ = ተማር -ህ/ክ | (ተማርህ፣ ተማርክ) |
| አንቺ = ተማር-ሽ | (ተማርሽ) |
| እናንተ = ተማር -አችሁ | (ተማራችሁ) |
| እሱ = ተማር -ኧ | (ተማረ) |
| እሷ = ተማር -ኧች | (ተማረች) |
| እነሱ = ተማር -ኡ | (ተማሩ) |

ግስ     የርባታ ቅጥያ ምስላድ

፬. ከዚህ በታች በቀረበላችሁ ሰንጠረዥ ቅጽል መስራች ቅጥያ ምዕላዶች ቀርበዋል:: በተራ ቁጥር 1 በተሰጠው ምሣሌ መሠረት በእያንዳንዱ መስራች ምዕላድ ስር አምስት አምስት ምስርት ቅጽሎችን ዘርዝሩ::

| ተ.ቁ | [-ኣማ] | [-ኧኛ] | [-ኣም] | [-ኣዊ] |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ፍሬያማ | ሞገደኛ | ኮተታም | መንፈሳዊ |
| 2. | | | | |
| 3. | | | | |
| 4. | | | | |
| 5. | | | | |

፭. ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 3 እና 4 ከሰራችሁት መልመጃ ምሳሌ በመጥቀስ በእርባታና በምስረታ ቅጥያ ምዕላዶች መካከል ያለውን ልዩነት በአንድ አንቀጽ አብራሩ::

## ክፍል ስድስት:- ስነጽሑፍ

ከዚህ በታች አዒ ቴዎድሮስንና የአገዛዝ ዘመናቸውን የተመለከቱ ቅኔዎች ቀርበዋል:: ህብረ-ቃላቸውን ከለያችሁ በኋላ በስምና በወርቅ ፍቷቸው::

***ምሳሌ፣***

*ሞጣ ቀራኒዮ ምነው አይታረስ፣*
*በሬ ሰላይ መጣሁ ከዚያ እስከዚህ ድረስ::*

ህብረ-ቃል = በሬ ሳላይ

***ሰሙ*** = ሞጦ ቀራኒዮ ያልታረሰው ለምን ይሆን? ከዚያ አንስቼ እዚህ እስክደርስ ድረስ የተጠመዱ (የሚያርሱ)በሬዎች አላየሁም::

***ወርቁ*** = ከዚያ አንስቼ እዚህ እስክደርስ ድረስ በየቦታው በሬሳ ላይ ተራምጄ መጣሁ (ህዝቡ አልቋል)::

1. አንጥረኛው ብዙ ከንጉሡ ቤት፣
   ባላልቦ አደረጉት ይህን ሁሉ ሴት።

2. እጅግ ሥራ ዐዋቂ ትናንትና ሞተች፣
   መድኃኒቱን ምሳ ታበላኝ ነበረች።

3. በሰንሰለት ታስሮ ዓመት ካራት ወር፣
   ማንን ዋስ አግኝቶ ተፈታ ጎንደር።

4. የሸዋ፣ የጎጃም፣ የወሎ፣ የትግሬ ተበትኖ ከብቱ
   ገዛው አባታጠቅ ሰብስቦ በሐብቱ።

5. አባትና እናቱ አላንድ አልወለዱ፣
   አባ ታጠቅ ካሣ ያው አንዱ ያው አንዱ።

# የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ አርበኝነት በጦር ሜዳ ለእናት ሀገር በጽናት መዋጋት ብቻ ሳይሆን በልዩ ልዩ የሙያ መስኮች በመሰማራት ለሀገርና ለወገን የሚጠቅምና የሚያኮራ ተግባር መፈፀምን እንደሚያጠቃልል ተረድተናል፡፡ ከዚህ አንፃር በተለያዩ ሙያ መስኮች ለራሳቸውና ለሀገራቸው መልካም ተግባር ያከናወኑ ጀግኖችን በማንሳት የፈፀሙትን አኩሪ ሥራ አነጻጽረናል፤ ለዛሬው ትውልድ ያላቸውን አርኣያነትም ተመልክተናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም አዳምጠንና አንብበን የተረዳነውን ሐሳብ በራሳችን አባባል እንደገና መግለጽ ችለናል፡፡ የጥልቅ ንባብ ስልትን ተጠቅመን የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በማገላበጥ ያገኘናቸውን መረጃዎች መልሰን ገልፀናል፡፡ ከዚህም ሌላ በተሰጡን ርዕሶች ላይ የዱብዳ ንግግር አድርገናል፡፡

በሌላ በኩል የመረጃ ምንጭ አጻጻፍ ስርዓትን ጠብቀን መጻህፍትን መዘርዘር ችለናል፡፡ በተጨማሪም ግለ ታሪካችንንና የመረጥነውን የአንድ ሰው የህይወት ታሪክ መረጃ አሰባስበን ጽፈናል፡፡ የተሰጡንን ዓረፍተነገሮች ከአማርኛ ቋንቋ ወደ አገርኛ ቋንቋና ወደ እንግሊዝኛ መተርጎም ችለናል፡፡

ስለቃል ክፍሎች ሙያ ባነሳንበት ክፍልም በተለያዩ ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉ ቃላትን በየቃል ክፍላቸውና በየሙያቸው ዘርዝረን ማሳየት ችለናል፡፡ በተሰጡን ዓረፍተነገሮች ውስጥ የሚገኙ ማሰሪያ አንቀጾችን መርምረንም ሙያቸውን አድራጊ፣ ተደራጊ፣ አስደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ እያልን ለይተናል፡፡

የቅጥያ ምዕላዶችን ዓይነትና ተግባር በተመለከትንበት ክፍል ደግሞ፣ ቅጥያ ምዕላዶችን የእርባታና የምስረታ በሚል በሁለት ከፍለን፣ የእርባታ ምዕላዶች እንደ ቁጥር፣ መደብ፣ ጾታ፣ ወዘተ.ን ለማመልከት እንደሚያገለግሉና የሚቀጠሉበትን ቃል፣ የቃል ክፍሉን እንደማይለውጡ፤ ቃላትን እያረባን ተመልክተናል፡፡ በአንጻሩ የምስረታ ምእላዶች የሚቀጠሉበትን ቃል፣ የቃል ክፍል እንደሚለውጡ ቃላትን እየመሰረትን ተመልክተናል፡፡ የተጠቀምንባቸውን የእርባታና የምስረታ ቅጥያ ምዕላዶች ተግባርንም መግለጽ ችለናል፡፡ መጨረሻም የተለያዩ ቅኔዎችን ህብረ-ቃላት በመለየት በሰምና በወርቅ መፍታት ችለናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

**፩. የሚከተሉትን ስም መስራች ምዕላዶች ተጠቅማችሁ በምሳሌው መሠረት ሦስት ሦስት ምስርት ስሞችን ዘርዝሩ።**

1. [-ኧት] እሙቀት ______ ______ ______
2. [-ኧኛ] ልግመኛ ______ ______ ______
3. [-ኤ] ገጠሬ ______ ______ ______
4. [-ኦ] ጥርሶ ______ ______ ______
5. [-ኢያ] መጥረቢያ ______ ______ ______
6. [-ኤታ] ጠቀሜታ ______ ______ ______
7. [መ-] መጥፋት ______ ______ ______

**፪. ሰጣት [ሰጥ-ኧ-ኣት] እና ሸልማት [ሸልም-ኣት] በሚሉት ቃላት ውስጥ በመድረሻ የገባችው [-ኣት] በሁለቱም አገባብዋ አንድ አይነት ምዕላድ ናት ማለት እንችላለን? ለምን?**

**፫. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ የሚገኙትን ቅጥያ ምዕላዶች ተንትናችሁ ካሳያችሁ በኋላ፣ የእርባታ ቅጥያ ምዕላድና የምስረታ ቅጥያ ምዕላድ በማለት ለዩ።**

1. ሽምግልና
2. አትምረጉ
3. ይዝለሉ
4. ይፍለጡ
5. አትጥረቢ
6. ስንፍና

**፬. የዋቢ መጻሕፍት የአደራደር ስርዓት ቅደም ተከተልን በምሳሌ በማስደገፍ በጽሑፍ ግለጹ፡፡**

**፭. የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች ወደምታውቁት ቋንቋ ተርጉሟቸው፡፡**

1. በተሰለፈበት ሙያ ስኬታማ የሆነ ሰው በኑሮውም ደስተኛ ይሆናል፡፡
2. አዘውትሬ ስላላጠናሁ ከዚህ ፈተና ጥሩ ውጤት አልጠብቅም፡፡
3. ጓደኛዬ ያልገባው ትምህርት ሲያጋጥመው ጎበዝ ተማሪዎችን ፈልጎ ይጠይቃል፡፡

**፮. የእርባታና የምስረታ ቅጥያ ምዕላዶች አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው? በምሳሌ በማስደገፍ አብራሩ፡፡**

**፯. የሚከተሉትን ቅኔዎች ህብረ-ቃል ከለያችሁ በኋላ፣ በሰምና በወርቅ ፍቷቸው፡፡**

1. አንተ ልጅ አጥብቀህ ልጓሙን ያዘው፤
 በቅሎ አያውቅምና እንዳንት ያለ ሰው፡፡
2. ደንቢያና ፎገራን የላም አገር ትቶ፣
 ወተት ወተት ይላል እከተማ ገብቶ፡፡
3. አዲስ አበባ ላይ ቡና ቢወደድ፣
 ከጅማ ሰው ካለ ይመጣል በግድ፡፡

# የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ቀጥሎ በዚህ ምዕራፍ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል። በዚሁ መሠረት፣ በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ (√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ተ ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (Ⅹ) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የቀረበውን ጽሑፍ አንብቤ ተረድቻለሁ። | | | |
| 2 | በመልካም ስራቸው አንቱ የተባሉ ሰዎችን በማነጻጸር ገልጫለሁ። | | | |
| 3 | በአረፍተነገር ውስጥ የሚገኙ የቃል ክፍሎችን ዘርዝሬ ሙያቸውን ገልጫለሁ። | | | |
| 4 | በእርባታና ምስረታ ምዕላዶች መካከል ያለውን ልዩነት ገልጫለሁ። | | | |
| 5 | ከአማራጭ መልሶች መካከል የቃላትን ቀጥተኛ ፍቺ መምረጥ ችያለሁ። | | | |
| 6 | የዱብዳ ንግግር ላይ የነቃ ተሳትፎ አድርጌያለሁ። | | | |
| 7 | ሃሳብን በራሴ አባባል በማሳጠርም ሆነ በማስፋፋት መግለፅ ችያለሁ። | | | |
| 8 | በጥልቅ ንባብ ስልት ተጠቅሜ ያነበብኩትን የሕይወት ታሪክ መግለጽ ችያለሁ። | | | |
| 9 | የመረጃ አጻጻፍ ስርዓትን በመጠበቅ የመረጃ ምንጮችን መፃፍ ችያለሁ። | | | |
| 10 | ግለ-ታሪክ ወይም የሕይወት ታሪክ መፃፍ ችያለሁ። | | | |
| 11 | በዓረፍተ ነገር ደረጃ የቀረበልኝን ጽሑፍ ከአማርኛ ወደማውቀው ቋንቋ መተርጎም ችያለሁ። | | | |
| 12 | ቅኔዎችን በሰምና በወርቅ ያፈታት ዘዴ ግልጽ አድርጌ መናገርና በጽሁፍም ማቅረብ ችያለሁ። | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ (?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።

# ምዕራፍ ስምንት

# ትውፊት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡- ተማሪዎች! ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- ✓ ስለትውፊት ምንነትና አገልግሎት ትናገራላችሁ፤ ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ ስለቀደምት የሕብረተሰብ አኗኗር ዘይቤና ትውፊታዊ ቅርሶች ታስረዳላችሁ፡፡
- ✓ ክርክር ታካሄዳችሁ፡፡
- ✓ ሐሳብን አሳጥራችሁ በራሳችሁ አባባል ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ የእርባታና የምስረታ ቅጥያዎች ተጠቅማችሁ ቃላትን ታረባላችሁ፤ ትመሰርታላችሁ፡፡
- ✓ ከመገናኛ ብዙሃን፣ ከቃለ-መጠይቅና ከአውደጥበብ መረጃዎችን አሰባስባችሁ እንዳስፈላጊነቱ ትጠቀማላችሁ፡፡
- ✓ በምሳሌያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮች ትገለገላላችሁ፡፡
- ✓ አንድን ሐሳብ ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ ትተረጉማላችሁ፡፡
- ✓ ጽሑፎችን በጥልቅ ንባብ ዘዴ ታነባላችሁ፡፡

**መነሻ የመወያያ ነጥቦች**

1. ትውፊት ሲባል ምን ይታወሳችኋል?
2. ትውፊት የሌለው ማሕበረሰብ ይኖራል ብላችሁ ትገምታላችሁ? ለምን?
3. "የስልጣኔ መስፋፋት የማሕበረሰቡን ጥንታዊና ባህላዊ ቅርሶች ያጠፋል" የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ እናንተስ ታምኑበታላችሁ? ለምን?

# ትውፊት

ትውፊትን ወይም የእንግሊዝኛ አቻውን ፎክሎርን "እንዲህ ነው" ብሎ ባጭሩ መበየን አስቸጋሪ እንደሆነ ይነገራል፡፡ አስቸጋሪነቱ የሚመነጨው ቃሉ በውስጡ ከያዛቸው ዝርዝር ጉዳዮች ብዛትና ስፋት ነው፡፡ ያም ሆኖ፣ ትውፊት አንድ ማህበረሰብ በረጅም ዘመን ታሪኩ ያከማቻቸውንና የሚከውናቸውን ተረቶችን፣ ቀልዶችን፣ ሐተታ ተፈጥሮዎችን፣ አፈ-ታሪኮችን፣ ምሳሌያዊ ንግግሮችን፣ እንቆቅልሾችን፣ ድግምቶችን፣ ምርቃቶችን፣ እርግማኖችን፣ መሀላዎችን፣ የሐገረሰብ ልብስን፣ ዳንስን፣ ድራማን፣ ጥበብን፣ እምነትን፣ መድሃኒትን፣ የሙዚቃ መሳሪያዎችን፣ ዘፈኖችን፣ ዘዬዎችን፣ ዘይቤዎችን፣ ስሞችን፣ የቃል ግጥምን፣ የመቃብር ጽሑፎችን፣ የመጸዳጃ ቤት ግድግዳ ላይ ጽሑፎችን፣ ጨረቃ ድንቡልቦቃዎችን፣ ገበጣዎችን፣ ሰንጠረዦችን፣ ጸሎቶችን፣ ዘር ቆጠራዎችን፣ የምግብ ዓይነቶችን፣ ጥልፎችን፣ ስፌቶችን፣ የቤትና የአጥር ዓይነቶችን፣ የለማኝ መማጠኛዎችን፣ ዓመት በዓሎችን (ገና፣ አረፋ፣ ጥምቀት፣ መውሊድ...)፣ ድግሶችን፣ የዕረፍት ቀኖችን፣ የድልና የልደት በዓላትን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡

በተጨማሪም ትውፊት ከዚህ በላይ በተዘረዘሩ ሁኔታዎችና ማህበራዊ አጋጣሚዎች የሚከወኑ ተግባራትን ይጨምራል፡፡ በመሆኑም ባንድ በኩል ለልዩ ልዩ ጥበባዊ ቅርጾች የጋራ መጠሪያ ሆኖ ሲያገለግል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ራሱን የቻለ የምርምርና የዕውቀት ዘርፍ ነው፡፡ ታዋቂው የፎክሎር ፕሮፌሰር ቤን-አሞስ " ፎክሎር (ትውፊት) በአነስተኛ ቡድኖች

ያለ ኪናዊ ተግባቦት ነው" ይለዋል፡፡ ይህ አጭር ብያኔ ቢሆንም፣ ብዙ ጽንሰሐሳቦችን አምቆ የያዘ ነው፡፡ ዘርዘር አድርጎ ለማየት እንዲቻል "ኪናዊ ተግባቦት" የሚለውን እሳቤ በሦስት ከፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡

የመጀመሪያው ሰዎች በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው የማያቋርጥ ተግባቦት ሲያከናውኑ የሚሏቸው (የሚናገሯቸው) ነገሮች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- እናንተ አስረኛ ክፍልን ማለፍ ያልቻለ ጓደኛችሁ ሲያዝን ብታገኙት "አይዞህ! 'ላለፈ ክረምት ቤት አይሰራም፡፡' አሁን በርትተህ ካጠናህ እንደኛ ታልፋለህ! ተስፋ አትቁረጥ" ብላችሁ ብትመክሩት ንግግራችሁ ጥበባዊ ሆኖ ታገኙታላችሁ፡፡ ጥበባዊነቱ ከተጠቀማችሁት ምሳሌያዊ ንግግር የሚመነጭ ነው፡፡

የኪናዊ ተግባቦት ሁለተኛው መገለጫ ሰዎች ከሚከውኗቸው ነገሮች የሚመነጭ ነው፡፡ ሰዎች ኪናዊ ተግባቦት ሲያከናውኑ በጋራና በተናጠል የሚከውኑት ነገር አለ፡፡ ለምሳሌ፡- ተረት ተራቹ ሲናገር ያስመስላል፤ የአካል እንቅስቃሴ ያደርጋል፤ የገፀባህርያቱን ሁኔታና ድርጊት የሚገልፀው በክዋኔ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ተረቱ ሲተረት፣ ምሳሌው ሲመሰል፣ የቃል ግጥሙ ሲገጠም፣ ፉከራው ሲፎከርና ሽለላው ሲቅራራ፣ ዝም ብሎ ሳይሆን ከክዋኔ ጋር ተዋህዶ ጥበባዊ ተግባቦትን እውን በማድረግ ነው፡፡

ሦስተኛው የኪናዊ ተግባቦት መገለጫ ሰዎች የሚሠሯቸው (የሚፈጥሯቸው) ነገሮች ናቸው፡፡ አንድ ማህበረሰብ የሠራቸው ቁሳቁሶች ስለሠሪው የሚያስተላልፉት ኪናዊ መልዕክት አለ፡፡ ለምሳሌ፣ በሀገራችን ሕዝቦች ለመጠጫ የሚያገለግሉ ከቅልና ከቀንድ የተሠሩ ጌጠኛ ዋንጫዎች፣ የወተት ዕቃዎች፣ የምግብ መመገቢያ ዕቃዎች፣ የስፌት ውጤቶች፣ የሥራ መሣሪያዎች፣ የጦር መሣሪያዎች፣ ሐውልቶች፣ ትክል ድንጋዮች፣ ወዘተ. ጥበባዊ ከመሆናቸው ባለፈ ስለሠራቸውና ስለሚገለገልባቸው ማህበረሰብ የሚያስተላልፉት መልዕክት አላቸው፡፡ "ያ ትውልድ እንዴት ጥበበኛ ነበር?" እስከማለት ያደርሳሉ፤ ያስደምማሉ፡፡ ለዚህ ነው እንግዲህ ትውፊት ኪናዊ ተግባቦት ነው የሚባለው፡፡

ትውፊት ወይም ፎክሎር አራት ዘርፎችን አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡ እነሱም ስነቃል፣ ሐገረሰባዊ ትውን ጥበባት፣ ሐገረሰባዊ ልማድና ቁሳዊ ባሕል ናቸው፡፡

***ስነቃል፡-*** የልዩ ልዩ ቅርጾች ጥቅል መጠሪያ ሲሆን በውስጡም ተረቶችን፣ ሐተታ ተፈጥሮዎችን፣ አፈታሪኮችን፣ ምሳሌያዊ ንግግሮችን፣ እንቆቅልሾችን፣ እንካሰላንቲያዎችን፣ ቃል ግጥሞችንና የመሣሰሉትን በቃል አማካይነት የሚገለጹትን ጥበቦችና እነሱን የሚያጠናውን ሙያ የሚያጠቃልል ነው፡፡

***ሐገረሰባዊ ትውን ጥበባት፡-*** በዚህ ጥቅል መጠሪያ የሚካተቱት ደግሞ ሐገረሰባዊ ሙዚቃ፣ ሐገረሰባዊ ዳንስና ሐገረሰባዊ ድራማ ሲሆኑ፣ ስሙ እነዚህን ለሚያጠናው የሙያ መስክ መጠሪያነት ጭምር ያገለግላል፡፡ ሐገረሰባዊ ትውን ጥበባት የሐገረሰብ ልብስ ተለብሶ፣ በሐገረሰብ ሙዚቃ መሣሪያዎች ታጅቦ፣ አስፈላጊው መኳኳልና መጊያጊያጥ ከተደረገ በኋላ የሚከወነውን ሁሉ ይመለከታል፡፡ ሙዚቃን ዳንስንና ድራማን ለመረዳት እንዲያመቻችሁ ነጣጥለን አቀረብናቸው እንጂ፣ ብቻ ብቻቸውን የቆሙ አይደሉም፤ በክዋኔ ጊዜ አንዳቸው ባንዳቸው ውስጥ ይኖራሉ፡፡ ልዩ ልዩ የሐይማኖት ሥርዓቶችን (ለምሳሌ፤ የመስቀል፣ የጥምቀት በዓላትን የቅዳሴ ሥርዓቶችን) የሠርግና የልቅሶ ሥነስርዓቶችን "አዶከብሬን"፣ የልደትና የግርዘት ሥነስርዓቶችንና የመሳሰሉትን ቀረብ ብለን ብንመለከት ሙዚቃ፣ ዳንስና ድራማ ምን ያህል የተሳሰሩ እንደሆኑ እንረዳለን፡፡

***ሀገረሰባዊ ልማድ፡-*** በዚህ የትውፊት ዘርፍ አራት አበይት ርዕሰ ጉዳዮች ይካተታሉ፡፡ የመጀመሪያው የፌስቲቫልና ክብረበዓል ከበራ ነው፡፡ የፌስቲቫል አብይ ጉዳይ ሰዎች ባንድነት ሆነው እንዲቦርቁ ማድረግ ነው፤ በዚህ ሂደት የቡረቃው ተሳታፊዎች አንጻራዊ የሆነ የመንፈስ መታደስ፣ የአእምሮ እረፍት ያገኛሉ፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ባህላዊ መዝናኛዎችንና ጨዋታዎችን የሚመለከት ነው፡፡ ባህላዊ ጨዋታዎች ለተጫዋቹ አካላዊ ሥነልቦናዊና ምናባዊ ሐሴትን በማስገኘት በኩል ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ ሦስተኛው የሐገረሰብ መድሃኒት ሲሆን፣ በስሩ ተፈጥሮአዊ የባሕል መድሃኒቶች ይገኛሉ፡፡ አራተኛው ርዕሰ ጉዳይ

ሐገረሰባዊ ሐይማኖት ነው፡፡ ይህ በሐይማኖቶች አካባቢ በመስጊድ፣ በቤተክርስቲያንና በመሳሰሉ የአምልኮ ቦታዎች የሚካሔዱትን መስተጋብሮች የሚመለከት ነው፡፡

***ቁሳዊ ባህል፡-*** በዓይን የሚታየውን በእጅ የሚዳሰሰውን ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ መስፋፋት በፊት አንስቶ የሰው ልጅ ፈጥሮ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች፣ እነዚህ ቁሳቁሶች የተሰሩበትን ዘዴ፣ የልዩ ልዩ ባህላዊ ምግቦች አሠራርን፣ የልብስን፣ የቤትንና የአጥር አሠራርን፣ ሰዎች ሥራ የሚያከናውኑባቸውን ባህላዊ መሣሪያዎችና ሌሎችንም መሰል ነገሮችን ያጠቃልላል፡፡

**ከዚህ በላይ ስለ አራቱ የትውፊት (ፎክሎር) ዘርፎች እጅግ ጠቅለል ያለና መነሻ ሐሳብን የሚፈነጥቅ ገለፃ ቀርቧል፡፡ እስቲ ንባባችሁን እዚህ ላይ ገታ አድርጉና፣ ከገለፃው ያገኛችሁትን ሐሳብ በመመርኮዝ፣ ትውፊት ለሚገለገልበት ማህበረሰብ ምን ፋይዳ ይኖረዋል ብላችሁ ትገምታላችሁ?**
**መልሳችሁን በማስታወሻችሁ በማስፈር ንባባችሁን ቀጥሉ፡፡**

እያንዳንዱ የትውፊት (ፎክሎር) ዓይነት ለፈጠረውና ለሚገለገልበት ማህበረሰብ ምን ፋይዳ አለው? ብለን ስንጠይቅ የሚከተሉትን ሐሳቦች ልናገኝ እንችላለን፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ማህበረሰቡ የሚያከናውናቸው ተግባራት ከሥነቃል ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ተረቶች ሲተረቱ፣ ምሳሌዎች ሲመሰሉ፣ እንቆቅልሾች ሲጠየቁ፣ የቃል ግጥሞች ሲደረደሩ … የየራሳቸው ተግባራት አሏቸው፡፡ የስነቃል ተግባራት ብዙ ቢሆኑም ከዚህ በታች ሁለቱን በማንሳት እንመለከታለን፡፡

***የመትከል (የማጠናከር) ተግባር፡-*** ማህበረሰቡ "ጠቃሚ ናቸው" ብሎ ያመነባቸው እሴቶች ተጠብቀው እንዲኖሩ በሥነቃሉ አማካይነት ይተክላቸዋል፡፡ በአባላቱ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ ልዩ ልዩ ሥነቃላዊ ቅርጾችን ይጠቀማል፡፡ ለምሳሌ፡- እንደቅንነት፣ ደግነት፣ ቸርነት፣ ጀግንነት፣ ታታሪነት … የመሳሰሉትን መልካም ባሕሪያት

አባላቱ እንዲጠብቋቸው የሚያደርገው በተረቶች፣ በምሳሌያዊ ንግግሮች፣ በአፈታሪኮችና በመሳሰሉት ሥነ ቃሎች አማካይነት ነው፡፡

***የማስተማር ተግባር፡-*** ዘመናዊ ትምህርት ከተስፋፋበት ዘመን አንስቶ ሕብረተሰቡ ልጆቹንና አባላቱን ስለ ልዩ ልዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ስለአኗኗርና አሰራር ሥርዓቶች፣ ስለ አበላልና አለባበስ ሥርዓቶች የሚያስተምረው በሥነቃሉ አማካይት ነው ለምሳሌ፡- "ድር ቢያብር አንበሳ ያስር" በማለት የህብረትን አስፈላጊነትና ጥቅም ያስተምራል፡፡ በዚህ ዓይነት በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የተነገሩትን ምሳሌዎች፣ ተረቶች፣ ቃል ግጥሞች ይዘት ብንመረምር ትልቅ ማህበራዊ ፋይዳ ያላቸው ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

*(መነሻ ሐሳብ፣ ፈቃደ አዘዘ (1991) የስነቃል መመሪያ፣ ቤን-አሞስ (1982) ፎክሎር ኢን ኮንቴክስት፡፡)*

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ፡- አንብቦ መረዳት

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ፡፡**

1. የክዋኔ ምንነትን አንድ ትውፊታዊ ቅርስ በመውሰድና በመከወን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ፡፡
2. ‹‹ጥንት ሰዎች የሠሯቸው ባህላዊ ቁሳቁሶች ኪናዊ ተግባቦት ይገለጽባቸዋል›› ሲባል፣ ምን ማለት ነው? የሐገራችን ሕዝቦች ከሰሯቸው ጥንታዊ ባሕላዊ ቁሳቁሶች ውስጥ የምታውቁትን አንድ ቁስ በምሳሌነት በመውሰድ አብራሩ፡፡
3. በሐገረሰባዊ ትውን ጥበባት ስር ከሚካተቱ የሐገራችን ሙዚቃዎች አንዱን በመምረጥና በማዜም የሐገረሰባዊ ትውን ጥበባትን ምንነት አስረዱ፡፡
4. በተራ ቁጥር 3 ያዜማችሁትን ሙዚቃ በምሳሌነት ወስዳችሁ ሐገረሰባዊ ሙዚቃ፣ ሐገረሰባዊ ዳንስና ሐገረሰባዊ ድራማ ተነጣጥለው የሚታዩ እንዳልሆኑ አስረዱ፡፡

5. በአካባቢያችሁ የምታውቁትን አንድ ሐገረሰባዊ መድሃኒት ጠቅሳችሁ እንዴት በሕመምተኛው እንደሚወሰድ በዝርዝር አስረዱ።

**፪. ከዚህ በታች በቀረቡ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ እየተሰመረባቸው ለቀረቡት ፈሊጦች አገባባዊ ፍቻቸውን በቃል አስረዱ።**

**ምሳሌ:-** <u>የአዛኝ ቅቤ አንጓች</u> ሁሉ ተሰብስቦ ማሸርገዱን ተያይዞታል። እወደድ ባይ፤ የፈለገውን እስኪያገኝ ተመሳስሎና ተቀራርቦ "ልነጠፍልህ" እያለ የሚኖር።

1. <u>ጓዳየን ያወቀ</u> ጓደኛ ሲከዳኝ አልወድም።
2. ከልጅነቱ አንስቶ <u>አፉን ይይዘዋል</u>።
3. <u>ቤቴ ሲዘጋ</u> የት ዋልክ የሚለኝ ዘመድ አጣሁ።
4. ይህንን <u>የዛር ፈረስ</u> ጓደኛህን ወደ ቤቴ አታምጣብኝ።
5. የልብስ ስፌት መኪናየን <u>ጆሮ ግንዱን</u> አልኩት።
6. <u>አቋቋሚነት</u> ስለተጠራሁ የነገ ጧቱን ቀጠሮ ሰርዣለሁ።
7. አባቷ ለልጃቸው የመጣውን ባል ባይወዱትም <u>መቀነቷን ትፍታ</u> በማለት ዳሩለት።

## ክፍል ሁለት:- መናገር

**፩. ከዚህ በታች የቡድን ክርክር ለማድረግ የሚያስችሏችሁ የክርክር ርዕሶች ቀርበዋል፤**

1. መምህራችሁ ስለርዕሶቹ፣ ስለተከራከሪ ቡድኖችና ስለዳኞች አመራረጥ የሚሰጧችሁን ማብራሪያ በመከተል ተከራካሪ ቡድኖችን መስርቱ፤ ዳኞችን ሰይሙ።
2. በተከታዩ ክፍለ ጊዜ በየቡድናችሁ ሆናችሁ በርዕሳችሁ ላይ ተዘጋጅታችሁ በመምጣት ተከራከሩ።

## የክርክር ርዕሶች

ሀ. ከዕውቀትና ከገንዘብ እጅግ አስፈላጊው ገንዘብ ነው።

ለ. የጽሑፍ መስፋፋት ጽሑፍ ባልነበረ ጊዜ በቃል ሲተላለፉ የኖሩ የማህበረሰቡን የሥነ ቃል ሐብቶች ያጠፋል።

ሐ. የሠርግ ሥነስርዓትን ተበድሮም ተለቅቶም በመደገስ ማድመቅ ተገቢ ነው።

መ. የሐገራችን ወጣት ትውልድ ከቀደሙት አባቶቹ በዕውቀት ይበልጣል።

## የክርክር መመሪያ

ክርክር ባንድ ርዕስ ጉዳይ ላይ ተቃራኒ እይታ ባላቸው ሁለት ሰዎች ወይም ቡድኖች መካከል ተናግሮ ለማሳመን የሚካሔድ ሙግት ነው። ሙግቱ የተሟጋቾችን ሐሳብ መዝነው ፍርድ የሚሰጡ ዳኞች ይኖሩታል። ተከራካሪ ወገኖችም በቂ ዝግጅት ማድረግና የክርክር አቀራረብ ስልትን ማወቅ ይጠበቅባቸዋል።

**1. የክርክር ዝግጅት፡-**

1.1. ርዕሱን በሚመለከት ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ሐሳብ መሰብሰብ፣

1.2. ከሰበሰባችሁት ሐሳብ ውስጥ ለክርክሩ ጠቃሚ ናቸው የምትሏቸውን መምረጥ፣

1.3. የሚቀርቡበትን ቅደም ተከተል መወሰን፣

1.4. ጊዜው ደርሶ የመከራከሪያ ሐሳባችሁን ከማቅረባችሁ በፊት ልምምድ ማድረግ፣

1.5. በክርክሩ ላይ አለባበሳችሁን አስተካክላችሁና ስነስርዓት ጠብቃችሁ መገኘት ያስፈልጋል።

**2. የክርክር አቀራረብ፡-**

2.1. ደግፋችሁ ወይም ተቃውማችሁ የምትከራከሩበትን ርዕስ ለአድማጫችሁ ማስተዋወቅ፤ (ክርክሩ በቡድን ከሆነ ርዕስ ማስተዋወቁ በቡድን መሪዎች የሚከናወን ይሆናል)

2.2. በተዘጋጃችሁት መሠረት በልበ ሙሉነትና በረጋ መንፈስ የመከራከሪያ ሐሳባችሁን በቅደም ተከተል በቃል ማቅረብ፣

2.3. ሐሳባችሁን በተገቢ የአካል እንቅስቃሴዎች ማገዝ፣

2.4 ተቃዋሚያችሁ የሚያነሳቸውን ነጥቦች በትክክል መመዝገብና የተቃውሞ ሀሣብ ማዘጋጀት፣

2.5 ለክርክሩ በሚሰጣችሁ ጊዜ በሚገባ መጠቀም፣

2.6 ከርዕሳችሁ ላለመውጣት መጠንቀቅ፣

2.7 ሐሳባችሁን ምስጋና በማቅረብ ማጠናቀቅ ያስፈልጋል፡፡

## ክፍል ሦስት፡- መጻፍ

፩. በቡድን ሆናችሁ በአካባቢያችሁ ስለሚካሔድ ፌስቲቫል ወይም ክብረ በዓል አከባበር አዋቂ ሰዎችን ቃለ-መጠይቅ አድርጋችሁ ያገኛችሁትን መረጃ አጠናቅራችሁ አቅርቡ፡፡

፪. በስነቃል የመግለጽ፣ የመግታትና የማምለጥ ተግባር ላይ ከመገናኛ ብዙሃን፣ ከአውደ ጥበብና ከትውፊት መጻሕፍት በየግላችሁ መረጃዎችን ሰብስባችሁ በጽሑፍ በማጠናቀር ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

፫. የትውፊት ምንነትን፣ ዓይነትንና ማህበራዊ ፋይዳን የሚያትቱ ልዩ ልዩ ጽሑፎችን ከመጻሕፍት፣ ከመጽሔቶችና ከጋዜጦች በማፈላለግ በጥልቅ ንባብ ስልት ካነበባችሁ በኋላ፣ ያገኛችሁትን ሐሳብ በጽሑፍ አቅርቡ፡፡

**፬. ከዚህ በታች የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች ወደምትችሉት ቋንቋ ተርጉማችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።**

ሀ. ትውፊት ጥበባዊ ተግባቦት ነው።
ለ. የትውፊት አንዱ ባህሪ ጥንታዊ ባህላዊነቱ ነው።
ሐ. ትውፊት ብዙ ፍችዎች አሉት።
መ. ሀይማኖታዊ ፌስቲቫልን ለመካፈል ዕድል አግኝታችሁ ይሆናል።
ሠ. ባህል በማያቋርጥ አኳኋን እየተለወጠ ነው።

## ክፍል አራት:- ስነልሳን

**፩. ከዚህ በታች የቀረቡትን ቅጥያ ምዕላዶች በተሰጡ ቃላት መድረሻ ላይ በመቀጠል ካረባችሁ (ከመሰረታችሁ) በኋላ፣ የቅጥያ ምዕላዳቹን ተግባር ግለፁ (አንድ ቃል ከአንድ በላይ ቅጥያዎችን ሲቀበል ይችላል)።**

***ምሳሌ:-***

ሰላም - ሰላም-ነት = ሰላምነት (ረቂቅ ስምን መመስረት)
ሰላም-ታ = ሰላምታ (ውልድ ስም መመስረት)
ሰላም-ኤ = ሰላሜ (ዘርፍነትን ማመልከት)

*ቅጥያዎች፣*

| | | |
|---|---|---|
| -ኧት | -ታ | -ኧኛ |
| -ነት | -ኤ | -ኣማ |
| -ኣት | -ኢያ | -ኣም |

*ቃላት፣*

| | | |
|---|---|---|
| እሾህ | ገጠር | ቂም |
| መላክ | ይሁን | ቀንድ |
| አክስት | አጎት | ነጋዴ |
| ክብር | ብልህ | ብልጥ |

፪. በተራ ቁጥር 1 ላይ ከተዘረዘሩት ቅጥያዎች ለእርባታ እና ለምስረታ ያገለገሉ ቅጥያዎች የትኞቹ ናቸው?
፫. ቅጥያዎቹ በእርባታም ሆነ በምስረታ ጊዜ በቅርጽ አንድ በመሆናቸው ልዩነት የላቸውም ማለት እንችላለን? ለምን?

## ክፍል አምስት፡- ስነጽሑፍ

**፩. ከዚህ በታች በቀረበው ምሳሌ መሠረት ለቀረቡላችሁ አምስት ርዕሶች በሐሳብ የሚስማሙ ሦስትና በላይ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ሰብስቡ፡፡**

**ምሳሌ፤** ርዕስ፡- <u>ችኮላ</u>

**ምሳሌያዊ ንግግሮች፡-**

- የቸኮለች አፍስሳ ለቀመች፤
- ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል፤
- የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል፤
- የነቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ፤
- የተጣደፈን ቅቤ ያንቀዋል፡፡

**ሀ. ዕውቀት**

1. ____________
2. ____________
3. ____________
4. ____________

**ለ. ክፋት ምቀኝነት**

1. ____________
2. ____________
3. ____________
4. ____________

**ሐ. ሕብረት**

1. ______________
2. ______________
3. ______________
4. ______________

**መ. ቁጥብ አንደበት**

1. ______________
2. ______________
3. ______________
4. ______________

**ሠ. ፍቅርና ወዳጅነት**

1. ______________
2. ______________
3. ______________
4. ______________

**፪. ከላይ ለየርዕሶቹ በሰበሰባችኋቸው ምሳሌያዊ ንግግሮች በመጠቀም በአምስቱም ርዕሶች አንድ አንድ አንቀጽ ጻፉ።**

**፫. በ "ሀ" ስር የተዘረዘሩትን የቃል ግጥሞች ተመሳሳይ ከሚሆኗቸው በ "ለ" ስር ከተዘረዘሩት ምሳሌያዊ ንግግሮች ጋር አዛምዱ፡፡ (አንድ ጥያቄ ከአንድ በላይ መልስ ሊኖረው ይችላል)**

| "ሀ" | "ለ" |
| --- | --- |
| 1. አዲስ ቤተ ሠሪ ይፈልጋል ማገር፣ | ሀ. ላለው ቅንጭብ ያረግዳል፡፡ |
| ሆዱ ከቆረጠ ያም ሀገር ያም ሀገር፡፡ | ለ. የደላው ሙቅ ያኝካል፡፡ |
| 2. አስራ ሁለት ሆነን አንዲት ልጅ ወደን፣ | ሐ. ይበጃል ያሉት ኩል፣ |
| እሷ ትስቃለች እኛ ተጨንቀን፡፡ | ዐይን አጠፋ፡፡ |
| 3. እኔስ ብየሽ ነበር ያይኔ ጉድፍ አውጪ፣ | መ. እውነትና ንጋት |
| እንዲህ በስተኋላ ነገር ልታመጪ፡፡ | እያደር ይጠራል፡፡ |
| 4. ይህንን ማጣቴን ችግሬን ጠላሁት፣ | ሠ. እኛ ባገራችን ዳቦ |
| ልብሽ ወደ ሀብታም ሲያደላ እያየሁት፡፡ | ፍሪዳችን፤ |
| 5. አንቺ ነሽ ወይ እኔ የከዳነው በፊት፣ | ረ. ያልተነካ ግልግል |
| ሥራ ቡቃያ ነው ይለያል ወደፊት፡፡ | ያውቃል፡፡ |
| | ሰ. ደፋርና ጭስ መውጫ |
| | አያጣም፡፡ |
| | ሸ. ቤተሰሪ ደም የለውም፡፡ |

**፬. በቀረቡት የሰው አካል መጠሪያዎች ላይ የሚመሰረቱ አምስት አምስት ፈሊጦችን ከሰበሰባችሁ በኋላ በተሰጡት ምሳሌዎች መሠረት ዓረፍተነገር በመሰራት ፍችና አጠቃቀማቸውን አሳዩ፡፡**

*ምሳሌ፡-*

1. ***ዐይን***

በዐይነ ስጋ = በህይወት፣ በአካል

ዓረፍተ ነገር = በዐይነ ስጋ እስክንገናኝ ድረስ በሰላም ያቆየን፡፡

2. **ራስ፣**

ራስ የሌለው= ይሉኝታን የማያውቅ፣ ይሉኝታ ቢስ

ዓረፍተ ነገር= ራስ ከሌለው ሰው ወዳጅነት መመስረት አያስፈልግም።

3. **አፍ፣**

አፌን ይዤ = ጠበቃየን ይዤ

ዓረፍተ ነገር = ፍርድ ቤት የተገኘሁት አፌን ይዤ ነበር።

4. **እጅ፣**

እጅ መንሻ = ገፀ በረከት፣ ስጦታ

ዓረፍተ ነገር = አያና አንድ ሙክት እጅ መንሻ ይዞ ቀረበ።

5. **እግር፣**

እግረሰላቢ = ኮቴቢስ፣ ኮቴው የማይሰማ

ዓረፍተ ነገር = እግረሰላቢ ሰው ወሬ ለቃሚ ይመስለኛል።

# የምዕራፉ ማጠቃለያ

በምዕራፍ ስምንት ስለትውፊት ምንነት፣ ዓይነትና ማህበራዊ ፋይዳ በማንሳት ተወያይተናል፡፡ ለትውፊት ወይም ለፎክሎር አጭር ብያኔ ለመስጠት ቢያስቸግርም በውስጡ የሚያካትታቸውን ነገሮች በመዘርዘር ማሳየት እንደሚቻል ተመልክተናል፡፡ "ትውፊት በአነስተኛ ቡድኖች ያለ ኪናዊ ተግባቦት ነው" የሚለውን የፕሮፌሰር ቤን-አዋሰን ብያኔ ወስደን ትውፊት የሚገለጽባቸውን መንገዶች ሰዎች ከሚናገሩት፣ ከሚከውኑትና ከሚሰሩት አንጻር ዘርዘር አድርገን አይተናል፡፡

ስለትውፊት ዓይነቶችና አገልግሎታቸው በተመለከትንበት ክፍልም ትውፊት በስሩ ሥነቃልን፣ ሐገረሰባዊ ትውን ጥበባትን፣ ሐገረሰባዊ ልማድንና ቁሳዊ ባሕልን አደሚጠቀልል፣ እንዲሁም እነዚህ የትውፊት ዓይነቶች በሥራቸው የሚያካትቷቸውን የትውፊት ቅርሶች ተመልክተናል፡፡ ትውፊት ፈጥሮ ለሚገለገልበት ማህበረሰብ በርካታ ተግባር ወይም አገልግሎት እንዳለው አንስተን በተለይ ስነቃል ያለውን የመትከል (የማጠናከር) ተግባርና የማስተማር ተግባርን ዘርዘር አድረገን አይተናል፡፡ በየግላችን ቀሪ የትውፊት ተግባራትን የመረጃ ምንጮችን በማገላበጥ (የመግለጽ፣ የመግታትና የማምለጫነት ተግባር) በዝርዝር አብራርተናል፡፡

ስለክርክር ምንነትና ባሕሪ ባነሳንበት ክፍልም፣ ክርክር የሚደረግባቸውን ርዕሶች በመምረጥና መመሪያን ተከትለን ዝግጅት በማድረግ ክርክር አካሂደናል፡፡ በአካባቢያችን ወቅት ጠብቆ ስለሚካሔድ ፌስቲቫል ወይም ክብረበዓል አከባበር ቃለ-መጠይቅ አዘጋጅተን አዋቂ ሰዎችን በመጠየቅ መረጃ ሰብስበናል፤ አጠናቅረን አቅርበናል፡፡ ቀደም ሲል በምዕራፍ ሰባት ክፍል ሦስት ስለጥልቅ ንባብ ምንነትና አጠቃቀም በተወያየነው መሠረት ስለትውፊት ምንነት፣ ዓይነትና ማህበራዊ ፋይዳ የሚያወሱ ልዩ ልዩ ጽሑፎችን በጥልቅ ንባብ ስልት በማንበብ ሐሳባቸውን አጠናቅረን አቅርበናል፡፡ ከዚህም ሌላ ከአማርኛ ወደ ሀገርኛ ቋንቋዎች እንዲሁም ከአማርኛ ቋንቋ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ የመተርጎም ልምምድ አካሂደናል፡፡

በሌላ በኩል በተሰጡን ቃላት ላይ ልዩ ልዩ ቅጥያዎች በመጨመር ቃላት ቅርጻቸውንና ባሕሪያቸውን እንደሚለዋውጡ ከመመልከታችንም በላይ የቅጥያ

ምዕሳዶቹን ተግባር ስይተናል፡፡ በተጨማሪም በልዩ ልዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ሰብስበን አጠቃቀማቸውን በጽሑፋችን ውስጥ በማስገባት አሳይተናል፡፡

በመጨረሻም ምሳሌያዊ ንግግሮችን በሐሳብ ከሚመስሏቸው የቃል ግጥሞች ጋር አዛምደን የሚያስተላልፉትን መልዕክት ከማየታችንም በላይ በሰው የአካል መጠሪያዎች (ራስ፣ ዐይን፣ አፍ፣ እጅ፣ እግር) ላይ የሚመሰረቱ ፈሊጦችን በመሰብሰብ አጠቃቀማቸውን ዓረፍተ ነገር በመሥራት አሳይተናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

፩. "ትውፊት የልዩ ልዩ ጥበባዊ ቅርሶች የጋራ መጠሪያ ነው"፤ "ትውፊት እራሱን የቻለ የምርምርና የዕውቀት ዘርፍ ነው" የሚሉትን ሐሳቦች በምሳሌ በማስደገፍ አብራሩ፡፡

፪. በሀገረሰባዊ ልማድ ስር የሚካተቱ ትውፊቶችን በመዘርዘር ስለ እያንዳንዳቸው በምሳሌ የተደገፈ አጠር ያለ ማብራሪያ ስጡ፡፡

፫. ቁሳዊ ባህልን ቀደም ሲል፣ በምዕራፍ ሁለት ከተማርነው ግዝፈት ካለው ቅርስ ጋር በማነጻጸር ሁለቱ የሚመሳሰሉበትንና የሚለያዩበትን ነጥብ (ካለ) ዘርዝራችሁ አብራሩ፡፡

፬. ለሚከተሉት ፈሊጦች ፍች ከሰጣችሁ በኋላ፣ ዓረፍተነገር ስሩባቸው፡፡

1. የቁም እስር
2. ቆራጭ ፈላጭ
3. ትከሻውን አሳየኝ
4. ዋጋ ሰባሪ
5. ዙሪያ ገባው
6. የሕልም ሩጫ

**5. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጅምር ምሳሌጣዊ ንግግሮች አሟሉ፡፡**

1. ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል፣ ____________________________::
2. ከእባብ እንቁላል፣ ____________________________________::
3. አጉል ባልንጀራ፣ _____________________________________::
4. በሚያዝያ ጎመን የዘራ፣ ______________________________::
5. መንደር ከዋለ ንብ፣ __________________________________::
6. ልብ ያሰበውን አፍ ይናገረዋል፤ ዓይን ያየውን፣______________::
7. ልክን ማወቅ፣ _______________________________________::
8. አንችው ሲሳይ፣ የተጫንሽው ሲሳይ፣____________________::

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ

፩. ቀጥሎ በዚህ ምዕራፍ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል:: በዚሁ መሠረት፣ በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ (√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ::

| ተ .ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስለትውፊት ዓይነትና ማሕበራዊ ፋይዳ ከሰዎችና ከመጻሕፍት ሐሳብ አሰባስቤ አቅርቤያለሁ:: | | | |
| 2 | በተሰጡኝ ቃላት ላይ ቅጥያዎችን እያከልኩ ቃላቱ በቅጽና በባሕርይ ለውጥ ማስከተላቸውን አሳይቻለሁ:: | | | |
| 3 | በምሳሌያዊና በፈሊጣዊ አነጋገሮች ተጠቅሜያለሁ:: | | | |
| 4 | ስለትውፊት ምንነትና ማሕበራዊ ፋይዳው ከልዩ ልዩ ምንጮች መረጃዎችን በጽሑፍ አሰባስቤ አቅርቤያለሁ:: | | | |
| 5 | መመሪያዎችን ተከትዬ በተሰጡኝ ርዕሶች ላይ ተከራክሬያለሁ:: | | | |
| 6 | አጠርአጠር ያሉ ዓረፍተነገሮችንና አንቀጽን፣ ወደማውቀው አገርኛ ቋንቋ (እንግሊዝኛ) ተርጉሜያለሁ:: | | | |
| 7 | የጥልቅ ንባብ አነባበብ ዘዴን ተጠቅሜ፣ ካነበብኩት ጽሑፍ ውስጥ ያገኘሁትን ሐሳብ በጽሑፍ አቅርቤያለሁ:: | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ::

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# ስኬት

**የምዕራፉ ዓላማዎች:- ተማሪዎች! ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ:-**

- ✓ ስኬትን የተመለከቱ የመገናኛ ብዙሃን ፕሮግራሞችን ተከታትላችሁ፣ ያዳመጣችሁትን ሐሳብ ትናገራላችሁ፤ ትጽፋላቸሁ::
- ✓ የዱብዳ ንግግር ታደርጋላችሁ::
- ✓ የውይይት መመሪያን ተከትላችሁ በሚሰጣችሁ ርዕስ ላይ ትወያያላችው::
- ✓ ሐሳብን በማወዳደር ትጽፋላችሁ::
- ✓ የቃለ-መጠይቅ ቅጽ ታዘጋጃላችሁ::
- ✓ ባዘጋጃችሁት የቃለ መጠይቅ ቅጽ መረጃ ትሰበስባላችሁ::
- ✓ የሕይወት ታሪክና የግለ-ታሪክ አጻጻፍ አንድነትንና ልዩነትን ታስረዳላችሁ::
- ✓ መመሪያን ተከትላችሁ የሚቀርብላችሁን ጽሑፍ በሲሶ ታሳጥራላችሁ::
- ✓ ለሚቀርቡላችሁ ምሳሌያዊ ንግግሮች ተመሳሳይና ተቃራኒ የሚሆኑ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ትመርጣላችሁ::
- ✓ ለፈሊጣዊ አነጋገሮች ተመሳሳይ ፈሊጦችን ለይታችሁ ታመለክታላችሁ::

## የመነሻ መወያያ ጥያቄዎች

1. ስኬት ምንድነው?
2. ሰኬታማ መሆን የሚቻለው እንዴት ነው?
3. የስኬታማ ሰዎችን የህይወት ተሞክሮ መመልከት ምን ጥቅም አለው?

## ታሳቁ የሚዲያ ሰው...

የአማርኛ ክፍል ቴክኒሺያኑና ፕሮግራም አስፈፃሚው የዜና ሰዓት በመድረሱ ዝግጅት ማድረግ ጀምረዋል፡፡ ለወትሮው ቢሆን የዕለቱ ዜና አንባቢ ተገኝቶ ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ ነበረበት፤ ዛሬ ግን የዕለቱ ዜና አንባቢ በማይታወቅ ሁኔታ አልመጣም...

ይህ ክስተት ዕለት በዕለት የሚያጋጥም ባለመሆኑ፣ ለክፉም ለደጉም ተብሎ ተጠባባቂ አልተመደበም፡፡ አገር ምድሩ ዜና እየጠበቀ እያለ፤ በአንባቢ መጥፋት ምክንያት ዜናው ሳይቀርብ ቢቀር አስገራሚ ነው የሚሆነው፡፡ ወይንም ደግሞ፣ «አድማጮቻችን ዛሬ ምሽት አንባቢው ባልታወቀ ምክንያት ስለቀረ ዜና ባለማቅረባችን ይቅርታ እንጠይቃለን!» ሊባል? አይደረግም፡፡ አጋጣሚ ሆኖ፣ የአማርኛ ዜና ክፍል ዳይሬክተሩ ከዚህ ቀደም ስቱዲዮ ገብተው ዜና አንብበው አያውቁም፡፡ እና ጭንቀቱ ከወዲያ ወዲህ ያንጎራድዳቸው፤ ያቁነጠንጣቸው ጀመር፡፡

በዚህ ጭንቀት ውስጥ እያሉ ነበር፣ ድንገት ያ - ማታ ማታ ስቱዲዮ እየገባ ስለአሰራሩ እንዲመለከት የተፈቀደለትን ተማሪ ልጅ ያዩት፡፡ ዜናው ደግሞ የግድ ለአየር መብቃት አለበት፡፡ ዳይሬክተሩ ጭንቀታቸው እየበረታ ሄደ፡፡

«ይሄ ልጅ ይግባ? ወይስ እራሴ ልግባ?» ግራ ተጋብተው ሲንቆራጠጡ፣ ሰዓቱ ደረሰ፤ አሁን ያላቸውን አማራጭ መጠቀም ካልቻሉ ችግር ሊሆን ነው፡፡ ወደ ልጁ ተጠጉና ሲፈሩ ሲቸሩ፣ «ትሞክር!» አሉት፡፡ ይሄ ጥያቄ ጋዜጠኛ ለመሆን ነፍሱ ለተራበች ልጅ ሀሴት ውስጥ የሚከት ነበር፡፡ ልጁ ምንም የጥርጣሬ ፊት ሳያሳይና ጨርሶ የፍርሃት ስሜት ዝር ሳይልበት በድፍረት፣ «አነባለሁ!» አለ፡፡ ዳይሬክተሩ “ይኸ ልጅ ወይ እንደጀማሪ ፊደል ሲቆጥር ቢገኝ፣ አሊያም እንደኮልታፋ ምላሱ ቢተሳሰር፣ ወይ

ደግሞ የስቱዲዮው ቤተ መቅደሳዊ ድባብ አስፈርቶት ከጥቂት መንተባተብ በኋላ ንባቡን ቢያቋርጥ፣ አልፎ ተርፎም ወረቀት እያንኮሻኮሸ ምን እየቀደዱ ነው ቢያስብል፣ የማን ያለህ ሊባል ነው?” እያሉ አወጡ አወረዱ:: ነገር ግን፣ ከዚህ በላይ የማሰቢያ ጊዜ ሊኖራቸው አይችልም::

ተማሪዎች! እስቲ እዚህ ላይ ንባባችሁን ገታ አድርጉና፡-

1. እናንተ የአማርኛ ዜና ክፍል ዳይሬክተሩን ብትሆኑ፣ ዜናውን ማን እንዲያነብ ትወስናላችሁ? ለምን?
2. ልጁ ካሳየው ድፍረትና ልበሙሉነት በመነሳት ዜናውን እንዲያቀርብ ቢፈቀድለት፣ ያለስህተት የሚያነበው ይመስላችኋል?

በጭንቀት ነፍሳቸው እንደተጠበበች በግዳቸው ዜናውን ሰጡትና አብረውት ወደ ስቱዲዮ ገቡ:: ያ ልጅ ግን ስቱዲዮ ውስጥ መግባት ያለበት አንባቢ ብቻ እንደሆነ ሰሞኑን ካየው ነገር ተገንዝቧል:: ስለዚህም ዳይሬክተሩ ያበላሸዋል ብለው እንደፈሩ ገብቶታል:: ዳይሬክተሩ ፊት ላይ ፍርሃት እየጎላ ሲታይ፣ ንባቡ እንዲቀጥል የሚጠቁመው የስቱዲዮ ቀይ መብራት ብልጭ አለ:: ዜናው መነበብ ጀመረ::

«እንደምን አመሻችሁ? ዜና እናሰማለን፤ ዜናውን የማቀርብላችሁ ታደሰ ሙሉነህ ነኝ...›› ቅልጥ አድርጎ አነበበው ፤ ያለ ስህተት ተወጣው::

ታደሰ ሙሉነህ በዚህ ዓይነት ገና የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሆኖ የጋዜጠኝነት ሙያን ተቀላቀለ:: በዚያን ጊዜ ታዋቂ ጋዜጠኛ የነበረው አሳምነው ገብረወልድ በታደሰ ችሎታ ተደንቆ፣ "አንተ ነህ ታደሰ ሙሉነህ ማለት?" ብሎ ይጠይቀዋል:: "አዎ እኔ ነኝ" ሲል፣ ‹‹ግሩም ዜና አንባቢ ነህ፣ እንግዲህ አህያ በወለደች አረፈች›› ማለት ይሄ ነው አለው:: ይህ ንግግሩ ብርቱ መነቃቃት እንደፈጠረለት ይናገራል::

ታደሰ ሙሉነህ የተወለደው በአዲስ አበባ ከተማ፣ በ፲፱፻፵፩ ዓ.ም ነበር:: አሳዳጊ አጎቱ ዘንድ ሆኖ፣ በአራት ዓመቱ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን

በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት መማር ጀምሮ፣ እዚያው አጠናቋል። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቱን፣ በጊዜው ከመላው ኢትዮጵያ ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ለዩኒቨርሲቲ ትምህርት ወደሚዘጋጁበት፣ በዕደማርያም ትምህርት ቤት ገብቶ ተከታትሏል። ቀዳማዊ ሀይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ (ያሁኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) ገብቶም፣ በዩኒቨርስቲው ኪነጥበባት ወቲያትር ውስጥ ይሳተፍ ነበር።

ማንኛውም ሰው ቢሆን፣ የማህበራዊ ግንኙነቱና የህይወት ተሞክሮው ውጤት እንደመሆኑ፣ ስብዕናው የሚቀረጸው በቤተሰቡና በማህበረሰቡ ነው። ያም ሆኖ፣ እንደግለሰብ የሚኖረው አስተሳሰብና እራሱን ባንድ በተለየ እንቅስቃሴ ለመግለጽ የሚያደርገው ጥረት፣ ከሌሎች የተለየ ያደርገዋል። ታዴም ገና ዩኒቨርሲቲ በመማር ላይ ሳለ፣ በዚያን ጊዜ ከአሜሪካን አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡትን የሰላም ጓዶች አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምር አንድ ቡድን ወደ አሜሪካ እንዲሄድ ተፈለገ። ለዚህ ቡድን ምልመላ ሲካሄድ ከተመራጮቹ አንዱ ታዴ ሆነ፤ በ፲፱ ዓመቱም ከቡድኑ ጋር ወደ አሜሪካ ተጓዘ።

እዚያም እያለ፣ የጋዜጠኝነት ሙያ ጽንሰሀሳብ በጣም እየገባው፤ ውስጡም እየጠለቀ ሄደ። በተማረባቸው ኔዘርላንድስ፣ ስዊድን፣ ቸኮዝሎቫኪያ፣ ኬኒያና ሌሎችም በርካታ የጎበኛቸው ሬዲዮና ቴሊቪዥን ጣቢያዎች የጋዜጠኝነት ሙያው እንዴት ተግባራዊ እንደሚያደርጉት ሲመለከት፣ ሙያው ውስጥ ጠልቆ መግባት እንዳለበት ወሰነ።

ታደሰ፣ በትምህርቱ ከፍተኛ የጋዜጠኝት ትምህርት የተከታተለ ሲሆን፣ የጋዜጠኝነት ስልጠናም በአፍሪካ ፣ በመካከለኛው ምስራቅ ፣ በአውሮፓና በአሜሪካ ተዘዋውሮ ወስዷል። ከዚያም ወደ ሀገሩ በመመለስ፣ በማስታወቂያ ሚኒስቴር ተቀጥሮ መሥራት ጀመረ። በመጀመሪያ፣ ዜና አንባቢነት (ዜና ክፍል)፤ በተርጓሚነት ከዚያም፣ በዜና ክፍል አዘጋጅነት ሠራ። ቆይቶም፣ የአማርኛ ፕሮግራም ክፍል ኃላፊ ሆነ። ከፕሮግራም ክፍል ኃላፊነት ደግሞ፣ ወደ ዋና ፕሮዳክሽን ክፍል ኃላፊነት ተሸጋገረ። ቆይቶም፣ የፕሮግራም ክፍል ዋና ኃላፊ ሆነ፤ እንዲህ እያለም፣ እስከ

መምሪያ ኃላፊ ባሉ የኃላፊነት እርከኖች ተዘዋውሮ አገልግሏል፡፡ በነዚህ ዓመታት አያሌ መሰል ባለሙያዎችን በማፍራት የላቀ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ታደሰ በብሔራዊ ደረጃ ለሙያው ባበረከተው ድንቅ አስተዋጽኦ ሐገር አቀፍ ተሸላሚ ለመሆን በቅቷል፡፡

በማስታወቂያ ሚኒስቴር፣ በሬዲዮ ዘርፍ ለብዙ ፕሮግራሞች መጀመር ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ነው-ታዴ፡፡ እጅግ በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያለው አድማጭ ካተረፉለት ፕሮግራሞች መካከል የቅዳሜ ከሰዓትና የእሁድ ጠዋት ፕሮግራም፣ የእሁድ ቀንና እርሶም ይሞክሩት የሚባሉት ጉልህ ስፍራ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ የፎን ኢን (የአድማጭ የቀጥታ የስልክ ተሳትፎ) ፕሮግራም እንዲጀምር ያደረገም እሱ ነው፡፡ የቅርብ ጓደኞቹ «ታዴ ሬዲዮ ላይ ሳይሠራ ከዋለ ያመዋል» እስከሚሉ ድረስ፣ በሁሉም የሬዲዮ ፕሮግራሞችና ዜና ሥራዎች ውስጥ ከፍተኛ ተሳትፎ ነበረው፡፡ "ሬዲዮ ላይ መሥራት በእርግጥ ደስ ይለኛል" የሚለው ታዴ፣ መሥራቱ ሰው እንዳደረገው፤ እንደተማረበት ያምናል፡፡ «ሁል ጊዜ፣ ሁል ቀን ተማሪ ነህ» ስለሚልም፣ በሙያው ውስጥ በሳል እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በመስኩም ብዙ ወጣት ጋዜጠኞችን መቅረጽ ችሎአል፡፡

ታዴ ስለስኬት አስተያየቱን ሲሰጥ፣ "ሰው የሚመኘውን ነገር በጥንቃቄ ማወቁ ለስኬቱ ታላቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን፣ መመኘት ብቻ ከግብ ስለማያደርስ የተመኙትን ለማግኘት መንቀሳቀስ ግድ ይላል፡፡ ምኞታችን እቤታችን ድረስ አንኳኩቶ አይመጣም፤ ለመሆን የምትፈልግበት ቦታ ለመድረስ መታገል አለብህ፡፡ እንቅፋቶችን ሁሉ ባግባቡ መዝለል አለብህ፡፡ ስኬት ለኔ ከዚህ ጽንሰሃሳብ በጣም የሚርቅ አይደለም" ይላል፡፡

በመጨረሻም ለአንድ በሙያው ፍቅር ገና ከወጣትነቱ ጀምሮ ልቡ ለነደደ ጋዜጠኛ ለሕዝብ ዓይንና ጆሮ ከመሆን፣ ሕዝብን ከማገልገል፣ ከማሳወቅ፣ ከማዝናናትና ተገቢውን መረጃ ከመስጠት የበለጠ ስኬት የለምና-ታደሰ ሙሉነህ በዚህ በኩል ብቃቱን አስመስክሯል፡፡

*(ተክሉ ፤ ከስኬት በስተጀርባ፤ 1998፣111-134 ለማስተማሪያ እንዲሆን ተሻሽሎ የቀረበ)*

# መልመጃዎች

## ክፍል አንድ:- አንብቦ መረዳት

**፩. ከዚህ በታች የቀረቡላችሁን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ፡፡**

1. የዜና ክፍል ዳይሬክተሩ የዜና ንባቡን ለታደሰ ሙሉነህ ለመስጠት ያቅማሙባቸው ምክንያቶች ምን ምን ነበሩ?
2. ዳይሬክተሩ የዕለቱ ተረኛ አንባቢ ሲቀርባቸው ዜናውን እራሳቸው ለምን አላነበቡም?
3. በመጨረሻ ሰዓት የዜና ክፍል ሀላፊው አንድም ቀን ዜና አንብቦ ለማያውቀው የዩኒቨርሲቲ ተማሪ እንዲያነብ መፍቀዳቸው ተገቢ ነበር? ለምን?
4. ታዋቂው ጋዜጠኛ አሳምነው ገብረወልድ «እንግዲህ አህያ በወለደች አረፈች» ሲል፣ ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
5. «ማንኛውም ሰው የማህበራዊ ግንኙነቱና የተሞክሮው ውጤት ነው» የሚለውን ሐሳብ አብራሩ፡፡
6. አንድን ሰው ከሌሎች የተለየ እንዲሆን የሚያደርገው ምንድን ነው?
7. የያዙትን ሙያ አጥብቆ መውደድና መሥራት ለስኬት ያለውን ድርሻ ከምንባቡ ማስረጃ በመጥቀስ አብራሩ፡፡
8. ጋዜጠኛ ታደሰ ሙሉነህ ስኬትን እንዴት ይመለከተዋል? እናንተስ?

**፪. ከዚህ በታች ለቀረቡላችሁ ቃላትና ሐረጋት መዝገበ ቃላትን ተጠቅማችሁ ቀጥተኛ ፍቺያቸውን ከሰጣችሁ በኋላ፣ ዓረፍተነገር ስሩባቸው፡፡**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. መዳረሻ | 3. ንረት | 5. የነፍስ ወከፍ | 7. እርቃን |
| 2. መድበል | 4. ምዝበራ | 6. ውል ተቀባይ | 8. ተጫረተ |

## ክፍል ሁለት:- መናገር

**፩. በምዕራፍ ሰባት ክፍል ሶስት ስር የዱብዳ ንግግር ማድረግ የሚያስችሉ ጠቃሚ ነጥቦችን ተመልክተናል፡፡ በዚሁ መሰረት በጥንድ በጥንድ እየሆናችሁ መምህራችሁ ከመምህር መምሪያ በሚሰጧችሁ ርዕሶች ላይ የአምስት ደቂቃ የዱብዳ ንግግር አድርጉ፡፡**

**ፍንጭ፤**

- የመጀመሪያው የጥንዱ አባል በተሰጠው ርዕስ ላይ ከሶስት ደቂቃ የማይበልጥ ንግግር ያደርጋል፡፡
- ሁለተኛው የጥንዱ አባል ከጓደኛው ንግግር የሚደግፈውን በማጠናከር፣ የማይደግፈውን ደግሞ በሱ አመለካከት ምን መሆን እንዳለበት በትህትና እየገለጸ ይናገራል፡፡

**፩. በልዩ ልዩ የሥራ መስኮች ተስማርተው ለስኬት የበቁ ግለሰቦችና ማህበራት በመገናኛ ብዙሃን (በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በጋዜጣ፣ በመጽሔቶች) በተደጋጋሚ ይቀርባሉ፡፡ ከዚህ ቀደም የሰማችሁትን ወይም ያነበባችሁትን የስኬት ታሪክ በማስታወስ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡**

**፪. በምትኖሩበት የገጠር ቀበሌ ያሉ ሞዴል አርሶአደሮችን ወይም በምትኖሩበት ከተማ ያሉ ሞዴል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪ ማህበር አባላትን በመውሰድ ለስኬት የበቁበትን ተግባር አስረዱ፡፡**

**፫. ከዚህ በታች የቀረበላችሁን የውይይት መመሪያ ተከትላችሁ «ለስኬት የሚያበቁ ዋና ዋና የሕይወት መርሆች ምንድን ናቸው? ሰዎች እንዴት ለስኬት ይበቃሉ?» በሚሉ ርዕሶች ለመወያየት እንድትችሉ፣**

1. መምህራችሁ በሚመሯችሁ መሠረት ከመካከላችሁ አወያይ የሚሆን አንድ፣ ተወያይ የሚሆኑ አራት በድምሩ አምስት ተማሪዎችን ምረጡ፡፡
2. የተመረጣችሁ ተማሪዎች በርዕሶቹ ዙሪያ መረጃዎችን በማሰባሰብ ለውይይት ተዘጋጁ፡፡
3. በተከታዩ ክፍለጊዜ የተመረጡ ተማሪዎች በእናንተ ፊት ውይይት ሲያካሂዱ፣ የቀራችሁት እያንዳንዱ የውይይቱ ተሳታፊ የሚሰነዝራቸውን ዋና ዋና ሐሳቦች በማስታወሻ በማስፈር ስለውይይቱና ስለተደረሰበት መደምደሚያ አጭር ዘገባ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ ታቀርባላችሁ፡፡

## የውይይት አዘገጃጀትና አቀራረብ

ውይይት ጊዜና ቦታ ተወስኖለት፣ ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሰዎች ሐሳባቸውን የሚለዋወጡበትና በርዕሱ ዙሪያ ከአንዳች መግባባት ላይ የሚደርሱበት በዓላማ የሚፈፀም ክንውን ነው፡፡ ውይይት ለማካሄድ ስታቅዱ፣ ለመዘጋጀት ጊዜ እንዲኖራችሁ ማድረግ በመጨረሻ ለምትደርሱበት ድምዳሜ ትክክለኛነት አወንታዊ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

1. **የውይይት ዝግጅት**
   - 1.1. ርዕሱን በሚገባ መረዳት፣
   - 1.2. ርዕሱን የተመለከቱ ትክክለኛ መረጃዎች ማግኘት፣
     - 1.2.1. ርዕሱን የተመለከቱ ጽሑፎችን አፈላልጎ ዋና ዋና ፍሬ ሐሳቦችን መሰብሰብ፣
     - 1.2.2. ስለርዕሱ የጠለቀ እውቀት ያላቸው ሰዎችን በማፈላለግ የተገኘውን ዋና ዋና ፍሬ ነገር መመዝገብ፣
   - 1.3. ከንባብ ወይም ከቃለ መጠይቅ የተገኙት ፍሬ ሐሳቦች የውይይቱን ታዳሚዎች የሚመጥኑ መሆናቸውን መመርመርና መለየት፣
   - 1.4. ጥሬ ሐሳቦቹን በቅደም ተከተል በመያያዝ የርዕሱን የተለያዩ ገጽታዎች መዳሰስ መቻላቸውንና ወቅታዊነታቸውን መመዘን፣ የተጓደለ ሐሳብ ያለ ከመሰለን ማሟላት፣

2. **የውይይት አቀራረብ**
   - 2.1. አለባበስና ንጽህናን ጠብቆ መገኘት፣
   - 2.2. ጥሩ ስነምግባር ማሳየት (ተራ ጠብቆ መናር፤ የሌሎችን ሐሳብ ማክበር፣ ያልተንዛዛና የተመጠነ ሐሳብ መሰንዘር)
   - 2.3. ውደይቱን ርዕስና ዓላማ ባጭርና ግልፅ ቋንቋ ማሳወቅ፣
   - 2.4. ሲናገሩ ድምፅን መመጠን፣ ፍርሃትና ግድየለሽነትን ማስወገድ፣

2.5. የውይይቱን ጭብጦች በቅደም ተከተል ማቅረብ፣
2.6. ፍሬ ሐሳቦችን በበቂ ምክንያትና በማስረጃ ማስደገፍ፣
2.7. ተገቢ የአገላለጽ ስልቶችን መከተል፣ አንደበተ ርቱዕ መሆን፣
2.8. ከታዳሚዎች የሚቀርቡ አስተያየቶችንና ጥያቄዎችን በሚገባ አድምጦ ማስታወሻ በመያዝ ተራ ሲደርስ ተጨባጭ የመፍትሔ ሐሳቦችን ማቅረብ፣

**፫. በምዕራፍ ሰባት ክፍል አራት ላይ ግለ-ታሪክና የሕይወት ታሪክ መጻፋችሁ ይታወሳል፡፡ በግለ-ታሪክና በሕይወት ታሪክ መካከል የተገነዘባችሁት ልዩነት ምንድን ነው?**

## ክፍል ሶስት፡- መጻፍ

**፩. በአካባቢያችሁ ስለሚገኝ የሕዝብ ቤተመጻሕፍት፣ የጤና ድርጅት፣ የትምህርት ተቋም፣ የቀበሌ መስተዳድር... በቃለመጠይቅ መረጃ መሰብሰብ እንድትችሉ፣**

1. ባለ አምስት አባላት ቡድን በመመስረት መረጃ ለመሰብሰብ የምትችሉበትን አንድ ተቋም ተወያይታችሁ ምረጡ፡፡
2. ስለመረጣችሁት ተቋም በቂ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ከሶስት ያልበለጡ ሰዎችን ምረጡ (የምትመርጧቸው የተቋሙ መሪዎች፣ በተቋሙ ረጅም ዘመን ያገለገሉ ሠራተኞች፣ የተቋሙ ተገልጋዮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
3. ከዚህ በታች የሰፈረውን የቃለ-መጠይቅ አዘገጃጀት መመሪያ ተከትላችሁ ጥያቄዎችን በማዘጋጀትና ቃለ-መጠይቁን በማካሄድ ያገኛችሁትን መረጃ በጽሑፍ አጠናቅራችሁ በቡድን መሪዎቻችሁ አማካይነት አቅርቡ፡፡

**ፍንጭ፡-** ጥያቄዎቻችሁ በተቋሙ አመሰራረት፤ የሰው ኃይል፤ የተገልጋዩ ማንነት፤ የአገልግሎት ሽፋን (ለምን ያህል ህዝብ?)፣ የአገልግሎት ጥራት፣ የተገልጋዩ እርካታ የተመዘገቡ ስኬቶች፣ የወደፊት ራዕይ… ላይ ሊያተኩር ይችላል፡፡

## የቃለ-መጠይቅ አዘገጃጀትና አቀራረብ

ቃለ-መጠይቅ ስለምንፈልገው መረጃ የጠለቀ እውቀት አላቸው የሚባሉ ሰዎችን በመጠየቅ መረጃ የምንሰበስብበት መሳሪያ ነው፡፡ ቃለ-መጠይቅ የተዋቀረና ያልተዋቀረ ቃለ-መጠይቅ በመባል በሁለት ይከፈላል፡፡ ከዚህ በታች የተዋቀረ (አስቀድሞ ለቃለ መጠይቁ የሚሆኑ ጥያቄዎች የሚነደፍበት) ቃለ-መጠየቅ አዘገጃጀትና አቀራረብን እንመለከታል፡፡

1. **ዝግጅት**
    - 1.1. ጥያቄዎቹን መንደፍ፣
    - 1.2. የነደፍናቸው ጥያቄዎች የምንፈልገውን መረጃ ሊያስገኙ መቻላቸውን መርምሮ ማረጋገጥ፣
    - 1.3. ስለ ቃለ-መጠይቁ ሁኔታ የሚያብራራና ለተጠያቂው የሚቀርበውን አጭር ጽሑፍ ማዘጋጀት
    - 1.4. የቃለ-መጠይቁን አላማ አስረድቶ ከተጠያቂዎቹ ጋር ቀጠሮ መያዝ፣
    - 1.5. ለቃለ-መጠይቁ መሳሪያዎችን (መቅረፀ ድምፅ፣ የቴፕክር…) መጠቀም ካስፈለገ አስቀድሞ ማዘጋጀት፣
    - 1.6. የቀጠሮ ቀን ሲደርስ ሰዓት አክብሮ መገኘት ናቸው፡፡

2. **አቀራረብ**
    - 2.1. ለቃለ መጠይቁ ዝግጁ በመሆናቸው ተጠያቂዎችን ማመስገን፣

2.2 ስለ ቃለ መጠይቁ አላማ የተዘጋጀውን ማብራሪያ መስጠት፣

2.3 ጥያቄዎችን በቅደም ተከተልና ትህትና በተላበሰ አኳኋን ማቅረብ፣

2.4 መልሶችን በጥሞና ማዳመጥ፣

2.5 ዋና ዋና ሐሳቦችን እያዳመጡ ማስታወሻ መያዝ፣

2.6 ቃለ-መጠይቁ ሲጠናቀቅ ተጠያቂውን ማመስገን፣

**፩. በቡድን ሆናችሁ በአካባቢያችሁ ወይም በሐገር አቀፍ ደረጃ አርአያነት ያለው ተግባር ያከናወኑ (በሕይወት ያሉ ወይም ያለፉ) የአንድ ሰው የሕይወት ታሪክ መጻፍ እንድትችሉ፣**

1. እየተወያያችሁ የሕይወት ታሪክ የምትጽፉላቸውን ሰው ምረጡ፣
2. ወደ ቤተመጻህፍት በመሄድ ከተለያዩ መጻሕፍት፣ መጽሔቶች፣ ጋዜጦች ስለ ሰውየው የሚገልፁ መረጃዎችን ሰብስቡ፣
3. የቃለ-መጠይቅ ጥያቄዎችን በመንደፍ ግለሰቡን፣ ቤተሰቦቻቸውንና የቅርብ ጓደኞቻቸውን በመጠየቅ መረጃ ሰብስቡ፤
4. ከመረጃ ማግኛ ጽሑፎችና ከቃለ-መጠይቅ የሰበሰባችሁትን መረጃ በማጠናቀር የግለሰቡን የሕይወት ታሪክ ጽፋችሁ ለተከታዩ ሳምንት አቅርቡ።

**፪. በምዕራፍ ሁለት ክፍል ሶስት ስር የቀረበውን የአጎጽሮተ ጽሑፍ መመሪያ ተከትላችሁ:-**

1. ቀጥሎ የቀረበውን ስለጀግናው አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ የሚያወሳ ጽሑፍ በሲሶ (1/3) አሳጥራችሁ ጻፉ፤
2. ላሳጠራችሁት ጽሑፍ ተገቢ የሆነ ርዕስ በመስጠት ለመምህራችሁ አቅርቡ።

ውድድሩ የመጨረሻ ዙር ላይ ደርሷል፤ ፓልቴርጋት እየመራ ነው፡፡ በሚያስገርም ብቻ ሳይሆን በሚያስደነግጥ ሁኔታ ኬንያዊው ፓልቴርጋት እየመራ ነው፤ ኃይሌ ገብረስላሴ ከኋላ እየተከተለው ይገኛል፡፡ ይህ በታሪክ ሆኖ የማያውቅ ክስተት በመሆኑ የኃይሌን መሸነፍ ዓለም ቢሰማ ጉድ ይላል... የአለም ጋዜጠኞችም «የኃይሌ ማሸነፍ ዜና አይሆንም» እንዳሉት ተሸንፎላቸው ጮማ ዜና ሊያገኙ በመሆኑ አሰፍስፈዋል፡፡ ምክንያቱም ዝንተዓለም የኃይሌን አሸናፊነት መዘገብ ሰልችቷቸዋል፡፡

አሁን ውድድሩን የሚመለከት ሁሉ ትንፋሹን መቆጣጠር ያልቻለበት ቅፅበት ላይ ይገኛል፡፡ ሁሉም በሚያሳቅቅ ጭንቀት ውስጥ ነው፡፡ ከ27 ደቂቃ በፊት የውድድሩን መጀመር ያበሰረው ጥይት ሲተኮስ የነበሩ ሀያ-ሩዋጮች የሉም፡፡ ሁለቱ ብቻ እልህ አስጨራሽ የሞት ሽረት ትግል እያካሄዱ ነው፡፡ ይህ ለፓልቴርጋት የመጨረሻ እድል ነው፤ ማሸነፍ አለበት፡፡ ይኸው ደግሞ ውድድሩን በጥቂት ርቀትም ቢሆን እየመራ ነው፡፡ ታሪክ ይቀይራል፤ ታሪክ ይሰራል፤ የሱ ብቻ ሳይሆን የኃይሌም ታሪክ ይቀየራል - በተሸናፊነት፡፡

ውድድሩ ሊጠናቀቅ 50 ሜትር ብቻ ይቀራል፤ እየመራ ያለው ፓልቴርጋትና ኃይሌ ገብረስላሴ ትንቅንቃቸው ቀጥሏል፡፡ በሩጫው ዓለም ከቶውንም ቢሆን ኃይሌን አሸንፎ የማያውቀው ፓልቴርጋት ዛሬ ያለ የሌለ ኃይሉንና የመጨረሻ ጉልበቱን ሊጠቀም ነው... ቀኑ የሱ ይሆን?

ሩጫውን በታላቅ ጉጉት እየተከታተለ የሚገኘው መላው የስቴዲየሙ ተመልካች ሁሉ ከመቀመጫው ተነስቶ ቆሟል፤ በመላው ዓለም ውድድሩን በቴሌቪዥን የሚከታተሉ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች ከመቀመጫቸው ጫፍ ላይ ደርሰው አፍጥጠው እየተመለከቱ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ እጅግ ታላቅ ምጥ ውስጥ ነው:: ሁለቱን ሯጮች የማሸነፊያው መስመር እጅግ እየቀረባቸው ነው፡፡ ከሰባት ያልበለጡ ርምጃዎች ብቻ ቀሩ፤ በኃይሌ ገብረስላሴ አእምሮ ይቻላል! ይቻላል! የሚል ድምፅ እያቃጨለ ነው፡፡

ኃይሌ ፓልቴርጋትን ሲደርስበትና ትከሻ ለትከሻ ሲገጣጠሙ ቅልጥ ያለ ጩኸት ይሰማ ነበር፡፡ በዚያች ቅጽበት በግራ ጎኑ፣ በግራ ዐይኑ በጨረፍታ ሲመለከት ከ ፓልቴርጋት ጋር እኩል ሁኔታ ላይ ናቸው፡፡ ያኔ እጆቹን እንደ ክንፍ ዘረጋ፡፡ ትንሽ ቴክኒክ መጠቀም ካልቻለ መሸነፉ ነው፡፡ እርግጠኛ ሆኖ የመጨረሻውን እርምጃ ሰነዘረ፡፡ የማይረሳ ድል ነበር! የሴኮንድ ዘጠኝ መቶ ሽርፍራፊ ላይ አሸነፈ! ኃይሌ ገብረስላሴ የዓለማችን ታላቁ የረጅም ርቀት ሻምፒዮንነቱን ያወጀበት ጣፋጭ የድል ቀን ...

*(ተክሉ ጥባሁን፣ ለማሸነፍ የተቀባ፣ 1998፣11-19 ተሻሽሎ የቀረበ)*

## ክፍል አራት፡- ስነጽሑፍ

**ፊ. በ«ሀ» ስር የተዘረዘሩትን ምሳሌያዊ ንግግሮች በ «ለ» ስር ከቀረቡትና በፍች ተመሳሳይ ከሆኑት ምሳሌያዊ ንግግሮች ጋር ኣዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ትለብሰው የላት፣ ትከናነበው አማራት፡፡ | ሀ. የዘመድ ቁስ እየፈታ ያለቅሳል፡፡ |
| 2. ቅርብ ያለ ጠበል፣ ልጥ ይነከርበታል፡፡ | ለ. ያልተነካ ግልግል ያውቃል፡፡ |
| 3. ሽል ከሆነ ይገፋል፣ ቂጣ ከሆነ ይጠፋል፡፡ | ሐ. ያልተገላበጠ ያራል፡፡ |
| 4. ኮሶ ላልቀመሰው፣ ይመር አይመስለው፡፡ | መ. አባቷን አታውቅ፣ አያቷን ትናፍቅ፡፡ |
| 5. የዘመድ ዘመድ፣ ወንዝ ያሻግራል፡፡ | ሠ. የጨነቀው እርጉዝ ያገባል፣ |
| 6. እልፍ ቢሉ፣ እልፍ ይገኛል፡፡ | ረ. በእጅ ያለወርቅ እንደመዳብ ይቆጠራል፡፡ |
| | ሰ. እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል፡፡ |
| | ሸ. ምንም ቢከፋ ዘመድ፣ ምንም ቢጠብ መንገድ፡፡ |

**፱. ለሚከተሉት ፈሊጦች ከተሰጡት አማራጮች በፍች ይበልጥ የሚስማማውን ፈሊጣዊ አነጋገር ምረጡ።**

1. **እጢው ዱብ አለ፤**
   ሀ. እቀልቡ ገባ ሐ. ቀላድ ጣለ
   ለ. ውቃቢ ራቀው መ. ቀልቡ ወደደው
2. **ሆዱ ሻከረ፤**
   ሀ. ሆዱ ጎሸ ሐ. ሆደ ሰፊ
   ለ. ሆደ ባሻ ሆነ መ. ሆድ ሰጠ
3. **ሆደ ቡቡ፤**
   ሀ. አንጀት የራቀው ሐ. እናት አንጀት
   ለ. አንጀታም መ. አንጀተ ጥኑ
4. **እንባ አድርቅ፤**
   ሀ. ማጽናኛ ሐ. ደረቅ ምች
   ለ. ደረቅ ጣቢያ መ. ለዛ ቢስ
5. **ልበ ድፍን፤**
   ሀ. ድንጋይ ራስ ሐ. ድንጋይ በግሩ
   ለ. ድንጋይ ኳሱ መ. ክቡር ድንጋይ

**፲. በ«ሀ» ስር የተዘረዘሩትን ምሳሌአዊ ንግግሮች በ«ለ» ስር ከቀረቡት በፍች ተቃራኒ ከሆኑ ምሳሌያዊ ንግግሮች ጋር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ዝምባለ አፍ፤ ዝምብ አይገባም። | ሀ. ያልጠረጠ፣ ተመነጠረ። |
| 2. ለድካም የጣፈኝ፣ ብነግድ አይተርፈኝ። | ለ. አትሩጥ፣ አንጋጥ። |
| 3. ያገር ልጅ፣ የማር እጅ። | ሐ. ለሰው የማይል ሰው፣ ሞት ሲያንሰው |
| 4. ለሰው ብሎ መሞት፣ አምላክነት ያሻል። | መ. ያልጠሩት ሠርገኛ በትረኛ። |
| 5. የማይተማመን ባልንጀራ፣ በየወንዙ ይማማላል። | ሠ. ካለመናር ደጃዝማችነት ይቀራል። |
| | ረ. ከአብሮ አደግህ ጋር አብረህ አትሰደድ። |
| | ሰ. አትረፍ ያለው በሬ፣ ቆዳው ከበሮ ይሆናል። |

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የስኬት ምንነትና ለስኬት የሚያበቁ ነገሮችን በታዋቂው የሬዲዮ ጋዜጠኛ በታደሰ ሙሉነህ የስኬት ጉዞ መነሻ ተመልክተናል፡፡ በዚህም የምንፈልገውን በመሆን ስኬትን ለመጨበጥ ዕቅድ ማውጣት፣ ዕቅዳችንን ተግባራዊ ማድረግና የሚያጋጥሙንን መሰናክሎች ሁሉ በጽናት ታግለን ማሸነፍ እንደሚጠበቅብን ተገንዝበናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የዱብዳ ንግግር ለማድረግ የሚስችሉ ጠቃሚ ነጥቦችን ተረድተን የዱብዳ ንግግር ማድረግ ችለናል፡፡ በዕለት ተዕለት የተግባቦት ሂደት እንብዛም ሳልተዘወተሩ አዳዲስ ቃላት መዝገበ ቃላትን አገላብጠን ቀጥተኛ ፍቻቸውን ሰጥተናል፡፡ ከመገናኛ ብዙሃን የሰማናቸውንና ያነበብባቸውን እንዲሁም በዐይናችን የተመለከትናቸውን የስኬት ታሪኮች አስታውሰን መናገር ችለናል፡፡ የውይይት መመሪያን ተከትለን ለስኬት በሚያበቁ ዋና ዋና የሕይወት መርሆችና መንገዶች ዙሪያ ውይይት አካሂደን የደረስንበትን መደምደሚያ ዘግበናል፡፡ በግለ-ታሪክና በሕይወት ታሪክ (የሌላ ሰው የሕይወት ታሪክ)መሀል ያለውን ልዩነት አብራርተናል፡፡ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች መረጃን በመሰብሰብና ቃለ-መጠይቅ በማድረግ የምንፈልገውን ሰው የሕይወት ታሪክ ጽፈናል፡፡

በመጨረሻም የአህጽሮተ ጽሑፍ መመሪያን በመከተል የቀረበልንን ጽሑፍ በሲሶ አሳጥረናል፡፡ ለምሳሌያዊ ንግግሮች ተመሳሳይና ተቃራኒ ምሳሌያዊ ንግግሮችን መስጠት ችለናል፡፡ ለቀረቡልን ፈሊጣዊ አነጋገሮችም ተመሳሳይ የሚሆኑ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን መርጠናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

፩. እናንተ አስራ አንደኛ ክፍል እስክትደርሱ በተለያዩ ስኬቶች ውስጥ አልፋችኋል፡፡ ስኬቶቻችሁን ባጭሩ ከጻፋችሁ በኋላ ለስኬት ያበቋችሁ ነገሮች ምን ምን እንደነበሩ ግለጹ፡፡

፪. በህይወታችሁ ያቀዳችሁት ባለመሳካቱ የወደቃችሁበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ ይህንኑ ባጭሩ በጽሑፍ ካሰፈራችሁ በኋላ፣

1. ለውድቀት ያበቋችሁ እንቅፋቶች ምን ምን እንደነበሩ ዘርዝሩ፤
2. ከውድቀታችሁ መማር የቻላችሁትን ቁም ነገር ግለጹ፡፡

፫. ወደፊት ስኬታማ ለመሆን ምን ይጠበቅብናል ብላችሁ ታስባለችሁ?

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ቀጥሎ በዚህ ምዕራፍ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት፣ በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ከመረጃ ምንጮች ያዳመጥኩትን ሃሳብ በራሴ አባባል ገልጫለሁ፡፡ | | | |
| 2 | በተሰጠኝ ርዕስ የዱብዳ ንግግር አድርጌያለሁ፡፡ | | | |
| 3 | ሐሳቦችን በመረጃ አስደግፌ አወዳድሬያለሁ፡፡ | | | |
| 4 | ርዕስ ጠብቄና የውይይት ሥርዓትን ተከትዬ ተወያይቻለሁ፡፡ | | | |
| 5 | የቃለ-መጠይቅ አዘገጃጀት መመሪያን ተከትዬ ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ መረጃ ሰብስቤያለሁ፡፡ | | | |
| 6 | በተሰጠኝ ርዕስ ላይ የቃለ-መጠይቅ ቅጽ አዘጋጅቻለሁ፡፡ | | | |
| 7 | ከመረጃ ጽሑፎችና ከቃለ-መጠይቅ ያገኘኋቸውን ሐሳቦች ተጠቅሜ፣ የሕይወት ታሪክ ጽፌያለሁ፡፡ | | | |
| 8 | ለምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ተመሳሳይና ተቃራኒ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን መርጫለሁ፡፡ | | | |
| 9 | ለፈሊጣዊ አነጋገሮች ተመሳሳይ የሆኑ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ለይቼ አመልክቻለሁ፡፡ | | | |
| 10 | መመሪያን ተከትዬ የቀረበልኝን ጽሑፍ በማሳጠር አቅርቤያለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ (?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ አስር

# ኪነጥበብ

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡- ተማሪዎች! ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- ✓ የድራማን ምንነት ታስረዳላችሁ፡፡
- ✓ የድራማን ሙያዊ ቃላት በመጠቀም ስለድራማ ትናገራላችሁ፡፡
- ✓ ድራማ ከሌሎች የስነጽሑፍ ዘርፎች ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ ድራማን ትተውናላችሁ፡፡
- ✓ የዕለት ተዕለት የሕይወት ገጠመኞችሁን በማስታወሻ ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ የቃል ክፍሎችን ሙያ ከዓረፍተነገሮች ውስጥ ለይታችሁ ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ ከመገናኛ ብዙሃን የሚተላለፉ ድራማዎችን ተከታትላችሁ መልዕክቱን ታስረዳላችሁ፡፡
- ✓ ሐሳባችሁን በመረጃ በማዳበር ትገልፃላችሁ፡፡

## መነሻ የመወያያ ነጥቦች

1. ድራማ ተመልክታችሁ ታውቃላችሁ? መልሳችሁ "አዎን" ከሆነ ምን የተሰኘ? በማን የተዘጋጀ? የት የታየና የድራማው ጭብጥ ምን እንደነበር ተናገሩ።
2. ድራማ፣ ተውኔት፣ ቲአትር በሚሉ ቃላት መካከል ያለው የፍች ልዩነት ምንድን ነው?
3. ቀጥሎ "ድራማ" በሚል ርዕስ አንድ ምንባብ ቀርቦላችኋል። ከርዕሱ ተነስታችሁ ምን ምን ፍሬ ሐሳቦችን ይዟል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

# ድራማ

***ድራማ (ተውኔት)፣*** በመድረክ የሚቀርብና የሚተረጎም የኪነጥበብ ውጤት ነው። ኪነጥበብ ስነጽሑፍን፣ ስነስዕልን፣ ሙዚቃን፣ ቅርጻቅርጽንና የፊልም ጥበብን ያጠቃልላል። ድራማ የሚለው ቃል የተገኘው ድርይን (Draen) ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን፣ ትርጉሙም "ማድረግ" ወይም "መከወን" እንደማለት ነው። የድራማ ምንነትን ታላቁ ፈላስፋ አሪስቶትል ሲገልጽ ‹‹ድራማ ከሰው ልጆች እውነተኛ ድርጊት የሚከተብ የኪነጥበብ ዘርፍ ነው›› ይለዋል።

ድራማ በውስጡ ከሚይዛቸው አላባዎች አንዱ ከሥነጽሑፍ ይመደባል። ሥነጽሑፍ ደግሞ፣ የተጻፈውን ሥነጽሑፍና ያልተጻፈውን ነገር ግን፣ በቃል ከትውልድ ትውልድ የሚሸጋገረውን ይጠቀልላል። ድራማም ጽሑፈ ድራማ (እስክሪፕት) ያለው ወይም የሌለው ሊሆን ይችላል። በባሕላዊ ክንዋኔዎች ላይ ተመስርቶ በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ የሚቀርብ ድራማ ጽሑፍ የሌለው ሲሆን፣ ትውፊታዊ ድራማ በመባል ይታወቃል። ስክሪፕት ያለው ድራማ ደግሞ ጽሑፋዊ ድራማ ሲባል፣ ምድቡም ከተጻፈው ሥነጽሑፍ ጎራ ነው። ድራማ፣ ብዙ ጥበቦች በአንድ ላይ አብረው የሚገኙበት የጥበቦች መናኸሪያ ነው። ሙዚቀኛው፣ ሰዓሊው፣ ጸሐፊ ተውኔቱ፣ መራሄ ተውኔቱ (አዘጋጁ)፣ የመብራትና የድምጽ ባለሙያው... ባንድ ላይ ጥበቡን አዋጥቶ ድራማን ከየአቅጣጫ

ይከሽነዋል፡፡ የድራማ ተመልካቹም፣ ድራማን ተመልክቶ ለማጣጣም የተለየ እውቀት አያስፈልገውም፤ ያለፈበት የሕይወት ልምዱ በቂ ነው፡፡

የድራማ ጥበብ የራሱ የሆኑ ሙያዊ ጽንሰሐሳቦችና ስያሜዎች አሉት፡፡ ከስያሜዎቹ መካከል የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡


***ጸሐፌ ተውኔት፡-*** የድራማ ጥበብ የአያሌ ሰዎችን ድካም የሚጠይቅ ቢሆንም፣ የድራማውን መሠረታዊ መልክ የሚነድፈው ደራሲ ፀሐፌ ተውኔት ይባላል፡፡

***ቃለ ተውኔት፡-*** በድራማ ውስጥ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ገፀባህሪያት ወይም እነሱን ተክተው በሚጫወቱ ተዋንያን መካከል የሚደረግ ንግግር ቃለ ተውኔት ወይም የተውኔት ቋንቋ በመባል ይታወቃል፡፡ ታዋቂው የሐገራችን ፀሐፌ ደበበ ሰይፉ "የትያትር ጥበብ ከፀሐፌ ተውኔቱ አንፃር" በሚለው መጽሐፉ ይህንኑ ሲያስረዳ፣ ፀሐፌ ተውኔቱ የሚጽፈው በተዋንያን አማካይነት እንዲሰማለት እንደመሆኑ መጠን ቃለ ተውኔት ቁጥብና ግለጽ ሆኖ መጻፍ እንዳለበት አጥብቆ ይመክራል፡፡ ቃለ ተውኔት፣ የገፀባህሪያትን አካላዊና ሕሊናዊ መልክ ለመጠቆም፣ በተውኔቱ ድርጊት ውስጥ መውጣትና መግባትን ለማመልከትና የመድረክ ቁሳቁሶችና አልባሳት ምን መምሰል እንዳለባቸው ለማስታወቅ በፀሐፌ ተውኔቱ የሚሰጠውን ገለፃ አይጨምርም፡፡


***ተዋንያን፡-*** በጸሐፌ ተውኔቱ ድራማው ከተጻፈ በኋላ በውስጡ ያሉትን ገፀባህሪያት ስብዕና፣ ውስጣዊ አስተሳሰብና ማንነት የራሳቸው አድርገው በመድረክ ላይ የሚተውኑ የጥበብ ሰዎች ናቸው፡፡

***የተውኔት መዋቅር፡-*** ስለተውኔት መዋቅር ፋንታሁን እንግዳ ‹‹የተውኔት ድርሰት አጻጻፍ ዘዴ›› በሚለው መጽሐፉ እንደገለፀው፣ የተውኔት አላባውያን (መቼት፣ ሴራ፣ ቃለ ተውኔትና፣ ጭብጥ) በተገቢው መንገድ ተዋህደው ሲቀርቡ የሚገኘው ቅርጽ የተውኔት መዋቅር እንደሚባል ያስረዳል፡፡ ማንኛውም በጥሩ ግጭት መሠረት ላይ የተጻፈ ተውኔት

ሦስት ዓበይትና አምስት ንዑሳን ክፍሎች እንዳሉት እንደሚከተለው ያብራራል፡፡
ሦስቱ ክፍሎች (ውጠት፣ ጡዘት፣ ዝቅጠት)




አምስቱ ንዑሳን ክፍሎች (እውቂያ፣ ትውስብ፣ ጡዘት፣ ቅልበሳና ልቀት)




በሁለቱ ፒራሚዶች እንደሚታየው ሦስቱ ክፍሎች (ውጠት + ጡዘት + ዝቅጠት) የመጀመሪያ የመካከለኛና የመጨረሻ የመዋቅር ክፍሎችን ያመለክታሉ፡፡ በመጀመሪያው የውጠት ደረጃ ገፀባህሪያቱ፣ አጠቃላይና ውስን መቼቱ፣ ግጭቱ ርዕሰ ጉዳዩና ድባቡ የሚተዋወቁበት ነው፡፡ ከመስተጋብራቸው የሚመነጨው ግጭት ቀስ በቀስ ያድግና ይጦዛል፡፡ ከዚያ ግጭቱ ወደመፍትሄ ይሸጋገራል (ቅልበሳ ይካሄዳል)፡፡ በመጨረሻም ፍፃሜው (ልቀቱ) ይከሰታል፡፡ በዚህ ዓይነት ድራማው የዝቅጠት ደረጃን ያጠናቅቃል (ይፈፀማል)፡፡

ቀደም ሲል በምዕራፍ ሦስት፣ አራትና ስድስት የተመለከትናቸው የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶች (ወግ፣ ልቦለድ፣ ግጥም) እና አሁን የያዝነው ርዕስ (ድራማ) ከመዋቅራቸው አንፃር ሲነፃፀሩ የአንደኛው ከሌላው የተለየ ነው፡፡ የአንዱ የፈጠራ ሥራ መዋቅር ከሌላው እንዲለይ ምክንያት የሆኑ ነገሮች ብዙ ቢሆኑም፣ የድርጊቶች አገላለጽ፣ የሴራ አወቃቀር፣

የገፀባህሪያትና የመቼት ገለፃ እንደየስነጽሑፍ ዓይነቱ የተለየ ባህሪ ያለው መሆኑ ዋነኛው ነው፡፡

ጸሐፌ ተውኔቱ በድራማው አንድን ድርጊት፣ ገፀባህሪ፣ መቼት በስፋት ሳይሆን በቁጥብነት ይገልፀዋል፡፡ የልቦለድ ደራሲ ግን በቂ ጊዜና ቦታ ስላለው በሴራው አወሳሰን፣ በገፀባህርያት እውቂያና አሰረጫጨት፣ በመቼት ገለፃ የተሻለ ነፃነት አለው፡፡ ይህም ሲባል፣ ገፀባህሪያቱን በስፋትና በጥልቀት የመሳል፣ ብዙ መልክኣ ምድራዊ አቀማመጦችን በመቼት ቀረፃው የማካተት እድል ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ በዚህ የተነሣ የልቦለድ መዋቅር ከድራማ መዋቅር ይለያል፡፡ እንደ ድራማና ልቦለድ መዋቅር ሁሉ የግጥም፣ የወግ፣ ያጭር ልቦለድ መዋቅሮችም ከድራማ መዋቅር የተለዩ ናቸው፡፡

***ገቢር፡-*** የድራማ ዓቢይ ክፍል ነው፡፡ ድራማ በገቢር ተከፋፍሎ ሲቀርብ ከአንዱ ገቢር ወደሌላው ገቢር የሚደረገው ሽግግር ብዙውን ጊዜ መጋረጃ በመጣል ወይም መብራት በማጥፋት ይከናወናል፡፡ መጋረጃ የመጣሉና መብራት የማጥፋቱ አላማም በድራማዊ ድርጊቱ ውስጥ የቦታ ወይም የጊዜ አለያም የሁለቱም ለውጥ መደረጉን ለተደራሲያን ለማሳወቅ ነው፡፡

***ትዕይንት፡-*** የገቢር ንዑስ ክፍል ሆኖ አከፋፈሉ እንደገቢር የድራማው ድርጊት የሚፈፀምበት ጊዜ ወይም ቦታ መለወጡን አያመለክትም፡፡ በትዕይንት አከፋፈል ላይ ወጥ የሆነ ጸሐፌ ተውኔቶችና ሀያሲያን የሚከተሉት አሰራር የለም፡፡ አንዳንዶች ገፀባህሪያት በተውኔቱ ታሪክ ውስጥ የሚጫወቱትን ሚና ለመጀመር ወደድርጊቱ መጥተው ሲጨመሩ የትዕይንት ሽግግር (ለውጥ) ያደረጋል ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ አንድ ትዕይንት አልቆ ሌላ ትዕይንት ተጀመረ የሚያስብለው በመድረክ በመከናወን ላይ ያለው ድራማዊ ድርጊት አልቆ መድረኩ ለቀጣዩ ድራማዊ ድርጊት በፀዳ ጊዜ ነው ይላሉ፡፡ ያም ሆነ ይህ ትዕይንት የመጋረጃ መዘጋት የማያስፈልገው አንድ የተውኔት ንዑስ ክፍል ነው ማለት ይቻላል፡፡

**መነባንብ:-** የገፀባህሪውን ስውር ሕሊናዊ መልክ ለተደራሲ ለማሳየት ሲባል፣ ያ ገፀባህሪ በዙሪያው ሌሎች ገፀባህሪያት በሌሉበት ጊዜ ለራሱና ለተደራሲ የሚያነበንበው የግል ንግግር ነው፡፡

**ጎንታ:-** እንደመነባንብ የብቻ ንግግር ሆኖ እውነተኛውን ነገር ግን ለሌላው ገፀባህሪ ድብቅ የሆነው ፍላጎት የሚገለጽበት ነው፡፡ ጎንታ ተናጋሪው በመድረክ ላይ አብረውት ያሉት አንድ ወይም ከአንድ በላይ ገፀባህሪያት እንደማይሰሙ አድርጎ በመቁጠር ለራሱና ለተደራሲያን እንደሁኔታው በሹክሹክታ አለያም ፊቱን ወደ ተደራሲ በማድረግ ከፍ ባለ ድምጽ የሚናገረው የብቻ ንግግር ነው፡፡

ከዚህ በላይ በተነሱ ሀሣቦች አማካይነት የድራማን ጥበብ በመጠኑም ቢሆን እንደተረዳችሁ እንገምታለን፡፡ ለበለጠ ግንዛቤ በድራማ ዙሪያ የተጻፉ መጻሕፍትን በማንበብና በጥበቡ ቀጥተኛ ተሳታፊ በመሆን እውቀታችሁን ማዳበር እንደምትችሉ በመጠቆም እዚህ ላይ እንቋጫለን፡፡

## ክፍል አንድ:- አንብቦ መረዳት

**፩. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. ድራማ የሚለው ቃል በተገኘበት ድርይን (Draen) በሚለው የግሪክ ቃል ፍችና ዛሬ ድራማ በምንለው ኪነጥበብ መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?
2. ‹‹ድራማ ከሰው ልጆች እውነተኛ ድርጊት የሚከተብ የኪነጥበብ ዘርፍ ነው›› ሲል ምን ማለቱ ነው?
3. የድራማ ተመልካች፣ ድራማን ተመልክቶ ለማጣጣም የተለየ እውቀት ባለቤት እንዲሆን የማይጠበቀው ለምንድን ነው?
4. ተዋንያን በድራማ ውስጥ ያሉ ገፀባህርያትን ስብዕና፣ ውስጣዊ አስተሳሰብና ማንነት እንዴት የራሳቸው ማድረግ ይችላሉ?

5. በድራማ ውስጥ ከገፀባህሪያቱ መስተጋብር የሚመነጨው ግጭት ተፀንሶ ትውስብ ደረጃ ከደረሰ በኋላ የሚያልፍባቸውን ቀሪ ደረጃዎች ግለጹ፡፡

**፪. የሚከተሉት ከምንባቡ የወጡ ሐረጎች የያዙትን ፍች በቃል አብራሩ፡፡**

1. የጥበቦች መናኸሪያ
2. ጽሑፋዊ ድራማ
3. ትውፊታዊ ድራማ
4. መራሔ ተውኔት
5. ከየአቅጣጫው ይከሽነዋል
6. የመድረክ ድባብ
7. የመድረክ ትወና

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

**፩. በቡድን ሆናችሁ፡-**

1. "ድራማ" በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ መልዕክት ላይ ተወያይታችሁ የምንባቡን አጠቃላይ መልዕክት በመለየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
2. በድራማ ምንነት፣ ከሌሎች የሥነጽሑፍ ዘርፎች ባለው ግንኙነትና ልዩነት ላይ ከተወያያችሁ በኋላ፣ የደረሳችሁበትን በተወካያችሁ አማካኝነት የቃል ማብራሪያ ስጡ፡፡

**፪. በመገናኛ ብዙሃን (በሬድዮና በቴሌቪዥን) ከሚተላለፉና ከምትከታተሏቸው ድራማዎች አንዱን መርጣችሁ ድራማው በሚያስተላልፈው መልዕክት ዙሪያ የሦስት ደቂቃ ገለጻ ስጡ፡፡**

## ክፍል ሦስት፡- መጻፍ

፩. ማንኛውም ሰው በየዕለቱ በተለያዩ ገጠመኞች ውስጥ ያልፋል፡፡ አንዳንዶቹ ገጠመኞች ድራማዊ ከመሆናቸው የተነሳ በአእምሮ የማይረሳ ምስል ይተዋሉ፡፡ እስቲ እናንተ ባለፈው ሳምንት የነበሩና እስከያዝነው ሳምንት ማለቂያ ድረስ የሚኖሩ ገጠመኞቻችሁን ተከታትላችሁ በማስታወሻ በመመዝገብ ለተከታዩ ሳምንት ይዛችሁ ቅረቡ፡፡

፪. በጥንድ ሆናችሁ የጻፋችኋቸውን ገጠመኞች በመለዋወጥ ካነበባችሁ በኋላ፣ ከቃላት አጠቃቀሙ ከመልዕክቱ ግልፅነትና ከገጠመኛችሁ መመሳሰል ወይም መለያየት አንፃር ለጓደኛችሁ አስተያየት ስጡ።
፫. ከላይ በተራ ቁጥር ሁለት የነበራችሁ ሁለት ጥንዶች እየተጣመራችሁ አንድ ቡድን በመመስረት ከጻፋችኋቸው ገጠመኞች ውስጥ አንድ ገጠመኝ ምረጡ።
፬. በመረጣችሁት ገጠመኝ ላይ ተመስርታችሁ አንድ ጭውውት በጽሑፍ ካዘጋጃችሁ በኋላ፣ መምህራችሁ በሚነግሯችሁ ቀን ጭውውቱን አጥንታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።
፭. የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን (መጻሕፍት፣ ሬድዮ፣ ቴሌቪዥን፣ አውደጥበብ፣ ቃለ መጠይቅ...) ተጠቅማችሁ ስለ ኪነጥበብና ድራማ ምንነትና ግንኙነት ያገኛችሁትን ሐሳብ በማጠናቀር ከሁለት ገጽ ያልበለጠ ጽሑፍ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

## ክፍል አራት:- ሥነልሳን

፩. በቡድን ሆናችሁ በመወያየት በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉ የቃል ክፍሎችን ሙያ በምሳሌው መሠረት ከዘረዘራችሁ በኋላ፣ በቡድን መሪያችሁ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ማብራሪያ ስጡ።

**ምሳሌ:-** ወ/ሮ አልማዝ የአቶ ከበደ ባለቤት በጣም ታጋሽ ናቸው።

| ቃል/ሐረግ | ሙያ |
|---|---|
| ወ/ሮ አልማዝ | የዓረፍተነገሩ ባለቤት |
| የአቶ ከበደ ባለቤት | የባለቤት ተጣማሪ |
| በጣም ታጋሽ | የማሰሪያ አንቀጹ መሙያ |
| ናቸው | ማሰሪያ አንቀጽ |

1. የኛ ፈረቃ አስተባባሪ ታታሪ ናቸው።
2. አቶ አየለ መኪናውን ለማይታወቅ ሰው ሸጠ።
3. ገበያው ደራ።
4. ትምህርት ቤቱ ለሥነጽሑፍ ክበብ ገንዘብ መደበ።

5. ዶ/ር ከበደ፣ የኛ ሠፈሩ ሐኪም፣ ለወላጆቹ ትልቅ ሙክት ገዛ፡፡
6. የሂሳብ መምህራችን የቤት ሥራ ያልሰሩትን ተማሪዎች አንበረከኳቸው፡፡

## ክፍል አምስት፣ ሥነጽሑፍ

**ሀ. እያንዳንዳቸው ሁለት ወንዶችና አንዲት ሴት በአባልነት የሚያቀፉ ቡድኖችን ከመሠረታችሁ በኋላ፣ ከዚህ በታች የቀረበውን አጭር ተውኔት በማጥናት በተከታዩ ክፍለ ጊዜ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተውኑላቸው!**

### ጭንቀት የወለደው ቆራጥነት፡፡

*ከአበበ ወርቄ፡፡*

***(ልጅ፣ አባትና እናት በመንገድ ላይ ሲሄዱ ይታያሉ፡፡ ልብሳቸው ዘባተሎ ነው፡፡)***

"ትሁኔ" ብሎ አባትየው ተጣራ፡፡

"አቤት!" አለችው፡፡

"የእኔና የአንቺ አብሮ መኖር ይገርመኛል፡፡"

"እንዴት?"

"ባልና ሚስት ሊኖሩ የሚገባቸው ሲኖራቸው ነው፡፡"

"እሺ!"

"እኔ አንዲት ነገር የለኝ፡፡"

"ታዲያስ?"

"ስለዚህ በምኔ ላኑርሽ?"

"እስከዛሬ በምን አኖርሽኝ?"

"እስከዛሬ በምን አኖርሽኝ! እስከ ዛሬ በምን አኖርሽኝ !"

እስከዛሬ ያኖረሽ መለኮት ነው፤ እኔ አይደለሁም፡፡"

"እንግዲያስ እስከዛሬ ያኖረኝ መለኮት ወደፊት ሊያኖረኝ አይችልም?"

"በቃ! ይህ ጥያቄሽ መልስ አይኖረውም፡፡"

"ለምን? ፈጣሪ መኖሩን ትክዳለህ? ይህን ታደርግ እንደሆነ እስከዛሬም ካንተ ጋር በመኖሬ ልማረር ይገባኛል፡፡"

“ይህስ አይደለም፤ እንዲህ ያለ ሐሳብ በኔ ዘንድ ቦታ አይሰጠውም፡፡ አንቺ ግን ብዙ በመጠየቅ አታሰልቺኝ፡፡ ልናገረው የምፈልገው ብዙ ቢሆን ልናገረው የምችለው ጥቂት ነው፡፡”

“ምን ሆንህብኝ? ዛሬ እንደዚህ የሚያናግርህ ምንድነው? ልትናገረው የምትፈልገውና ልትናገር የምትችለው እንደምን እኩል አይደሉም? ለምንስ አይሆኑም?”

“በቃ ይህ ጥያቄሽ መልስ አይኖረውም፡፡”

“ግሩም! የምትናገረው በፍፁም አልገባኝም፡፡ አሁን እመንገድ ላይ ስንጨቃጨቅ የሚሰማን ሁሉ ዕብዶች ናቸው ይለናል፡፡ ቢተው! እንዲያውም ስመለከትህ ዛሬ ደህና አይደለህም፡፡ ስለዚህ ሐሳብህን እቤት እስክንደርስ ልታቆየው አትችልም?”

“አልችልም፡፡ አልችልም፡፡ እኔ ዕብድ አይደለሁም፡፡ ስለዚህ ያላበድሁት ሰው ‘ሰው ዕብድ ይለኛል’ ብዬ ፍርሃት በልቤ አላሳድርም፡፡ ቤትም ስለምትይው፣ ቤት ከዛሬ ወዲያ የለኝም፡፡ ቤቱ ለኔ አይደለም፡፡ እኔም ለቤቱ አይደለሁም?”

***(ይህ ሁሉ ሲሆን ልጃቸው ተስፋዬ ቆሞ ያዳምጥ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ግን የመደንገጥ መንፈሱ ወደ ድፍረት ተለውጦ ወደ አባቱ በመጠጋት፤)***

“አባባ፤ ዛሬ ምን ነክቶሃል?”

***(ብሎ ሲያቅፈው አባቱ ልጁን ከአንገቱ ላይ አስለቅቆ ራቅ ብሎ ይቆማል፡፡ ወዲያውም)***

“አትጠጋኝ ተስፋዬ፤ ማን ነኝና ትጠጋኛለህ?”

“አባባ፣ እኔ አንተን እንዳጣህ ነው ማንነትህን የምትጠይቀኝ?”

“አንተ የምታውቀኝ በቢተውነቴ ብቻ ነው በሌላ በምንም አታውቀኝም፡፡”

“በቢተውነትህ የሚያውቁህ ሁሉ የእኔ የተስፋዬ አባት በመሆንህም ጭምር ያውቁሃል፡፡ ስለዚህ እኔም የማውቅህ በቢተውነትህ ብቻ ሳይሆን አባቴ በመሆንህም ጭምር ነው፡፡ እማማ፣ የተሳሳትሁ ይመስልሻል?”

“በቃ፤ ለዚህ ጥያቄህ መልስ እንድትሰጥህ አይፈቀድም፡፡ ስሚ ትሁኔ፣ በቅድሚያ ልነግርሽ የፈለግሁት ከዛሬ ወዲያ ባልሽ እንዳልሆንሁ ነው፡፡ እኔን ያገባሽ ጊዜ ከችግር መጋባትሽን አላወቅሽም ነበር፡፡

ባለማወቅሽ እስከ ዛሬ ተጎዳሽ ፡፡ ዛሬ ግን እኔ ስፈታሽ ችግርም አብሮኝ እንደሚፈታሽ ስለተማመንሁ፤ ፈትቸሻለሁ፡፡”

“አባባ፤ ምን ሆነሃ- “ ***(የጀመረውን ዓረፍተነገር ሳይጨርስ)***

“ተራህን ጠብቅ፤ ላንተም ልሰጥህ የሚገባህን አልነሳህም፡፡”

“ቢተው ምን አልህ? ምን አልህ? አልገባኝም፡፡”

“ሌላ ትርፍ ጥያቄ አትጠይቂኝም?”

“አልጠይቅህም፡፡”

“እንግዲያውስ በቀላል አነጋገር ከዛሬ ጀምሮ ባልሽ አይደለሁም ነው ያልሁሽ፡፡”

***(በድንጋጤ ብዛት የምታደርገውን አጥታ ቁጭ ትላለች)***

“አባባ፤ ስማ አባባ -”

***(መልሱ ትንሽ ይዘገያል፡፡)***

“እባክህ ተወኝ፡፡ የኔ አባትነት ያቆየህ የችግርና የሥቃይ ኑሮ ነው፡፡ የኔ አባትነት አንተን በምንም አልጠቀመህም፡፡ ስለዚህ አባባ፣ አባባ ስትለኝ ብትኖር ምንም ጥቅም አታገኝም፡፡ ይህን የደረቀ ሰውነት ይዘህ ለመታየት የበቃኸው ከእኔ በመወለድህና የኔ ልጅ በመሆንህ ነው፡፡ ፀሐይ ብርሃኗን ካልነፈገችው ተወልደህ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ጭለማ ባልለበስህ ነበር፡፡ የእናትህ እናትነት ያልተዛነፈ ነው፡፡ በእሷ እናትነት ጥፋት አላየሁባትም፡፡ የሰጠኋትን ወደ ጐኗ አላለችም፡፡”

“አባባ፣ ካንተ በመፈጠሬ እኔ አላማረርሁም፤ ከምትበላው አያበላህ፣ ከመንጋጋህ እያላቀቅህ፣ እያካፈልህ አሳድገኸኛል፡፡ እንደምን ምንም አላደረኩልህም ትለኛለህ? የሌለህን አትስጠኝ እንጂ፣ ያለህን አልነፈግኸኝም፡፡”

“በቃ ተስፋዬ፣ ብዙ ብናገር ብዙ አሳዝንሃለሁ፡፡ ስለዚህ ንግግሬን ለማሳጠር ያህል፣ አስቀድሜ ያሰብሁት ነገር ስለሆነ፣ ሐሳቤን ስለማልለውጠው፣ ከዛሬ ወዲያ አባትህ አይደለሁም፡፡ ይህ ትንሽ ግር ይል ይሆናል፡፡ ሊልም ይገባል፤ የተለመደ አይደለም፡፡ ልጄ በድሎኛልና ከዛሬ ወዲያ ልጄ አይደለም አላልሁም፡፡ በድየሃለሁና

አባትህ አይደለሁም ነው፣ ያልሁህ፡፡ በቃ! ደህና ሁን፡፡ ደህና ሁኚ ትሁኔ፡፡ ደኅና ሁኑ!”

***(ልጁ ዘልሎ ይደዘዋል አባትዬው ከልጁ ለመሳቀቅ ሲል ሲገፋው ልጁ ተንገዳግዶ እናቱ አጠገብ ይቆማል፡፡)***

“አባባ፣ እንደምን ልጅህን በእንደዚህ ያለ ሁናቴ የትም ጥለህ ትሄዳለህ? አባባ እኔ ተስፋዬ አይደለሁም እንዴ?”

“ነህ፡፡ ልጄ ግን አይደለህም፡፡”

***(ብሎ እናትና ልጁን በእንደዚህ ያለ ባሳሰቡት ሁናቴ ልክ እንደሰከረ ሰው ጥሏቸው ሄደ፡፡ ለጥቂት ሲኮንደች ያህል ተፋጠው ቁጭ ብለው ከቆዩ በኋላ እናት ንግግር ትጀምራለች)***

“ልጄ ምን ይሻልሃል? የኔ እንኳን ቀላል ነው፡፡ አንተ ግን ያላባት ቀረህ፡፡”

“ምን ያለባት ብቻ! እናትስ የት አለኝ?”

“እኔ፣ የኔ ልጅ መሆንህን አልካድሁም፡፡ እናትህ እኔ ነኝ፡፡ እስከዛሬ አባትህ ቢተው ነበር፤ ዛሬ አባት አጣህ እንጂ፡፡ እናትህ ምን አልሁህ? እናትህ እኔ ትሁኔ ነኝ፡፡ ዘጠኝ ወር አርግዤ፣ በስቃይና በሕማም ተገላግዬ፣ ሦስት ዓመት ታቅፌ፣ ተሸክሜ፣ አዝዬ፣ አንቆራጥጬ፣ ተርቤ አብልቼ፣ ተጠምቼ አጠጥቼ፣ ከአከላትህ አንዲቷን እንኳን ሳላስነካ ያሳደግሁህና እዚህ ያደረስሁህ እናትህ እኔ ነኝ፡፡”

“እማማ፣ ተጠራጠጥሬሽ እኮ ነው! ዛሬ አባቴን አጣሁ፤ ነገ ደግሞ አንችን ላለማጣቴ ምን መተማመኛ አለኝ?”

“እንዴት፣ ተስፋዬ አባትህ የችግርና የስቃይ ኑሮ መሮት፣ ጉስቁልናችን ቆጥቁጦት ቢለየን፣ እኔ ለችግርና ለመከራ የምንበረከክ እንዳይመስልህ፡፡ አንተ እስክታድግልኝ ጉልበቴን ሳልቆጥብ፣ ሥራ ሳልመርጥ፣ ላይ ታች ብየ በማገኘው ገንዘብ እንተዳደራለን፡፡ አንተ ስትደርስልኝ ደግሞ ማን ያውቃል? ከዚህ ኑሮዬ ታላቅቀኛለህ ይሆናል፡፡ አይደል?”

“አዎ! እማማ፣ ቶሎ አድጋለሁ፤ ደግሞ ትልቅ ስሆን አሳርፍሻለሁ!...”

***(ስደርስ አሳርፍሻለሁ እያለ ከኋላ ኋላዋ ተከተላት)***

***(እንዲህ ነው፤ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የሥነጽሑፍ መጽሔት፣ 1957፣ 32 በመጠኑ ተሻሽሎ የቀረበ)***

ለ. ከዚህ በላይ በተወናችሁት ድራማ ጭብጥ ላይ ያላችሁን አስተያየት ባጭሩ ግለጹ::

ሐ. በተዋንያኑ የአተዋወን ብቃት ላይ አስተያየት ስጡ::

መ. ቢተው ችግር ስላስመረረው ቤተሰቡን መለየቱ ተገቢ ነበር ትላላችሁ? ለምን?

መ. አሁን ያለውን "ጭንቀት የወለደው ቆራጥነት" የሚለውን ርዕስ የሚተካ ሌላ ርዕስ ስጡ::

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የኪነጥበብ ውጤት የሆነውን የድራማን ጥበብ ምንነት፣ ዓይነትና ከሌሎች የኪነጥበብ ሥራዎች የሚለይበትን ባህሪ ተመልክተናል:: ድራማ በውስጡ ከያዛቸው ፍሬ ነገሮች (አላባዎች) አንፃር ሲታይ ምድቡ ከሥነጽሑፍ እንደሆነና እንደስነጽሑፍ ሁሉ የተፃፈና ያልተጻፈ ድራማ እንዳለ ተረድተናል::

የድራማ ጥበብ የራሱ የሆኑ ሙያዊ ጽንሰሐሳቦችና ስያሜዎች እንዳሉት በተመለከትንበት ክፍል፣ ጥበቡን ለመረዳት የሚያስችሉ ዋና ዋና የድራማ ሙያዊ ቃላትን ከተመለከትን በኋላ ስለ ድራማ በተወያየንባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ ተጠቅመንባቸዋል:: ድራማ መዋቅሩ ከሌሎች የሥነጽሑፍ ዘርፎች የተለየ እንደሆነና በድራማ ውስጥ ከገፀባህሪያት መስተጋብር የሚመነጩት ግጭቶች የእውቂያ፣ የትውስብ፣ የጡዘት፣ የቅልበሳና የልቀት ደረጃዎችን እንደሚያልፉ እንዲሁም እነዚህ ደረጃዎች በሦስት ክፍሎች (ውጠት፣ ጡዘትና ዝቅጠት) ተጠቃለው እንደሚታዩ በዝርዝር አይተናል::

በሌላ በኩል፣ በድራማ ምንነትና ከሌሎች የሥነጽሑፍ ዘርፎች ባለው ግንኙነትና ልዩነት ላይ ተወያይተናል:: በመገናኛ ብዙሃን የሚተላለፉ ድራማዎችን አዳምጠን ጭብጣቸውን አብራርተናል:: የየዕለት ገጠመኞቻችንን በመጻፍ ከገጠመኞቻችን የሚነሳ ጭውውት አዘጋጅተን በመማሪያ ክፍላችን ተውነናል:: በዓረፍተነገሮች ውስጥ የቃል ክፍሎችን ሙያ መዘርዘርና ማብራራት ችለናል:: በመጨረሻም “ጭንቀት የወለደው ቆራጥነት በሚል ርዕስ በአበበ ወርቄ የተጻፈ ድራማን በመተወን በጭብጡ ላይ አስተያየት መለዋወጥ እንዲሁም ለድራማው ሌላ ርዕስ መስጠት ችለናል::

## የክለሳ ጥያቄዎች

**ከመጻህፍት፣ ከመጽሄቶችና ጋዜጦች አንድ ጽሑፈ ድራማ (የድራማ ስክሪፕት) ካነበባችሁ በኋላ፣**

1. በድራማው ተሳታፊ ገጸባሕርያትንና ያላቸውን ግንኙነት ዘርዝሩ::
2. ድራማው ምን ያህል ገቢርና ትዕይንት እንዳለው ግለጹ::
3. የድራማውን ግጭት በመለየት የእውቂያ፣የትውስብ፣ የጡዘት፣ የቅልበሳና ልቀት ደረጃዎችን እንዴት እንዳለፈ በዝረዝር አስረዱ::
4. በድራማው ውስጥ መነባንብና ጎንታ ካለ፣ ለይታችሁ የትኛው ገጸባሕሪ ለምን ዓላማ እደተናገረ አብራሩ::

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ቀጥሎ በዚህ ምዕራፍ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል። በዚሁ መሠረት፣ በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ (√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስለድራማ የቀረበውን ጽሑፍ አንብቤ ተረድቻለሁ። | | | |
| 2 | የድራማን ምንነትና ከሌሎች የሥነጽሑፍ ዘርፎች ጋር ያለውን ልዩነት ገልጫለሁ። | | | |
| 3 | በተወንኩትና ከመገናኛ ብዙሃን በተከታተልኩት ድራማ ላይ አስተያየት ሰጥቻለሁ። | | | |
| 4 | ስለድራማ አስተያየት ስሰጥ የድራማን ሙያዊ ቃላት ተጠቅሜያለሁ። | | | |
| 5 | በዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉ የቃል ክፍሎችን ሙያ ለይቻለሁ። | | | |
| 6 | ከመረጃ ምንጮች ሐሳብን አቀናብሬ በመጻፍ አቅርቤያለሁ። | | | |
| 7 | ስለዕለት ተዕለት የሕይወት ገጠመኜ ማስታወሻ መያዝ ችያለሁ። | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ (?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።

# አባሪዎች

## ፩. ተጨማሪ የንባብ መጻሕፍት

### 1. ግጥሞች


መንግሥቱ ለማ (1955) *የግጥም ጉባኤ፡፡* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ሰይፉ መታፈሪያ (1981) *ውስጠት፡፡* አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፡፡

በዕውቀቱ ስዩም (2001) *ስብስብ ግጥሞች (ኗሪ አልባ ጎጆዎች፣ የሳት ዳር ሐሳቦች እና ሌሎች አዳዲስ ግጥሞች)* አዲስ አበባ፣ ፋር-ኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ.የግ.ማህበር፡፡

አረጋሽ ሰይፉና ሌሎች (1990) *እኛ፣ 170 ግጥሞች፡፡* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ደበበ ሰይፉ (1980) *የብርሃን ፍቅር፡፡* አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፡፡

ፀጋዬ ገ/መድህን (1966) *እሳት ወይ አበባ፡፡* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡


### 2. ወጎች


መስፍን ሀብተማርያም (1996-1999) *የቡናቤት ስእሎችና ሌሎች ወጎች ፡፡* አዲስ አበባ፤ ኤማይ ፕሪንተርስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፡፡

________________ (1992) *የሌሊት ድምጾች እና ሌሎች ወጎች፡፡* አዲስ አበባ፤ ሜጋ አሳራሚ ድርጅት፡፡

## 3. ተውኔቶች


መንግሥቱ ለማ (1961) *ጠልፎ በኪሴ።* አዲስ አበባ፣ ቼምበር ማተሚያ ቤት።

___________ (1961) *የተውኔት ጉባኤ።* አዲስ አበባ፣ ተራመድ ማተሚያ ቤት።

ተስፋዬ ገሠሠ (1961) *ዕቃው።* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

ፀጋዬ ገብረመድህን (1958) *የከርሞ ሰው።* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።


## 4. አጫጭር ልቦለዶች


ሰለሞን ለማ (1979) *የእግር እሳትና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች።* አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

አብዱ ራህመቶና ንጉሴ (1979) *ሙሽራው እና ሌሎች አጫጭር ልቦለዶች።* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

አበራ ለማ (1980) *የማለዳ ስንቅ፣ ግጥሞችና አጫጭር ልቦለዶች።* አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

አብዱ ራህመቶና ሌሎች (1980) *አጫጭር ልቦለዶች።* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት (1975) *ጉዞውና ሌሎችም ልቦለዶች።* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

## 5. ረዳጅም ልቦለዶች


ሀዲስ ዓለማየሁ (1958) *ፍቅር እስከ መቃብር።* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

____________ (1980) *የልምዣት።* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

በዓሉ ግርማ (1975) *ሀዲስ።* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ኃይለመለኮት መዋዕል (1982) *ጉንጉን።* አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማረሚያ ቤት።

አስፋው ዳምጤ (1980) *አንድ ለአምስት።* አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

ዳኛቸው ወርቁ (1962) *አደፍርስ።* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።


## ፯. ማጣቀሻ መጻሕፍት


መኩሪያ ወርቁ (1982) *ምሳሌያዊ አነጋገር።* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ማህተመ ስላሴ ወ/መስቀል (1999) አማርኛ ቅኔ ከነፍቻቸው። አዲስ አበባ፣ እሌኒ ማተሚያ ቤት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር።

በድሉ ዋቅጅ (1996) *በስነጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር።* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ባየ ይማም (2002) *አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው።* አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚዎች።

ብርሃኑ ገበየሁ (1999) *የአማርኛ ስነግጥም።* አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚዎች።

ተሰማ ሀ/ሚካኤል (1951) *ከሳቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት።* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

አለም እሸቱ (1992) *መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አጻጻፍ።* አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት።

አማረ ማሞ (1968) *የልብ-ወለድ ድርሰት አጻጻፍ።* አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ መጻህፍት ድርጅት።

__________ (1976) *የቀለም ጠብታ፤ የኢልቦለድ አጻጻፍ።* አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ መጻህፍት ድርጅት።

አምሳሉ አክሊሉና ደምሴ ማናህሎት (1982) ጥሩ ያማርኛ ድርሰት እንዴት ያለ ነው? አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

አምሳሉ አክሊሉና ዳኛቸው ወርቁ (1979) *የአማርኛ ፈሊጦች።* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ዘሪሁን አስፋው (1992) *የስነጽሑፍ መሠረታውያን።* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

የሻው ተሰማ (1996) *ልሳነ ብዕር ከመ ልሳነ ሰብዕ።* አዲስ አበባ ብራና ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል (1993) *አማርኛ መዝገበ ቃላት።* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ደረጀ ገብሬ (1996) *ተግባራዊ የጽሕፈት ማስተማሪያ።* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ደበበ ሰይፉ (1973) *የቲያትር ጥበብ ከጸሐፌ ተውኔቱ አንጻር፡* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ዳኛቸው ወርቁ (1988) *የጽሑፍ ጥበብ መመሪያ።* አዲስ አበባ፣ ሜጋ ህትመት ኢንተርፕራይዝ።

ጌታሁን አማረ (1989) *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ።* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ፈቃደ አዘዘ (1991) የስነቃል *መመሪያ።* አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚዎች።

ፋንታሁን እንግዳ (1992) *የተውኔት አጻጻፍ ዘዴ።* አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

## ፫. ቃላት ከነፍቻቸው

| ቃላት | ፍቻቸው |
|---|---|
| ሀገረሰባዊ | ባህላዊ |
| ሁለንተና | ጠቅላላ አካል፣ ሁለመና |
| ሁነኛ | ቁም ነገረኛ፣ ታማኝ፣ ዓይነተኛ፣ ተስማሚ፣ ጠቃሚ |
| ሃሌታ | ምስጋና፣ የምስጋና መጀመሪያ |
| ሃመልማል | ልምላሜ፣ አረንጓዴነት |
| ለዛ | ወዝ፣ ውበት፣ የነገር ጣዕም |
| ለይስሙላ | ለወሬ፣ ለስም ያህል፣ በትንሹ |
| ሉአላዊ | ነጻ የሆነ፣ ምሉዕ ስልጣን ያለው (ሀገር፣ መንግሥት) |
| ልቀት | የግጭት መፍትሔ |
| ሎጋ | ቅርጹ ሰፋ ያለ፣ ረጅምና ጠንካራ የሆነ ጦር |
| ሎጤ | ሳይጠሩት ወይም ሳይፈልጉት ከተፍ የሚል፣ ቀላዋጭ |
| ሐራጅ | እንዲሸጥ የተወሰነ ንብረት በጨረታ ወይም ገበያ ላይ በተገኘው ዋጋ የሚሸጥበት መንገድ |
| ሐሴት | ደስታ |
| ሐዋላ | በባንክ ወይም በፖስታ ቤት አማካይነት ገንዘብ የሚላክበት መንገድ |
| መሳ | አቻ፣ እኩል |
| መሳፍንት | በቀድሞ ጊዜ ከንገሡ ጋር በዝምድና የተሳሰሩና በስልጣን ላይ የነበሩ የገዢ መደብ አባላት |
| ማዕረግ | ሹመት፣ ስልጣን፣ ደረጃ፣ ክብር |
| ምንዝር | አለቃ ያልሆነ፣ የበታች ሰራተኛ |
| ምግባረ ሰናይ | መልካም ሥራ |

| | |
|---|---|
| ምፀት | በቀጥታ የቀረበውን ወይም የተነገረውን ሀሳብ ትርጉም ተቃራኒ የሚያሳይ የንግግር ስልት፣ የዘይቤያዊ አነጋገር ዓይነት፣ ነገረ ግልባጭ |
| ሞረሽ | በጭለማ ወይም ባደጋ ጊዜ ራቅ ብሎ የሚገኝን ሰው ለመጥራት የሚያገለግል የስም ምትክ |
| ሞገደ | አወከ፣ እምቢተኛ ሆነ፣ አስቸገረ፣ አሻፈረኝ አለ |
| ሞገገ | ደረቀ፣ ከሳ፣ አጥንቱ ወጣ |
| ሟርት | መጥፎ ትንቢት፣ ምልኪ፣ መተት፣ ደንቃራ |
| ሠራዊት | የወታደራዊ ክፍል አባላት በሙሉ፣ ለአንድ አላማ የተሰባሰበ ብዙ ህዝብ |
| ረድኤት | በረከት፣ እርዳታ |
| ረጃት | ከአባት ከእናት የወረደ (የመጣ) ቅርስ |
| ረጠጠ | አመቀ፣ ተጫነ |
| ረፈረፈ | ጣለ፣ ለሸለሸ፣ አስተኛ፣ አጋደመ |
| ራሮት | አዘኔታ |
| ራእይ | በእንቅልፍ ወይም በተመስጦ ጊዜ የሚታይ ህሊናዊ ትርኢት፣ ህልም |
| ሰቀጠጠ | ዘገነነ |
| ሰታታ | ወጣ ገባ ያልሆነ፣ ለጥ ያለ፣ ዝርግ |
| ሰነበጠ | በጣ፣ ቆረጠ፣ ቀደደ፣ ሰነጠቀ |
| ሰገባ | አፎት፣ የሰይፍ ማህደር |
| ሸለገ | አሰበ፣ አሰላ፣ ለካ፣ ገመተ፣ መዘነ፣ መጠነ |
| ሸንኅበት | የአገጭ ላይ ጢም |
| ሸፈጠ | ከዳ፣ ካደ፣ አበለ፣ ዋሸ |
| ቀመር | ቁጥር፣ ስሌት |
| ቀረርቶ | ሽለላ፣ የጦር፣ የጀግንነት መቀስቀሻ ዜማ |
| ቀየደ | አሰረ፣ ጠፈረ፣ ሰነከለ፣ መናገር ከለከለ፣ |
| ቀደምት | የቀደሙት፣ የዱሮዎቹ፣ የጥንቶቹ፣ የመጀመሪያዎቹ |

| | |
|---|---|
| ቃንዛ | የደም ስርን የመጠዝጠዝ፣ የመንዘር ሕመም |
| ቃፊር | የጠላትን እንቅስቃሴ ለመሰለል የተመደበ የጥበቃ ጓድ ወይም ወታደር |
| በለተተ | አረጀ፣ ሸመገለ |
| በተሃ | ጌሾ ያልበዛበት ለጋ ጠጅ |
| ቡፍና | ጌሾ የሌለው ቀጭን ጠላ፣ ቡቅሬ |
| ቦረቀ | ፈነጨ፣ ፈነጠዘ፣ ዘለለ |
| ቧልት | ፌዝ፣ ቀልድ፣ ዋዛ ፈዛዛ፡፡ ተረብ |
| ተራክቦ | ግንኙነት፣ ሰጥቶ የመቀበል ተግባር፣ መስተጋብር |
| ተቀናቃኝ | ባላንጣ፣ ተፎካካሪ |
| ተቆራቆሰ | ተጋጨ፣ ተጣላ፣ ጠብ ጦርነት ጀመረ፣ አጫረ |
| ተግሳጽ | ቁጣ፣ ምክር |
| ተግባረ እድ | እንደአናጢነት፣ ሜካኒክነት፣ወዘተ. ያለ የእጅ ሙያ |
| ተጠናወተ | ጥል ፈለገ፣ ባላጋራ ሆነ፣ ተተናኮለ፣ ተጣላ፣ አዘውትሮ በተደጋጋሚ አመመ |
| ተፋተተ | እየቆረሰ ወይም እየገመሰ ተከፋፈለ |
| ታከተ | ሰለቸ፣ ደከመ |
| ቸልተኝነት | ግዴለሽነት፣ ምን ቸገረኝ ባይነት |
| ቸነፈር | የተላላፊ በሽታ ዓይነት፣ ወረርሽኝ፣ ተስቦ፣ እልቂት፣ መቅሰፍት |
| ቻርኔላ | ዚፕ |
| ነሸጠው | በል በል አድርግ አድርግ የሚል ስሜት ተሰማው፣ ገፋፋው፣ አነሳሳው |
| ነውጥ | ሁከት፣ ብጥብጥ፣ ሽብር፣ ርደት፣ ንቅናቄ |
| ነፀብራቅ | ብልጭታ፣ አንድን ሁኔታ ወይም አስተሳሰብን የሚያመለክት ድርጊት ወይም ሀሳብ |
| አረበረበ | ውሃ ረጨ፣ አርከፈከፈ፣ ንግግር አበዛ፣ ለፈለፈ |

| | |
|---|---|
| አረፈቀ | አቅም አጣ፣ ደከመ፣ ወደቀ፣ እቤት ዋለ |
| አርምሞ | ጸጥታ፣ ዝምታ |
| አተመ | በማተሚያ መሳሪያ ጻፈ፣ በማህተም ረገጠ ወይም ማህተም አደረገ |
| አንደበት | ለመናገር የሚያስችል የሰውነት ክፍል፣ ልሳን |
| አዘቦት | በዓል ያልሆነ ተራ የሥራ ቀን |
| አገና | በሻጭና በገዢ መካከል የሚደረግ ስምምነት፣ ውል |
| አግቦኛ | አሽሟጣጭ፣ አሽሙረኛ |
| አጭልግ | አታላይ፣ ሌባ |
| ኢምንት | በጣም ትንሽ፣ ቅንጣት፣ ከቁጥር የማይገባ |
| እቅጩን | እርግጡን፣ እውነቱን |
| እክታም | ኮተታም፣ ቅራቅንቧም |
| እውን | እውነት፣ እርግጥ |
| እንቦቀቅላ | ያልጠና፣ ለጋ (ልጅ፣ ቀንበጥ…) |
| ከወነ | አዘጋጀ፣ አሰናዳ፣ ፈጸመ፣ ጨረሰ |
| ክትት አለ | መዞር ተወ፣ ወዲያ ወዲህ ማለት ተወ፣ ተሰበሰበ |
| ክፍለ ዘመን | የአንድ መቶ ዓመት ጊዜ |
| ወረግቡ | ልትወልድ የደረሰች፣ ዘጠነኛ ወሯን የያዘች (ሴት) |
| ውርጭ | በበጋ ወራት በአየር ቅዝቃዜ የተነሳ ሌሊቱን መሬት ላይ ወይም ሳር ላይ ተጋግሮ የሚገኝ ርጥበት |
| ዐቃቤ ስራይ | የባህል መድኃኒት አዋቂ |
| ዚቀኛ | ተረበኛ፣ ተረብ አዋቂ |
| ዛበረ | ለፋ፣ ባከነ፣ ቃዠ፣ ለፈለፈ |
| ዝሃ | ድር |
| ዝማም | ያማረ፣የተዋበ፣ የተወለወለ |

| | |
|---|---|
| ዞማ | ለስላሳ፣ ያማረ (ለፀጉር) |
| የክት | የዘወትር ያልሆነ |
| ይሙት በቃ | የሞት ፍርድ፣ የሞት ቅጣት |
| ይፋ | ገሀድ፣ ግልጽ |
| ደረመን | እከክ፣ ፎከት |
| ደርግ | ኮሚቴ |
| ድድር | ጥጥር፣ ጠንካራ |
| ጀሌ | የጦር መሳሪያ ያልያዘ ዘማች፣ ተራ ህዝብ፣ መሪ ያልሆነ፣ ተከታይ |
| ጀማ | ለአንድ የተወሰነ ጉዳይ የተሰበሰቡ ሰዎች፤ ጉባኤ |
| ጅጊ | የእያንዳንዱን ሰው ስራ በየተራው ቡድን እየሆኑ ለማከናወን በስምምነት የሚፈጠር ጊዜያዊ የስራ ህብረት፤ ደቦ፣ ወበራ |
| ገርጃፋ | ያለእድሜው ሰውነቱ የገዘፈ፣ ያለእድሜው ያረጀ የሚመስል |
| ጎነቆለ | የተነከረ ባቄላ፣ አተር፣... መብቀል ሲጀምር |
| ጥሞና | እርጋታ፣ ዝግታ |
| ጨረፍታ | በመጠኑ፣ በከፊል፣ በትንሹ |
| ጭብጥ | የአንድ ነገር ወይም ጉዳይ ፍሬ ሀሳብ |
| ፀዳል | ብርሃን ወይም የብርሃን ፍንጣቂ |
| ጽልመት | ጨለማ፣ ጥቁረት |
| ጽጌ | የአበባ ወቅት |
| ፈተተ | ቆረሰ፣ ገመሰ |
| ፈገመ | ወደቀ፣ ተደፋ፣ ሞተ |
| ፈግጠው | ተወው፣ የራስህ ጉዳይ፣ እንደፈለግህ |
| ፊጥ አለ | ከፍ ያለ ቦታ ላይ ወጥቶ ቁጢጥ አለ፣ ቁጭ አለ፣ ቁብ አለ |
| ፋኖ | ሳይታዘዝ በፈቃዱ የሚዘምት፣ ወዶ ዘማች |

## አባሪዎች

| | |
|---|---|
| ፍርኩታ | የተቦረቦረ ዋሻ፣ ጎሬ |
| ፎጠና | ወጣት፣ ሶታ፣ ኮበሌ |
| ፖሊሲ | በመንግስት፣ በፖለቲካ ፓርቲ ወይም በኩባንያ የሚዘጋጅ የተግባር መመሪያ |

## ፬. ፈሊጣዊ አነጋገሮች ከነፍቻቸው

| ፈሊጣዊ አነጋገሮች | ፍቻቸው |
|---|---|
| ሀይ በል አለ | ጀመረ፣ ተነሳ፣ |
| ሆዱን ሰጠ | ሀሳቡን አካፈለ፣ ሀሳቡን ተናገረ |
| ሆድና ጀርባ | ፈጽሞ አለመግባባት፣ መቃቃር |
| ልቅም ያለች | እጅግ ባለሙያ የሆነች/ቆንጆ |
| ልብ ወረደው | ሰውነቱ ዛለ |
| መከራውን በላ | ተጎሳቆለ፣ ተሰቃየ |
| ምርግ | ዝምተኛ ሰው |
| ምድር ዋጠው | ጨርሶ ጠፋ |
| ረጋ ሰራሽ | መናኛ ሥራ፣ ጥራት የሌለው |
| ሬሳ ሆነ | ዛለ፣ ቀጠነ፣ ኮሰመነ |
| ሰመር ገባ | ተያዘ፣ ተሸነፈ |
| ሰምና ፈትል | ፍጹም ህብረት፣ ፍጹም ስምምነት |
| ስሙን መነዘሩት | ስሙን በሀሜት አጠፉት፣ አለስሙ ስም ሰጡት |
| ሽክሙ ወረደለት | ሀሳቡ ተቃለለ፣ ከማሰብ አፎይ አለ |
| ቃል አሰረ | ተፈጣጠመ፣ ቀለበት አደረገ፣ ቃል ኪዳን ገባ |
| ቅጠ ቢስ | የማያምር |
| ቆርጦ ቀጥል | ቀጣፊ፣ ውሸታም፣ አስመሳይ፣ አባይ |

| | |
|---|---|
| በሆነ ባልሆነ | በሚረባ በማይረባው፣ በትልቁ በትንሹ፣ በየምክንያቱ |
| ቢከፍቱት ተልባ | ቁም ነገር የሌለው፣ ከውጪ ሲታይ ደህና የሚመስል ግን ውስጡ መናኛና የማይረባ ሆኖ የተገኘ |
| ብስል ከጥሬ | ጥሩና መጥፎ |
| ተው ባይ | መካሪ |
| ተጫጫነው | ህመሙ በረታበት |
| ትከሻ ሰጠ | ተኩራራ |
| ቸበቸበው | በርካሽ ሸጠው |
| ነበር ቤት አይሰራም | ባለፈ ታሪክ መኩራራት አይጠቅምም |
| ነውር ጌጡ | ልክስክስ፣ ይሉኝ አይል |
| ዐይን በላው | ሞተ |
| ኩፍ አለ | አኮረፈ፣ አዘነ፣ ተቀየመ |
| ክፉ ባለዳ | ተበድሮ የማይመልስ |
| ወለባ ሰኪ | እዩኝ እዩኝ ባይ፣ ልታይ ልታይ ባይ |
| ዋንጫ ልቅለቃ | የአንገት እስክስታ፣ |
| ዐይኑ ቀላ | ተመቀኘ |
| ዐይነ ልም | ተንኮለኛ |
| ዐይን በላው | ቡዳ በላው፣ እንደተጠበቀው ሳይሆን ቀረ፣ ተበላሸ |
| ዝንፍ አለ | ከመጠን አለፈ፣ ትርፍ ነገር ተናገረ |
| የለበጣ አነጋገር | የሽንገላ አነጋገር፣ |
| የቀለም ቀንድ | ሊቅ፣ አዋቂ፣ ተመራማሪ |
| የወሬ ወሬ | የስሚ ስሚ፣ ጭምጭምታ |
| ይዞህ ይሂድ | ለሞት ይዳርግህ፣ ይግደልህ |
| ደረቷን ጣለች | ክፉኛ አዘነች |
| ደዌ ነፍስ | ኃጢአት |
| ዱር ቤቴ | ሽፍታ፣ አመጸኛ |

| | |
|---|---|
| ጆሮ ስጠኝ | ስማኝ፣ አዳምጠኝ |
| ገልብጣ ለብሳለች | አዝናለች |
| ገንዘቡን አቃጠለ | ባልባሌ ነገር ገንዘቡን አጠፋ፣ ላልረባ ነገር አዋለው |
| ጉዳዩን ተኮሰ | አከናወነ፣ ፈጸመ |
| ግብረ ጠል | ግብር ያልተገበረበትና ለሌላ ሰው ሊሰጥ የሚችል መሬት |
| ጥርቅም አለ | ዝም አለ፣ ድንገት ሞተ |
| ጨርቅ ለባሽ | መናጢ ድሃ |
| ፊቱን ያዘ | አፈረ |

## ፭. የአማርኛ ቁጥሮች

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ፩----1 | ፲፩----11 | ፲----10 | ፻፲፭----115 | ፴፻----3000 |
| ፪----2 | ፲፪----12 | ፳----20 | ፻፳----120 | ፵፻----4000 |
| ፫----3 | ፲፫----13 | ፴----30 | ፪፻----200 | ፶፻----5000 |
| ፬----4 | ፲፬----14 | ፵----40 | ፫፻----300 | ፹፻----8000 |
| ፭----5 | ፲፭----15 | ፶----50 | ፭፻----500 | ፼----10000 |
| ፮----6 | ፲፮----16 | ፷----60 | ፯፻----700 | ፪፼-----20000 |
| ፯----7 | ፲፯----17 | ፸----70 | ፲፻----1000 | ፱፼----90000 |
| ፰----8 | ፲፰----18 | ፹----80 | ፲፱፻፺----1990 | ፲፼----100000 |
| ፱----9 | ፲፱----19 | ፺----90 | ፳፻----2000 | ፳፼---200000 |
| ፲----10 | ፳-----20 | ፻----100 | ፳፭፻----2500 | ፻፻፻----1000000 |